"The Word Was God"
Published by the Mekane Yesus Seminary
Theological Literature Fund
May 1995, Addis Ababa, Ethiopia.
Copyright, 1995, Meseret Sibhat Leab.

# ቃል እግዚአብሔር ነበረ።
# ሁሉ በእርሱ ሆነ።

## ከመሠረት ስብሐት ለአብ።

በ1987 ዓ.ም. ታተመ።

## ማውጫ


| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ። | 3 |
| ሥላሴ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ። | 6 |
| ኩነታዊ ሦስትነት። | 10 |
| ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል ተፈጠሩ። | 12 |
| የእግዚአብሔር የመናገሪያ ቃሉ የባሕርዩ ቃል ነው። | 13 |
| የእግዚአብሔር ቃል የኃይል ቃል ነው። | 15 |
| የልዑል እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ኃይልና ችሎታ። | 21 |
| ስለ ጥበብ። | 23 |
| አርዮሳውያን ይሆዋህ የሚሉት ምንን ነው? | 26 |
| አርዮሳውያን መጽሐፍ ቅዱስን ስለመተዋቸው፣በእርሱ ፋንታ ሌላ መጽሐፍ ስለመጻፋቸው። | 36 |
| ጥበብ በእግዚአብሔር ባሕርይ ያለ ነው። | 39 |
| የጥበብ ህልውና በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት ነው? | 42 |
| አርዮሳውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ዳኝነት ከተከሰሱበት ክስ ሊነጹ አይፈልጉምን? | 48 |
| ልዑል እግዚአብሔር ብቻውን ፍጥረታትን ስለመፍጠሩ። | 50 |
| መፍጠሩና ጠባቂነቱ የተያያዙ ናቸው። | 53 |
| ሐተታ። | 56 |
| አሻራ። | 61 |
| ቃል ከመቼ ጀምሮ ይኖር ነበር? | 66 |
| ቃል ከሁሉ በፊት ነበረ። | 71 |
| በመጀመሪያና በመጀመሪያ ተብለው በኦሪት ዘፍጥረትና በዮሐንስ ወንጌል በተነገሩት ሁለት ተውሣከ ግሦች መካከል ግንኙነትና ልዩነት። | 74 |
| በኦሪት ዘፍጥረት ያለው «በመጀመሪያ» ተብሎ የተነገረው ተውሣከ ግሥ በአጉላማሽነቱ ያበረከተው ሙያዊ ድርሻ። | 76 |
| የአንጻር አወራረድ ዘይቤ። | 79 |
| ፈጠረና ነበረ ስለ ተባሉት ቃላት ዘይቤያዊ ፍቺ የፈጠረና የነበረ ዘይቤያዊ ፍቺ። | 80 |
| ዘመናት የማይወስኑት መጀመሪያ «ዘለዓለማዊነት» ። | 84 |
| ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። | 86 |
| ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። እንደምን ነበረ? የት ዘንድ ነበረ? | 90 |
| ከምንጭ በሚፈልቅ ምንጭ መካከል የባሕርይ ልዩነት የለም። | 93 |
| ወልደ አብ ዋሕድ። | 115 |
| ዋ ሕ ድ ወ በ ኩ ር | 141 |
| በብሉይ ኪዳን በባሕርየ ልደት የተመሠረተ ሌላ የብኩርና አቋም ይገኛል። | 149 |


# ቃል እግዚአብሔር ነበረ።

## መግቢያ

## የትምህርተ መለኮት መሠረት በተመርሆ ልቡናዊ።

የእግዚአብሔር ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ በየቦታው ተጽፈው ይገኛሉ።

1፥ <u>የአንድነቱ ስሞች</u>፣

| | |
|---|---|
| አምላክ | መዝ. 17/18/፥31። |
| መለኮት | ሮሜ 1፥21፤22። |
| እግዚአብሔር «ኤልሻዳይ» | ዘፍጥ. 14፥1። |
| አዶናይ | ሕዝ. 7፥5። |
| እግዚአ ፀባዖት «የሠራዊት አምላክ የሠራዊት ጌታ» | ኢሳ. 6፥6። |
| እግዚእ እግዚአብሔር «ይሆዋህ» | ዘፀአ. 6፥31። |
| እግዚአብሔር አምላክ | ዘፍጥ. 2፥4፣8። |

2፥ <u>የሦስትነቱ ስሞች</u>፣

| | |
|---|---|
| አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ | ማቴ. 28፥19፣20። |
| ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ፥ | መዝ. 32/33/፥6፤11። |
| ወላዲ/ተወላዲ ሠራጺ | መዝ. 2፥7፤ ም.109/110/፥3። |
| አሥራጺ | ዮሐ. 15፥26። |

ይሁን እንጂ እነዚህን አስማት ወይም ስሞች በረድፍ በረድፉ እያደረግን ማቅረባችን ከእነርሱ ከራሳቸው የተለያየ ትምህርታዊ ምሥጢር ተቋጥሮባቸው የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን ያንኑ በገዛ ራሳቸው እያንጸባረቁ እንዲገለጹ ስለሚያደርጉ ነው።

የትምህርተ መለኮት ሊቃውንት የአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እምነትና የትርጓሜ አባባል አንድ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ በቅዱሳት መጻሕፍት ከእግዚአብሔር የተተነፈሰውን የቃሉን መሪነት በትሕትና ሆነው እያደመጡ

ከመንፈስ ቅዱስ ለመመራት አስቀድመው ራሳቸውን ታዛዥ አድርገው አቅርበዋል። በመሠረቱም የምሥጢሩን ኃይለ ቃል በየዘመዱና በየመልኩ በአግባብ በአግባቡ ይሄድ ዘንድ የመመሪያ መንገድ ፈልመው አስቀምጠዋል።

ይኸውም፦ ማንኛውም ስም ምድቡ ከየት ወይም ከምን እንደሆነ ህላዌው «አቋሙ» ወይም ልኩ እንዴት እንደሆነ፤ ተለይቶ የሚታወቅበት በተመርሆ ልቡናዊ ተጠናቅቆ የሚገኝ የስመ ህላዌያት አውታረ ስም ነው።

አስቀድመን የዋነኞቹን ስሞች አመሠራረት ብናይ መልካም ነው።

1ኛ፥ «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ» የሚሉ ስሞችም በመጽሐፍ ቅዱስ ተደጋግመው የተገለጡ ናቸው።

ማቴ. 3፥17። ም. 28፥19፤20።

2ኛ፥ «ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ የሚሉ ስሞችም እግዚአብሔራዊ ስሞች ሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጠዋል።

መዝ. 32/33/፥6፤11።

3ኛ፥ ወላዲ፥ ተወላዲ፥ ሠራፂ አሥራፂ የሚሉ ስሞችም አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሚሉ ስሞች ላይ እየተቀጸሉ መነገራቸው በብሉይም በአዲስም ተነግሮ ይገኛል።

መዝ. 2፥7። ም. 109/110/፥3። ዮሐ. 15፥26።

እንግዲህ እዚህ ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ በየረድፉ ቀርበው የተጠቀሱት የሦስትነት ስሞች ምድባቸው ከየትና ከምን እንደሆነ አቋማዊ መልካቸው እንዴት ያለ እንደሆነ ለይቶ በሚያስታውቅ ስመ ህላዌያት «አውታረ ስም» እንመልከት።

1፥ ይህም አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሲባሉ የአካላት ስሞች መሆናቸውን፦

2፥ ልብ፥ ቃል፥ እስትንፋስ ተብለው በሚነገሩበት ጊዜም የኩነታት ስሞች መሆናቸውን፦

3፥ ወላዲ፥ አሥራፂ፥ ሠራፂ፥ እየተባሉ በሚነገሩበት ጊዜ የግብር ስሞች መሆናቸውን ነው።

ይህም ቅዱሳት መጻሕፍት አቅርበዋቸው ከሚገኙ የአካላትና የኩነታት፥ የግብራት ስሞች አራቅቆ፥ አመሥጥሮ ማሳካቱንና መዝና ወይም አስታርቆ ጽንዐ ቃላቱን፥ ጽድቀ ትምህርቱን ቀና ውሳኔውን ፈታሒ ችሎት ላለው ለሰው ሕሊና «መጽሐፋዊ አእምሮ» መተዉ፥ የትምህርተ መለኮት ጠባይዐዊ መንገድ ነው እንጂ፤ የፈጠራ አስተሳሰብ እንዳልሆነ በቅጥነተ ሕሊና የሚከታተለው ሰው ይረዳዋል።

በመሠረቱም ከቅዱሳት መጻሕፍት ከሚገኙ ኃይለ ቃላት አገባብ ሳይወጡ በመንፈስ ቅዱስ በሚቃኝ ልቡናዊ ተመርሆ ሆና የትምህርቱን እውነት በሥርዓት



ኀሠሣ «ምርምር» መከታተልና የእርሱ በርሱ «ኅብረተ ቃላት» መዛመድን በዚሁ ፈታሒ ጠባይ ማየትና መበየን ይሆናል።

ከቅዱስ መጽሐፍ ሳይዛነፍ በመንፈስ ቅዱስ በሚቃኝ ልቡናዊ ተመርሆ መበየን እንደዚህ ያለ የጸጋ ስጦታ ኃላፊነት መቀበሉ የነገረ መለኮትን ትምህርታዊ አቋም በየመልኩና በየዓይነቱ በየስልቱ ዘይቤያዊ ቅርፅ መረዳትን የሚሻ ሁሉ እንዲያተኵርበት አይደለምን?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ኃይለ ቃላት በትምህርተ መለኮትና በልቡናዊ ተመርሆ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ባያቀዩልን ኖሮ፥ እጅግ በጣም እንጉዳ ነበር። ይህንም የምናየው እላይ የተገለጸው ትምህርታዊ መራቀቅን የማይወዱና ከዚህ ሸሽተው በራሳቸው አእምሮ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን ለማብጠልጠል የተነሡት መናፍቃን፥ በተለይም አርዮሳውያን አወዳደቃቸው የቱን ያህል ከባድ እንደሆነ መረዳት ብቻ ይበቃል። ብዙ ሰዎች እነዚህን ስመ ህላዌያት እንደፈታዳቸው ይናገሩባቸዋል። እኛም ብዙ ጊዜ እንደዚሁ ተነጋግረንባቸዋል። ያም ሆነ ይህ አሁን በምንጽፈው ትምህርተ መለኮት በተለይም ስለ አርዮሳውያን ሐሰተኛ ትምህርት ለማረም ስንል፤ የዚህን ጥቅም ጉላ አድርገን ለማስታወቅ ከልብ እንጥራለን።

አርዮሳውያን ግን የትምህርተ መለኮትን ሥርወ ምሥጢር አራቅቆ ለመረዳት ከዘይቤው መደረግ ያለበት ስልታዊ ኀሠሣ በልቡናዊ ተመርሆ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት አይፈልጉም።

ከዚህ የተነሣ በግልጽ የተነገረውን የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥሬ ንባብ መረዳት ሲያቅታቸውና ግራ ሲገባቸው፤ እየሠረዙ ወይም እየለወጡ እንደዚሁም በአሉታቸው ጸንተው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን እምነት ፊት ለፊት ለማጥፋት ሲጋደሉ ይታያሉ።

# ምዕራፍ ፩

## ሥላሴ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ።

<u>የሥላሴ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም በተርቱሊያኖስ ነው የተፈጠረ ማለታቸው፦</u>

አርዮሳውያን «የሥላሴ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም» ብለው ይከራሉ። እንደዚሁም «ሥላሴ» የሚል ትምህርት በኋላ የተነሡና በ250-260 ዓ.ም. አካባቢ የነበሩ እነተርቱሊያኖስና እነአርጌንስ የተባሉ መምህራን የፈጠሩት ነው እንጂ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተነገረም» ይላሉ።

«የሥላሴ ትምህርት ጨርሶ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተነገረም አልተገለጠም» የሚሉትን የአርዮሳውያንን አባባልና አስተሳሰብ፥ በትዝብት ሆኖ የተመለከተ ሰው በዚሁ በሙሌነት ፈሊጣቸው ግሩምኛ ሳይደነቅ አይቀርም። የቅድስት ሥላሴን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭና ጥግ የለሽ ወይም መናኛ ነገር አድርገው ለማሳየት መሞከራቸው፥ እጅግ አድርጎ የሚያሳዝን ነው። ይኸውም በ250 ዓ.ም. ገደማ በነበሩት በእነተርቱሊያኖስ መጽሐፍ እስኪፈጠር ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ አልተነገረም፣ አልተገለጠም ብለው መናገራቸው የሚያስገርም ነው።

በእውነቱ እንዲህ ብለው መናገራቸው ምንን ፈልገው ይሆን? ብለን ልንጠይቅ እንገደዳለን። ምናልባት የአላዋቂውን ሰው ዓይነ ልቡና እንዲጭበረበር አስበው ይሆን? ወይም እነሱ ራሳቸው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28፥19፣20። ላይ «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አጥምቁአቸው» ተብሎ በጉልህ የተጻፈውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ሳያነቡ ቀርተው ነው?

መቼም ቢሆን ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን እውነት እያየ፥ ተሳስቶ ሌላውን ለማሳሳት በሽንገላ ለመመራት ዐውቆ ይሠራል ብለን አናስብም። ሮሜ 1፥31፣32።

በማቴዎስ ወንጌል ም. 28፥19፣20 ላይ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው ተብሎ በግልጽ ተጽፎአል። «አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ» የሚሉ ስሞች በዋዌ «በአጫፋሪ» ከአንድ ቦታ ተደርድረው በመጽሐፍ ይገኛሉ። እነዚህን ስሞች እስቲ እንቍጠራቸው ስንት ናቸው? ሦስት ሆነው እናያቸው የለምን? አዎን እነዚህ በዋዌ «በአጫፋሪ» አገባብ ወይም በወደረኛ መስተፃምር ተፃምረውና ተጫፍረው የተያያዙ ስሞች ሁለት ብቻ አይደሉም። አራተኛ ስምም አልታከለባቸውም። ነገር ግን «አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስም» ተብለው በሦስት ስሞች ብቻ ቆመው በሦስት ስሞች ብቻ ተወስነው ተጽፈው እናያቸዋለን።



እንግዲህ «ሥላሴ ወይም ሦስትነት በነተርቱሊያኖስ ዘመን ነው የተጻፈና የተነገረ እንጂ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ አልተነገረም» ብሎ መተረክ፥ ስሕተቱ የማን ሊሆን ነው? መጽሐፍ ቅዱስንና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ያላየና ያልተመለከተስ የማን ዓይን ሊሆን ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ሆኖ «አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስም» ተብሎ የተነገረውንና የተጻፈውን በሙሉ አሉታ ክዶ ገሮችና የመጽሐፍ አላዋቂዎች ቢገኙ ለማስካድ፣ ቆዳ ነክ በሆነ የታሪክ ቅርንጫፍ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥርወ ቃል ለማፈንና ለመጨፈን የታሰበ ዘዴ መሆኑ ያለጥርጥር የሚታይ አይደለምን? ኧረ ለመሆኑ ስለ ሦስትነት ከተነገረው ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና ስለ ተርቱሊያኖስ ከተነገረው ታሪክ የቱ ነው የሚቀድም? በማቴዎስ ም.28፥19፣20 ላይ፥ «በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁአቸው» ተብሎ ለሐዋርያት ሲነገር፣ «አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ» ተብለው በዝርዝር የተጠሩ ስሞች ሦስት አይደሉምን? «አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» ተብለው በዝርዝር የተጠሩ ስሞችስ እንዲያው በህሉና ሳይታወቁ ማለት የመኖር አቋም ሳይኖራቸው ነውን? የለም። የህሉና አቋም ሳይኖራቸው በእንዲያው የተነገሩ አይደሉም። ማናቸውም ስም የሚወጣለት ወይም በስም የሚጠራ ሁሉ መኖሩ ታውቆ ህሉናው ተረጋግጦ «አለ» ለተባለ እንጂ፣ ህሉናው ላልታወቀ ላልተረጋገጠ በህሉና «በአቋም» ለሌለ፣ ወይም የሌለ ከሆነ፣ ስም አይሰጠውም። ስምም አይወጣለትም። የለምና፤ ከሌለ ምን ተብሎ ስም ይወጣለታል? ህሉና ሲባል ማንም ወይም ከማናቸውም ይሁን ያለና መኖሩ ወይም የመኖሩ አቋም «አለ» ተብሎ የሚታወቅና የተረጋገጠ ታዋቂ ነዋሪ ነው። ስም የሚወጣለት ነዋሪ በመሆን ለታወቀ በህሉና ላለ ነው። ከሌለና «አለ» ተብሎ ካልታወቀ ወይም የሌለና ያልኖረ ከሆነ ግን፣ በህሉና የሌለና ያልኖረ ነውና፣ ስም አይሰጠውም። /ሰዋስወ ግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ መመልከት ነው።/

አርዮሳውያን ይህን ታላቅ ቁም ነገር ያለበትን ድንጋጌ ማስተዋል ይገባቸዋል። በዚሁ ድንጋጌ የገዛ ራሳቸው ካላመኑበት፣ «በህሉና ለሌለ ነገር ስም ይሰጠዋል ወይም ስም ይወጣለታል» የሚል ቁም ነገረኛ ሰው ካገኙ፣ አጥብቀው ይጠይቁ፦ መሠረታዊ ውሳኔ ነውና።

በህሉና የሚታወቁ ወይም መታወቅ ያለባቸው ስመ ህላዌያት፦ «አካል፥ ኵነት፥ ባሕርይ፥ ህልውና» ናቸው። እነሆም፦ «አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» የሚል መጠሪያ በአካላት ስሞቻቸው ለታወቀ የተሰጠ ስያሜ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን። ማቴ. 3፥17። ማር. 1፥10፣11። ሉቃ. 3፣22። 2ቆር. 13፥13። ዮሐ. 16፥26-28። ም. 14፥16፣17። አዎን «አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» በሚል መጠሪያ የታወቁ ስሞች የባሕርይ ወይም የህልውና የኵነት ወይም የግብር፥ ህሉናን «አቋምን» የሚያሳዩ ሳይሆኑ፣ የአካላት ህሉናን «አቋምን» ብቻ የሚያሳዩ ናቸው። ይህንም ለመረዳት ማቴ. 3፥17። ሉቃ.10፥22። ዮሐ. 17፥1-51። ም. 16፥28። ቍ. 26-28። ሮሜ

8፥26-27። ቆላ. 33፥34። ኤፌ. 2፥18። 1ዮሐ. 2፥23፣24። መመልከት ነው።

አስቀድመን ስለ አካል ስሞቻቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸውን እናሳይ ብለን ነው እንጂ፣ በዙንታትም በግብርም ስሞች የሥላሴ ወይም የሦስትነት እግዚአብሔራዊ ህሉና በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተገልጾ የተነገረ ነው። ይህንም በዚሁ ጽሑፍ በምንሰጠው መግለጫ በተለያዩ አርእስት እናብራራዋለን።

ከላይ እንደተናገርን በህሉና መኖሩ ለሚታወቅ ሁሉ ስም ይሰጠዋል። በህሉና አቋም መኖሩ ያልታወቀ ከሆነ ግን፣ ስም አይወጣለትም። የት አለና! በቍጥርም እንደዚሁ ነው። ህሉናው ለታወቀ ስም አለው። ቍጥር ወይም አኀዝ ይሰጠዋል። ይህም ማለት በህሉና መኖሩ የታወቀው አንድ ከሆነ፣ አንድ ይባላል። በህሉና መኖራቸው የታወቁ ሁለት ከሆኑም፣ ሁለት ይባላሉ። ሦስት ከሆኑም ሦስት ይሰኛሉ። የሌለ ከሆነ ደግሞ መቼም የለምና፣ የአኀዝ ቍጥር የለውም። አይሰጠውም። «ጉደሎ አይቈጠርም።» ተብሎ በመጽሐፈ መክብብ የተገለጸው በትምህርተ መለኮታዊ ቀዋሚ ድርሻ አለው። መክ. 1፥15።

<u>ለምሳሌ</u>፡- እኔ እግዚአብሔር ይመስገንና «ሁለት ዓይኖች አሉኝ» ብዬ ለመናገር እችላለሁ «ሁለት ዓይኖች አሉኝ» ለማለት የቻልሁ ሁለት ዓይኖች ስላሉኝ ወይም ዓይኖቼ ሁለት ስለሆኑ ነው። ይሁን እንጂ በአንደኛው ዓይኔ ላይ አንድ የሚል የቍጥር ወይም የአኀዝ ጽሑፍ፥ በሁለተኛው ዓይኔ ላይም ሁለት የሚል የቍጥር ወይም የአኀዝ ጽሑፍ አልተጻፈባቸውም። ሆኖም ህሉናቸው ስለተረጋገጠ «ሁለት ዓይኖች አሉኝ» ብዬ ብናገር፣ እውነቱን ተናግሬአለሁ እንጂ፣ አልዋሽሁም። የሚያየኝም ሁሉ ሁለት ደኅና ዓይኖች እንዳሉኝ ካወቀ ዘንድ፣ ስለእኔ ዓይኖች አንሥቶ «ሁለት ዓይኖች አሉት» ብሎ ቢናገር እውነቱን ተናግሮአል እንጂ፣ አልዋሸም። ይህ የተመርሆ ልቡና ብያኔ «ፍትሐ ጽድቅ» ነው።

«አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» ተብለው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠሩ የተነገሩ መለኮታውያን ስሞችንም ሁለት ሳይሆኑ፣ አራትም ሳይሆኑ፣ ሦስት ብቻ ሆነው በአካላት ህሉና ተገኝተዋልና፣ ማቴ. 28፥19፣20። «ሥላሴ» ተብለዋል። ሥላሴ ማለት «ሦስት ወይም ሦስትነት» ማለት ነውና፣ ሦስት የሆነውን ሦስት፥ ወይም እንደ ግዕዙ አነጋገርም «ሥላሴ» ቢባል የእውነት አነጋገር ነው እንጂ፣ የውሸት አይደለም። ውሸት ይሆን የነበረስ፥ ህሉናው በሦስትነት ቆሞ እያለ፣ አራት ወይም አምስት ሲሉ ነው። ውሸት ይሆን የነበረስ አንድ ግለሰብ በአንድ እጁ አምስት ጣቶች እያሉት በዚሁ እጁ ሁለት ወይም አራት ጣቶች ብቻ ናቸው ያሉኝ። ብሎ ቢናገር ነው። ባጭሩ ውሸት የሚሆን የሌለውን እንዳለ አድርጎ ቍጥር መስጠትና፥ ያለውን ደግሞ እንደሌለ አድርጎ የሚገባውን ቍጥር አለመስጠት ነው። አርዮሳውያን ይህን ለይተው እንዲገነዘቡት እናሳስባቸዋለን።

መጽሐፍ ቅዱስ፡- «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ» ተብለው የተጠሩ ስሞች «ሦስት» ብቻ ሆነው በአካላት ህሉና ቀዋምያን አድርጎ ገልጾአልና፥ ሥላሴ



«ሦስትነት» መባላቸው ተርቱሊያኖስ እስኪነግ ድረስ ጊዜን የሚያስጠብቅ የትርጉም ቀጠሮ አልነበረም። ትምህርቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ተነግሮ በተመርሆ ልቡናዊ እሙንነቱ ተረጋግጦ ያደረ የዋለ ነበረና።

ሐዋርያት «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነዋል። ማቴ. 28፥19። 2ቆሮ. 13፥13፣14።

«አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ» ብለው እነዚያን ስሞች ሲጠሩ ሦስት መሆናቸውን አያውቁም ነበረ ማለት ነውን? ደግሞ ወልድ ራሱ «ከአብ ወጣሁ ወደ ዓለም መጣሁ ወደ አብ እሄዳለሁ፤ ከአብ የሚወጣ ከእኔ የሚወስድ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ» እያለ ሲያስተምራቸው ሁሉ ሐዋርያት የሦስቱን አካላውያን ስሞች በሦስትነት መታወቅ አልተቀበሉም ማለት ነው? ዮሐ. 16፥28-30። ም. 15፥26። ሐዋርያት «አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» እያሉ በብዙ ቦታ ላይ ጽፈዋል» በእግዚአብሔር ህላዌ መለኮት ውስጥ አራተኛን ወይም አምስተኛን ለምን አልጨመሩም? የሌለውን ከየት አምጥተው ይጨምሩት! ማቴ. 3፥17። ም. 28፥19፣20። ሉቃ. 3፥21፣22። 2ቆሮ. 13፣14። ኤፌ. 2፥18። 1ጴጥ. 1፥1፣2። ዮሐ. 14፥15-17። ቍ. 23-26። ሮሜ 11፥36።

ታዲያ ተርቱሊያኖስ «አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» ተብለው የተነገሩ ሦስት አምላካውያን ስሞች በሦስትነት መታወቃቸውን ዐውቆ፥ ተረድቶ «ሥላሴ» ብሎ ቢጽፍ፣ እርሱ ይህን መሠረተ እምነት ፈልስፎ እንደፈጠረ ይታያል ወይ?

ተርቱሊያኖስ የትምህርቱን መሠረት ጠንቅቆ ዐወቀ፣ ተረዳና ጻፈ። መልካም አደረገ ልንል እንችላለን። የሐዋርያትን መጻሕፍት በጥሩ ዓይኑ አንብቦአልና እምነታቸውንም በትውፊት ተቀብሎአልና ነው።

እንዲያው ለነገሩ ተርቱሊያኖስ ከቅዱሳት መጻሕፍት መሠረተ ሐሳቡን ሳይገነዘብ በልብ ወለድ «ሥላሴ» ብሎ ጽፎ ቢሆን ኖሮ፥ ማን ሊቀበለው በቻለ? የቤተ ክርስቲያን መምህር እርሱ ብቻ ነበርን? መጽሐፍ ቅዱስስ በእርሱ እጅ ብቻ ነበርን? የሐዋርያት ተከታዮች በሆኑ በአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲያስተምሩ በነበሩ ሊቃውንት እጅ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረምን? ቱርቱሊያኖስ ስለ ሥላሴ ትምህርት ቢጽፍ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብለው ከሚያምኑት አበው ይልቅ፥ የሥላሴን ትምህርት መሥራች የሚያደርገው ምንድን ነው? አርዮሳውያን ይህን አባባል ከፍ አድርገው ለማሳየት የሚፈልጉት የሥላሴን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለና ሰው ሠራሽ ለማድረግ ነው እንጂ፣ ተርቱሊያኖስ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጎ የሥላሴን ትምህርት በማብራራቱ ሊያወድሱት አስበው አይደለም። ነገር ግን እንደዚህ ያለ ፈሊጥ ለምን ይረባል?

# ምዕራፍ ፪

## ኵነታዊ ሦስትነት።

ምስጋና ክብርም ለእርሱ ብቻ ይሁንና፣ ልዑል እግዚአብሔር በበጎ ፈቃዱና በታላቅ ፍቅሩ ብዛት በፍጡራን አእምሮ ሊታይና ሊታወቅ ሊወሰን በማይቻል በመለኮቱ ህልውና ያለውን የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር በትምህርተ መንፈስ ረገድ ደካሞች ለሆኑ ለባውያን ፍጡራን በተለይም ለሰው ልጆች አእምሮ ሊገባ በሚችል ምሳሌ ገልጦአል።

ከእነዚህም ምሳሌዎች አንዱ ልብ ቃል እስትንፋስ የተሰኙ ጠባይዓት የሚገኙባት ሊካድ በማይቻል ሁናቴ ቀዋሚት የሕይወት ምሰሶ አድርጎ በሰው ውስጥ ያስቀመጣት የሰው ነፍስ ወይም መንፈስ ናት። ኢሳ. 42፥5። ም. 57፥16።

የሰው ነፍስ ወይም መንፈስ አንዲት የዓለመ መንፈስ «ርቀት» አካል መሆንዋ ሲታወቅ፣ ምን ጊዜም በማይለይዋት ጠባይዓት ወይም ኵነታት በልብና በቃል በእስትንፋስ ትመሰላለች። የሰው ነፍስ «መንፈስ» በዚሁ አቋምዋ በእግዚአብሔር ፍቅር የተደረገ መጠነኛ ማንጸሪያ በመሆን ወደ አንዱ እግዚአብሔር ባሕርያዊ ህልውናና መሠለስ «በሦስትነት» በመምራት ረገድ የሰውን ለባዊ አእምሮን ታንቀሳቅሳለች። ምሳሌ. 20፥27።

ይኸውም አንዱ እግዚአብሔር ልቡና ቃል እስትንፋስ እንዳሉት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ ይገኛልና ነው። መዝ.32/33/፥6፣11። ኢዮብ 32፥8። ም. 32፥4፤ ም. 26፥13። ዕብ. 1፥3። ዮሐ. 1፥1፤3።

እነሆም ልዑል እግዚአብሔር ልብ ቃል እስትንፋስ ባሉዋት በሰው ነፍስ ምሳሌ እርሱ ራሱ ልብ ቃል እስትንፋስ ያሉት መሆኑን በመግለጽ ሕያውነቱን አስረድቶናል። መዝ. 32፥33፣6።

ሕያው እንደመሆኑ መጠን ደግሞ፥ በልቡናውና በቃሉ በእስትንፋሱ፥ ፍጥረታት ተፈጥረው ተደግፈው ገሚሶቹ የክብሩ መግለጫ ሆነው ሊኖሩ ገሚሱም ሕያዋን ሆነው ሊኖሩ እንደበቁ አስገንዝቦናል። ኢዮብ 26፥13። መዝ. 32፥6-9። ዘፍጥ. 1፥2።

የፍጥረት መፈጠር በሌላም አገላለጽ ካለመኖር ወደመኖር መጥቶ መገኘትና ተደግፎ መኖር፣ ከልዑል እግዚአብሔር ባሕርይ ከማይለዩ ከልብ ከቃል ከእስትንፋስ አኳኋንነት የተነሣ ሆኖ መገኘቱ ቀዋሚ ትምህርት ይሰጠናል።



ይህን ከተገነዘብን በኋላ፣ ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል ስለመፈጠራቸው ወደ ተገለጸበት ዝርዝር ገብተን በመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት አተኵረን እንመረምራለን፣ ለምሳሌ ማናቸውም በልቡ ለባዊ፥ በቃሉ ነባቢ «ተናጋሪ» በእስትንፋሱ ሕያው የሆነ ሰው በቃሉ ቢናገርና በእስትንፋሱም ቢተነፍስ «የመተንፈስ ግብርን ቢፈጽም» የተናጋሪው ቃሉና የመንፈሱ ግብር ወይም ሥራ በራሱ ህላዌ እንደተከናወነ ያውቃል። ይኸውም ተናጋሪ ቃሉና ሕያው እስትንፋሱ ከራሱ ህላዌ «ከሁለንተናው» በስተውጭ አይደለምና ነው። ኢዮብ 27፥3። ም. 32፥17፣18።

በዚሁ ትይዩም በልቡ ለባዊ በቃሉ ነባቢ «ተናጋሪ» በእስትንፋሱ ሕያው የሆነ እግዚአብሔር በልቡናው ዓዋቂ «ለባዊ» በቃሉ ተናጋሪ «ነባቢ» በእስትንፋሱም ሕይወት ሰጭ ሆኖ፥ ዓለማትን ቢፈጥርና ቢመግብ፣ ከራሱ ከህላዌ መለኮቱ በስተውጭ ቃልንና እስትንፋስን ፈጥሮ ዓለማትን አልፈጠረምና ነው።

እንግዲህ ሰው ራሱ በቃሉ የተናገረውን «የሌላ ሰው ንግግር ነው» እንደማይል ሁሉ፥ እንደዚሁም የገዛ ራሱ የተነፈሰውን ትንፋሹን ሌላ ሰው የተነፈሰው ነው ብሎ እንደማያስብ ሁሉ፥ በራሱ ሁለንተና የፈጸመውን ድርጊት የገዛ ራሱ መሆኑን አረጋግጦ በሚያውቅበት በራሱ ማስረጃነት አንጻር «ትይዩ፥» እግዚአብሔርም በራሱ ቃል ተናግሮ ዓለማትን እንደፈጠረ፣ ነዋሪነታቸውም በመንፈሱ ምግብና እንዳጸና፣ ማንም ሰው ሳይቸገር ለማወቅና ለመረዳት ይችልበታል ማለት ነው። ኢሳ. 55፥11። ዘካ. 12፥1። ኢሳ. 51፣16።

ስለዚህ ሰው ሊክደው በማይችል ከራሱ ውስጥ ባለውና ባገኘው ማስረጃ ተጠቅሞ በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ፥ ኃይላቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ነው ተብሎ የተጻፈውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲመለከት፣ ከእግዚአብሔር ባሕርያዊ ህልውና ባለው ቃል ሰማያት እንደተፈጠሩና ኃይላቸውም «ነዋሪነታቸውም» ከአፉ እስትንፋስ እንደሆነ፣ ያለጥርጥር ሊገነዘብና ሊያውቅ ይችላል። ይህ ማስረጃ እያለለትም ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩት ከፍጡር ቃል ነው፣ ኃይላቸው ወይም ነዋሪነታቸውም ከፍጡር እስትንፋስ ነው ለማለት አይችልም፣ ማለት ነው። ሰው ከራሱ የቀረበ ምስክር የለውምና እግዚአብሔር ሰው በሰው ዘንድ ራሱን ያለ ምስክር አልተወም። የሐዋ. 17፥24-28። ም. 14፥17። እግዚአብሔር ሊካድ የማይቻል የነፍስ «መንፈስ» ምስክር በሰው ባሕርይ ያስቀመጠለት ሰው በዚሁ ማንጸሪያ «ትይዩ» የራሱን የእግዚአብሔርነቱን መለኮታዊ ህልውናን ለፍጡራን ያለው አደራረግን አነጻጽሮ እንዲገነዘብበትና እንዲያውቅበት ነው።

እንዳንሳሳትና ከመንገዱም ውጭ እንዳንጠፋበት አስቦ በቸርነቱና በፍቅሩ ለባዊትና ነባቢት ሕያዊት ነፍስን የሕይወት ማኅተም አድርጎ ለሰጠን ለእርሱ ምስጋና ክብርም ይሁን። ኢዮብ 38፥26። ም. 32፥8። ም. 35፥10፣11።

እንግዲህ በዚህ የተገለጸውን ተመርሆ ካየን ችግር አይኖርምና፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ መሠረት ዓለማትና የሚኖሩባቸውም ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ስለ መፈጠራቸው ወደምንግርበት እንራመድ።

# ምዕራፍ ፫

## ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል ተፈጠሩ።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ዓለማት እንደተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን። «ይላል» ዕብ. 11፥3። እንደዚሁም በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ «ይላል» መዝ. 32/33/፥6።

እነሆም ዓለማትና ያሉባቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ቃልና በአፉ እስትንፋስ ተፈጥረውና ተደግፈው አየን። ኢዮብ 26፥13። ዕብ. 1፥2፣3።

መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረታት የተፈጠሩበት ቃል በእግዚአብሔር የመናገሪያ ቃሉ እንደሆነ ይገልጻል። ይህም በስድስት ቀናት በተፈጠሩት ፍጥረታት ዝርዝር በግልጽ ተጽፎ ይገኛል።

1፥ «እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ።» ብርሃንም ሆነ። ዘፍጥ. 1፥3።

2፥ እግዚአብሔርም በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን በውኃ መካከልም ይከፈል አለ... እንዲሁም ሆነ ዘፍጥ. 1፥6፣7።

3፥ እግዚአብሔርም ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ የብሱም ይገለጥ አለ። እንዲሁም ሆነ... እግዚአብሔርም ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድር ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዘርን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ። ዘፍጥ. 1፥9፣13።

4፥ እግዚአብሔር አለ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ አለ... እንዲሁም ሆነ። ዘፍጥ. 1፥14፣15።

5፥ እግዚአብሔርም አለ። ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፣ ወፎችም ከምድር በላይ በሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ። ዘፍጥ. 20፥23።

6፥ እግዚአብሔር አለ ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደወገኑ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ።

እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፣ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩና በምሳሌው ፈጠረ። ዘፍጥ. 1፥24-28።

ይኸውና እግዚአብሔር «አለ ይሁን» ሲል ፍጥረታት ሁሉ እንደተፈጠሩ እዚህ ላይ በዝርዝር ባቀረብናቸው ሥነ ፍጥረታት ተመለከትን። ዘፍጥ. 2፥1። እግዚአብሔርም በዚሁ በቃሉ ኑንት ፍጥረታትን ፈጥሮ በማስገኘት የባሕርይ ግብሩን ገልጾ አሳይቶአል።



# ምዕራፍ ፬

## የእግዚአብሔር የመናገሪያ ቃሉ የባሕርዩ ቃል ነው።

እነሆም ዓለማትን የፈጠረ በቃሉ ሲሆን «እግዚአብሔር» አለ ይሁን በማለት በመናገሪያ ቃሉ ፍጥረታትን መፍጠሩን ለምን ገለጸ? ብሎ የሚጠይቅ ሰው ይኖራል። መልሱ ግናቸውም ሰው የመናገሪያ ቃሉን ከልቡ ውስጥ ያገኘዋል እንጂ፣ ከውጭ አያገኘውምና፣ ይህን እንደማወቁ መጠን፣ እግዚአብሔርም ዓለማትን የፈጠረበት ቃልም ከውጭ ሳይሆን ከራሱ ከልቡ ያለ፣ የመናገሪያ ቃሉ መሆኑን አነጻጽሮ እንዲያውቅበትና እንዲገነዘብበት ነው። ከዚህም በላይ ደግሞ በሰው ያለው የመናገሪያ ቃል ከልቡ ከዕውቀቱ ጠባይዓዊ አንድነት የማይለይ እንደመሆኑ መጠን፣ ዓለማት የተፈጠሩበት የእግዚአብሔር ቃልም የመናገሪያው ቃል በመሆን መገለጹ፣ ከእግዚአብሔርነቱ ባሕርያዊ አንድነት ከቶ የማይለይ መሆኑ እንዲታወቅበት ነው። መዝ. 118/119/፥89-91። ኢሳ. 45፥5-7። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ከእርሱ በማይለይ በመናገሪያ ቃሉ ዓለማትን መፍጠሩ በእግዚአብሔርና በፍጥረታት መካከል በጣልቃ የገባ ሌላ ፈጣሪ ሳይኖር፣ ራሱ እግዚአብሔር በባሕርዩ ቃል የፈጠራቸው እንደመሆኑ፣ ፍጥረታት ሁሉ የእግዚአብሔርነቱ ጥሪትና ንብረት የእርሱ ገንዘብ መሆናቸውን አውቀው ተጠንቅቀው እንዲያመልኩትና እንዲያመሰግኑት ነው። መዝ. 148፥1-13። እነሆም ከዚህ በላይ ያየነው ገለጻ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ብሩህ ሆኖ የተነገረና ለሰው አእምሮ የሚገባ ነው። እግዚአብሔር የህላዌ መለኮቱን አኗኗር ራሱ በሚያውቅበት ገንዘብ ራሱን በልቡና በቃሉ፣ በእስትንፋሱ እንዴት እንደሆነ ሲገልጽና ለፍጡራኑም ይልቁንም ለሰው ልጆች አእምሮ እንዴት ሊገባቸው እንደሚችል በሚረዱበት መጠን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲያስገነዝብ በእርሱ ተነጻጻሪ ሆነው የቆሙት አርዮሳውያን ደግሞ ይህን ሲቃወሙ መገኘታቸው የሚያሳዝን ነው።

እነሆም፣ «ይሁን» እያለ በባሕርይ ቃሉ የፈጠራቸውንና ያመጣቸውን በአፉ እስትንፋስ የሚመግባቸውንና የሚያኖራቸውን ዓለማት በፍጡር ቃል ነው መፈጠር ያለባቸው ይላሉና ነው።

አርዮሳውያን እግዚአብሔር በሚናገርበት ቃሉ ዓለማትን ስለመፍጠሩ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ሆኖ የተጻፈውንና የተነገረውን እያዩና እየሰሙ ሳለ፣ ቀጥታ ጥንባር ለግንባር ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የሚጋጭ ተቃርኖን በልባቸው ፈጥረው በቀን ብርሃን አምፀው አደጋን ለመጣል ሲጣጣሩ ይታያሉ። ኢዮብ 24፥13፡ አዎን፥ አርዮሳውያን እላይ በዝርዝር ላቀረብነው ለመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተቃራኒ ሆነው ቆመዋል።

1ኛ፥ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ባሰበ ጊዜ «ከባሕርዩ ውጭ የሆነ ባዕድ ቃልን መፍጠር ግድ ሆነበት» ይላሉ።

2ኛ፥ «ፍጡራን ሁሉ የተፈጠሩት እግዚአብሔር በፈጠረው ቃል ነው» ብለው ይናገራሉ። መቼም ይገርማል? እንደዚህ ዓይነቱን አስተሳሰብ ለምን ሲሉ ከልባቸው እንዳፈለቁት እንደፈጠሩት የሚደንቅ ነው?

በኦሪት ዘፍጥረት 1፥3-23 ላይ በግልጽ ተጽፎ እንደሚታይ እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ በነባቢ ቃሉ በተናገረ ቍጥር፥ ፍጥረታት ሁሉ እንደተፈጠሩ ካለመኖር ወደመኖር ካለመሆን ወደመሆን እንደመጡ ተነግሮአል።

እነሆም ይህን አስቀድሞ ያነበበና ያጠና ሰው፥ አርዮሳውያን ከራሳቸው ፈጥረው በተናገሩት አባባላቸው፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ብሩህ እውነት ፊት ለፊት ሲቃረኑ አይቶ ቢደነቅ ይበዛበታልን?

ዘመናውያን አርዮሳውያን ወደ ሀገራችን ገብተው ይህን ከላይ የተጠቀሰውን አነጋገራቸውን ምንም ሳያፍሩ ባሰሙበት ጊዜ፤ ብዙ ሰው በመደመም ያተኰረው ከንግግራቸው ይልቅ ወደ ሕሊናቸውና ወደ አስተሳሰባቸው ነበር።

ይኸውም፦

1ኛ፥ እግዚአብሔር ይሁን ብሎ በሚናገርበት ጊዜ፤ ፍጥረታት እንደተፈጠሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብ ግልጽ ሆኖ የተጻፈውን በመተዋቸው ነው።

2ኛ፥ ይባስ ብለው ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተነገረውና በተጻፈው ፈንታ፥ ተቃራኒ የሆነ ነገር ከገዛ ሕሊናቸው አውርዝተው «እግዚአብሔር ባዕድ ቃልን ፈጥሮ ነው፤ ፍጥረታትን የፈጠረበት» ብለው በመናገራቸው ነው። የተጻፈውን ትቶ ያልተጻፈውን ማንበብ፥ የተነገረውን አስቀርቶ ያልተነገረውን መናገር፥ የሚያስደንቅ አይደለምን?

እንዲህ ሲያደርጉ ድርጊታቸው እውነትን የሚቃረን መሆኑን ዘንግተውት ነውን? ምናልባትም እውነትን የሚቃረን ነገር ሁሉ ውሸት ያይደለና ከውሸት የማይቈጠር መስሎአቸው ይሆን?

ይህንና የመሳሰለን ጥያቄ በልቡ ሲያወጣና ሲያወርድ መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበ ሰው በእነዚህ ሰዎች አባባል ተጨንቆበታል ተደንቆአልም። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው እግዚአብሔር «ይሁን አለ» እያለ በሚናገር ጊዜ፤ በዚሁ ነባቢ «ተናጋሪ» ቃሉ ፍጥረታት መፈጠራቸው በግልጽ የሚታይ ነው።

ይኸውም፦ እግዚአብሔር ይሁን ብሎ የገዛ ራሱ እየተናገረ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃሉ የመናገሪያ ቃሉ መሆኑ ታውቆ እያለ፤ የመናገሪያ ቃሉን ፈጠረ ለማለት እንደማያስችል ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው ሁሉ፥ ይስተዋል ተብሎ የማይታሰብ ነው። እንደዚሁም ደግሞ እግዚአብሔርን ኢነባቢና የመናገሪያ ቃል ያልነበረው ዲዳ እንደሆነ የሚቈጥረው የመጽሐፍ ቅዱስ አማኒ የማይኖርና የማይገኝ ነው። እነዚህ ግን ምን መሆናቸው ነው. መዝ 93/94/፥11። ዘጸአ.4፥11።



# ምዕራፍ ፫

## የእግዚአብሔር ቃል የኃይል ቃል ነው።

መዝ. 28/29/፥4።

እኔም ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጕልህ ሆኖ የተገለጸውን ትምህርት አርዮሳውያን ለምን እንደጠሉትና በልባቸው ሊገባ እንዳልቻለ፥ በአሳባቸው ውስጥም ስፍራ ያጣው በምን ምክንያት እንደሆነ፥ ይልቁንም የዚህን ያህል ከእውነት ለመሸሽና ለመራቅ የበቁበት ምክንያት ከምን የተነሣ እንደሆነ ለመረዳት ተጨንቄ አስብበት ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሥረ ነገሩ ለብዙ ጊዜያት አልተገለጸልኝም ነበር።

ሆኖም! ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ የአርዮሳውያን አስተማሪ እቤቴ ድረስ መጣና ስለሚያስተምረው ትምህርቱ ይናገር ጀመር። በዚህም ጉዳይ እየተጠያየቅን በምንናገርበት ጊዜ፤ አርዮሳዊው አስተማሪ ሳያስበው በድንገት አንድ ፍንጭ አወጣልኝ።

እርሱስ ለካ በዘመናውያን አርዮሳውያን ልብ የተረገዘ፥ ከትክክለኛው ልቡናዊ ተመርሆ ባዕድ የሆነ፥ ተፈላሰፍን ብለው የያዙት ግኖስቲኮች የተጧጠጠ የራሳቸው አስተሳሰብ ኖሮአቸዋል።

ይህም አርዮሳዊው ሰው ሳያስበው ያወጣልኝ ፍንጭ እንደሚከተለው ነው። «እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሊፈጥር ባሰበ ጊዜ፤ እንደ መኪና ያለውን መሣሪያ መፍጠር ግዴታ ስለሆነበት፤ ይህን መሣሪያ ፈልስፎ ፈጠረና፤ ቃል ብሎ በመሰየም በዚሁ ፍጡር ቃል ፍጥረታትን መፍጠር ቀናው ወይም ቻለ» የሚል ነው።

እኔም ምነው! ልዑል እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ የሆነ የሚናገርበት ቃል አለው። በዚህ በዘለዓለማዊ ቃሉም እየተናገረ፤ ፍጥረታትን እንደፈጠረ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾአል። ታዲያ ኢፍጡር በሆነ ቃሉ ዓለማትን ለመፍጠር አልቻለም፤ አይቻለውምም ማለትህ ነው? ወይስ በዚሁ ባሕርያዊ ቃሉ «ይሁን» እያለ ፍጥረታትን ለመፍጠር ኃይልና ችሎት አይኖረውም ማለትህ ነው? ብዬ ጠየቅሁት። ዘፍጥ. 1፥3-21። መዝ. 32/33/፥9።

እርሱም መልሶ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር የሚቀናውና የሚሰላለት፤ ፍጥረታትን ለመፍጠር የሚያስችል ኃይልና ችሎት ያለውን መሣሪያ ፈጥሮ፤ እርሱንም ቃል ብሎ በመሰየም ፍጥረታትን ቢፈጥር እንጂ፤ የመናገሪያ ቃል ቢኖረውም ለመፍጠር ኃይለኛ ችሎታ ስለማይኖረው፤ አልፈጠረበትም አለ። ወዲያውም ንግግሩን በመቀጠል ለምሳሌ አለና ጣቱን ወደ እኔ በመቀሰር እነሆ

በመናገሪያ ቃልህ አንድን ነገር ልታደርግ አትችልም። እግዚአብሔርም እንደዚሁ ነው እያለ፣ ሁሉን ከሚችል እግዚአብሔር ጋር ያመሳስለኝ ጀመረ።

ለቅዱስና ለክቡር ስሙ ኃይልና ታላቅነት ችሎትና ገናናነት ይሁንና ልዑል እግዚአብሔርንና ቃሉን፥ ኃይልና ችሎታ በሌለው፣ ፍጡር በሆነ ሰውና በሚናገርበት ቃሉ ዐቅምና መጠን እያመሳሰለና እያወዳደረ እያመጣጠነና እያስተካከለ ይህ አርዮሳዊ ተናገረ።

እኔም እንዴት እንደዚህ አድርጎ ሊያስብ እንደበቃ ከጠየቅሁት በኋላ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ማስረጃ እያቀረብሁ ላስረዳው ሞከርሁ። እርሱም ይህ ያመነበት የወገኖቹ ፍልስፍናዊ አመራር መሆኑን፣ ከዚሁ አመራሩ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሺ የማስረጃ ጥቅስ ቢቀርብ፣ ባጭሩ የመጣ ቢመጣ ፍንክች «ንቅንቅ» የማይል መሆኑን በቀጥታ አስታውቆኝ ተለያየን።

አርዮሳዊው መምህራቸው ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ተፈላስፍን ብለው የሚጓዙበትን አስተሳሰብ እንደገለጸልኝ፣ በጣም ገረመኝ። ብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ስንከራከር፥ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት እየጠቀስን ስናሳያቸው ለመረዳት እያማራቸው፣ እንደገና የሚድረቀረቁትና እንዳይገባቸውም የሚከላከሉት ለካስ ለእዚሁ በልባቸው ውስጥ ከተደበቀውና እንደ ትልቅ ፍልስፍና አድርገው ከሚቈጥሩት አስተሳሰባቸው የተነሣ ኖሮአል!

በእውነቱ እኔ እውነተኛ ትምህርትን እንዳይቀበሉ ከውስጥ ወደ ውጭ እየገፋ የሚያስቸግራቸው ይኸው ድብቅ ፅንስ መሆኑን አላውቅም ነበር። ይህ አርዮሳዊ አስተማሪ ምሥጢራቸውን ከገለጸልኝ ወዲህ ግን፣ እስከዚህ ድረስ ከእውነት ርቀው በመሄዳቸው አዘንሁ።

በሚመኩበት በዚሁ አለን በሚሉት ፍልስፍናቸው አንጻር «ትይዩ» ፈጽሞ ሊዘነጋ የማይገባ ትልቅ ነገር እንደነበረ አላስታወሱም። ይኸውም እግዚአብሔር እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ ነበር። ዘጸአ.3፥14፡ መዝ. 82/83/፥18።

አዎን! ይህን ቢረዱ ኖሮ፥ እግዚአብሔር ራሱ «ይሁን» እያለ ተናግሮ ዓለማትን የፈጠረበት ቃሉን ውሱን ሆኖ በተፈጠረው ሰውና በሰብአዊ ቃል ዓቅም መጠን ለማስተካከል ባላሰቡምና ባልቃጡም ነበር። መዝ. 88/89/፥6-8። ኢሳ. 44 6፤7። ም. 55፥11። በሕገ ምጣኔ የማይታሰብ የማይቃጣ ነውና!

አዎን! በሰው ልጆች ታሪክ እንደሚታወቀው ሁሉ፥ ፍጡር ሰው በቃሉ ተናግሮ ስንኳን ያልነበረውን ነገር ካለመኖር ወደመኖር ሊያመጣና ሊፈጥር ቀርቶ፣ ከቤት ውስጥ የሚገኝን መናኛ ዕቃ እንኳ ከዚህ ተነሥተህ ሂድ ወይም ወደዚህ ና ብሎ ቢናገር ቢያዝዝ ዕቃውን ካለበት ሊያንቀሳቅሰው አይችልም። አይቻለውምም። ይኸውም ከሰው የሚነገር ቃል ምንም እንኳ ከውስጣዊ አሳቡና ፈቃዱ የተያያዘ ቢሆንም፣ ከሰው የሚነገር ቃል አንድን ነገር ከቦታ ወደቦታ ለማዟዟርም ሆነ ለማራቅ፣ ለማቅረብ ሆነ ፈቀቅ ለማድረግ የማይቻለው የሕገ ተፈጥሮ ድንጋጌ በመሆኑ ነው። ኢዮብ 39፥37። ም.34፥35።



እግዚአብሔር ግን እግዚአብሔር ነው። ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፣ በዓለም የሚኖሩ ሁሉም ከእርሱ የተነሣ ይደንግጡ። እርሱ ተናግሮአል፣ ሆኑም። እርሱ አዘዘ ጸኑም። መዝ. 32/33፥8፤9። እርሱ ብሎአልና ሆኑም። እርሱ አዝዞአልና ተፈጠሩም። ዘፍጥ. 1፥3-27። ኢሳ. 14፥24። ም. 55፥11። እያለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገርለታል።

እነሆም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በእግዚአብሔር ቃል መካከልና ውሱን ሆኖ በተፈጠረ ሰው ቃል መካከል ያለው የዐቅም ከሂል «የችሎታ» መጠን የቱን ያህል የተራራቀና የተለያየ መሆኑን የእግዚአብሔርን ማንነት ያወቀ ሰው የሚረዳው ነው። ኢዮብ 36፥22፤23። መዝ. 101/102/፥2፤3-26።

አርዮሳውያን ግን እንደዚህ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን መሠረተ ነገር በማየትና አውጥተው አውርደው በማመዛዘን ፋንታ የግፋን የግልንቢጦሽ ይናገራሉ።

1ኛ፥ የልዑል እግዚአብሔር ዘለዓለማዊና የማይወሰን ፍጹም ኃያልና ከሀሊነት «ችሎታ» እንደሌለው፣ ከባሕርዩ ህልው በሆነ ቃሉ ተናግሮ ዓለማትን ወይም ፍጥረታትን መፍጠር እንደማይቻለው አድርገው ውሱን በሆነ በሰው ዐቅምና በሰው ቃል ምጣኔ ወሰኑት። ፍጥረታትን ለመፍጠር መለኮታዊ ኃይልና ችሎታ የሌለውን አንድ ፍጡር ፈጥረው፣ ደግሞ ይህ ነው ዓለም የተፈጠረበት ቃል እያሉ፣ የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር በባሕርይ ቃሉ የፈጠረውን ዓለም «ፍጥረት» ወስደው ለፍጡሩ ቃላቸው በነፃ ሸለሙት።

2ኛ፥ ልዑል እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ተናግሮ፥ ዓለማትን ከፈጠረበት ከባሕርያዊ ቃሉ ኃይልና ከሂል ይልቅ፣ «ፍጥረታት እንዲፈጠሩበት መፈጠር አለበት ለሚሉትና የገዛ ራሳቸው ቃል» ብለው ለሰየሙት ፍጡራቸው ከባሕርይ ግብር የሌለበትን የፈጣሪን ውዳሴ አከናነቡት።

ይህንም ተፈላሰፍን ብለው በሚራቀቁበት ሁኔታ ሰው በተፈጥሮው ዓቅም ስለሚያንሰው የሚፈለገውን ሥራ ለማከናወን ከራሱ ሁለንተና ውጭ ኃይልና ጉልበት ያላቸው እንደ መኪና እንደ ሸማኔ መወርወሪያ፣ እንደ መዶሻ ያሉትን ነገሮች ፈልስፎ ሠርቶ እንደሚጠቀም ያህል፣ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ኃይልና ከሂል «ችሎታ» በማገማመት አስተካክለው ማየታቸው ነው።

ኧረ ለመሆኑ! የእግዚአብሔር ባሕርያዊን ኃይልና ከሂል ተሻምተው በመንጠቅ እግዚአብሔር ለማያውቀው በገዛ ራሳቸው ፈጥረው የዓለማት ፈጣሪ ላደረጉት ቃላቸው ሲሰጡትና እግዚአብሔር በባሕርዩ ቃል የፈጠራቸውን ዓለማት ወይም ፍጥረታት እየሰጡ ሲያመልኩ አምልኮታቸው ከየት ተነሥቶ ወደየት ተሻግሮ እንደሄደባቸው ዘወር ብለውም እንኳ አላዩ! ይገርማል!

ሐዋርያው ጳውሎስ «የማይታይ ባሕርዩ እርሱም የዘላለም ኃይሉና ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና» ብሎ ስለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ኃይልና ባሕርይ ከገለጸ በኋላ

«የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ፣ በፈጣሪም ፋንታ የተፈጠረውን አመለኩና አገለገሉ።» እያለ ከተናገረላቸው ከአሕዛብ አምልኮት፣ የእነዚህ የአርዮሳውያን ወገኖች አምልኮት ምን ያህል ነው የሚራራቀው! ሮሜ 1፥20፤21-25። እስቲ ነገሩን በቁም ነገር እንመርምረው።

እነዚህ አርዮሳውያን ልዑል እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ መጠን እንዳይመለክ፣ ከእግዚአብሔርነቱ የዘለዓለም ኃይሉንና ብርታቱን ነጥቀው ፍጥረታት እንዲፈጠሩበት መፈጠር አለበት ለሚሉት፣ ለፍጡር ቃላቸው ወስደው አከናንበውታል።

እግዚአብሔርን ዐውቀው እንደ አምላክነቱ መጠን አከብረውታል እንዳይባል፣ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ኃይልና ከሀሊነት ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ ካልተገኘ፣ ፍጥረታት እንዲፈጠሩበት መፈጠር አለበት ከሚሉትና በአሳባቸው ከወለዱት በመሣሪያነት አቋም ከሚመለከቱት ከፍጡር ቃላቸው ዝቅ ያለና ያነሰ አድርገውታል።

ከልዑል እግዚአብሔር የላቀ የኃይልና የችሎታ ብልጫ እንዳለው በመገመት ከገዛ ራሳቸው የፈለሰፉት ቃላቸው ደግሞ የክብረ ምልክና አምልኮትም ሊሰጠው ፈጽሞ የማይቻል ነውና፣ ፍጡር ግቡር እየተባለ ደግሞ ክብር ምልክና አምልኮትም ሊሰጠው ፈጽሞ የማይቻል ነውና።

ከባሕርዩ ኃይልና የመፍጠር ችሎታ ሳይኖረው እንዲህ ተደርጎ የሚመለክ አምላክ በአሕዛብ አስተሳሰብ ይኖር እንደሆን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው በተማሩ ክርስቲያኖች ዘንድ መቼም መች አልተሰማም፣ አልታየም። ኤር 10፥11። አርዮሳውያን የማይታየውን ባሕርይ ይኸውም የዘላለም ኃይሉና አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ግልጽ ሆኖ ታውቆ የሚታየውን ከእግዚአብሔር ገፍፈው ለፍጡር ቃላቸው ለማጎናጸፍ ታጥቀው መነሣታቸው የሚገርም ነገር ነው። ነገር ግን ይቻላቸዋል ወይ?

እነሆም ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጭ፣ ያለ መንፈስ ቅዱስ መሪነት የሚነዳና በገዛ ራሱ አሳብ በምን አለብኝ ተመክቶ ብቻውን የሚጓዝ ሰው ከአንዱ እርከን ሲወድቅ፣ እየነጠረ ወደሌላ እርከን በመንደባለል እየተፈረካከሰ እንደሚወርድ የገደል ናዳ፣ ከአንዱ ስሕተት ወደ ሌላው ውድቀት እየቀጠለ መሄዱን በዚሁ ማየት ነው።

እነዚህ ሰዎች መጀመሪያ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ቃል እንደ መናኛ ነገር ጠሉ። ቀጥለውም ለመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተቃራኒ የሆነ፣ ከንባብ ያልተገኘ ትርጓሜን ፈልስፈው በተመሩ ጊዜ፣ አህዛብ ከሚያመልኩት ኃይልና ችሎት ከሌለው ጣዖት በምንም ያልተለየ ግራ የሚያጋባ አምልኮትን ፈጥረው ተጓዙ።

የሚገርመው ደግሞ የዚህን ያህል ርቀው እየነጐዱ ሳለ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሊጠቅሱ ይቃጣሉ። በእውነት በቁም ነገር እንደሚገባ ቢያስቡበት ኖሮ፣ ልዑል እግዚአብሔርን የመፍጠር ኃይልና ችሎታ እንደሌለው ቈጥረው፣ ኃይሉንና



ክሂሎቱን ከእርሱ ነጥቀው ፍጥረታትን ለመፍጠር የሚቻለው በመሳሪያነት የቆመና የተፈጠረ ቃል ነው ብለው በገዛ ራሳቸው በዳሰሳ ወይም በመላ ለፈጠሩት ፍጡር የፈጣሪነትን ሥራና ሙያ ሰጥተው፣ እንዲህ ባለው አምልኮት ሊመሩ በበቁ ነበርን? 1ቆሮ. 12፥2። ኤፌ.4፥17፤18።

በመጽሐፈ ምሳሌ የእግዚአብሔር ቃል የተፈተነች ናት። እርሱ ለሚታመኑበት ጋሻ ነው። እንዳይዘልፍህ ሐሰተኛ እንዳትሆን በቃሉ አንዳች አትጨምር ተብሎ የተነገረው እንዲህ እንዳይሆን አልነበረምን? ምሳ. 30፥5፤6።

የልዑል እግዚአብሔር የምልዐተ ባሕርይ ግብር የሆነውን ኃይል፥ ችሎት ገፍፈው ለአምላክነቱ የተገባውን ክብረ ምልክና ሊያሳጡት እስኪነሡ ድረስ፣ ይህን ያህል መጣጣራቸው ምን እንዲያገኙ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ላላወቀው፥ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ ላልታወቀ ከአሳባቸው ፈጥረው ዓለም ተፈጠረበት ለሚሉት መሣሪያ ለመሰሉት ቃል፣ የመፍጠር ኃይልና ችሎታ እንዳለው ለማድረግስ መፈለጋቸው ለምንድን ነው? ምንስ እንዲጠቀሙ ነው?

አንባቢ ሆይ! ይህን ከልዑል እግዚአብሔር ይልቅ ኃይልና ችሎት ኖሮት «ዓለማትን ሊፈጥር ይችላል» የሚሉት መሣሪያ ጠቀስ ቃላቸው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ ያልታወቀና ፈጽሞ ያልተነገረ ነው ማለታችንን ሰምተሃል። ይህ እግዚአብሔር ዓለማትን ለመፍጠር ኃይልና ችሎት ስላልነበረው፣ በመሣሪያነት ሊጠቀምበት መሣሪያ ጠቀስ ነገር ፈጥሮ በዚሁ መሣሪያ ጠቀስ ዓለማትን ፈጠረ የሚል ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ስፍራ ጭራሽ የማይገኝ መሆኑን ስለተገነዘብንና አንተም ራስህ አንብበህ የምትረዳው መሆንህን ስላወቅን ነው።

እንደዚህ ያለው አሳብና አስተሳሰብ ከአርዮሳውያን አንጎል የወረዛ ነው እንጂ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳብና አስተሳሰብ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ስላልታወቀና ስላልተነገረም እኛም ያላወቅነው ከዚሁ የተነሣ መሆኑንም ማንም ይወቅልን። በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ ግን ፍጡር ያልሆነ በልዑል እግዚአብሔር ህልውና የኖረ ሕያው ማሕየዊ የሆነ እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ በሚናገርበት ጊዜ ፍጥረታትን የፈጠረበት ካለመኖር ወደመኖር ፍጥረታትን ያመጣበት የመናገሪያ ቃሉን ነው። ዮሐ.1፥1። መዝ. 32/33፥8፤9። ዘፍጥ.1፥3-27። ዕብ.2፥10

ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ፍቆ ለማስተባበል እስካልተቻለ ድረስ፥ ዓለማትን በመፍጠር ፍጡር ፈልስፎ ለመተካት እንደማይቻል አርዮሳውያን ሊያስቡበት በተገባቸው ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል የመናገሪያ ቃል ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረና ያለ፥ ከእርሱም የማይለይ በሆነበት ኑባሬ፣ እግዚአብሔር ራሱ የፍጥረታት ፈጣሪ እንደሆነ መገለጹ በማያሻማ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ መስክሮለት አድርጓል። መዝ. 32/33/፥8-9። ዘፍጥ. 1፥3-27። ዮሐ. 1፥1-3።

ይህም ልዑል እግዚአብሔር ይሁን እያለ ተናግሮ ፍጥረታትን ወይም ዓለማትን የፈጠረበት ቃሉ ከፍጥረታት የማይደገፍና የማይታገዝ መለኮታዊ ኃይልና ከሂል «ችሎት» ያለው ለመሆኑ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኙ የቅዱሳት መጻሕፍት ኅብረተ ቃላት እያመሳከርን እንደሚከተለው እንገልጻለን።



# ምዕራፍ ፯

## የልዑል እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ኃይልና ችሎታ።

ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል «ከሀሌ ኵሉ» የሚሳነው ወይም የሚያቅተው ነገር የሌለ፣ ኃይሉና ክሂሎቱ በሰው ዐቅምና ችሎታ የማይመጠን የማይነጻጸር፣ የማይገመት፥ መመጣጠኑና መገመቱ ቀርቶ በሰው አሳብና አእምሮ እንኳ ሊመጠን፥ ሊወሰን ፈጽሞ የማይቻል ስለመሆኑ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተነገረና የተገለጸ ነው። መዝ. 65፥3። ም. 23/24/፥8። ም. 6፥26። ኢዮ. 5፥22። መዝ. 88/89/፥8። ይሁዳ. ቍ. 25። ራዕ. 4፥11።

ዳግም ሁሉ ከእርሱ፥ ሁሉ በእርሱ፥ ሁሉ ለእርሱ ሲፈጠር፣ ያለምንምም ባዕድ ተጨማሪ ፍጥረትን ፈጥሮ ማምጣቱና፣ በሚፈጥር ጊዜ፣ ፍጥረቱን በሚመግበበት በሚያስተዳድርበት ጊዜ፣ በሚያድንበትም ጊዜ ሁሉ፣ እንደዚሁ በራሱ ለራሱ ያከናውናል እንጂ፣ ከመለኮታዊ ባሕርዩ ወይም ህልውናው ውጭ አጋዥ ረዳት ደጋፊ አማካሪ፣ አስተማሪ፣ ያላሻው የማያሻው የማያስፈልገው ስለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ አድርገው ሲያብራሩ ይገኛሉ። ኢሳ. 40፥12-28። ም. 45፥12፣18። ኢዮብ 41፥2፣3። ም. 26፥2፣14። ዳንኤ. 2፥20። ኤር. 32፥17፣19 ቍ. 27። ም. 10፥6፣13። ነህ. 9፥6። ሮሜ 11፥36። ኢሳ. 51፥1፣13። 2ሳሙ. 7፥7 21፣22። ኢዮብ 36፥5። ም. 37፥23።

ስለዚህ እንደተጻፈው ኢፍጡርና ከተፈጥሮ ንጹሕ ወይም ነፃ ከሆነ መለኮታዊ ባሕርዩ በሚገኝ ቃሉ ተናግሮ ዓለማትን የማይፈጥርበት ምክንያት ስለሌለ «ይሁን» እያለ ያለ ውጭ አገዝና እርዳታ በመናገሪያ ቃሉ ዓለማትን ፈጥሮአል። ዘፍጥ. 3፥26። ዕብ. 11፥3። ኢዮብ 38፥8፣11።

### የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና አድራጊ ስለመሆኑ፣

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጸ የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና አድራጊ ነው። ሕያውና አድራጊ በሆነ ቃሉ ልዑል እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ሲናገር፣ ፍጥረት ሁሉ ካለመኖር ወደመኖር ከኢምንት ወደ ምንት በቅጽበት መጣ። ሆነ ተፈጠረ እንጂ፣ አልመጣም አልሆንም አልፈጠርም ብሎ በእምቢታ የቀረ ወይም የሚቀር ፍጥረት ፈጽሞ አልተገኘም። ዘፍጥ. 1፥2፣22። ዕብ. 12። ም. 11፥3። ም. 1፥2። ቈላ. 1፥15፣17። 2ጴጥ. 3፥5፣7። ኢሳ. 55፥10፣11። ኢዮብ 2፥11።

ባጭሩ እስመ ውእቱ ይቤ ወኮኑ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ ወዓቀሞሙ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ትእዛዘ ወሀቦሙ ወኢኃለፉ፡-

እርሱ በተናገረ ጊዜ ሆኑ። እርሱ ባዘዘ ጊዜም ተፈጠሩ ለዘላለም በደነገገላቸው አቋምም ኖሩ። ትእዛዝ ሰጣቸው አልተላለፉም ሲል ዳዊት በመዝሙሩ ገልጾታል። መዝ. 148፥1፤6።

## የእግዚአብሔር ቃል ሁሉን በችሎቱ ሥልጣን የሚይዝ ቃለ ኃይል ነው።

እነሆም «ዘይእኀዝ ኵሎ በቃለ ኃይሉ» በቃሉ ችሎት ሁሉን የሚይዝ «የሚደግፍ» ዕብ. 1፥3። እርሱ ባለ ጊዜ ወይም በተናገረ ጊዜ ሆኑ ባዘዘ ጊዜም ተፈጠሩ ሲባል፤ የእግዚአብሔር ቃለ ኃይል በሆነና በተናገረበት ቃሉ ዓለማት ለመፈጠራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ታውቆ ተጠንቅቆ ተነግሮአል። ዕብ. 1፥1፤3። ኢሳ. 14፥24። ም. 55፥10፤11። 2ጴጥ. 3፥5፤7።

ከማሁ ውእቱ ቃልየ ዘይወጽእ እምአፉየ ኢይትመየጥ እስከ ይገብር ኵሎ ዘፈቀድኩ ወይሜርሕ ፍኖትየ ወትእዛዝየ ኢስፍርት። ኢሳ. 55፥10፤11።

ታዲያ «እግዚአብሔር አለ፤ አዘዘ ተናገረ» ተብሎ ሲነገር ይህ የተባለው እዝ ሆኖ የተነገረ ቃል አርዮሳውያን ፍጡር ከሚሉት ቃል ጋር ይዛመዳልን? እንዲሁም እግዚአብሔር አለ፤ አዘዘ፤ ተናገረ እየተባለ ሳለ፤ የተፈጠሩና የሆኑ ፍጥረታት ሁሉ በፍጡር ቃል ተፈጠሩ ለማለት በልቡናዊ ተመርሆ ያስኬዳልን?

ደግሞስ እግዚአብሔር ተናግሮ ፍጥረታትን የሚፈጥርበት ወይም የፈጠረበት ሕያውና አድራጊ ከሃሊም ቃል እያለው፤ እንደገና ተመልሶ ፍጥረታትን የሚፈጥርበት ከባሕርዩ ውጭና ሌላ ባዕድ ቃል ለመፍጠር የሚያስጨንቀው ምን ጉዳይ ይገኛል ተብሎ ነው? ኢሳ. 14፥24።

እንዲያው በከንቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና እምነት ያልመነጨውንና በምንም አኳኋን ተዘምዶ የሌለውን አሳብ በመፍጠር በተጻፈው ቅዱስ ጽሑፍ ፋንታ፤ ያልተጻፈውን ተክቶ በመናገር የልዑል እግዚአብሔርን ከሂልና የኃይል ታላቅነት እስከዚህ ማጉደፍ፤ ለምን እንደሚጠቅም ሲያስቡት በእውነቱ ይቸግራል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡- ስለ እግዚአብሔር ቃል ስንናገር በእግዚአብሔርና በቃሉ ስላለው የህልውና አንድነት በዚሁ ካየን፤ ቃሉ ዝርው ቃል ብቻ አለመሆኑን ቃሉ አካላዊ መሆኑን ወደፊት ገለጻው እየበራ ሲሄድ አካልነቱ እየጉላ የሚታይበት ቦታ መኖሩን ለአንባብያን እንገልጻለን። ዮሐ. 1፥1-3።



# ምዕራፍ ፯

# ስለ ጥበብ፤

## አርዮሳውያን እግዚአብሔር ጥበብን ፈጥሮ ዓለማትን ፈጥሮአል እንጂ፤ ከባሕርዩ በሚገኝ ጥበብ ዓለማትን አልፈጠረም ይላሉ።

አርዮሳውያን ከዚሁ ሸሽት በማለት «ዓለም የተፈጠረ በጥበብ ነው፤ ጥበብም የተፈጠረች ናት» ይላሉ።

ይኸውም ያልተፈጠረውን የእግዚአብሔር ቃል መጀመሪያ የተፈጠረ ነው፤ ብለው ከጭንቅላታቸው አወርዝተው በልብ ወለድ እንደተናገሩ ሁሉ፤ አሁንም ያልተፈጠረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ መጀመሪያ የተፈጠረ ነው በማለት ከሐሳባቸው አወርዝተዋል።

ይህን ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ይሁን እያለ እየተናገረ በመናገሪያ ቃሉ ዓለም እንደፈጠረ የተገለጸውን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ከደው ዓለም የተፈጠረው በፍጡር ቃል ነው እያሉ፤ እንደተናገሩ ሁሉ፤ ስለ እግዚአብሔር ጥበብም በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን ከደው እግዚአብሔር ከባሕርዩ ጥበብ ያልነበረው አድርገው ጥበብን ፈጥሮ ሲያበቃ ዓለምን ፈጠረ በማለት ይናገራሉ።

እንዲያው ለነገሩ፥ በፍጡር መፈጠርን የወደዱት ስለምን ይሆን? እነሆም በቃል ተፈጠርን ሲሉ ቃልን ፍጡር አድርገው ነው። በጥበብ ተፈጠርን ሲሉም ጥበብን ፍጡር አድርገው ነው። ለመሆኑ በፍጡር መፈጠርን የወደዱት ለምን እንደሆነ ብንጠይቃቸው ይነግሩን ይሆን? ከመደበኛ ዘለዓለማዊ ርኅሩኅና ጻድቅ ከሆነ ከባሕርይ ፈጣሪ ይልቅ፥ የተሠራ የተደረገ፤ የተፈጠረ የተከወነ የጣዖት ውሽማ ሰብአዊ ሕሊናን የሚያረካና የሚያዛልቅ መስሎአቸው ይሆን! ሆሴ. 4፥12።

እኔ ግን የባሕርይ አምላክ የሆነ ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ፤ እንኳን በፍጡር አልተፈጠርሁ እንጂ፤ በፍጡር ተፈጥሬ ብሆን ኖሮ፥ ምን ያህል በቀፈፈኝ እውነቱን ብናገር፥ የማደርገው ባጣ፥ ታንቄ እሞት ነበር። የፍጡር ፍጡር መሆን ቀርቶ፥ የፍጡር ባሪያ መሆን እንኳ፥ ምን ያህል ሥቃይና ጭቆና አለበት። ያም ሆነ ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ፤ በማስተዋልም ሰማያትን አጸና በእውቀቱም ቀላያት ተቀደዱ። ደመናትም ጠልን ያንጠባጥባሉ ይላል። ምሳ. 3፥19፤20።

ደግሞ ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለምን በጥበቡ የመሠረተ፥ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው ይለዋል እንጂ፤ ጥበብን ፈጥሮ ከዚያ በኋላ ዓለምን ፈጠረባት አይልም። ኤር. 51፥15።

«ዘገብረ ሰማያተ በጥበቡ ወአጽንዐ ለምድር ዲበ ማይ፣ ሰማያትን በብልሃቱ የሠራ ምድርንም በውኃ ላይ ያጸናት» እያለ በፍጡር ጥበብ ሳይሆን፣ ከባሕርዩ በሚገኝ ጥበብ እንደፈጠረን፣ እየገለጸ መጽሐፍ ቅዱስ ያስደስተናል። መዝ. 135/136/፥5። ኢሳ. 40፥28።

አርዮሳውያን ስለ እግዚአብሔር ህሉና «አኗኗር» ባላቸው አስተሳሰብ አንድ ችግር እንዳለባቸው ይታያል። ይኸውም ሕይወትና ልቡና አሳብና አእምሮ እውቀትና ጥበብ ማስተዋልና ሕሊና ኃይልና ክሂል ቃልም ባጭሩ እነዚህና የሚመስሉአቸው በዐውደ ልባዊ አእምሮና ሕይወት የሚገኙት የባሕርይ መግለጫዎች ሁሉ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ አሉ። የባሕርይ ገንዘቦች ሆነው ይኖራሉ። ብለው ሊያረጋግጡ አለመፍቀዳቸው ነው። ሕሊናቸው ለመረዳት በሚነቃበት ጊዜ እንኳ፣ ስለዚህ ያላቸው አስተሳሰብ ጭራሹን የመነመነ ነው።

እንደዚህም መሆናቸው ስላልገባቸው ይሁን፣ ወይም ሞገደው ይሁን አናውቅም። መረዳቱ ይቸግራል። ስለዚህም እግዚአብሔር በዕውቀቱ በማስተዋሉ በጥበቡ በኃይሉ፣ በክሂሎቱ፣ በቃሉ ዓለማትን ፈጠረ ሲባል፣ እነዚህን የተጠቀሱትን ከባሕርዩ ውጭ ፈጥሮ እንደፈጠረባቸው ያስባሉ። ከባሕርያዊ ህልውናው ከሚመነጨው ዕውቀቱና ማስተዋሉ፣ ጥበቡና ኃይሉ፣ ከሃሊነቱና ቃሉ ዓለማትን እንደፈጠረ መረዳት ግን፥ ግራ ይገባቸዋል። ይህ ለእነርሱ እንደከባድ ሸክም ሆኖ መረዳቱ ቢያቅታቸውም ደግሞ ቀጥሎ ባለው ምሳሌ ራሳቸውን ለማጽናናት ይሞክራሉ።

ይኸውም ቤትን ለመሥራት የሚፈልግ ሰው በገዛ እጁ ለመቈፈር፣ በገዛ እጁ ድንጋይ ለመፍለጥ፣ በገዛ እጁ ዕንጨትን ለመጥረብ ስለማይችል፣ ከሰውነቱ ውጭ ዶማና መዶሻ፣ መጥረቢያም አስቀድሞ መሥራት ወይም ፈልጎ ማግኘት ያሻዋል። እንደዚሁም ሁሉ እግዚአብሔር ዓለምን ለመፍጠር ሲሻ፣ አስቀድሞ ቃልን ወይም ጥበብን መፍጠር የግድ ያስፈልገዋል። ወይም የግድ ሆነበት። በሚል ግኖስቲኮች በተገኙ የፍልስፍና ፍርፋሪ አፋቸውን ይሞላሉ። ጠበቅ ያለ ጥያቄም ሲቀርብላቸው መምህሮቻቸው የሚናገሩት ይህን ነው።

በአባባላቸው ያለው አሳብ፦

1፥ እግዚአብሔር ዓለማትን ለመፍጠር የሚችልባቸው ቃልና ኃይል ወይም ጥበብና ክሂል ከእግዚአብሔርነቱ ወይም ከባሕርየ መለኮቱ ህልውና በስተውጭ ፈጥሮ እንዲያገኝ ተቀዳሚ ግዴታ መሆን እንዳለበት ነው።

2፥ እግዚአብሔር ከባሕርየ መለኮቱ ህልውና ውጭ ፍጡራን መሆን ያለባቸውንና ኃይልና ጥበብን ቃልና ክሂልን ፈጥሮ እስካላገኘ ድረስ ግን፣ መፍጠር የማይቻለው እንደሆነ ነው።

3፥ ፍጡራን በእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ በክሂልና በቃልም ሳይሆን፣ ከፍጡራን በሚገኝ ኃይል ነው የተፈጠሩት ወይም የሚፈጠሩ ማለታቸው ነው። መቼም እግዚአብሔር ከባሕርየ መለኮቱ ህልውና ውጭ ቃልንና



ክሂልን ዕውቀትንና ማስተዋልን፣ ኃይልንና ጥበብን ወዘተ... ሠርቶ እስካላመጣ ወይም እስካላገኘ ድረስ፥ ከራሱ ከህላዌ መለኮቱ ልቡናና አሳብ ሕሊናና ዕውቀት ጥበብና ማስተዋል ቃልና ኃይል ምክርና ክሂል የሌሉትና፣ በእነዚህም በባሕርዩ ግብራት ዓለማትን ሊፈጥርባቸው እንደማይቻለው አድርገው ሠርዘውታል፣ ይገርማል! እስከዚህ ድረስ ርቆና ጭልጥ ብሎ መሄድ ካልታጣ መጽሐፍ ቅዱስ ምነው እስከዚህ ድረስ ርቃችሁ ትሄዳላችሁ!

መጽሐፍ ቅዱስ እኮ! እግዚአብሔር ቃሉን ወይም ጥበቡን ምክሩንና ማስተዋሉን ኃይሉንና ከሀሊነቱን ወዘተ... መፍጠር ግዴታ ሆኖበት ፈጠረ፣ በፍጡራንም ዓለማትን ፈጠረ አይልም። ይህን አልፋችሁ ምን ትሆኑ!

አርዮሳውያን ይህን እርምጃ የወሰዱት ወልድን ይጠሉታልና፣ እርሱን የጐዱት ቢመስላቸው ነው። አርዮሳውያን እግዚአብሔር ቃል ወልድን ለመጕዳት ፈልገው በተነሡበት ዓላማቸው ወልድን ከእግዚአብሔር ባሕርየ መለኮቱ አንድነት ገንጥለው ለማውጣትና ለመለየት ለይተውም ፍጡር ለማድረግ ሲሞክሩ የተሳካላቸው መስሉአቸዋል። ይሁን እንጂ፣ በዚሁ ይዞታቸው ከቶውኑም እግዚአብሔርን አባቱን ባሕርያዊ ጥበብና ማስተዋል የሌለው ባሕርያዊ ልቡናና አሳብ የሌለው ባሕርያዊ ቃልና ኃይል የሌለው፥ ባሕርያዊ ጥበብና ማስተዋል የሌለው አድርገዉት ዐረፉ። እንዲህ እንደሚሆንባቸው አያውቁም ነበርን? በሀገራችን ሲተረት «የቆጡን አወርዳለሁ ብላ የ... ጣለች» የተባለው ቃል የደረሰባቸው ይመስላል።

# ምዕራፍ ፰

## አርዮሳውያን ይሆዋህ የሚሉት ምኑን ነው?

አርዮሳውያን ልዑል እግዚአብሔር ራሱ በባሕርይ ቃሉ ወይም ጥበቡ የፈጠራቸውን ፍጡራን በገዛ አሳባቸው ወስደው መጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ ለማያውቅላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ላልታወቀ፣ እነርሱ ራሳቸው በልብ ወለድ ለፈጠሩት ፍጡር ቃላቸው ወይም ጥበባቸው ሰጡበት። እግዚአብሔር ግን፣ የባሕርይ ሕይወትና ልቡና የባሕርይ ዕውቀትና አእምሮ፥ የባሕርይ ማስተዋልና ጥበብ፥ የባሕርይ ሕሊናና አሳብ የባሕርይ ቃልና ኃይል የሌለው ጉልት አምላክ ሊያደርጉት ተመኙ።

በዚህ ዓይነት ጉልት ድንጋይ ያደረጉት አምላክ ምን ዓይነት አምላክ ሊሆን ነው? መቼም እንደዚህ ያለው ጉልት አምላክ የእነርሱ ይሆናል እንጂ፣ መቼውንም የእኛ አምላክ አይደለም። 1 ነገ. 16፥25-39።

የሚገርመው ነገር ደግሞ «ይሆዋ» ማለታቸው ነው። ድንጋይ መሰል ይሆዋ አለ ወይ? ምን ዓይነት ድንጋይ መሰል ይሆዋ! ቋንቋው ዕብራይስጣዊ የአቋሙ አስተሳሰብ አረማዊ ስሙ ይሆዋ አኗኗሩ ድንጋይ አከል መሰል! ወይ ፈሊጥ! ግሩምኛ ፈሊጥ ነው እንደዚህ ያለም ይሆዋ የለ!

የሕያው እግዚአብሔርን ስም ይሆዋ በሚል በዕብራይስጣዊ ቋንቋ በመሸፈን በባሕርዩ ሕይወት፥ ልቡና፥ አሳብ፥ ሕሊና፥ ዕውቀት፥ አእምሮ፥ ጥበብ፥ ማስተዋል፥ ኃይል፥ ቃል፥ ከሂል፥ ፈቃድ፥ ምክር የሌለውን ሰው ሠራሹን ያውም እነርሱ ራሳቸው በአሳባቸው የፈጠሩትን ጉልት አምላክ ሊያስመልኩን ይሻሉን?

ዕብራውያንስ ይሆዋ የሚሉት፥ እንደዚህ ያለ ጉልት አምላክ አይደለም። የያዕቆብ ዕድል ፋንታ እንደዚህ አይደለም። እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና። ኤር. 10፥16።

ዕብራውያንስ «እግዚአብሔርን ግን እውነተኛ አምላክ ነው» እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው። ከቍጣው የተነሣ ምድር ትንቀጠቀጣለች። አሕዛብም መዓቱን አይችሉም። እናንተም ሰማይንና ምድርን ያልፈጠሩ እነዚህ አማልክት ከምድር በታች ይጠፋሉ ትልዋቸዋላችሁ። ምድርን በኃይሉ የፈጠረ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትን በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው በማለት በግልጽ የሚመሰክሩ ናቸው። ኤር. 10፥12-16። ተመልከት።

ደግሞ፦ «እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ፣ ከአማልክትም ሁሉ እንደሚበልጥ አውቄአለሁና፣ በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆችም ሁሉ፣ እግዚአብሔር



የወደደውን ሁሉ አደረገ» እያሉ የአምላካቸውን ማንነት ጠንቅቀው በማወቅ ዕብራውያን ያስታውቃሉ። መዝ. 134/135/፥5፣6። እንዲሁም አላወቅህምን? አልሰማህምን! እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው። አይደክምም አይታክትም፣ ማስተዋሉም አይመረምርም እያሉ ዕብራውያን እምነታቸውን አስታውቀዋል። ኢሳ. 40፥12፣14፡ ቍ. 128-28። መዝ. 32/33/፥6-12።

ዕብራውያን ይሆዋ የሚሉት፥ ኃይልና ጥበብ ያለውን እግዚአብሔርን ነው። «ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና፣ የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ።» ዳንኤ. 2፥20።

አዎን! ጥበብና ኃይል የእርሱ ነው። ተብሎ ሲነገር ጥበብና ኃይል በዘለዓለማዊ ባሕርዩ ያልኖረው ነው ማለት ነውን? ዕብራውያን እንደ አርዮሳውያን በአሉታ አይፈቱትም። ዕብራውያን ጥበብና ኃይል የእርሱ ነውና «የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፣ አሉ እንጂ፣ ጥበብና ኃይል ከባሕርዩ በማጣቱ ዓለማትን የሚፈጥርባቸውን ፍጡራን ኃይልንና ጥበብን ፈጠረ» አላሉም። እንዲህ አድርገውም በእውነተኛ አምላክ አያምኑም።

በጠቅላላው ዕብራውያን እውነተኛውንና ሕያውን አምላክ «ይሆዋ» ብለዋል እንጂ፣ ሕይወት የሌለውን የማይሰማውንና የማይለማውን ዕውቀት ጥበብ ማስተዋልና አእምሮ ኃይልና ቃል ሳይኖረው ባዶ የሆነውን አምላክ፥ «ይሆዋህ» አላሉም። በመሠረቱ ዕብራውያን እግዚአብሔርን «ይሆዋህ» ብለው የሚጠሩት ይህን ስሙን በገለጸበት ግብሩ መሠረት ነው።

ቃሉ ከተመሠረተበት ቦታ እስቲ አቅርበን እንመልከተው። «እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረ አለውም፥ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ለአብርሃምም ለይስሐቅም ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ «ኤልሻዳይ» ...ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር «ይሆዋ» አልታወቀላቸውም ነበር።»

«የተሰደዱበትንም ምድር የእንግድነታቸውን ምድር እሰጣቸው ዘንድ ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳኔን አቆምሁ። ደግሞ እኔ ግብፃውያን የገዙአቸውን የእስራኤልን ልጆች ልቅሶ ሰማሁ። ቃል ኪዳኔንም አሰብሁ። ስለዚህም ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከግብፃውያን ባርነት አወጣችኋለሁ። ከተገዥነታቸሁም አድናችኋለሁ። በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ። ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላችኋለሁ። አምላክም እሆናችኋለሁ። እኔም ከግብፃውያን ባርነት ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ። ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያቆብም እሰጣት ዘንድ ወደማልሁባት ምድር አገባችኋለሁ እርስዋንም ርስት አድርጌ እሰጣችኋለሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና።»

እነሆም እግዚአብሔር ለሙሴ በተናገረው ቃል ውስጥ እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል ተብሎ ስለተገለጸበት ስሙና የሰጠውን የቃል ኪዳኑን ፈጻሚና

የተናገረውን የተስፋ ቃል በተግባር ላይ ሲያውል በሚገኝበት ጊዜ ስለሚታወቅ ስሙ ተለይቶ ተገልጾ እንመለከታለን። ዘጸአ. 6፥2-8።

1ኛ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብ ተስፋውን በሚሰጣቸው ጊዜ፣ ልጆቻቸውንም ከሚገዙለት ሕዝብ ከባርነት ቤት አውጥቶ ለራሱ ሕዝብ አድርጎ የከነዓንንም ምድር አወርሳችኋለሁ ባላቸው ጊዜ፣ ሁሉን እንደሚችል አምላክ ሆኖ ተገልጦላቸዋል። ዘፍጥ. 15፥13-16።

እነርሱም እኔ ኤልሻዳይ «ሁሉን የሚችል ወይም የሚይዝ» ነኝ ብሎ ራሱን በገለጠላቸው መሠረት፥ ስሙ ሁሉን የሚችል መሆኑን አምነው ተስፋውን ያለጥርጥር ተቀብለዋል እንጂ፣ የተስፋ ቃሉ እግብር ላይ ውሎ ያዩት የጨበጡት ነገር አልነበረም። ዘፍጥ. 17፥11። ም. 35፥11፥1፣2። የሐዋ. 7፥5-7።

2ኛ፥ አሁን እግዚአብሔር ለሙሴ ሲነግረው ግን፤ ያን ሁሉን በሚችል ስሙ የሰጠውን የተስፋ ቃል እግብር ላይ ሲያውል በሚገኝበት እግዚአብሔራዊ ስሙ ይኸውም ዕብራውያን «ይሆዋህ» በሚሉት በግዕዝ «እግዚእ» በአማርኛ «እግዚአብሔር» በመባል ይታወቅለታል።

በመሠረቱም እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጠውን የተስፋ ቃል እግብር ላይ የሚያውልበትንና የተስፋውን ቃል ለፍጻሜ መድረሱን በዚሁ ስሙ ያስታውቃል።

እነሆም በዚህ ስሙ ከግብፃውያን ባርነት አወጣችኋለሁ ከተገዥነታችሁም አድናችኋለሁ፣ በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላችኋለሁ፣ አምላክም እሆናችኋለሁ፣ እኔም ከግብፃውያን ባርነት አወጣችኋለሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ፣ እንደሆንሁ ታውቃላችሁ፣ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እሰጣት ዘንድ ወደማልሁባት ምድር አገባችኋለሁ። እርስዋንም ርስት አድርጌ እሰጣችኋለሁ ብሎ ተናገረ። ተናግሮም አልቀረም እግብር ላይ በማዋሉ የተናገረውን የተስፋ ቃል በተግባር ላይ የሚያውል አድራጊ ፈጻሚ... ስሙንም በዚህ አስታወቀ። እነሆም ዕብራውያን «ይሆዋህ» ሲሉ እንደዚህ ሆኖ በተገለጸ ስሙ ዐውቀውታለና ያምኑበታል። ኤር. 32፥20። ነሀ. 9፥10።

እነሆም «ይሆዋህ» የሚል ቃል የተመሠረተበትን መነሻ አየን። ይኸውም አርዮሳውያን የማይሰማና የማይለማ ዕውቀትና ኃይል፥ ማስተዋልና ጥበብ፥ ቃልና ችሎት የሌለው አድርገው እንደሚያስቡት ሳይሆን፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ኪዳኑን የሚያጸና ቃሉን የሚጠብቅ፥ በፈቀደ ጊዜ የተናገረውን እሥራ ላይ በማዋል የሚገልጽና እግብር ላይ ማዋሉን የሚያሳውቅ ሆኖ እናገኘዋለን።

ስለዚህ እነሆ አስታውቃቸዋለሁ በዚህች ጊዜ እጄንና ኃይሌን አስታውቃ ቸዋለሁ። እነርሱም ስሜ እግዚአብሔር እንደሆነ ያውቃሉ ተብሎ ተጽፎአል። ኤር. 16፥21።



በመሠረቱ ዕብራውያን «ይሆዋህ» ሲሉ ስሙንና ተግባሩን ዐውቀው ይጠሩታል አርዮሳውያን «ይሆዋህ» ሲሉ በዕብራውያን አጠራር መሠረት ስሙንና ተግባሩን ዐውቀው ጠንቅቀው እንዲጠሩት እንመኝላቸዋለን።

## የአርዮሳውያን አስተሳሰብና ድቀት።

አርዮሳውያንን እንዲህ እስከመሆን ያደረሳቸው ከመሠረቱ ሲታይ፣ ቀጥለው ባሉት ነጥቦች ልንገልጽ እንወዳለን።

1ኛ፥ አርዮሳውያን እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር፣ ከባሕርዩ ባሉት ጥበብ፥ ክሂል፥ ቃል፥ ኃይል ፍጥረታትን አልፈጠረም ይላሉና ነው።

2ኛ፥ አርዮሳውያን እግዚአብሔር ከባሕርዩ ህልውና ውጭ የሆነ ፍጡር ቃልን ወይም ጥበብን ፈጥሮ ሲያበቃ ዓለማትን ወይም ፍጥረታትን ፈጥሮአል ይላሉና ነው።

3ኛ፥ አርዮሳውያን እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ፈልጎ፥ ፍጡር ጥበብን ወይም ፍጡር ቃልን እስካላገኘ ድረስ፣ ከገዛ ራሱ ከባሕርዩ ፍጥረታትን ለመፍጠር ይቻለዋል ብለው አያስቡምና አያምኑም።

4ኛ፥ አርዮሳውያን እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ሲኖር፣ በኋላ ዓለምን ለመፍጠር ፈለገ። ዓለምን መፍጠር ባስፈለገው ጊዜ ደግሞ፣ አስቀድሞ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበት ዐወቀ። ይኸውም ከባሕርዩ ህልውና ውጭ ፍጥረታትን ለመፍጠር የሚችል ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን ነው እያሉ ይናገራሉ። በዚሁ አባባላቸውም የእግዚአብሔር ባሕርያዊ በሆነ በዘለዓለም የመፍጠር ችሎቱ ላይ፥ አዋዋይ ግዴታን ይጭኑበታልና ነው።

5ኛ፥ አርዮሳውያን ዓለማትን ይፈጥር በነበረ ጊዜ፣ «ይሁን» እያለ ከባሕርይ ህልውና በሚኖር ቃሉ ሲናገር፣ «ሁን» ያለው ነገር ሁሉ እንደሆነ፣ በማስተዋሉና በጥበቡ ተራቅቆ፣ አሳምሮ ፍጥረታትን እንደፈጠረ፤ በግልጽ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ሙሉ በሙሉ ይቃረናሉ። ይህም አንሶ ይባስ ብለው ደግሞ ዓለማት የተፈጠሩት ፍጡር በሆነ ቃል፣ ወይም ጥበብ ነው እያሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ፊት ለፊት ቆመው ከባድ ተቃውሞ ያደርጋሉ።

እነሆም አርዮሳውያን ከአንጎላቸው ውስጥ ካፈለቁዋቸው አሳቦችና አባባሎች እነዚህን ተመልክተናል። እነዚህም ደግሞ ያስከተሉባቸውን መዘዞች ልናይ ነው።

አርዮሳውያን በተባሉት አሳቦች ከተጠመዱበት ጊዜ ጀምሮ፥ ልዑል እግዚአብሔርን ራሱን ማን እንደሆነ ሊያውቁትና ሊያምኑበት ይገባቸው የነበረው መሠረታዊውን ትምህርት ማየት እስኪሳናቸው ድረስ፥ ጭልጥ ብለው እንደተወሰዱ ልናይ እንችላለን። በዚሁ ሁሉ ተደራራቢ ውድቀት ምንም ያልተሰማቸው መሆኑን እንመለከታለን። መዝ. 9፥15፤16። ሮሜ 1፥28።

አርዮሳውያን ያፈለቁአቸው አሳቦች መጽሐፍ ቅዱስ መሠረቱ በሆነ በክርስቲያን ትምህርተ መለኮት ሲመረመሩ፣ እግዚአብሔር ከእውነተኛ እግዚአብሔርነቱ ወይም ሕያው እግዚአብሔር ከሚሰኝበት ከምልዐተ ህልውናው ውጭ የሚያደርጉት ሆነው እናገኛቸዋለን።

የዚህንም እውነት ለመረዳት አርዮሳውያን ካፈለቁዋቸው አሳቦች እና ከስሕተቶች እንዛዝላዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ትይዩ እያቀረብን ብንመረምር ተገልጾና ተበጥሮ የሚታይ ነው።

1ኛ፥ በቅድሚያ አርዮሳውያን «እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር ከባሕርዩ ህልውና ባሉት በጥበብና በማስተዋል በምክርና በዕውቀት በአሳብና በቃል በኃይልና በክሂል ፍጥረታትን አልፈጠረም። ያሉትን እንይ፡-

ይህ አባባል ምን ማለት ነው? በአጭሩ በአንጻር አወራረድ ሲታይ፣ እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር ያለ ልቡናውና ያለፈቃዱ፤ ያለ ምክሩና ያለ አእምሮው፣ ያለ ጥበቡና ያለማስተዋሉ፣ ያለዕውቀቱና ያለ ሐሳቡ ያለ ሕሊናውና ያለቃሉ ከሂሉቱና ያለኃይሉ እንዲያው ዝም ብሎ ዓለማትን ፈጠራቸው የሚያሰኝ ሆኖ ይገኛል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ነገር ምን ይል ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር በባሕርዩ ፈቃዱ አስበ ፍጥረታትን መፍጠሩ ሲያጸና በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ እግዚአብሔር የወደደውን አደረገ ይላል። መዝ. 134/135/፥6። ም. 113/114/፥11። ራእ. 4፥11።

ደግሞ በባሕርዩ ተጠብቦና አስተውሎ ፍጥረታትን ስለፈጠረ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በጥበቡ ምድርን መሠረተ፣ በማስተዋሉም ሰማያትን አጸና፣ በዕውቀቱም ቀላያት ተቀደዱ እያለ ተናግሮአል። ምሳሌ. 3፥19፤20። እንደዚሁም እግዚአብሔር በኃይሉና በዕውቀቱ በማስተዋሉም ዓለማትን ስለፈጠረ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፣ ዓለምንም በጥበቡ የመሠረተ፣ ሰማያትንም በማስተዋሉ ያጸና እርሱ ነው እያለ መስክሮለታል። ኤር.10፥12። ም. 51፥15።

ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች እግዚአብሔር በቃሉ ይኸውም በችሎቱ ቃል፥ ፍጥረታትን ስለፈጠረና ስለደገፈ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ፣ በአፉ እስትንፋስም ኃይላቸው ነው፤ ደግሞ «በሥልጣኑ /በችሎቱ/ ቃል ሁሉን ይደግፋል ብሎአል»... መዝ. 32/33/፥6፤9። ዕብ. 1፥3።

እነሆም አርዮሳውያን እንዳሉት ቢሆን ኖሮ፥ እግዚአብሔር ከባሕርዩ ህልውና በሚገለጻቸው ከባሕርዩ በተገኙት እዚህ ላይ በዘርዝር ባየናቸው መግለጫዎች ዓለማት ተፈጥረዋል ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ባልተናገረም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ አይዋሽምና ምሳ 30፥5። ለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ



መሠረቱ በሚሆን በክርስትና ትምህርተ መለኮት ሲመረመር፣ ይህ አርዮሳውያን ያመጡት ፈሊጥ ከጤናማ ትምህርት ፈጽሞ የራቀ ነው። 1ጢሞ. 6፥3-5።

2ኛ፥ አርዮሳውያን እግዚአብሔር ከባሕርዩ ህልውና ውጭ የሆነ ፍጡር ቃልን ወይም ጥበብን ፈጥሮ ዓለማትን «ፍጥረታትን» ፈጠረ። ያሉትን ነጥብ አቅርበን እንመለከታለን።

ይህ የአርዮሳውያን አባባል እውነት ያይደለና እውነትም ሊሆን የማይችል መሆኑን ቀጥለው በሚገኙት ማስረጃዎች እንገልጻለን።

ሀ/ በመጀመሪያ ነገር ፍጡራንን ይፈጥርበት ዘንድ፥ ማንንም ፍጡር አልፈጠረም። ፈጽሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ ነገር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ገልጾ የሚናገረው እግዚአብሔር ከራሱ በሆነ በመናገሪያ ቃሉ «ይሁን» እያለ ፍጥረታትን ሁሉ እንደፈጠረ ነው። ደግሞ ሁሉ በእርሱ «በቃሉ» ወይም በጥበቡ ሆነ። ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም እያለ ነው። ዘፍጥ.1፥3-27። መዝ.32/33/፥6-9። ምሳ. 3፥19፤20።

ለ/ ዳግመኛም አርዮሳውያን «እግዚአብሔር ከባሕርዩ ህልውና ውጭ ፍጥረታትን ሊፈጥርበት ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን ፈጠረ» እያሉ ሲናገሩ፣ ሞቅታ ይሰማቸው ይሆናል። በዚሁ አባባል የሚሠነዘር የአፍ ሞቅታ ግን፣ በተመርሆ ልቡናዊ መሠረት ለሚያስከትልባቸው ጥያቄዎች ዋስትና የለውምና፣ ዞሮ ያሳጣቸዋል።

<u>ለምሳሌ</u>፡-

1፥ ፍጥረታትን ይፈጥርበት ዘንድ ከባሕርዩ ህልውና ውጭ ፍጡርን ወይም ፍጡርን ቃል ወይም ፍጡርን ጥበብ መፍጠር ለምን አስፈለገው?

2፥ ዘለዓለማዊ ከሚሆን ከባሕርዩ ህልውና ዘንድ ቃል ወይም ጥበብ ያልነበረው ሆኖ ነውን?

3፥ ከነበረውስ በዚሁ ከባሕርይ ህልውናው በሚገኝ ቃሉ ወይም ጥበቡ ፍጥረታትን ለመፍጠር የማያበቃ ምክንያት አለን? ብለው ቢጠይቁዋቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሰው ማስረጃን በማቅረብ ፈንታ የሚሰጡት መልስ ቍጣ ብቻ ነው።

ከዚህ በላይ በሌላ ፍጡር ቃል ፍጥረታት ተፈጠሩ እንዳይባል፣ «በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው በሆነ ቃል፥ ሁሉ ሆኖአል፣ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም» በሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተዘግቶባቸዋል።

4፥ አርዮሳውያን እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ፈልጎ ፍጡር ጥበብን ወይም ፍጡር ቃልን እስካላገኘ ድረስ፣ ከገዛ ራሱ ፍጥረታትን ለመፍጠር

ይቻለዋል ብለው ስላለማመናቸውና ስላለማሰባቸው ሁኔታ፥ ከዘረዘርናቸው ነጥቦች አንዱ ነው።

ይህም እንደሚከተለው ይታያል።

መጀመሪያ ነገር አርዮሳውያን፦ እግዚአብሔር በባሕርይ ህልውናው ጥበብና ቃል ማስተዋልና ዕውቀት ኃይልና ከሂል ይኖሩታል አይሉም። ይህን መናገር ዋናው ችግራቸው ነው።

በጥብቅ ሲጠየቁ ደግሞ የሚመልሱት፤ እግዚአብሔር ድምፅ ይኖረው ይሆናል፤ ይህ ድምፅ ግን ፍጥረታትን ለመፍጠር ኃይል የሌለው ነው፤ ብለው ይመልሳሉ። እነሆም በዚሁ አነጋገራቸው የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ የሆነ የቃል ባሕርይን ሲመቱት እንደሚጮህ የደወል ድምፅ በማስመሰል ሲያቃልሉት ይገኛሉ። ሮሜ 1፥19።

በዚሁ አባባላቸው ታዝሎ የሚገኘው መዘዝ እንደምን ያለ እንደሆነ በሚከተለው ይታያል።

ሀ/ «ልዑል እግዚአብሔር ፍጡር ጥበብን ወይም ፍጡር ቃልን ከፍጥረት ወገን ፈጥሮ እስካላመጣና እስካላገኘ ድረስ፤ የፈቀደውን ሊሠራና ሊፈጥር አይቻለውም ነበር» ማለት ነው።

ለ/ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ይፈልግ ኖሮ እንደሆነም፤ ከራሱ ከባሕርዩ ህልውና ውጭ አጋዥና እርዳታ ያገኝ ዘንድ የግድ ያስፈልገው ነበር ማለት ነው። በዚሁ በአርዮሳውያን አባባል አንጻር ወይም ትይዩ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ብለን እንጠይቃለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ልዑል እግዚአብሔር ከባሕርዩ ውጭ ይኸውም ከፍጥረቱ አንድም ረዳት ሠሪና አጋዥ ደጋፊ ፈጽሞ የማያስፈልገው መሆኑን በግልጽ ይናገራል። ይልቁንም ደግሞ ከባሕርዩ ከራሱ ህልውና በሚገኝ ጥበቡ ወይም ማስተዋሉ ቃሉ ወይም ኃይሉ ብቻ ሊሠራ ሊፈጠር እንደሚችል፤ በፈቀደ ጊዜም ምንም ሳይቸገር ሊፈጥር ሊሠራ እንደቻለ፤ በጕልህ ያስገነዝባል። ኢሳ. 40፥12፤ 18። ቈ. 26-28። ም. 42፥51። ኢዮብ 41፥31። 1ዜና ም. 29፥11-13። ሮሜ 11፥33-36።

ስለዚህ እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ መሠረት አርዮሳውያን እግዚአብሔርን የባሕርይ ጥበብና የባሕርይ ቃል የሌለው አድርገው እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር ከፈለገ፤ ከፍጡራን ወገን ቃል ወይም ጥበብ ማግኘት አለበት እያሉ የሚናገሩት የስድብ ቃል የእግዚአብሔር ምልዐተ ባሕርይን የሚያቃልልና የሚያዋርድ ነው እያልን እንጸየፈዋለን።

4ኛ፥ አርዮሳውያን ልዑል እግዚአብሔር ዓለማትን «ፍጥረታትን» መፍጠር በፈለገ ጊዜ፤ ፍጡራንን ለመፍጠር ችሎታ ያለውን ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን አስቀድሞ መፍጠር አስፈልጎታል በማለት በባሕርይ



የአምላክነቱ ችሎታ ላይ አዋዋይ ግዴታን ሲጭኑበት የሚያሳየውን ነጥብ እንወስዳለን።

አርዮሳውያን በባሕርይ አምላክ ችሎት ላይ የጫኑበት የአዋዋይ «የግዴታ ጭነት» በክርስቲያናዊ የትምህርተ መለኮት ብርሃን ሲገለጥ፤ ምንነቱንና ተደራርበው የተዛዛሉበትን ስሕተቶች አስተዋይ የሆነ ሰው ሊያስተውላቸው ይችላል ብለን እናስባለን።

ሀ/ አርዮሳውያን በአስተሳሰባቸው እግዚአብሔርን ፍጥረታትን ለመፍጠር ከፈለገ ወይም ካማረው፤ ከሁሉ በፊት ፍጡር ቃልን፤ ወይም ፍጡር ጥበብን መፍጠር ይኖርበታል ሲሉ፤ በአዋዋይ የግዴታ ውጥረት ውስጥ ማስገባታቸው።

ለ/ የእግዚአብሔር ፈቃድ በፍጡር አጋዥና እርዳታ ብቻ የሚንቀሳቀስ ያለ ፍጡር አጋዥና እርዳታ ግን ተገንዞ የታሰረ ማድረጋቸውን ያሳያል።

ሐ/ እግዚአብሔር ዓለማትን ሊፈጥር ቢፈልግም ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን ፈጥሮ እስኪያገኝ ድረስ፤ ምንም መፍጠር የማይችልና መፍጠር ቢያምረውም ፍጡር ቃልን ወይም ጥበብን እስኪያገኝ ድረስ ታግሦ መጠበቅ ያለበት ደጀ ጠኚ ማድረጋቸውን ያሳያል።

መ/ እግዚአብሔር ዓለማትን ወይም ፍጡራንን ለመፍጠር ዐቅምና ብቃት የሌለው ኃይልና ችሎት የተሳነው ማድረጋቸው ነው።

ሠ/ ኃይልና ችሎት ዐቅምና ብቃት አለው ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ከነገረን፣ በእግዚአብሔር ባሕርይ ከሚገኙት ከመለኮታዊ ፈቃድና ጥበብ ከመለኮታዊው ቃልና ኃይል ይልቅ፥ ለፍጡር ቃል ወይም ለፍጡር ጥበብ ያለው ኃይልና ችሎት ዐቅምና ብቃት ብልጫ ያለውና፤ ላቅ ያለ አድርገው ማሳየታቸው ነው።

እዚህ ላይ የተመለከትናቸውን የአርዮሳውያንን አባባሎችና የታቀፉዋቸው ስሕተቶች በዝርዝር እያቀረብን በመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ በምንመረምርበት ጊዜ፤ ከመሠረታዊው ትምህርተ መለኮት ምን ያህል የራቁ መሆናቸውን መረዳት አያዳግትም።

ሀ/ ፍጡር ቃልን ወይም ጥበብን ከፈጠረ በዚያ ፍጥረትን ሊፈጥር ይችላል። ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን ካልፈጠረ ግን፤ ፍጥረታትን ሊፈጥር እንደማይችል በመገመት ልዑል እግዚአብሔርን በአዋዋይ የውል ግዴታ ውጥረት ለማስገባት የተሞከረውን የአርዮሳውያን ክጀላ ተመልክተናል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር ምንም አልገለጸ ይሆን? እርሱስ ገልጾአል። እነሆም በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ፤ ከእጄም የሚያመልጥ የለም። እሠራለሁ የሚከለክለኝስ ማነው ብሎ ተናግሮአል። ኢሳ. 43፤13። የሚከተሉትንም ጥቅሶች ተመልከታቸው።

በምድርም የሚኖሩ ሁሉ በፊቱ እንደምናምን ይቈጠራሉ፣ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ ሁሉ፥ እንደ ፈቃዱ ያደርጋል። እጁንም የሚከለክላት የለም፣ ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም። ዳን. 4፥35። አቤቱ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እነሆ አንተ ሰማይንና ምድርን በታላቅ ኃይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል። ከአንተም የሚያቅት «የሚሳንህ» ነገር የለም። ኤር. 32፥17-27።

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም። ሉቃ. 1፥32። ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ አሳብህም ይከለከል ዘንድ እንደማይቻል ዐውቅሁ። ኢዮብ 42፥2። የኃይል ነገር እንደሆነ እርሱ ኃያል ነው። ኢዮብ 9፥19። አንባቢ ሆይ! አርዮሳውያን እግዚአብሔር ፍጥረትን ለመፍጠር ቢያምረው፣ ወይም ቢያስፈልገው፣ ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን አስቀድሞ መፍጠር አለበት። በሚል የአዋዋይ ግዴታዊ ውጥረት ውስጥ አግብተው ለማጥመድ የከጀሉትን ክጅሎትና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ችሎታና የሚሳነው ነገር ስላለመኖሩ የገለጸውን ገለጻ አይተሃል፣ በሁለቱ መካከል ያለውን መራራቅ በጭምትነት አስተውለሃልን?

ለ/ እንደዚሁም አርዮሳውያን የእግዚአብሔር ፈቃድ በፍጡር አገዝና እርዳታ ብቻ ካልሆነ፣ ምንም ለመሥራት ለመፍጠር የማይንቀሳቀስ የማይችል እስረኛ ማድረጋቸውን እናያለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህን አስተሳሰባቸውን እየተቃወመ፣ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና የእግዚአብሔር ፈቃድም በምንም ሁኔታ የማይታሰር ስለመሆኑ እንደሚከተለው ይገልጻል።

«በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆቹ ሁሉ እግዚአብሔር የወደደውን አደረገ» መዝ. 135/136/፥6።

«በሰማይና በምድር የፈቀደውን ሁሉ አደረገ» መዝ. 113/114/፥11።

«በሰማይና በምድር በሚኖሩ ላይ እንደፈቃዱ ያደርጋል። እጁንም የሚከለክላት የለም።» ዳን. 4፥35።

ሐ/ ዳግም አርዮሳውያን እግዚአብሔርን ዓለማትን ወይም ፍጡራንን ለመፍጠር ከባሕርዩ ዐቅምና ብቃት የሌለው ኃይልና ችሎት የተሳነው አድርገውታል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን «እግዚአብሔር ሆይ ታላቅነትህንና የጸናች ክንድህን ለእኔ ማሳየት ጀምረሃል። በሰማይና በምድርም እንደሥራህ እንደ ኃይልህም ይሠራ ዘንድ የሚችል አምላክ ማነው?» ዘዳግ. 3፥24። ይላል።

«ስምህ ታላቅና ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው። በምክር ታላቅ በሥራም ብርቱ ነህ።» ኤር. 32፥17፤19።



«እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ሥራህ ግሩም ነው፣ ኃይልህም ብዙ ሲሆን፣ ጠላቶች ዋሹብህ።» መዝ. 65/66/፥3።

ዳዊት «እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ሥራህ ግሩም ኃይልህ ብዙ ሲሆን፣ ጠላቶች ዋሹብህ... ሲል «ጠላቶች» የሚላቸው እነማንን ይሆን? ከባሕርዩ ሊሠራ አይችልም ኃይል የለውም ከሚሉና በውሸት ከሚያቃልሉት ሌላ ጠላቶች ይኖሩታል ብሎ አስቦ ይሆን?

መ/ አርዮሳውያን በእግዚአብሔር በባሕርዩ ህልውና ካለው ፈቃድና ማስተዋል ቃልና ጥበብ፤ ኃይልና ችሎት፤ ይልቅ የፍጡርና የግቡር ጥበብ ወይም ኃይልና ችሎት ይልቅ ብልጫ እንዳለውና እንደሚልቅ ለማሳየት ይጥራሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከእግዚአብሔር ከባሕርይ ህልውናው ከሚገኝ ምክር ወይም ጥበብ በላይ፣ ምንም ዓይነት ፍጥረት ነክ የሆነ ጥበብ ወይም ምክር ወይም ማስተዋል የማይኖር ወይም የማይገኝ መሆኑን ገልጾአል።

በመጽሐፈ ምሳሌ፦ ጥበብ ወይም ማስተዋል ወይም ምክር በእግዚአብሔር ላይ የለም፣ ተብሎአል። ምሳ. 21፥30። ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች ተመልከታቸው። ዘዳግ. 3፥24። መዝ.39/40/፥5። ም. 88/89/፥6፤8።

በእውነት ከነቢያትና ከሐዋርያት ከመጀመሪያይቱም ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በትውፊት እየተቀባበለ በየአብያተ ክርስቲያናቱ እጅ ተጠብቆ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየውን ባጭሩ ጌታ እስኪመጣ ድረስም ሳይቆምና ሳይገታ ጸንቶ የሚኖረውን መጽሐፍ ቅዱስን እየተው የገዛ ራስን አሳብ መከተል ከእውነት ውጭ ወደ ጥፋት መሄድ መሆኑን በዚሁ ለመረዳት ያስችላል።

# ምዕራፍ ፱

## አርዮሳውያን መጽሐፍ ቅዱስን ስለመተዋቸው፣ በእርሱ ፋንታ ሌላ መጽሐፍ ስለመጻፋቸው።

እዚሁ ላይ እኔን የሚገርመኝ፦ አርዮሳውያን ፍጡርን ፈጣሪ ለማድረግ ሲሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ እሉታ መቃረናቸውና መቃወማቸው ነው። መቼም መጽሐፍ ቅዱስን ደግሞ የተባሉት ዓለማት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር በባሕርዩ ቃል ወይም በመናገሪያ ቃል መሆኑን ስለገለጸና፣ እነርሱ ደግሞ ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን ፈጥሮ ዓለማትን ፈጠረ፣ በሚል አሳባቸው ፍጥረትን ከእርሱ እጅ አውጥተው ለመስጠት ሲከጅሉ፣ እውነትን በመናገሩ ስለተቃወማቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስን መካድ ይገባቸው ነበረን? በእውነቱ መጽሐፍ ቅዱስን መቃረንና መካድ አይገባቸውም ነበር። ነገሩ ከመሠረቱ ሲታይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ የአፉ እስትንፋስ እንደመሆኑ ሁሉ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ ኃይለ ቃላት ሰዎች ሊያስተውሉዋቸው ባይቻላቸውም፦ እንደ ዱር ቅዱሳን ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርገው ለመማር፥ ናፍቆታቸውንና ጉጉታቸውን መግለጽ፣ በጸሎትም መለመን ይኖርባቸዋል እንጂ፣ ካልገባን እንካደው፣ እንደ አሳባችን ካልሆነም እንቃወመው ማለት አይገባቸውም ነበር።

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን ነቢያትና ሐዋርያት ከተመሩባቸው መንገዶች ከዚህ ቀጥለን አንዳንዶቹን እናቀርባለን።

ከጀመርሁት ዘንድ፥ በዚህ አጋጣሚ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማንነትና አርዮሳውያን መጽሐፍ ቅዱስን ስለመተዋቸው ባጭሩ እንድናገር ይፈቀድልኝ ዘንድ አንባቢን እጠይቃለሁ።

«በሐዋርያትና በነቢያት ተመሥርታችኋል» ተብሎ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣት መጽሐፍ ቅዱስን አርዮሳውያን መልቀቃቸውን ትልቅ ስሕተት ነው የተሳሳቱት እላለሁ። ኤፌ. 2፥20። 2ጢሞ. 3፥13-17።

እንዲያው ለነገሩ ለባዊ ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ከልዑል እግዚአብሔር ከባሕርዩ ጥበብ ወይም ምክር ይልቅ፥ የበለጠ ፍጡር ጥበብ ይኖራል ብሎ እንደምንስ ቢሆን ያስባል? መዝ. 91፥4-6።



አርዮሳውያን እግዚአብሔር ዓለማትን ይፈጥር በነበረ ጊዜ፣ «ይሁን» እያለ ከባሕርይ ህልውናው በሚኖር ቃሉ ሲናገርና «ይሁን» ያለው ሁሉ እንደሆነ፣ በማስተዋሉና በጥበቡ ተራቅቆ አሳምሮ ፍጥረታትን እንደፈጠረ፣ በግልጽ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ሙሉ በሙሉ ተቃርነዋል። በዚያ ፋንታ ዓለማት የተፈጠሩት ፍጥረታትን ለመፍጠር በሚቻለው በፍጡር ቃል ወይም በፍጡር ጥበብ ነው በማለት መጽሐፍ ቅዱስን ግንባር ለግንባር ተቃውመዋል። እንዲያውም እንደ ሆኖሬ ያለ መጽሐፍ ለራሳቸው ጽፈው ይገኛሉ።

እነርሱ የተነሡት በታወቀ ዘመን እንደ ኤውሮፖ አቈጣጠር በ1886 ዓ.ም. ሲሆን፣ ዘመናውያን አርዮሳውያን እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ክደው፥ በዚያ ምትክ ሌላ መጽሐፍ ማውጣታቸው ለሰሚ ጆሮ የሚዘገንን ነው።

ይህን ለምን እንዳደረጉ ብንጠይቃቸው፣ ከግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ገለበጥነው ይላሉ። ይህን እነርሱ ራሳቸው ማለት ዘመናውያን አርዮሳውያን ተሰብስበው በእግዚአብሔር ላይ ሲዶልቱ የጻፉት መጽሐፋቸው፣ ከየትኛው የግሪክ መጽሐፍ ቅዱስ እንደገለበጡት ብንጠይቃቸው ግን፣ መልስ አይሰጡንም። ከየትኛው ኮዴክስ፥ ወይስ ከየትኛው አብነት፣ ወይስ ከየትኛው የግሪክ ሆነ የላቲን ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ያገኛችሁት! ቢሉዋቸው፣ ያው በተለመደው ተሳዳቢ አንደበታቸው ከመከላከል በቀር፤ ከዚህ ነው ብለው በሥርዓት ሊጠቅሱና ሊያስረዱ አይችሉም።

በአራተኛው ምእት ዓመተ ምሕረት አርዮስና አውናምዮስ፣ አኤትሮስ «ወልድን ፍጡር» ብለው መነሣታቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የታወቀ ነው፣ ታዲያ እነዚያ እንኳ በብሂል አተረጓጐም ወደቁ እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለመለወጥ አልቃጡም። እነዚህ በ1886 ዓ.ም. የተነሡት ዘመናውያን አርዮሳውያን ግን፣ እጅግ በጣም ደፋሮች ናቸው።

እስከ አሁን ድረስ ሐዋርያዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳታጐድልና ሳትጨምር ጠብቃ ያቆየችውን መጽሐፍ ቅዱስን ክደው፥ በለውጡ የገዛ ራሳቸው የፈጠሩትን መጽሐፍ ማውጣታቸው የሚያስገርም አይደለምን?

ኧረ ለመሆኑ፥ እንዴት ቢሰማቸው ይህን አሰቡ? በእግዚአብሔር መንፈስ ከተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስና በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጸው ቃሉ ይልቅ፣ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ከሚሆን ከሥጋዊ ሰው አንጎል የወረዛው አሳብ ይበልጣል ብለው ነውን? ኧረ እነዚህ እነማን ናቸው? ምነው አስተሳሰባቸውን ዞረው በተመለከቱት! ኢሳ. 40፥6-8። 1ጴጥ. 1፥24፣25።

ከመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስና አሳብ ውጭ የሚቆም እውነተኛ ክርስትና ያለ መስሎአቸው ይሆን? ምንን ይዞ ጉዞ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የአቋም መመሪያ እኮ ነው።

ሰው ሁሉ ስለ ክርስትና ትምህርተ መለኮት ጉዳይ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ የሆነውን አሳብ ከገዛ ልቡ እየፈጠረ ወይም እያስመሰለ፣ ለመናገር የሚችል፣

እንደዚሁም ሁሉ በየዘመኑ ከተነሡት ከእያንዳንዱ አስመሳዮች የተጻፉትን እየጨማመሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ውስጥ ለመደርደር የሚቻል ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በቀኖና ተወስኖ መገኘቱ ዱሮውንስ ለምን ያስፈልግ ነበር? 2ቆሮ. 10፥13-16። ገላት. 1፥8-10። 2ጢሞ.3፥16። ራእ. 22፥18-20።

የአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል መሆንዋና፣ የእምነትዋ ዓምድና የእውነት መሠረት አንድ መሆኑ ከዚህ የተነሣ አይደለምን? ቤተ ክርስቲያን በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት «መጽሐፍ ቅዱስ» ተመሥርታለችና። ኤፌ. 2፥20። ም.4፥4። ቍ.12-14። 2ጴጥ. 1፥1-21። 1ጢሞ. 3፥15።

መቸም አርዮሳውያን ማሰሪያቸውን በጣጥሰው እንደልባቸው ለመጋለብ እንዲመቻቸው ብለው፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ከተጻፈና መሠረታዊ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ጋጣቸው በመውጣታቸው ፈንጥዘው ተደስተውም ይሆናል። ፍርዱንና ሕጉን ለሰው ልጆች የሚደነግግና ጽፎ የሚሰጥ እግዚአብሔር እንጂ፣ የፍርድንና የሕግን ጽሑፍ አርቅቆ ለእግዚአብሔር የሚያወጣለት የሰው ልጅ እንዳልሆነ የሚያውቅ ሰው ግን፣ የአርዮሳውያን ደስታና ፍንጠዛ አጭር መሆኑን ያያልና በጥፋታቸው ብቻ ያዝናል። የሐዋ. 9፥4።

እነሆም አርዮሳውያን የደረሱበትን ሁኔታ፥ ከዚህ በላይ በዝርዝር ባቀረብናቸው ነጥቦች በመጠኑ አይተናል። የተከተሉዋቸውን ስሕተቶችና በስሕተቶቹ ላይ ደግሞ የተንጠለጠሉትን መዘዞች ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከክርስትና ትምህርተ መለኮት ተነጻጽረው ሲታዩ የቱን ያህል ርቀው እንደወደቁም ተመልክተናል።



# ምዕራፍ ፲

## ጥበብ በእግዚአብሔር ባሕርይ ያለ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ስፍራ «እግዚአብሔር ጠቢብ ነው፣» ተብሎ ተነግሮ ይገኛል። ጠቢብ ማለት ጥበብ ያለው፣ ባለ ጥበብ ወይም ጥበበኛ ማለት ነው። አሁን በዚሁ አነጋገር ጠቢብ ሲባል፣ ጥበብ የእግዚአብሔር የባሕርዩ ህልውና ገንዘብ መሆኑን፥ በሚያንጸባርቅ አነጋገር እንደሆነ ነው የሚያሰማ? ወይስ እግዚአብሔር ጥበብን ፈጥሮ እንደ ዕቃ ወይም ጥሪት ወይም ንብረት እንዳደረገው የሚያሰማ? ብለን እንጠይቃለን።

__ለምሳሌ__፡- አንድን ሰው ጠቢብ ጥበበኛ ወይም ባለ ጥበብና ጥበብ ያለው ስንል፣ ከባሕርዩ ውጭ ዲሠርቶ እንደሚገኝ ቤት፥ ከብት፥ እንደሚያፈራው ገንዘብና ጥሪት፥ አስበን መናገራችን ነውን? የለም! አይደለም። ከሰውየው ከአካላዊ ባሕርዩ የተገኘ ከውስጡ የሚፈልቅ፥ የልቡ ንቅዕ፥ የአሳቡም ምንጭ የማስተዋሉ ውጤት መሆኑን፥ በአእምሮ ግዕዛናችን ለይተን ባወቅነው መሠረት መናገራችን ነው።

ቤትና ከብት ጥሪትና ገንዘብ የመሳሰሉም ነገሮች ሁሉ፥ ከሰውየው ከተፈጥሮ ባሕርዩ ውጭ መሆናቸውን ሰውየው ሠርቶ ያገኛቸው ከአካላዊ ህሉናው «ከተፈጥሮ አቋሙ» በአፍአ «በውጭ» ያፈራቸው፥ ጥሪቱ ገንዘቡ መሆናቸውን መረዳት ለሰው ልጆች አስቸጋሪ አይደለም።

ሰው በባሕርዩ ውስጥ ባለውና፣ ሰው በዚህ ምድር ደክሞ ጥሮ በሚያገኘው ገንዘብ፣ ንብረት በሚያደርገው፣ መካከል ያለውን ልዩነት ኢዮብ ከተናገረው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን እናቀርባለን። ነገር ግን ጥበብ የምትገኘው ወዴት ነው? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው? ሰው መንገድዋን አያውቅም። በሕያዋን ምድር አትገኝም። ቀላይ በእኔ ውስጥ የለችም ይላል። ባሕርም በእኔ ዘንድ የለችም ይላል። በምዝምዝ ወርቅ አትገኝም። ብርም ስለ ዋጋ አይመዘንም። ወርቅና ብርጭቆ አይወዳደሩአትም። በጥሩ ወርቅም ዕቃ አትለወጥም። ስለ ዛጐልና አልማዝ አይነገርም። የጥበብ ዋጋ ከቀይ ዕንቍ ይልቅ ይበልጣል። የኢትዮጵያ ቶጳዝዮን አይተካከላትም፥ በጥሩም ወርቅ አትገመትም። እንግዲያስ ጥበብ ከወዴት ትመጣለች? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው? ኢዮብ 28፥12-20።

በመሠረቱም አእምሮው ያልተዛባበት ሰው ሁሉ፥ በተፈጥሮው የአካል ህሉና አብሮ በቀል ስለሚሆን ስለ ባሕርይ ገንዘብነትና ከተፈጠር የአካል ህሉና አብሮ በቀል ስላልሆነ ስለ አፍአዊ «ውጫዊ» ጥሪት ገንዘብነት ጠንቅቆ ያውቃል።

እያንዳንዱ ሰው ልቤ፥ ወይም ልቡናዬ፥ አሳቤ፥ ዕውቀቴ፥ ችሎታዬ፥ ጥበቤ፥ ማስተዋሌ፣ እያለ ስለ ረቂቁ ጠባይዓዊ ግብሩ ሲናገር፥ እንደዚሁም ደግሞ፥ እጄ ክንዴ ራሴ እግሬ፣ ዓይኔ ብሎ ስለ ግዙፉ ሕዋሳቱ የሚናገርበት ጊዜ አለ። እነዚህ የተጠቀሱት ሁሉ ሰው ሆኖ ሲፈጠርና በሰብአዊ አቋም ሲገኝ አብሮ በቀል የአካላዊው ህሉናው «ሁለንትናው» ገንዘቦቹ መሆናቸውን ዐውቆ ይናገራል።

በዚሁ ንጽጽር ደግሞ ሰው ቤቴ፥ ልብሴ፥ ወንበሬ፥ አልጋዬ ብሎ ይናገራል። ነገር ግን እነዚህ የመሳሰሉአቸውንም ከተፈጥሮ ባሕርዩ ከአካሉ ህሉና «አቋም» ውጭ በሥራው በድካሙ ያፈራቸው ገንዘቦቹ መሆናቸውን በማወቅ ነው የሚናገር፣

ይኸውና በሰው ስላለው ስለ ባሕርያዊ ገንዘብነትና ለሰው ስላለው ከባሕርዩ ውጭ ስለሆነው ስለ ሥራ ፍሬ ጥሪት ወይም ገንዘብነት በላይ በተገለጸ ምሳሌ ልዩነቱን አየን፣ እንግዲህ አሁን በእግዚአብሔር በኩል ስላለው ስለ ባሕርዩ ህልውና ገንዘብነትና ፈጥሮ ስላገኘው ስለ ሥራው ገንዘብነት ምን ዓይነት ልዩነት እንዳለ በጥንቃቄ እንመልከት።

እነሆም በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ፥ የመናፍስት አምላክ፥ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ተብሎ የተጻፈውን እንውሰድ፣ ዘኁልቍ 16፥22። ሐጌ. 1፥7። የሐዋ. 14፥15። እነዚህ ሠራዊት፣ መናፍስት፣ ሰማይና ምድር በተጻፈው የዓረፍተ ነገር ሐረግ አቀራረብ የእግዚአብሔር ገንዘብ እንደሆን ተገልጾአል። ግን የባሕርይ ህልውናው ገንዘቦቹ ናቸው ወይ? የለም አይደሉም። እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ካለመኖር ወደመኖር ካለመታየት ወደ መታየት በቃሉ ፈጥሮ ያመጣቸው ፍጡራን ገንዘቦቹ ናቸው። ዕብ. 11፥3።

አሁን ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልቡናና ፈቃድ የእግዚአብሔር አሳብና ዕውቀት የእግዚአብሔር ጥበብና ማስተዋል የእግዚአብሔር ቃልና ክሂል የእግዚአብሔር ኃይልና ሕይወት እየተባሉ ስለሚነገሩት እንመለከታለን።

እንግዲህ እነዚህን ልቡና፥ ፈቃድ፥ አሳብ፥ ቃል፥ ሕይወት፣ እውቀት፥ ጥበብ፥ ማስተዋል፣ ክሂል፥ ኃይል፥ ሕይወት የተባሉት የዐውደ አእምሮ ወገኖችን ሁሉ ምን እያልን እናስባቸዋለን? እግዚአብሔር ከውጭ ፈጥሮ ገንዘብ ያደረጋቸው ናቸው እንላለን?

በእውነቱ አንልም። ከሰው በወሰድነው ምሳሌ እንኳ የባሕርይ ገንዘብነትን፥ ከሥራ ፍሬ ገንዘብነት ሊኖረው የሚገባውን ልዩነት አውቀን በአግባብ በአግባቡ ጠንቅቀን ፈርደናል።

እንግዲያውስ እነዚህ የዐውደ አእምሮ ወገኖች ልብ ፈቃድ አሳብ ቃል ሕይወት ጥበብ ማስተዋል፣ ወዘተ... እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ በሕያውነቱ ሲኖር፣ ከባህርየ መለኮቱ አንድነት በዘላለምነት የኖሩ ከውጭ ፈጥሮ ያላመጣቸው የባህርዩ ገንዘብ እንደሆኑ፣ በአእምሮ ገዕዛን ማወቅ፣ መረዳት ይሳነናል? እግዚአብሔር ያለ እነዚህ የኖረበት ዘመን አለን?



እንግዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጥሬ ንባብ የተገለጸውን ማስረጃ በተመርሆ ልቡናዊ መሠረት እንመልከት።

1፥ እነሆም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸ፣ እግዚአብሔር ከዘለዓለም በሕይወት በለባዊነት፥ በነባቢነት፥ በሕያውነት ጸንቶ የሚኖር መሆኑን እናያለን። ኢሳ. 5፥23። ሮሜ 14፥11።

2፥ ልዑል እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ጠሊቅ ልብ ያለውና፤ በባሕርዩ ለባዊ እንደሆነ እናገኛለን። ሮሜ 11፥34። መዝ.32/22/፥11። አሞ.4፥13።

3፥ ልዑል እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ፈቃድ፥ ሥምረት፤ እንዳለው በባሕርየ መለኮቱ የፈቀደውን እንደሚያደርግ እናገኛለን። መዝ.113/114/፥11። ዳን.4፥35። ኤፌ.4፥6-11።

4፥ ልዑል እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ዕውቀት አእምሮ ከራሱ ከህላዌ መለኮቱ እንዳለው በዚሁም ሁሉን እንደሚያውቅ እናገኛለን። 1ሳሙ.2፥3። ሮሜ 11፥33 መዝ.138/139/፥6።

5፥ ልዑል እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ሐሳብና ሕሊና ከራሱ ከህላዌው እንዳለው ያሰበውንም እንደሚፈጽም እናገኛለን። መዝ. 32/33/፥11። ኢሳ.14፥26፣27።

# ምዕራፍ ፲፩

## የጥበብ ህልውና በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት ነው?

1፦ ልዑል እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ማስተዋልና ጥበብ ከራሱ ባሕርይ እንዳለው እናገኛለን። ኢዮብ. 12፥13።

2፦ ልዑል እግዚአብሔር ምክርና አእምሮ ከራሱ ከህላዌ መለኮቱ እንዳለው እናገኛለን። ኢዮብ. 26፥2፤3።

3፦ ልዑል እግዚአብሔር ያልተፈጠረ ቃልና ክሂል እንዳለው በዚህም ራሱን እንደሚገልጽ እናገኛለን። ዕብ. 1፥3። ዮሐ. 1፥1።

4፦ ልዑል እግዚአብሔር ኃይልና ሕይወት ከገዛ ራሱ ህልውና እንዳለው እናገኛለን። መዝ. 32/33/፥6። ኢሳ. 45፥23፤24።

ባጭሩ ዘለዓለማዊ በሚሆን መለኮታዊ አኗኗር ያሉት እነዚህ የዓውደ አእምሮና የዓውደ ሕይወት ሁኔታዎች የኖሩና በኋላ ፈጥሮ ያላገኛቸው፥ ወይም ለአገዘ ከሌላ ያልተበደራቸው፥ ተከራይቶ ያላመጣቸው፥ የባሕርይ ገንዘቦቹ መሆናቸውን በቅዱሳት መጻሕፍት መረጃዎች ዐውቀናል፤ እናምናለንም። ኢሳ. 40፥12-14።

እነዚህ በህላዌ መለኮቱ ስላሉትም፥ በእነዚህ ፈቅዶ ሠምሮ ወድዶ አስቦ ዐውቆ መክሮ አስተውሎ ተጠብቦ ሁሉን በሚችል ቃሉ ተናግሮ በኃይሉ እንደፈጠረ፤ ወልድም በእነዚህ ስም፤ እንደተጠራባቸው እናገኛለን። መጽሐፍ ቅዱስም አምልቶ አስፍቶ ይገልጻቸዋል። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኃይል፤ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደተባለ እናገኛለን።

ይህን ካየን አሁን በዓውደ አእምሮ ካየናቸው የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቦች መካከል በተለይ ስለ ጥበብ ከተነገረው ጠቅሰን እንይ።

### ጥበብ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላት ህልውና እንዴት ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጥበብ እንደሚከተለው ተገልጾአል። አንባቢ ፈቃድህ ቢሆን፤ ከዚሁ ጥበብ በሚለው እግርጌ አሥምርና ጥበብ ስለተነገረችበት አቋም መርምር።

1፦ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል አለ። ለእርሱም ምክርና ማስተዋል አለው። ኢዮብ 12፥13።

2፦ ኃይልና ጥበብ በእርሱ ዘንድ ናቸው። ኢዮብ 12፥16።



3፦ ልቡ ጠቢብ ነው። ኃይሉም ታላቅ ናት። ኢዮብ 9፥4።

4፦ ኃይል የሌለውን ምንኛ ረዳኸው? ብርታት የሌለውን ክንድ ምንኛ አዳንኸው? ጥበብስ የሌለውን ምንኛ መከርኸው? ብዙ እውቀትንስ ምንኛ ገለጽህለት? ኢዮ. 26፥2፤3።

5፦ ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና፤ የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ። ዳን. 2፥20።

6፦ «ሊያበረታችሁ ለሚችለው ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር፥ በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘለዓለም ክብር ይሁን።» ሮሜ 16፥27። ብቻውን ጥበብ ላለው የሚለውን አስተውል።

7፦ የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው? ሮሜ 11፥33።

8፦ እርሱ ደግሞ ጠቢብ ነው። ቃሉንም አይመልስም።

9፦ «አቤቱ ሥራህ እጅግ ታላቅ ነው። ሁሉን በጥበብ አደረግህ።» መዝ. 103/104/፥24።

10፦ «ጌታችን ታላቅ ነው ኃይሉም ታላቅ ነው ለጥበቡ ቍጥር የለውም።» መዝ. 146፥14፤5።

11፦ «ምነው እግዚአብሔር ቢናገርህ፤ በአንተም ላይ ከንፈሩን ቢከፍት የጥበቡን ምሥጢር ቢገልጥልህ ማስተዋሉ ብዙ ነውና።» ኢዮብ 11፥5፤6።

እዚህ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት ማስረጃዎች ፍሬ ነገሩን ለማየት እስቲ የሚከተሉትን ብቻ በድጋሚ እንመልከታቸው።

«በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል ምክርና ማስተዋል አለ። ብቻውን ጥበብ አለው።»

«በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል ምክርና ማስተዋል አለው።» ጥበብና ኃይል የእርሱ ነው። የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ፥ ዕውቀት፥ እንዴት ጥልቅ ነው። አቤቱ ሥራህ ታላቅ ነው። ሁሉንም በጥበብ አደረግህ። እርሱ ጠቢብ ነው። ልቡ ጠቢብ ነው፤ ኃይሉም ታላቅ ናት። በውኑ ጥበብስ የሌለውን ምንኛ መከርኸው ብዙ እውቀትስ የሌለውን ምንኛ ገለጥህለት!

አንባቢ ሆይ! አሁን ጥበብ በሚለው ቃል ሁሉ እግርጌ አስምረሃል! ከጥቅሶቹም ስለ ጥበብ አቋም የተነገረውን ሳትገነዘብ አትቀርም።

ታዲያ እንዴት ተሰማህ! አሁን በዚህ ጊዜ ጥበብ ምን ሆና ነው የተነገረች? ከእግዚአብሔራዊ ጠባይ ውጭ ንብረት ሆና ነው? ወይስ የባሕርይ ገንዘብ ሆና ነው? ለእግዚአብሔር ገንዘቡ ልትሆን የተፈጠረች ሆና ነው? ወይስ ከባሕርዩ እንደልቡና እንደማስተዋል እንደ ሐሳብና እንደ ኃይል ባለው አቋም መልክና

ሁኔታ ተገኝታ ነው? ልዑል እግዚአብሔርስ ለጥበብ ምንዋ እንደሆነ ነው የተነገረለት? ልዑል እግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ያለው ልቡ ጠቢብ ጥበበኛ፣ ምክርና ማስተዋል ያለው ሁሉን በጥበብ ያደረገ ሲባል፣ ጥበብን ፈጥሮ ገንዘብ ያደረጋት ማለት ነውን? ወይስ በልቡ ተጠባቢ ጥበበኛ ጥበብ ከምክርና ከማስተዋል ከኃይልና ከክሂል ጋር፥ በህላዌ መለኮቱ ያለው ማለት ነው።

የማንም ሕሊና እንዲነጻ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተነገሩ ጥቅሶች ላይ ለተጠየቁት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስን ለመስጠት መርምሮ መፍረድ፥ የክርስቲያናዊ ሁሉ ግዳጅ እንደሆነ ይሰማኛል።

በእውነት ካሰብንበት ሌላውስ ይቅርና ጥበብንስ የሌለውን ምንኛ መከርኸው? የሚለውንና «ልቡ ጠቢብ ነው» የሚለውን ጥቅስ ብቻ ይዘን፥ ብንመረምር ለጥያቄው የምንመልሰውን ተመርሆ ወስና ሲያሳየን እናገኛለን። ኢዮብ 26፣2፣3። ም. 9፥4።

መቼም ቢሆን እግዚአብሔር ጠቢብ የተባለው ጥበብ የምትባለዋን ነገር ፈጥሮ ሲያበቃ፣ በልቡ ውስጥ በማስቀመጡ ነው ብሎ የሚፈርድ የባለ ግዕዛን ሕሊና ያለ አይመስለኝም። ሕሊናን በመጣስ ግን፣ የማይደረግ ነገር የለም። ይኸውም እንደምንሰማው ነው! እነሆም እግዚአብሔር በልቡ ስለሚያስበውና ስለሚጠበበው መለኮታዊ ጥበብ እንጂ፣ ከባሕርዩ ውጭ ፈጥሮ ስለሚያገኘው ባዕድ ነገር አያሳይምና ነው።

እንደዚሁም ሁሉ እግዚአብሔር ጠቢብ ወይም ጥበብ ያለው ሲባል፣ ጥበበኛ ተጠባቢ መሆኑን የአስተሳሰቡ መራቀቅ ብልሀተኛነት ወይም የማስተዋሉ ዘዴን ስለሚያስገነዝብ፣ ይህ ከባሕርዩ እንጂ፣ ከውጭ የመጣለት ባዕዳዊ ነገር እንዳልሆነ ነው የሚያሳይ። ከዚህ በላይ በእግዚአብሔር ዐውደ አእምሮ ውስጥ ስላሉ፣ ባሕርያውያን ጠባይዐት ስለ አገላለጻቸው ግብር በማስረዳት የእግዚአብሔር የባሕርዩ እንጂ፣ ከውጭ ያላመጣቸው ስለመሆኑ ስንናገር፣ አርዮሳውያን ፍጥረት ናት ያልናት ጥበብን ነው እንጂ፣ እላይ የተነገሩትን ሁሉ አይደለም ማለታቸውን ሰምተናል። የተቃለለላቸው መስሎአቸው ምንም እንኳ ቢያስተባብሉም፣ ጥበብ ያልተፈጠረች የእግዚአብሔር ጥበብ ናት እስካላሉ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ እነርሱን ከማስረዳት አይመለስም።

ለመሆኑ አርዮሳውያን «ፍጥረት ናት» የምንል ጥበብን ብቻ ነው ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ይህችን ጥበብ ከእግዚአብሔር ልቡና ከፈቃድ ከአሳቡ ከምክሩ ከማስተዋሉ ከዕውቀቱ ከቃሉ ከኃይሉ ወዘተ ከሚገኝ ከዓውደ አእምሮ ወይም በዓውደ ሕይወት ለብቻዋ ተነጥላ ምን መስላ ታየቻቸው? እስከዚህ ድረሰ ፍጡርነትን የተመኙላት ምንኛ ቢወዱአት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ፍጥረታትን በመፍጠር ረገድ በእግዚአብሔራዊ ዓውደ አእምሮ ወይም ዓውደ ሕይወት ውስጥ ከተዘረዘሩት መካከል፥ ጥበብን ብቻ



ፍጥረት አድርጎ አያሳየንም። ለዚህም አንባቢን አስቀድሜ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንዲያነብልኝ እጠይቃለሁ።

እነሆም ጠቢቡ ሰሎሞን እግዚአብሔር በጥበቡ ምድርን መሠረተ። በማስተዋልም ሰማያትን ዘረጋ። በዕውቀቱም ቀላያት ተቀደዱ። ብሎአል። ምሳ. 3፥19፣20።

ኤርምያስም ምድርን በኃይሉ የፈጠረ ዓለምን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው ብሎአል። ኤር. 10፥12።

ዳዊት «ሰማያትን በጥበቡ የሠራ» ብሎአል። መዝ. 135/136/፥5

ኢሳይያስም እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው፣ አይደክምም አይታክትም ማስተዋሉም አይመረመርም። ኢሳ. 40፥28።

በመዝሙራት ዘዳዊትም በሰማይና በምድር በጥልቀቶችም ሁሉ እግዚአብሔር የፈቀደውን አደረገ ተብሎአል። መዝ. 134/135/፥6።

እነሆም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተመለከተው ማስተዋል እውቀት ኃይል ፈቃድ ልቡና ወዘተ... እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሲፈጥር ሳለ፣ በመፍጠር ሥራ እንደተገኙ ተገልጾአል። እንግዲህ አርዮሳውያን ጥበብን ብቻ ፈጥሮ ነው ዓለምን የፈጠረ የሚሉ ከሆነ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ መሠረት ለእነማስተዋል ለነ ዕውቀት ለእነ ኃይል ወዘተ... በመፍጠር ሥራ ያላቸው ቦታ የት ላይ ነው?

በእውነቱ አእምሮን ሰብስብ አድርጎ በቅንነት ማሰብ በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ዓለማትን በሚፈጥርበት ጊዜ ልቡናው፥ ፈቃዱ ሐሳቡ፥ ዕውቀቱ፥ ማስተዋሉ ጥበቡ ቃሉ ኃይሉ ወዘተ... የእግዚአብሔር ዐውደ ልቡና ዐውደ አእምሮ ወይም ዐውደ ሕይወት ናቸው። ስለዚህም እግዚአብሔር ከእነዚህ በአንድ ሠርቶ በሌላው ሳይሠራ አልቀረም። እነሆም በጥበብ ተጠብቦ በማስተዋል ሳይጠቀም፥ በልቡ ፈቅዶ በሕሊና ሳያስብ፥ በቃሉ ተናግሮ በኃይሉ በክሂሉ ሳይጠቀም፥ በአእምሮው ሳያውቅ ዓለማትን አልፈጠረም። የባሕርይ ግብሩ መግለጫ ናቸው።

በጥበቡ ፈጠረ ማለት ያን ሊፈጥር የፈለገውን ወይም የፈቀደውን ፍጥረት አስቀድሞ ቅርፁ እንዴት መሆን እንዳለበት የአቋሙ ሥርዓት ውበቱ፣ ጌጡ፣ መጠኑ ወዘተ... እንደምን መሆን እንደሚኖርበት ሳያስብበት ሳያውቀው አልፈጠረውም።

ፕላኑን ንድፉን ቅርፁን መጠኑን መዝኖ ሠፍሮ ለክቶ ደንግጎ ወስኖ የአኗኗሩን ሥርዓት አስተካክሎ አስቦ በእውቀቱ በብልሃት በማሰብ በማስተዋል ዐውቆ ተጠብቦ ሲያበቃ፣ ፈጠረው ማለት አይደለምን? ጥበብ ማለትስ በዚሁ አኳኋን የተገለጸው አይደለምን? መዝ. 148/149/፥5፣17። ም. 146/147/፥4፣5። ም. 103/104/፥1-24። ኢዮብ 28፥29። ኢሳ. 40፥12፥14። እንግዲህ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በፈጠረ ጊዜ፣ በጠቅላላው ዓውደ አእምሮው ውስጥ

ከተነገሩት ሁሉ አንዱን ሳያስቀር የፈለገውን ወይም የፈቀደውን እንደፈጠረባቸው ለማስረዳት መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በጥበቡ ምድርን መሠረተ በማስተዋሉም ሰማያትን አጸና በእውቀቱ ቀላያት ተቀደዱ ሲል ገልጾ ያስገነዝባል። እንዲሁም ምድርን በኃይሉ የፈጠረ ዓለምንም በጥበቡ መሠረተ፥ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ፥ እያለ ያስረዳል። ምሳ. 3፥19። ኤር. 10፥12።

ታዲያ! በእውነቱ እግዚአብሔር እኔን የፈጠረኝ በጥበቡ ብቻ ነው እንጂ፣ የእግዚአብሔር ማስተዋል ወይም ፈቃዱ የእግዚአብሔር ኃይል ወይም ቃሉ ወዘተ... እኔን በመፍጠር ሥራ አልነበሩበትም። የሚልና ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ዓውደ አእምሮ ኃይላት ወይም የባሕርይ ንብረት ውጭ እንደተፈጠረ የሚያስብ ክርስቲያን ይኖር ይሆን?

ጥበብ ከእግዚአብሔራዊ ዐውደ አእምሮ ተነጥላ፥ ልዩ መስላ እንድትታይ የሚያደርግ አንድም ፍንጭ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፈጽሞ አይገኝም። ጥበብ ሲል ምክርን ማስተዋልን ዕውቀትንም ጭምር ይይዛል።

ሌላው ቀርቶ ጥበብ የሚባል ስያሜ ከዐውደ አእምሮ ወይም ከዐውደ ሕይወት ውጭ መቼ ይገኝና ነው! አንዳንድ ጊዜ የሰው ሠራሽ ሐረግ ጌጠኛ ዕቃ፥ የእጅ ሥዕል ውበት አይሮፕላን የመሳሰለውም በምንመለከትበት ጊዜ፣ አየ ጥበብ! እያልን መናገራችን ማድነቃችን የማይካድ ነገር ነው።

ታዲያ በቁም ነገር ከታሰበበት አየ ጥበብ! ስንል የተናገርንበትና የተደነቅንበት ዋና ነገር፦ በሐረጉ አጣጣልና በሥዕሉ ውበት ወይም በአውሮፕላኑ የአየር በረራ ላይ የተወሰነ አነጋገር ነውን? የለም የተወሰነ አይደለም። በነገሩ አተኵረን አስበንበት በምልዐተ አካል የሚገኝ የሰው ልጅ እንዴት አስቦና ተራቅቆ እንዴትስ አስተውሎ፣ ተጠብቦ ስልትና ብልሃት አውጥቶ ሊሠራው ቻለ? በሚያሰኝ መጠይቅ ተጠባቢና ፈልሳፊ ወደሆነው በሰው ዐውደ አእምሮ ውስጥ ወደሚገኘው ጥበብና ማስተዋል መርቶ እንደወሰደን እናገኛለን።

የሰው ልጅ የሠራቸው ሰው ሠራሽ ነገሮች እንኳ፣ አየ ጥበብ ቢባሉም የስያሜው ነጸብራቃዊ ምሥጢር ከእነርሱ ላይ እያስተጋባ እነርሱን በፈለሰፏቸው በሰው ልጅ ዐውደ አእምሮ የሚገኘውን በልቡ የሚፈልቀውን አሳቡንና መራቀቅን፣ ማስተዋልንና ጥበብን ሄደን እንጨብጥ ዘንድ መርቶ ሲያደርሰን እናያለን።

ይኸውም አየ ጥበብ! ስንል የተደነቅንበት ሰው ሠራሽ ነገር መነሻውና ግቡ ሰው ሠራሹ ዕቃ እንዲህ ባለው ውበትና ጌጥ እንዲገኝ ያደረገውን ሰውንና በዓውደ አእምሮው ውስጥ ያለውን ጥበብና አሳብ ማስተዋል እንደሆነ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስገነዝበናል ማለት ነው።

አየ ጥበብ! ስንል በተደነቅንበት ሰው ሠራሽ ጥበቡ መንሥኤነት መነሻውና ግቡ በሰው ዐውደ አእምሮ ውስጥ ወዳለው ጥበብ፥ ማስተዋል ሲመራን ካየን፣ እግዚአብሔር አስጊጦና አሳምሮ ከፈጠራቸው ዓለማት የተመለከትነው ጥበቡና



ማስተዋሉ ከዘለዓለማዊ ባሕርዩ ዘንድ ለመሆኑ፥ እንዴት አያስገነዝብም? መዝ. 18፥19። ስለዚህ ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው የተጠቀሱትን እንመልከትና እንፍረድ።

የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበቡ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው? ሮሜ 11፥33። አቤቱ ሥራህ ታላቅ ነው! ሁሉን በጥበብ አደረግህ። መዝ. 103/104/፥24።

እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ በማስተዋልም ሰማያትን አጸና። በእውቀቱ ቀላያት ተቀደዱ፥ ምሳ. 3፥19፣20። እዚህ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርለት ጥበብ ከእግዚአብሔራዊ ባሕርየ መለኮትና ከህላዌ መለኮቱ ዓውደ አእምሮና ሕይወት ውጭ ሊታይና ፍጡር ሊደረግ አይቻልም። መዝ. 29። ኢዮብ 28፥20-27።

ፍጡር እናድርግህ ቢሉትስ ከእግዚአብሔራዊ ባሕርየ መለኮት ከሚገኝ ዐውደ አእምሮና ሕይወት ተገንጥሎ ይወጣልን?

ስለዚህ የእግዚአብሔር ጥበብ እየተባለ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚነገርና ፍጥረታትም ካለመኖር መጥተው የተፈጠሩበት ጥበቡ የእግዚአብሔር የባሕርዩ ጥበብ ነው።

ዓለምንም ከኃጢአት ሊቤዥና ሊያድን ከድንግል ማርያም የሰውን ሥጋ የለበሰ በቀራንዮ መስቀልም የተሰቀለና ከሙታን ተነሥቶ በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ ጥበቡ ያው ከባሕርዩ የመጣ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። ይህም ጥበብ ወልድ ነው። 1ቆሮ. 1፥21፣25፣30። ክብርና ምስጋና ለእርሱ ለአባቱ ለቅዱስ መንፈሱ ይሁን ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አሜን።

# ምዕራፍ ፲፪

## አርዮሳውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ዳኝነት ከተከሰሱበት ክስ ሊነጹ አይፈልጉምን?

ርግጥ ነው አርዮሳውያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብና ከአተረጓጐሙ የልቡናዊ ተመርሆ ውጭ በመሄዳቸው፣ በትምህርተ መለኮት የጎሠጣ ሥነ ሥርዓት ከሰናቸዋል።

ከከሰስናቸው ክስ ራሳቸውን ንጹሕ ለማድረግ ቢፈልጉ፣ ከዚህ በላይ በሰጠናቸው መሠረት የተናገሩትን የስሕተት ቃል ሁሉ ያስተባብሉ፣ ቢያንስ ቢያንስም ለእነዚህ ጥያቄዎቻችን የእሽታን መልስ ይስጡን፤

1ኛ፦ እግዚአብሔር የባሕርይ ጥበብ አለው። ፍጥረታትንም የፈጠረ በዚህ በባሕርይ ጥበቡ ነው ይበሉ። ምሳሌ 3፥19፣20። ጥበብ የባሕርይ ገንዘቡ በሆነ በፍጹም አምላክ ይመኑ።

2ኛ፦ በአይሁድ ቋንቋ ይሆዋ የሚሉትን አምላክ ዐውደ ሕይወት፥ ዐውደ አእምሮ የሌለው ማድረጋቸውን ይተውና አይሁድ ይሆዋህ ሲሉ ይጠሩት በነበረ ሕያውና ለባዊ ነባቢ በሆነ በእውነተኛ አምላክ ስም ይጥሩት፣ ኤር. 10፥12።

3ኛ፦ ፍጥረትን ለመፍጠር ዓቅምና ከሂል ያለው ፍጡር ጥበብ ወይም ፍጡር ቃል ነው ማለታቸውንና እግዚአብሔር ከባሕርዩ ዐቅምና ከሂል «ችሎታ» የሌለው ሆኖ፣ እርዳታና ድጋፍ የሚያገኘው ከፍጥረት ነው ማለታቸውን ይተው። አምላካችንንም አያዋርዱ፣ እኛንም የፍጡር ፍጡራን ናችሁ እያሉ አይስደቡን። ኢሳ. 40፥12-14። ቍ. 28።

4ኛ፦ እግዚአብሔር የባሕርይ ጥበብ ካለው፣ በባሕርዩ በሚገኝ ጥበቡ ዓለማትን ይፈጥራል እንጂ በፍጡር ጥበብ ዓለማትን ለመፍጠር የሚገደድበት ምክንያት የለም ይበሉ። ጉደሎ አምላክ አድርገው አይጥሩት። መዝ. 135/136/፥5።

5ኛ፦ ዓለማትን የባሕርይ ጥበቡ በሆነ በወልድ አስጊጦ አስውቦ አሳምሮ አስተካክሎ በመፍጠሩ ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚአ ወኵሎ በጥበብ ገበርከ፣ «አቤቱ ሥራህ እጅግ ታላቅ ነው። ሁሉን በጥበብ አደረግህ» ተብሎ የተመሰገነበትን ፍጡር ለሆነው ጥበባቸው ወስደው አይስጡበት። መዝ. 103/104/፥24።



6ኛ፦ የዓለምን ቤዛነት በጥበቡ በሚሆን በወልድ መስቀል በማከናወኑ ይኸውም የእግዚአብሔር ጥበብ በሚሆን በክርስቶስ አድርጎ በፈጸመው ፍቅር እግዚአብሔር የተመሰገነበትን ፍቅር ቀምተው፥ ለፍጡር በመስጠት የእግዚአብሔርን ፍቅር አያቃልሉ። 1ቆር. 1፥18-31።

አርዮሳውያን በእውነቱ በእነዚህ ነገሮች ልባቸውን ዳኛ አድርገው ካመዛዘኑና እንደሚገባ ካሰቡበት፣ ፍጹም የሆነውን አንዱን አምላክ አብረውን የሚያመልኩበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ እናደርጋለን።

# ምዕራፍ ፲፫

## ልዑል እግዚአብሔር ብቻውን፥ ፍጥረታትን ስለመፍጠሩ።

በዘለዓለማዊ እግዚአብሔር አንጻር «ትይዩ» ከፍጡር ወዲያ ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ህላዌ ውጭ ባዕድና ሌላ ሊባል የሚገባው ምን ይገኛል? እግዚአብሔርማ በዘለዓለማዊነትና በሕያውነት እግዚአብሔር አይደለምን?

በቅዱሳት መጻሕፍት ልዑል እግዚአብሔር በቀጥታ ብቻውን ፍጥረታትን እንደፈጠረና ፍጡራንም የማንም ጣልቃ ገብነት ሳይኖር፤ ወይም ረዳትና አማካሪ ሳይኖርበት ከራሱ ክንዛ እጁ እንደተፈጠሩ ተገልጾ ተጽፎአል።

«ከማኅፀን የሠራህ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ፤ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ማን ነበር?» ኢሳ. 44፥24። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላ ማንም የለም፤ ብርሃንን ሠራሁ ጨለማውንም ፈጠርሁ ደኅንነትን እሠራለሁ መከራንም እፈጥራለሁ፤ እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።» ኢሳ. 45፥6፤7።

«አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ ሰማዩንና የሰማያት ሰማይን ሠራዊታቸውንም ሁሉ ምድሩንና በእርስዋ ያሉትንም ሁሉ ባሕሮችንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ፈጥረሃል ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል። የሰማይም ሠራዊት ላንተ ይሰግዳሉ።» ነህ. 9፥6።

አሁንም እኔ ብቻዬን እንደሆንሁ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ አድንማለሁ፤ እኔ እመታለሁ እፈውስማለሁ። ከእጄም የሚያድን የለም። እጄን ወደ ሰማይ እዘረጋለሁና እንዲሁም እላለሁ። ለዘላለም እኔ ሕያው ነኝና። ዘዳግ. 32፥39፤40። 2ነገ. 19፥15።

እስቲ እዚህ ላይ ካቀረብናቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሐሳባችንን ሰብስበን ዓይነ ልቡናችንን አንቅተን በማተኰር ብቻዬን ወይም አንተ ብቻ የሚለውን እንዲሁም ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም የሚለውን ለየት አድርገን እንውሰድና በየእግርጌያቸው እናሥምርባቸው። እነሆም በእነዚህ ጥቅሶች እንደምንመለከተው ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን ሲፈጥር ሳለ፤ ብቻውን ሆኖ እንደፈጠራቸው እንዲሁም ፍጥረታትን ሲፈጥር ሳለ ማንም ከእርሱ ጋር እንዳልነበረ በተብራራ አኳኋን ተገልጾአል።



እንዲህም ከሆነ አርዮሳውያን እንደሚሉት እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር በፈለገ ጊዜ ከራሱ ከሆነ ከመለኮታዊ ባሕርዩ ውጭና ባዕድ የሆነውን ሌላ ፍጡርን ፈጥሮ ቃል ወይም ጥበብ ብሎ ሰይሞ ፈጡራንን ቢፈጥርበት ኖሮ፤ ብቻውን ሆኖ ፈጠረ ያሰኘው ነበርን? በእርግጥ አያሰኘውም ነበር። እንደማያሰኘውም ግልጽ ነውና፤ ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ብቻዬን የዘረጋሁ ምድርን ያጸናሁ እግዚአብሔር ነኝ። ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም ብሎ በተናገረ ነበርን?

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠና እኛም ያለ ጥርጥር እንደምናምንበት፥ ሰው ይዋሻል እንጂ፤ ከዘለዓለም በእውነተኛነቱ ጸንቶ እውነትን ለዘላለም የሚጠብቅ እግዚአብሔር አምላካችን፥ ምን ጊዜም ቢሆን ሐሰት ሊናገር አይችልም። ደግሞስ ምን ቢቸግረው ይዋሻል? ዘኁል. 23፥19። መዝ. 50/51/፥4። ሮሜ 3፥4-8። ቲቶ 1፥1፤2። መዝ. 145/146/፥5፤6።

ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር አንድ ብቻ ሲሆን፤ አርዮሳውያን ግን ዓለማት በፍጡር ቃል ወይም ጥበብ ተፈጠሩ እያሉ ዓለማት ተፈጠሩበት የሚሉት ፍጡር ቃል፥ ወይም ፈጡር ጥበብን ሊያቀርቡልን ይፈልጋሉ። ያው ግን የገዛ ራሳቸው ፍጡር ግቡር ብለውታልና ከአንዱ እግዚአብሔር ባሕርይ ባዕድና ልዩ የተለየ ለመሆኑ በማንም ዘንድ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው።

ከእግዚአብሔር ባሕርያዊ ህልውና ማዶ፥ ወይም አንጻር ባዕድና ሌላ ሊባል የሚገባው ከፍጡር ወዲያ ምን ይገኛል?

ከእግዚአብሔራዊ ህላዌ መለኮት ውጭ ከሚገኝ ፍጥረትስ ወዲያ፤ ሌላ የሚባል ምንድን ነው? ከህላዌ መለኮት ህልውናስ ባዕድ የሆነ «ሌላ» ከተባለ ፍጥረት ወዲያ፥ ማን ሊሆን ነው? ልዑል እግዚአብሔር ደግሞ ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም ሲል፤ የምሩን እንደሚናገር የታወቀ ሆኖአል።

ይህም ልዑል እግዚአብሔር ማንም ሳይኖር ማንም ሳያግዘው ብቻውን ሆኖ ፍጥረታትን በፈጠረ ጊዜ አርዮሳውያን አስቀድሞ እርሱን ፈጥሮ ፍጥረታትን ፈጠረበት የሚሉት ፍጡር ቃል ወይም ፍጡር ጥበብ ጨርሶ እንዳልነበረ፤ በማያወላውል አኳኋን ብሩህና ግልጽ አድርጎ የሚያስገነዝብ ነው።

ልዑል እግዚአብሔር ማንም ሳይኖርና ሳያግዘው ፍጥረታትን ሲፈጥር በነበረ ጊዜ፤ ለብቻው ስለነበረ፤ ብቻዬን ፍጥረታትን ፈጠርሁ ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም። ብሎ በገዛ ራሱ ለራሱ ከመመስከሩና ከማስታወቁ ወዲያ፥ ምን ይጠብቃል?

አርዮሳውያን ፍጥረታት ተፈጠሩበት የሚሉት ከእግዚአብሔር የባሕርይ ህልውና ውጭና ባዕድ ወይም ሌላ የሆነ በልብ ወለድ የፈጠሩት ፍጡር ቃላቸው ወይም ፍጡር ጥበባቸው በዚያን ጊዜ፤ ይኸውም ማለት ልዑል እግዚአብሔር ለብቻው ሆኖ ፍጥረታትን በፈጠረ ጊዜ፤ ያልነበረና፤ በመፍጠር ሥራም ያላገዘ

በመሆኑ በዚህ አካባቢ መቼም ቢሆን ስፍራ ወይም ቦታ የለውም። ኢሳ. 40፥12-15።

ካግራቸውና ከተዋጠላቸው ደግሞ ለዚያ ለፍጡር ቃላቸው ሌላ ጊዜና የሥራ ቦታ ፈልገው ቢያገኙለት አንቃወማቸውም። እግዚአብሔር ብቻውን ዓለማትን በፈጠረ ጊዜ ግን መቼም አልነበረም። አይኖርም።

እንዲያው ለነገሩ እግዚአብሔርን የሚያህል ሕያው አምላክ በአርዮሳውያን ልብ ወለድ የተጠነሰሰ ፍጡር ቃልን ወይም ፍጡር ጥበብን ካልፈጠረ ለብቻው እንደሆነ ከማንም አጋዥ ሳይፈልግ ፍጥረታትን የማይፈጥርበት ምክንያት ወይም ችግር ምንድን ነው?

መጀመሪያ ነገር ማንም ባዕድ ፍጡር በአጠገቡ ያልነበረ እርሱ ብቻውን ከዘላለም የኖረ ነው። ኢሳ. 57፥15። መዝ. 73/74/፡12። መዝ. 89/90/፥1፤2። ዳን. 6፥26።

ደግሞ እርሱ የዘላለም አምላክ የማይታክት የማይደክም ማስተዋሉ የማይመረመር በኃይሉ ብዛትና በችሎቱ ብርታት ምንም ማድረግ የማይሳነው ማንም የማይከለክለው ጌታ ነው። 40፥26-28። ኤር. 32፥17፤18።

እንደዚሁም ከባሕርዩ በሚሆንና ኢፍጡር በሆነው ቃሉ «ይሁን» ባለና በተናገረ ባዘዘም ጊዜ፤ አልፈጠርም አልሆንም፤ አልመጣም የሚልና በእምቢታ ከመፈጠር የሚቀር የሌለ ነው። ዘፍጥ. 1፥3፤27። መዝ. 32/33/፥6፤9። ም. 148/149/፥6።

ይህንም በገዛ ራሱ በነቢዩ አፍ ገልጾታል። «እንዲህ ይላል እግዚአብሔር ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም፤ ከእኔም በኋላም አይሆንም። እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም። ተናግሬአለሁ አድኜማለሁ አሳይቼማለሁ። በእናንተም ዘንድ ባዕድ አምላክ አልነበረም። ስለዚህ እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል። እግዚአብሔር እኔም አምላክ ነኝ። ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ፤ ከእጄም የሚያመልጥ የለም፤ እሠራለሁ የሚከለክል ማነው?» ኢሳ. 43፥10፤13።

እነሆም ልዑል እግዚአብሔር ፍጥረታትን በፈጠረበት ጊዜ በእርሱ ጐን ሆኖ የሚያግዘው ከእርሱ በፊት ሆነ ከእርሱ በኋላ የተሠራ አንድም ባዕድ አምላክ እንዳልነበረ፤ ራሱ የፈለገውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ለመሥራት ከፈለገ ደግሞ፥ የሚከለክለው ምንም ነገር ወይም ምክንያት እንዳልነበረ ከዚሁ ለመረዳት ይቻላል። ዘዳግ. 3፥24። ኢሳ. 13፥14፤28።

ታዲያ! እግዚአብሔር ራሱ በገዛ እጁ ፍጥረትን መፍጠሩን ሳያፍርበት፤ አርዮሳውያን ያፍሩበታልን? አክብረውትስ ወይስ አዝነውለት ይሆን? እግዚአብሔር ራሱ ፍጥረታትን ፈጠርሁ እያለ ሲመካ፤ አርዮሳውያን የለም እርሱ ራሱ ፍጥረታትን አልፈጠረም ፍጥረታት የተፈጠሩ በፍጡር ነው እያሉ ያስተባብላሉና ትምክህቱን ሊያቃልሉበት ይጣጣራሉ።



# ምዕራፍ ፲፩

## መፍጠሩና ጠባቂነቱ የተያያዙ ናቸው።

ልዑል እግዚአብሔር ማንም ከባሕርዩ ህልውና ውጭ የሆነ ረዳትና አማካሪ አጋዥ በአጠገቡ ሳይኖር ወይም ሳያስፈልገው ብቻውን ሆኖ በገዛ እጁ ፍጥረታትን መፍጠሩ ለምስጋናው ክብር ትምክህት መሆኑን፥ አምልኮትም ለእርሱ ለራሱ ለብቻው እንዲገባለት ፈልጎ መሆኑን ሳይገልጽ አላለፈም። እንዲያውም እያስጠነቀቀ እያወጀ አስታውቆበታል። ዘጸአ. 20፥3፤4። ዘዳግ. 4፥39። ኢሳ. 43፥6፤7። ም. 44፥21። በጸሎትና በልመናም ወደ እርሱ ብቻ እንዲቀርቡ ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ፤ ስለ ልጆቼና ስለ እጆቼ ሥራም እዘዙኝ፤ እያለ መጋቢነቱንና ጠባቂነቱን ከመፍጠሩ ሥራ ጋር አንድ አድርጎ ተስፋ ሰጥቶበታል። ኢሳ. 45፥11። ም. 57፥15፤19።

በመሠረቱ ፍጥረታት ሁሉ ይህን ሁሉ አውቀው ሊያመሰግኑት ሊባርኩት ሊያመልኩት የተገባና የሚገባቸው መሆኑን ተገንዝበውለታል። መዝ. 18/19/፥1፤6። ም. 144/145/፥9፤10።

እነሆም ሃሌሉያ እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት፥ በአርያም አመስግኑት፥ ሠራዊቱ ሁሉ አመስግኑት፥ ፀሐይ ጨረቃ አመስግኑት፥ ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ አመስግኑት፥ ሰማየ ሰማያት አመስግኑት። የሰማያት በላይም ውኃ አመስግኑት። እርሱ ብሎአልና ሆኑም እርሱ አዝዞአልና ተፈጠሩም። የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑት ትእዛዝን ሰጠ፥ አያልፉም ለዘለዓለም ዓለም አቆማቸው። መዝ. 148፥1፤5 ተብሎ መጻፉ ይታወሳል።

በተለይ ደግሞ ለባውያን የሆኑ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔራዊ የባሕርይ ህልውና ውጭ የሆነ ባዕድ ፍጡር ሳይፈጥራቸው፤ በልዑል እግዚአብሔር እጅ በመፈጠራቸው፤ ወደ እርሱ ወደፈጠራቸው የሚያቀርባቸው ሆኖ ስላገኙት፤ አምልኮታቸው ምስጋናቸው ጸሎታቸው በዚሁ መሠረት ላይ ማድረጋቸው ይታያል።

እነሆም ኢዮብ በፈተናው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይና ሲለማመጥ የራሱ ተፈጥሮ እንደምን እንደሆነ እያሳሰበ ሲማጠን የተናገረውን እንመልከት።

«እጅህ ለወሰችኝ ሠራችኝም። ከዚያም በኋላ አዙረህ ታጠፋኝ ዘንድ ፈለግህ፤ እንደጭቃ አድርገህ እንደለወሰከኝ አስብ፤ ወደ ትቢያም ትመልሰኛለህ። በውኑ እንደ ወተት አላፈሰስኸኝምን? እንደ እርጎስ አላረጋኸኝምን? ቁርበትና ሥጋ አለበስኸኝ። በአጥንትና በጅማትም አጠነከርኸኝ። ሕይወትና ቸርነት

አደረግህልኝ፣ መጎብኘትህም መንፈሴን ጠበቀች፣ ጥቂት ተወኝ፣ ልቀቀኝም» እያለ ለምኖአል። ኢዮብ 10፥8፣12። ቊ. 22።

ኢሳይያስም እንደ ኢዮብ ባለው ጸሎት ወደፈጣሪው ሲለማመጥ፥ ጥንተ ተፈጥሮውን እያሳሰበ እንዲህ ይላል። «አቤቱ አንተ አባታችን ነህ። እኛ ጭቃ ነን። አንተም ሠሪያችን ነህ። እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን። ... አቤቱ እጅግ አትቈጣ ለዘላለም ኀጢአታችንን አታስብ።» ኢሳ. 64፥8። ም. 29፥15። ሮሜ 9፥20፣21።

ዳዊት የልዑል እግዚአብሔር የእጅ ሥራ በመሆኑ በጣም እየተደነቀ ምስጋናውን ያቀርባል። አንተ ፈጠርኸኝ እጅህንም በላዩ አደረግህ፣ እውቀትህ ከእኔ ተደነቀች፣ መዝ. 138/139/፥5። ቊ. 13 «አንተ ኩላሊቴን ፈጥረሃልና፣ ቊ. 15 እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ አካሌም በምድር በታች በተሠራ ጊዜ አጥንቶቼ ካንተ አልተሰወሩም ገና ገና ሳይሠራ ያልተሠራ አካሌንም አስቀድመው ዓይኖችህ አዩ። ቊ. 14 ግሩም ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ» ብሎአል።

እንዲሁም ዳዊት «ኑ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ በእርሱ በፈጠረን ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንንበርከክ። እርሱ አምላካችን ነውና» እያለ ተናግሮአል። መዝ. 94/95/፥6፣7።

ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ እወቁ፣ እርሱ ሠራን እኛ አይደለንም። እኛስ ሕዝቡ የማሰማሪያው በጎች ነን። መዝ. 99/100/፥3 ይላል። የሐዋ. 14፥15። በዚህ ሁሉ የምንመለከተው ዋና ፍሬ ነገር እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ሲፈጥራቸው በሌላ ፍጥረት አማካይነት ሳይሆን በገዛ ራሱ የሠራቸው መሆኑን ከዚህም የተነሣ የእጅ ሥራውን የማይንቅና ተለምኖ የማይነሳና፣ ፈጥሮ የማይረሳ መሆኑን ነው። እርሱም በምስጋና ሆነ በልመና፥ በአምልኮት ሆነ በመገዛት ወደ እርሱ ለመጠጋት ድፍረና መታመን ሊሰጣቸው የቻለ፥ የእጁ ሥራ የራሱ የግሉ ፍጡራን የመሆናቸው ዋስትና ጽኑዕ መሆኑን በመረዳታቸው ነው። መዝ. 85/86/፥8፣10።

እኔም የፍጡር ፍጡር ባለመሆኔና ራሱ የባሕርይ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር በገዛ እጁ የፈጠረኝ፣ የሠራኝ በመሆኑ፥ በጣም ነው ደስ የሚለኝ። በዚሁ ያለኝ ክብር ትምክህት የሚሰማኝ የልብ ኩራት እጅግ ነው። እንዴት አድርጌ ልገልጸው እንደምችል ይቸግረኛል። ቃልም አላገኝለትም። በእግዚአብሔር እጅ መፈጠር በጣም ነው፣ ደስ የሚያሰኝ። የፍጡር ፍጡር መሆን ግን፣ ምን የሚያስደስት ነገር አለበት? አሣር እንጂ ክብር የለበትም እኮ! ምነው ይህ ለአርዮሳውያን ቢገባቸው?

የሰው አሳብ ግን የማይሄድበት መንገድ የለም። ልብ እንቅርት ይመኛል ይባላል። ይገርማል! ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር በገዛ እጁ እንጂ፣ በፍጡር አልፈጠረንምና ምስጋና ለስሙ ይሁን።



እንግዲህ አርዮሳውያን እንደሚሉት ፍጡራንን የፈጠረ ሌላ ፍጡር ከሆነ፣ ራሱ እግዚአብሔር እኔ ፈጠርኋችሁ ሌላ አታምልኩ እንዴት ሊል በቻለ?

ፍጥረታትም ቢሆኑ በተለይ ለባውያን የሰው ልጆች በሌላ ፍጡር ከተፈጠሩ፣ እግዚአብሔርን የእጅህ ሥራ ነን። አትናቀን አትጣለን እያሉ ለምን አሳሰቡ? ለምንስ ጸለዩና ማለዱ? ለምንስ ይህን እያሳሰቡ አመሰገኑት? ለምንስ አመለኩት? ከእግዚአብሔር በቀር የፈጠራቸው ሌላ ባዕድ ፈጣሪ እንደሌለ በመረዳታቸው አይደለምን? መዝ. 99/100/፥3። ዘዳግ. 32፥3፣7።

እነሆም ልዑል እግዚአብሔር በማይታበል ቃሉ «እኔ ለብቻዬ ሁሉን ፈጠርሁ፣ ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም።» ሲል፣ አርዮሳውያን ደግሞ በእርሱ አንጻር «ትይዩ» ሆነው እየተቃወሙት የለም ፍጥረታት ሲፈጠሩ፣ አንተ የፈጠርኸው ፍጡር «ካንተ» ጋር ነበረ። ፍጡራንም የፍጡርህ ፍጥረታት ናቸው ይሉታል።

ፍጡራን ሁሉ ይልቁንም ለባውያን የሆኑ ሰውና መላእክት ፈጣሪያቸውን ዐውቀው የፈጠረን እግዚአብሔር ነው ሲሉ፣ አርዮሳውያን ደግሞ የለም እግዚአብሔር ራሱ ቀጥታ አልፈጠራችሁም። የፍጡሩ ፍጡራን ናችሁ ይሉአቸዋል።

ይህም አርዮሳውያን ያፈለቁት ፍልስፍና፦

1ኛ፥ ልዑል እግዚአብሔር ለምስጋናው ክብር ትምክህት ሲል፣ በሥራው ተፈራራቂ ሳይኖረው በፈጠረው ፍጥረቱ ደስ እንዳይለው፣ የሰውን ልብ ከእርሱ ለማስከዳትና በዚሁ ሁኔታ እርሱን ለማሳዘን ነው። መዝ. 103/104/፥31። ም. 8፥1-3።

2ኛ፥ በእግዚአብሔር ባሕርየ መለኮት ውስጥ ያልታወቀውን ከልባቸው አንቅተው አንድ ፍጡር ፈጥረው ንዑስ አምላክን ፈጥሮ ፈጠረን እያሉ እግዚአብሔር የሚጠላውን አምልኮ ባዕድ ጣዖ አድርገው ለማቋቋም አስበው ካልሆነ በቀር፥ ሌላ ምን ጥቅም ሊገኝበት!

3ኛ፥ ለባውያን ፍጥረቶች ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ፈጠረን የራሱ የእጆቹ ሥራ ነን፣ ፈጥሮ አይጥለንም፣ ከእኛ ጋር ነው ይረዳናል ይጠብቀናል። ይመግበናል፥ ይመራናል፥ ይራራልናል፥ ያድነናል እያሉ፤ እንዳይማጠኑበት፥ እንዳይመኩበት፥ እንዳይታመኑበት፥ ከእርሱ በቀር ሌላ ፈጣሪ ገባሪ የባሕርይ አምላክ እንደሌለ ዐውቀው፥ ተረድተው፥ ብቻውን እንዳያመልኩትና እንዳይሰግዱለት፣ በእምነት በፍቅር በተስፋ እንዳይጠጉት፣ በእርሱ በሠራቸው ደስ ብሎአቸው እንዳይኖሩ፣ በጸሎትና በምስጋና እንዳይቀርቡትና እንዳይጠቀሙ ነው።

ባጭሩ እንደዚህ ያለው የአርዮሳዊ ፍልስፍና ውጤት እግዚአብሔርን ከፍጥረቱ፥ ፍጡራንም ከፈጣሪያቸው የሚያራርቅና የሚያለያይ የሚያቆራርጥ ከመሆኑ በቀር፣ በዚሁ ረገድ የሚጠቅም ነገር አለበት የሚያሰኝ የሚያመረቃ የመጽሐፍ የተመርሆ ልቡና ምሥጢር ፈጽሞ የለበትም።

# ምዕራፍ ፲፩

## ሐተታ

ባለፈው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረ ብቻውን ነው ሲልና፤ አርዮሳውያንም እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጡር ነው ፍጥረታት የተፈጠሩ ሲሉ ያሰሙትን በየወገኑ ስናይ ነበር። በዚህ ጊዜ ሁሉም እግዚአብሔር ፍጥረታትን በፈጠረ ጊዜ፤ ፍጡር ቃልን ፈጥሮ በእርሱ አማካይነት ፍጡራንን ሁሉ ይፈጥር ኖሮ እንደሆነ፤ ወይም ከእርሱ ጋር አብሮት የሚፈጥር ከግዕዘ ባሕርዩ ሌላ የሆነ ፍጡር ኖሮ እንደሆነ፤ ለማጣራት እንዲቻለን ከቅዱሳት መጻሕፍት ስንመረምር እንደነበርን የሚታወስ ነው።

በተለየ ግልጥ ሆኖ ሲነገር ያገኘነው ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርን ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ ከእኔ ሌላ ማንም አልነበረም። የሚልና የመሳሰለውም የመጽሐፍ ቅዱስ ኀብረተ ቃላት ሲሆን፤ ማንም ሳይኖር ለብቻው ሁሉን እንደፈጠረ የሚገልጽ ማስረጃ ነበረ። ኢሳ. 44፥24።

ይህም አባባል ፍጥረታት በተፈጠሩ ጊዜ ከእውነተኛው እግዚአብሔር ውጭና ባዕድ የሆነ የአርዮሳውያን ፍጡር ቃል ከእግዚአብሔር ጋር እንዳልነበረ፤ በማያሻማ ገለጻ የሚያስረዳ ዘይቤ ሆኖ መገኘቱ ነው።

በዚሁ አንጻር /ትይዩ/ ደግሞ ልዑል እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ተናግሮ በዚህ በተናገረበትና በእርሱ ህልው በሆነ ቃሉ ፍጥረታትን መፍጠሩ ከዚህ አስቀድሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ተብራርቶ መገለጹን ተገንዝበናል። ዘፍጥ. 1፥1-27። መዝ. 32/33/፥9።

እንግዲህ ልዑል እግዚአብሔር ፍጥረታትን ይፈጥር በነበረበት ጊዜ፤ «ይሁን» እያለ ተናግሮ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃል መኖሩ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ ከተረጋገጠ፤ ልዑል እግዚአብሔር ማንም ከእርሱ ጋር ሳይኖር፤ ለብቻው ፍጥረታትን ፈጠረ ለማለት ያስደፍራልን? ይኸው «ይሁን» እያለ ተናግሮ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃሉ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ይፈጥር በነበረ በዚያኑ ጊዜ፤ መኖሩ ተረጋግጦ ታውቆ የለምን? የሚል መብራራት የሚያስፈልገው ጥያቄ መቅረቡ ይታመናልና ነው።

ጥያቄው ምንም እንኳ እንደ አጣብቂኝ የተሠነዘረ የውጥረት መጠይቅ ቢመስልም፤ የፍሬ ነገሩ እውነተኛ መልክ፥ ብሩህ ሆኖ እንዲገለጽ የሚረዳ ነውና፤ ተገቢ መልስ ይሰጠው ዘንድ ይጠበቃል።



እምን! ልዑል እግዚአብሔር ፍጥረታትን ይፈጥር በነበረ ጊዜ፤ «ይሁን» እያለ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃሉ በእርሱ ዘንድ መኖሩ፥ የተረጋገጠና በመጽሐፍ ቅዱስ ብሩህ ሆኖ የተገለጸ ነው። ይኸው ሆኖ ሳለ ግን፤ ማንም ከእርሱ ጋር ሳይኖር ብቻውን እንደሆነ ፍጥረታትን ፈጠረ ተብሎ የተጻፈውንና የተነገረውን የሚጐንጥና የሚያፈርስ አይደለም።

እንግዲህ ቀጥሎ ያለውን በማስተዋል እንከታተል። እነሆም እግዚአብሔር አለ። ምን አለ! ብርሃን ይሁን አለ። ብርሃን ሆነ። በጠቅላላው እስመ ውእቱ ይቤ ወኮኑ ወውእቱ አዘዘ ወተፈጥሩ። እርሱ ይሁን ባለ ጊዜ፤ ይሁኑ የተባሉት ፍጥረታት ሆኑ፤ እርሱ ባዘዘ ጊዜም ተፈጥረው ተገኙ። እያሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኙ ጉልህ የሆኑ ጥቅሶች ያስረዱናል። ዓይነ ልቡናችንን ስክክ አድርገን መጽሐፍ ቅዱስ ወደሚለው በጥንቃቄ ብናተኵር፤ ትርጕሙ ከዚያ ከራሱ ሲብራራልን እናገኘዋለን። ዘፍጥ. 1፥3-27። መዝ. 32/33/፥9።

ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ተናግሮ ፍጥረታትን ይፈጥርበት የነበረ ቃሉ፥ የመናገሪያ ቃሉ ሆኖ መገኘቱ ነው።

ልዑል እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ተናግሮ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃሉ፥ የገዛ ራሱ የሚናገርበት የመናገሪያ ቃሉ ከሆነ ዘንድ፤ ከእግዚአብሔራዊ የባሕርይ ህልውና ውጭ ያይደለ ባዕድ ወይም ሌላ የማይባል እንደሆነ፤ ገሃድ ሆኖ የሚታይ አይደለምን? ልዑል እግዚአብሔር «ይሁን» እያለ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃሉ የመናገሪያ ቃሉ ሆኖ በተጨበጠ ማስረጃ ከመገለጹና ግሁድ ሆኖ ከመታወቁ ወዲያ፥ ምን ይፈለጋል? ዓለማትን የፈጠረበት ቃሉ ሆኖ ከተገኘ ዘንዳስ ከመፈጠር ነጻ የሆነ በባሕርይ ከእግዚአብሔር አንድነት ያለው ሆኖ ከመታወቅ ሌላ፥ ምን የሚያስተባብሉት መንገድ ይኖራል?

ምንም እንኳ ይህ ነገር ግልጽና በሰው ሁሉም ዘንድ የታወቀ በመሆኑ፤ ገላጭ ምሳሌ ያስፈልገው እንዳልነበረ ቢታወቅም ቅሉ፤ ያላሰቡበት ወገኖች ቢኖሩ፤ እንዲያስቡበት በማለት ምሳሌውን ከሰው ወስደን ማስረዳት የግድ ሳይሆንብን አልቀረም።

እነሆም፤ በነጠላ ቍጥር የሚጠራ አንድ ብቸኛ ግለሰብ ለምሳሌ አቅርበን፤ የገዛ ራሱን ድምፅ አሰምቶ በቃሉ ሲናገር እንስማ። ሰውየው እንዲህ ያለውን ድርጊት ሲፈጽም በሚገኝበት ጊዜ፤ ያው ራሱ አንድ ብቸኛ ግለሰብ ሆኖ ከመታየቱ በቀር፤ ሰውየው ሌላ፥ አሰምቶ የተናገረበት ቃሉም ከሰውየው ብውድና ሌላ አድርገን ለየብቻው እንገምግም። ነገር ግን በገዛ ቃሉ የሚናገር አንድ ሰው ብቻ መሆኑን፥ አረጋግጠን እናውቃለን።

በሌላም አገላለጽ እያንዳንዱ ሰው ወደ ፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ፤ የሚበየንበት ወይም የሚበየንለት /የሚፈረድለት/ በሚናገርበት ቃሉ እንደሆነ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ ተናግሯል። ይኸውም /እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእም ቃልከ ትትኴነን/ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ ከቃልህም የተነሣ

ይፈረድብሃል። ማለቱ ይታወሳል፡ ማቴ. 12፥37። እዚህ ላይ ሰውየው ብይን ወይም ፍርድ ሊቀበል የበቃው፣ የተናገረው ቃሉ ከእርሱ ባዕድ ስላልሆነ፣ ከሰውየው ልዩ ሆኖ የማይለይ አብሮ በቀል ቃሉ ስለሆነ አይደለምን?

በዚህም ሰውየው ሌላ፥ የተናገረበት ቃሉም ከሰውየው ባዕድና ሌላ ሊሆንና ሊታይ እንዳልበቃ በሚገባ ተመልክተናል። እንግዲያውስ አንዱ እግዚአብሔር አምላካችን «ይሁን» እያለ ተናግሮ ፍጥረታትን የፈጠረበት ቃሉ፥ ያው በእርሱ ህልውና ሆኖ የኖረ የመናገሪያ ቃሉ ነው እንጂ፣ ከእርሱ ባዕድ ወይም ሌላ ልዩ አይደለምና፣ «ልዑል እግዚአብሔር ማንም ሳይኖር ብቻውን ሆኖ ፍጥረታትን ፈጠረ።» ተብሎ የተነገረውን የሚያጸና እንጂ፣ የሚያፈርስ ወይም የሚያደናቅፍ ነገር የለበትም። ይኸውም ቃሉ ከእግዚአብሔራዊ ህልውና ከልቡና ከእስትንፋሱ «ከሕይወቱ» ልዩ ሆኖ አይታይምና ነው። ኢሳ. 42፥1-8። 45፥18-23።

እነሆም ወንጌላዊው ዮሐንስ በጥንተ ወንጌሉ፥ ቃል አስቀድሞ መኖሩንና ሲኖርም በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ መኖሩን፣ ከዚህም የተነሣ ራሱ ቃል እግዚአብሔር መሆኑን ገልጾ ከአንድ እግዚአብሔር ውጭ ተነጥሎ ወይም ሌላ ሆኖ የማይታይ መሆኑን አስታውቆአል። ከዚህም ጋር ሁሉ በእርሱ የሆነ፥ ያለእርሱ ግን ምንም የሆነ የሌለ ቃል ከነባቢው «ከተናጋሪው» ከእግዚአብሔር የባሕርይ አንድነት ያለ እንደመሆኑ፣ በአንዲት እግዚአብሔራዊነት ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ተብሎ መጠራቱን ያስታውቧል። ዮሐ. 1፥1፤3። ዮሐ. 1፥13።

ስለ ጥበብ ያለውም፣ ገለጻ ሐተታው እንደዚሁ ነው። አዎን፣ ልዑል እግዚአብሔር ማንም ከእርሱ ጋር ሳይኖር፣ ብቻውን ፍጥረታትን እንደፈጠረ የተነገረውና በመጽሐፈ ምሳሌ ደግሞ ጥበብ ሰማዮችን በዘረጋ ጊዜ አብሬው ነበርሁ፣ በቀላያት ፊትም ክበብን በደነገገ ጊዜ፣ ደመናትን በላይ ባዘጋጀ ጊዜ፣ የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ፣ ለባሕርም ዳርቻ በወሰነ ጊዜ፣ ውኃም ከትእዛዙ እንዳያልፍ የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ፣ ያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ። ዕለት፣ ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ። በፊቱም ሁልጊዜ ደስ ይለኝ ነበርሁ። ብላ እንደተናገረች ይታወሳል። ምሳ. 8፥27-30። በዚሁ ገለጻም የቃል አካላዊነት አጕልቶ ሲያስቀምጥ ያሳይሃል።

እነሆም አሁን እንባቢ፣ በአንድ ወገን ከማኅፀን የሠራህ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ሁሉን የፈጠርሁ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ፣ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ። ከእኔ ጋር ማን ነበረ! የሚለውንና የመሳሰለውን ሰምቶአል። ኢሳ. 44፥24።

ምንአልባት አንባቢው ሁለት ገለጻዎች የተለያዩ የተቃረኑ ይመስሉት ይሆን? ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የተጣላና ኅብረተ ቃላቶች የማይስማሙ ናቸው፣ ብሎ ይፈርድ ይሆን? ምናልባትም በመጽሐፍ ቅዱስ ከተነገረው አንድን ገለጻ ውድቅ አድርጎ፥ አንዱን መርጦ ይይዝ ይሆን? ነገር ግን አንባቢው በማንበብ ብቻ ሳይሆን፣ ጌታ በወንጌል መጻሕፍትን መርምሩ ባለው መሠረት፣ ጠንቅቅ



ብሎ ከመረመራቸው፣ አንድ ሆነው ያገኛቸዋል እንጂ፣ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሆነው አያገኛቸውም።

አዎን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ላይ ላዩን እያነበቡ መጻሕፍትን መርምሩ፣ የሚለውን አምላካዊን ድምፅ ሳይጠቀሙበት ለሚሄዱ የእንቅፋት ድንጋይ ሆኖ ጭራሹን እንዳይጥላቸው የሚያስፈራ ነው። 1ዮሐ. 5፥39። 1ጴጥ. 2፥7፤8።

የመጽሐፍ ቅዱስን አመራር ተከትሎ ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያጠና ደቀመዝሙር ግን፣ ልዑል እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠርሁ፣ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርን ያጸናሁ እኔ ነኝ ማንም አልነበረም። በማለቱና፣ ጥበብም ሰማያትን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ... የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ ያን ጊዜ እኔ እርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ፣ በፊቱም ደስ ይለኝ ነበረ። በማለትዋ መካከል፣ የሚያጣርስ ነገር የሌለበት፣ ይልቁንም እርስ በርሱ የሚስማማ ኅብረተ ቃላት መሆኑን በቶሎ ሊረዳ ይችላል።

ይኸውም ከሁሉ አስቀድሞ አንዱ እግዚአብሔር ልቡና፣ ዕውቀት፣ ጥበብና ምክር፣ ኃይልና ሕይወት ሕሊናና ቃል አሳብና ፈቃድ ያለው ሕያው አምላክ እንጂ፣ ምዉት አምላክ እንዳልሆነ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተረድቶ ያወቀ ነው።

ማለት፡- ልቡናና ዕውቀት ጥበብና ምክር ሕሊናና ቃል፣ ሐሳብና ፈቃድ ክሂል ወዘተ... ከእግዚአብሔርነቱ ባሕርይ የሚገኙ ከዘለዓለም ሲኖር በእርሱ ዘንድ በአንድነት ባለመለየት የኖሩ መሆናቸውን፣ በመበደር ሆነ በመፍጠር ከባሕርዩ ውጭ ያላመጣቸው መሆኑን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ጠንቅቶ ያስገነዝባልና ነው። ኤር. 10፥11-16።

እንግዲህ ከእነዚህ፣ እላይ ከተጠቀሱት መካከል አንድዋ፣ የሆነች ጥበብ ሰማያትን በዘረጋ ጊዜ አብሬው ነበርሁ። ያን ጊዜ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ ብላ ብትናገር፣ እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ብቻዬን ሰማያትን ዘረጋሁ ብሎ ቢናገር፥ በሁለቱ አነጋገር መካከል የሚጣረስና እርሱ በርሱ የሚቃረን አሳብ የለበትም። ላለመጣረሱ መታየት ያለበት መሠረተ አሳብ፣ ጥበብ አብሬው ነበርሁ፣ ስትል፣ ከባሕርዩ ውጭ ፈጥሮ አመጣኝ ያላለች መሆንዋ ነው። ዳግም ብቻውን ጥበብ ያለው አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚመሰክርለት ነው። ሮሜ 16፥27። ብቻውን ጥበብ ያለው አምላክ መሆኑ ደግሞ ያለ ጥበብ ያልኖረ አምላክ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ሮሜ 16፥27።

መሠረተ ነገሩ እስከዚህ ድረስ ከሆነም እግዚአብሔር ሰማይን በዘረጋ ጊዜ፣ ከባሕርዩ በሚገኙ ኃይሉና ጥበቡ እንደሆነ፣ ምድርንም ባጸና ጊዜ፣ ከባሕርዩ በሚገኝ ማስተዋሉ፣ ጥበቡም እንደሆነ፣ ጥልቆችን በቀደደ ጊዜ፣ ከባሕርዩ በሚሆን ዕውቀቱና ጥበቡ እንደሆነ፣ የተረዳ ሰው፥ እግዚአብሔር ሰማያትን ምድርን ወዘተ...በፈጠረ ጊዜ፣ ከራሱ ህላዌ ውጭ የሆነ አንድም ፍጥረት አልነበረምና፣ ማንም አላገዘኝም፣ እኔ ብቻዬን ነበርሁ፣ ብሎ የተናገረው የራሱን ሕይወትነት የሚገልጹ ከባሕርዩ የሚገኙ ጥበብ ቃል፣ አብረውኝ አልነበሩም ማለቱ እንዳልሆነ ማስተዋል አይቸግረውም።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ ባሕርይ ጥበብና እውቀት ሕይወትና ኃይል ሕሊናና ቃል ከሂል አልነበረኝም ሲል ተሰምቶ አያውቅም። ተመልከት? ብቻውን ጥበብ ያለው እግዚአብሔር፤ ብቻውን ሆኖ ሳለ ጥበብ ያለው አምላክ እንደሆነ አታስተውልምን?

እንዲያው ለነገሩ እግዚአብሔር ከባሕርዩ ጥበብና ዕውቀት ልብና አእምሮ ሕይወትና ኃይል ሕሊናና ቃል ሳይኖረው፥ ፍጥረታትን ቢፈጥር ኖሮ፤ ፍጥረታትም ያለዚህ ተሠርተው ቢሆኑ ኖሮ፤ ምን ዓይነት ቅርፅና መልክ ዓይነትና መጠን የኑሮ አቋምና የምግብ ሥርዓት እንደምን ያለ በሆነ ነበር? ቢሆን ኖሮ? ብለን ተናገርን እንጂ፤ ሊሆን ይችል እንዳልነበረ ዘንግተን አይደለም።

ይህ ሁሉ ግን ከዘላለም ህልውናው በነበረ ከባሕርዩ በተገኘ ሕይወቱ ኃይሉ ልቡናው ማስተዋሉ፤ ጥበቡና ቃሉ ዐውቆ ተጠብቦ፤ በመሥራቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቀ ዐቢይ ግብርከ እግዚአ ወኵሉ በጥበብ ገበርከ፤ አቤቱ ሥራህ ታላቅ ነው። ሁሉን በጥበብ አደረግህ እያለ በአድናቆት ይገልጸዋል። መዝ. 103/104/፥24። ም. 135/136/፥5፤9።

ልዑል እግዚአብሔር ይህን በባሕርይ ዕውቀቱና ጥበቡ ፍጥረታትን ይፈጥር ይሠራ በነበረ ጊዜ፥ ከባሕርይ እውቀቱ ከባሕርይ ጥበቡ ወዘተ... በቀር፤ ከአምላክነቱ ውጭ ማንም ረዳት ወይም የሚያግዘው አጋዥ አልነበረምና፤ ብሉ መንቲያ ስለሌለባት ስለ አንዲት የባሕርይ አምላክነቱ ልይት አድርጎ ቢናገር፤ እውነቱን አይደለምን? መቼውንም እርሱ አይዋሽምና ሁል ጊዜ እውነቱን ይናገራል። የለም ሁለተኛ አምላክ ፈጥረህ ከአጠገብህ አኑር ብለህ ልትመክረው ትፈልጋለህን?

ስለ ጥበብም ልዑል እግዚአብሔር በዘለዓለማዊ ህልውናው ሲኖር፤ በባሕርዩ ዕውቀትና ጥበብ አልቦ ሆኖ፥ ያልኖረ መሆኑን ሁሉንም በጥበብ መሥራቱ ግልጽ ስለሆነ ከባሕርዩ ተለይታ የማታውቅ ጥበብም ሰማያትን በዘረጋ ጊዜ አብረው ነበር... ያን ጊዜ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ ብላ ብትናገር፤ አነጋገርዋ እውነት አይደለምን? በተመርሆ ልቡናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተ ቃላት መስማማቱ የሚረጋገጠው በዚህ ገለጻ አኳኋን ርትዕ ሆኖ ለቅን ሕሊና ሲታይ ነው።

እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ፤ በማስተዋልም ሰማያትን አጸና፤ በዕውቀቱም ቀላያት ተቀደዱ። ደመናትም ጠልን ያንጠበጥባሉ። ምሳ. 3፥19፤20።

ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፤ ዓለምን በጥበቡ የመሠረተ፤ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው። ኤር. 10፥12። ም. 51፥15።

የጥበቡ ጥልቅ ሆይ፥ ሮሜ 11፥33። ሁሉ ከእርሱ፥ ሁሉ በእርሱ፥ ሁሉ ለእርሱ ነው፤ ሮሜ 11፥36። ለእኛስ ነገር ሁሉ፥ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን። ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን፤ አሜን፦ 1ቆር. 8፥6።



# ምዕራፍ ፲፮

# አሻራ

እንደዚሁም ሁሉ በእግዚአብሔር በቃሉ ስላለው የባሕርያዊ ህልውና አንድነት እየቀደመ እየተገለጸ በሄደ ቍጥር፥ የመተርጐማን ማወቅ ደግሞ እየቀደመ ይሰፋል።

እስካሁን ድረስ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ፍጥረታትም በእግዚአብሔር ቃል ስለመፈጠራቸው የተገለጸው ለማስረጃነት ብቻ፥ የሐዲስ ኪዳን ጥቅስ ባይታጣበትም አብዛኛው ከብሉይ ኪዳን መደብ የሚያንጸባርቅ ፍሬ ነገር እንደነበረ አንዘነጋም።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል የመናገሪያ ቃሉ ስለሆነ፤ በእርሱ ህልው ሆኖ የሚኖር መሆኑን ከዚህም የተነሣ ልዑል እግዚአብሔር ፍጡራንን ይፈጥር በነበረ ጊዜ፤ «ብቻዬን ፈጠርሁ፤ ከእኔ ጋር ማንም አልነበረም» በማለት ለህላዌ መለኮቱ በተጫፋሪነትና በመጋራት የሚታይ ባዕድ የሥራ ጓደኛ እንዳልነበረ ማስታወቁን አይተናል፥ ተረድተናልም። ይህን ሁሉ በአእምሮአችን እያስታወስን፥ እስቲ ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ወደ ተገለጸው ትምህርታዊ መመሪያ እርምጃችንን እናቅና።

እነሆም በሐዲስ ኪዳን ወንጌላዊው ዮሐንስ በጥንተ ወንጌሉ /ወንጌሉን/ ለመጻፍ አንድ ብሎ ሲወጥን፤» «በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፥ ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ በመጀመሪያ ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም ሕይወትም በእርሱ ነበረች» ብሎ ሲጽፍ እናያለን። ዮሐ. 1፥1፤3።

በዚሁ አነጋገር ውስጥ ወደሚገኘ ትምህርታዊ ፍሬ ነገር ከመግባታችን በፊት በድርሰቱ አቀራረብ የሚገኘ የአጻጻፍ ይዞታን በሥርዓቱ ለይተን ለማወቅ እንድንችል የአጻጻፉን ስልታዊ የአቀራረብ ዓመል አስቀድመን ብናውቅና ብንጠነቀቅ ጠቃሚ ይመስለናል። ሌላው ይቈይና በብሉይ ኪዳን በኦሪት ዘፍጥረት 1፥3-27። ፍጥረታትን የፈጠረ እግዚአብሔር ስለመሆኑ ሲፈጥርም ይሁን እያለ ተናግሮ በቃሉ ስለመፍጠሩ ግልጽ ሆኖ መናገሩን አይተናል።

ስለዚህም በዚሁ የአጻጻፍ ገለጻ ስንመረምር፤ የአንቀጹ ባለቤት እግዚአብሔር እንደሆነ ያለ ጥርጥር ለመረዳት ችለናል። ዘፍጥ. 1፥3-27። «ይሁን» እያለ የተናገረበት ቃል ግን ከእግዚአብሔር እየወጣ ሁሉን በአዋዳጅነት ሲያዋድድ፤ ሲያደርግ ተገልጾ እንደተነገረ ተገንዝበናል። ወንጌላዊው ግን በመጀመሪያው የነበረውን በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው የሆነውና ራሱም እግዚአብሔር የሆነው

ሁሉን እንዲሆን እንዲፈጠር ያደረገው ቃል መሆኑን እየገለጸ ቃልን ለተነገሩት አንቀጾች ሁሉ ባለቤት አድርጎ በአጻጻፉ አቅርቦት ይታያል። ዮሐ. 16፥26፣30። ም. 1፣2።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመዋቅር ተጀምረው ወደ መሠረት እየመሩ የሚያደርሱ ጥሬ ንባቦች ወይም የአጻጻፍ ስልቶች ይገኛሉ። ከእነዚህም ጥሬ ንባቦች አንዱ በዚህ ጊዜ ወንጌላዊው ዮሐንስ ለወንጌሉ ጥንት /መነሻ/ አድርጎ ጽፎት የምንመለከተው ሆኖ ይገኛል፣

ለዚህም የመጻሕፍት መፈክራን የሆኑ ብሔራውያን ሊቃውንት ምሳሌ ሲሰጡበት «መዋቅሩ እስከ መሠረቱ፣ መሠረቱም እስከ መዋቅሩ የተያያዘ ነው እንጂ የተለያየ አይደለም» ይላሉ።

ይህ አብነት በመጽሐፍ ቅዱስ የአተረጓጐም ዘዴ ራሱን የቻለ መመሪያ አለው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር «አለ፤ ይሁን» በሚልበት ጊዜ በቃሉ ፍጥረታትን ፈጠረ በሚያሰኝ አቀራረብ የግሥ አንቀጹ ባለቤት እርሱ እንደሆነ እየገለጸ ከመሠረቱ ቢጀምር፣ ወንጌላዊው ደግሞ «አስቀድሞ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ ቃልን ለግሥ አንቀጽ ባለቤት አድርጎ በመዋቅሩ ቢጀምር፣ የተያያዘ ነው እንጂ የተለያየ ሆኖ አይገኝም።

እንደዚህ ያሉ በመዋቅር የሚጀመሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባቦችና ዐውቆ ለማሳወቅ የሚጣጣር መምህር ሁሉ በመድረሻው የመነሻውን ምሥጢር ያገኝ ዘንድ በጽኑ ኀሠሣ «የጥናት ምርምር» ፍላጎት እንዲነሣሣ ለማነቃቃት ከአምላካዊ ምንጭ የተሰጡ መፈተኛዎች ይመስላሉ። በመነሻው ምሥጢራዊ መድረሻውን መረዳት ስንል፣ ከመድረሻው ውስጥ የተቋጠረውን ትምህርታዊ ምሥጢር ወይም ገለጻ በጥሬ ንባቡ አሻራ እየተመሩ ለማወቅ ለመጨበጥ መቻሉ ማለታችን ነው። ይህም ከተመርሆ ኀሠሣ ልቡናዊ አንድ መንገድ ነው።

<u>ለምሳሌ</u>፦ በአሁኑ ዘመን ስለ አሻራ ይዞታ ብዙ ሰው ሳያውቅ የሚቀር አይመስልም። ይልቁንም አብዛኛው ሕዝብ የሚፈርመው በጽሕፈት ሳይሆን በጣት አሻራ መሆኑ ታውቆ ያደረ ነውና ምሳሌ አድርገን ለመግለጽ ብንጠቀምበት አይከፋም ይሆናል።

በአሻራ ጥናት ሙያ የተሰማሩ ወይም በዚሁ ተግባር የሚሠሩ ሰዎችም አሻራው አስቀድሞ ከተገኘላቸው ዘንድ፥ በዚሁ በአሻራው ተመርተው ተፈጸመ ለሚባለው ድርጊት፥ አድራጊው ማን እንደሆነ ለማወቅ እንደማያዳግታቸውና እሙን ማረጋገጫ ለመጨበጥ እንደሚችሉበት ያምኑበታል።

አሻራ ሲባል የጣት ብቻ አይደለም የድምፅም የእግር ዱካ /ኮቴ/ ወይም እርምጃም የመሳሰለም ሁሉ አሻራ ሊሆን ይችላል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብም አሻራን የሚመስሉና በስተጀርባ በኋላቸው የተደበቁትን መርተው ለማሳወቅ የሚያበቁ የድምፅ፣ የእግር እርምጃ፣ የጣት



አሻራዎች ይገኛሉ። እነዚህንም ምሳሌ አድርገን እንገልጸው ዘንድ ላለን ትምህርት ብንጠቀምባቸው መልካም ነው።

1ኛ፥ <u>የድምፅ አሻራ</u>።

የዔሳውና የያዕቆብ አባት ይስሐቅ አርጅቶ ዓይኖቹ ደክመው ማየት በተሳነው ጊዜ፣ ታናሽ ልጁ ያዕቆብ በረከትን ከወንድሙ ከዔሳው ለመንጠቅ ፈለገ። ስለዚህም የጠቦትን ፀጉር በእጆቹና በአንገቱ አላክኮ፥ ወንድሙን ዔሳውን መስሎ፥ እኔ ልጅህ ዔሳው ነኝ እያለ ወደ አባቱ ቀረበ። ዘፍጥ. 27፥8፣20።

ይስሐቅ ግን በዳበሳ ጠጉሩን አይቶ ዔሳው መሰለው በድምፅ ግን የያዕቆብ መሆኑን አውቆ «እጆች ግን የዔሳው ናቸው። ድምፅም የያዕቆብ ነው» ብሎ ተናገረ። ዘፍጥ. 27፥22፣23።

እዚህ ላይ በመግለጫነት ረገድ ልንጠቀምበት የምንፈለገው አረጋዊው ይስሐቅ ምንም እንኳ በፀጉሩ በተደረገው አስመሳይነት ቢታለል፣ ራሱን የደበቀውን ያዕቆብን በድምፁ አሻራ ለይቶ የማወቁ ነገር ነው።

ራሱን ደብቆ እንዲያውም ስሙን ለውጦ የተናገረውን ያዕቆብን አባቱ ሊያውቀው የቻለ መጀመሪያ ምንን ይዞ ወይም ጨብጦ ነው? ቢሉ፣ ይስሐቅ በያዕቆብ ድምፅ ላይ የተለመደ ጥናት ስለነበረው ነው ለማለት ይቻላል። እንግዲህ በድምፁ ጥናት ተመርቶ ራሱን የደበቀውን ያዕቆብን ሊያውቀው ቻለ። ዘፍጥ. 27፥21፣23።

2ኛ፥ <u>የእግር ዱካ «ኮቴ» አሻራ</u>።

አዳም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተላለፈ ጊዜ፣ በገነት ውስጥ ሸሽት ጀምሮ ነበር። በዚህ ጊዜ በገነት የሚመላለሰውን ድምፅ ሰማ። ዘፍጥር 3፥8። ይህን በገነት ሲመላለስ የሰማው ድምፅ የእግዚአብሔር አምላክ ድምፅ እንደሆነ ዐወቀና ተሸሸገ። ያለጥርጥርም ያው የእግዚአብሔር ድምፅ ነበረ።

3ኛ፥ <u>የጣት አሻራ</u>።

ከዚህ ሁሉ ላቅ ያለና ሽብር ያልተለየው ፍላጎትን ቅስቀሳ ድርሱን «ልኩን» እስከታሳይ ያሯሯጠች አስደናቂ አሻራ ግን በባቢሎን ንጉሥ በብልጣሶር አደራሽ ስትጽፍ የታየች ጣት ነበረች። የዚህችን ታሪክ በመጠኑ ብንገልጽ ምሳሌነትዋ ልናብራራው የምንፈልገውን ትምህርት ያጐላልናል።

የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶር አዳራሽ ተገኝቶ ለመኳንንቱና ለመሳፍንቱ ለወይዛዝርቱ ለአእላፍ ሠራዊቱ ግብር አግብቶ ያበላ ያጠጣ ነበር።

በዚሁ ጊዜ በአደራሹ ልስን ግንብ ላይ የምትጽፍ ጣት ታየች። ስለዚህች ጣት መታየትና ስለጻፈችው ጽሕፈት በአዳራሹ ውስጥ ይበሉ ይጠጡ ይዘፍኑ በነበሩ ሰዎች ምን ዓይነት ሁኔታዊ አሳብ ወድቆ ይሆን?

እንዲህ ባለ የደስታ ፈንጠዝያ ተጥለቅልቀው ሳለ፣ የዚህች ጣት መታየት ደስታቸውን አደናቅፎ ሐሳባቸውን በሙሉ ለውጦ ወደዚህች ጣትና ድርጊትዋ እንዲሳቡ አድርጎታል። በተለይ አለቅጥ ፈንደቅ ብሎ ፈንጥዞ የነበረ ንጉሥ ብልጣሶር ፊቱ ተለውጦበት አሳቡ አስቸግሮት የወገቡ ጅማቶች ተፈትተው ጉልበቶቹም ተብረከረከውበት ነበር። መኳንንቱም ተደናግጠው ይታዩ ነበር። ዳን. 5፥5፣6።

በባቢሎን ትልቅ ቤተ መንግሥት ጣት ስትጽፍ ታየች ተብሎ ይህን ያህል ሽብር ምንድን ነው? የሚል ሰው አይጠፋም። ነገር ግን ከጣቲቱ መታየትና ከድርጊትዋ በስተኋላ የተደበቀ ኅቡዕ ኃይል መኖሩን እንደ አሻራ ሆና ትጠቁምና ትመራ ስለነበረ «ተርጉሙኝ» እያለች የሰዎቹን አሳብ ሁሉ በግድ ወደራስዋ በመማረክ ላይ ትገኝ እንደነበረች የተገነዘበ ሰው ስለ ጣቲቱ መታየትና ስለ ሰዎች መሸበር እንዲህ አድርጎ በቀላል ግምት አያስብም፣

ጣቲቱ የእጅ ጣት መሆንዋ፣ እጁም የሌላ ሳይሆን የሰው እጅ መሆኑ፣ በግልጽ ታይቶ ነበር። በእጅ ጣት የጻፈ ሰው የጽሑፉ ትርጓሜ ግን ያልታየና የተደበቀ ስዉር ሆኖ ነበር።

እንደዚህ ያለው ትርኢት በስተኋላው የተደበቀውን መርቶ እስካላሳየ ድረስ፣ የእጅን ጣት ትርኢት ብቻ ነጥሎ በመመልከት ሰብአዊ አእምሮ ይወስን ወይም አይወስን እንደሆነ ማንም ሰው በየራሱ መዝኖ የሚፈርደው ነው። በዚሁ ታሪክ ግን በትርኢቱ ብቻ ተወስኖ በዝምታ የቆመ አሳብ እንዳልተገኘ ተገልጾአል።

መኳንንቱን ያሸበረ ንጉሡንም ያስጨነቀ አሳብ የዚህች የሰብአዊ እጅ ጣት ባለቤት ማነው? የማን ጣት ናት? ከማን ዘንድ መጣች? ወይም ተላከች? አወጣጥዋ ከየት ነው? የሚል ጥያቄ በተፈላጊነቱ ልክ ከጽሕፈቲቱ ትርጓሚ ቅድሚያ ያለው ጥያቄ ነበረ። ይህም ምሥጢርን የማወቅ የተቋጠረውን ነገር የመፍታት ሀብት የተሰጠው ነቢዩ ዳንኤል ጽሕፈቲቱን ከመተርጐሙ አስቀድሞ የጣቲቱ አመጣጥና የማን እጅ ጣት እንደሆነች ለንጉሡ ሲነግረው በመገኘቱ ይታወቃል።

«እስትንፋስህንና መንገድህን በእጁ ካደረገ አምላክ ዘንድ ይህች የእጅ ጣት ወጣች።» /ተላከች/ ብሎ ለንጉሡ ለብልጣሶር እስኪገልጽለት ድረስ የብልጣሶርና የተከታዮቹ ጭንቀትና የመሻት ጥያቄ ሊረካ አልቻለም ነበር።

እነሆም ይህች ጣት ብቻዋን ከሥዋሬ ወደመገለጽ፣ ካለመታየት ወደመታየት በገሃድ ወጥታ የንጉሡንና የተከታዮቹን አእምሮ እያጣደፈች በሥዉር ሆኖ የላካትን አምላክ እስከታሳውቅ ድረስ ማጣደፍዋ ለዚህ መሆኑ ታየ።

በሌላ መንገድ ደግሞ ራሱን ሠውሮ ጣቱን የገለጠው የዚህች የእጅ ጣት ባለቤት የንጉሡን እስትንፋስና መንገድ በእጁ ያኖረ አምላክ መሆኑ ከጣቲቱ ጥቆማ የተነሣ በተደረገው ክትትል ተደርሶበት ታወቀ።



በጣቲቱ ጽሕፈት ፊት የተደበቀው ትርጒምም ዳንኤል ሲያብራራው ተገለጠ። የጣት አሻራ መርቶ እግቡ ሲያደርስ እንዲህ አይደለምን? እነሆም የጣት አሻራ እንዲህ አድርጋ እስከ ልኩ ድረስ መርታ አደረሰች። ዳዊትም በሥነ ፍጥረት ምርምር እግዚአብሔር እንደሚታወቅ ሲገልጽ፡- እስመ ንሬኢ ሰማያተ ግብረ አጻብኢከ ወርኀ ወከዋክብተ ዘለሊከ ሣረርከ ሰማዮች የጣቶችህ ሥራ እንደሆኑ አጻብኢከ ወርኀ ወከዋክብተ ዘለሊከ ሣረርከ ሰማዮች የጣቶችህ ሥራ እንደሆኑ
እናያለን። ጨረቃንና ከዋክብትን ያንተ ሥራ እንደሆነ እናያለን። ብሎአል። ም. 8፥3።

ዮሐንስ ቃል በመጀመሪያ ነበረ፣ ብሎ ሲጀምርም የቃል አቋም እየመራ የት እንደሚያደርስ ወይም በዚህ ቃል ላይ የሚደረገው ምርመራ ቃሉ የሚኖር በእግዚአብሔር ዘንድ ስለ መሆኑና ራሱም ቃሉ እግዚአብሔር ስለመሆኑ እየመራ ወደ አካላዊነት ማድረሱን የሚያስገነዝብ አሻራ አድርጎ አቅርቦታል። በመዋቅሩ ጀምሮ ወደ መሠረቱ ማድረሱ ነው።

ወንጌላዊ ዮሐንስ ለወንጌሉ ጥንት /መጀመሪያ/ አድርጎ ካስቀመጠው ንባብ ላይ አንፀባርቆ የሚገኝ የቃል ህሉናዊ አቋም የማናቸውም ጭምት ሰው አሳብ ወይም ዓይነ ልቡና ነቅቶ እንዲያተኵርበትና እንደምን እንዳለም አይቶ እንዲያስተውለው ከሩቅ ቆሞ ወደራሱ የሚጠቅስ የነጸብራቃዊ መብራት ዓላማን የሚመስል ነው። ዕብ. 1፥3።

እንዲህም ከሆነ ወንጌላዊው ወዳቀረበው ወደ ቃል ትርኢታዊ አቋም የተመለከተ ለባዊ ሁሉ ቢያንስ ቢያንስ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ይጠይቅ ዘንድ ሥርዓታዊ የአእምሮ ዘይቤ መሆኑን ያውቃል።

1፥ ቃል ከመቼ ጀምሮ ይኖር ነበር?
2፥ የቃል ህሉና መገኛ ወዴት ነው።
3፥ ቃል ራሱ ማን ነው?
4፥ ቃል ምን አድራጊ ነው?
5፥ ሕይወት በቃል ስትኖር እንዴት ነበረች?

የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ዘንድ መጠባበቅ መጓጓት የተመርሆ ልቡናዊን ውጤት ማግኘት ይሆናል። አሁን መልሱን ለማግኘት እየተከታተልን በጥቅስ የምንመረምረው ስለ አንደኛው ጥያቄ ይሆናል።

<u>ማስገንዘቢያ</u>፡-

ከዚህ የገለጽነውን ትምህርት የቃለ እግዚአብሔር ባሕርያዊ ህልውናን አስቀድመን ብንገልጽ የተገባ መሆኑን በመረዳት ቃለ እግዚአብሔር ከአብ ጋር ያለውን የህልውናን ባሕርያዊ አንድነት በሚያስገነዝብ የእግዚአብሔር የመናገሪያ ቃል ሆኖ ዓለማትን እንደፈጠረ ነበር ስንገልጽ የቆየን። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ይህን መሠረት ሳንለቅ የእግዚአብሔር ቃል ዝርው ቃል ሳይሆን አካላዊ ቃል መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት እየገለጽን ልናስረዳ ነን። ትምህርቱን ቀስ በቀስ አሳድገን ለማሳየት እንሞክራለን።

# ምዕራፍ ፲፯

# ቃል ከመቼ ጀምሮ ይኖር ነበር?

እንግዲህ ወንጌላዊ ዮሐንስ ለወንጌሉ ጥንት «መሠረት» አድርጎ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህም በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም» ብሎ ወደ አቀረበልን ወደ ቃል ህሉና ትርኢት እንመልከት።

ይህንም በምንናገርበት ጊዜ ደስ የሚያሰኘን ነገር ቢኖር፤ ከሁሉ አስቀድሞ የማናቸውም ጭምት ሰው አሳብ ወደ ቃል ህሉና ትርኢት /አቋም/ ነቅቶ ለማየት በተነሣ ጊዜ፤ የቃልን ህሉና /አቋም/ ብቻውን ነጥሎ እንደማናቸውም ነገር በችሎታ ለመመልከት አለመቻሉ ሲሆን፤ ይህ ለሰው ከተጣለበት ከፍተኛ ግምት ጋር የማይለይ የማስተዋል ችሎታው መሆኑን መረዳታችን ነው። ይህን ተስፋ በማድረግ ነው ቀጥሎ ያለውን ሐተታ የምናቀርበው*

አዎን! «ቃል» ሲባል ምን ማለት ነው? ከሚል ጥያቄ አንሥቶ ከመቼ ጀምሮ ይኖር እንደነበረ፤ የህሉናው መገኛ ምን? ወይም ከማን? እንደነበረ፤ ይነስ ይብዛ እንደሰው አባባል በተለመደው ጥያቄ መጠየቅ ሥርዓታዊ የአእምሮ ዘይቤ መሆኑን እናውቃለን።

አሁን «ቃል» ማለት ምን ማለት ስለመሆኑና ህሉናው እንዴት ወይም ከምን ስለመሆኑ አቅርበን ከመናገራችን በፊት፤ ይህ ቃል ከመቼ ጀመሮ ይኖር እንደነበረ ወንጌላዊው ከገለጸው ትምህርታዊ መሥመር ሳንወጣ ብንናገር፤ ለአቀራረባችን ቅደም ተከተል አመች ይሆናል።

## ቃል ከመቼ ጀምሮ ይኖር ነበረ?

ስለዚህ ነገር ወንጌላዊው ዮሐንስ ሲገልጽ «ቃል በመጀመሪያው ወይም አስቀድሞ ይኖር ነበረ» ይላል። ዳሩ ግን ይህ በመጀመሪያ «አስቀድሞ» የተባለ አነጋገር የትኛውን መንገድ ይዞ እንደተነገረ መገለጽ ይኖርበታልና፤ ምን አቅዋም እንዳለው ብቻውን በማተኮር ማየት ግዴታችን ይሆናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ «በመጀመሪያ» እየተባሉ የተጻፉት የጊዜና የውጥነት የህሉና የኑባሬ ትርጉም ያላቸው ቃላት ስለሚገኙ፤ ወንጌላዊው በመጀመሪያው ወይም አስቀድሞ ብሎ ያመጣው፥ በተባሉት መካከል ከየትኛው ይመሳሰል ወይም ይዛመድ እንደሆነ በሰዋስው መጽሔትነት እያስተያየን በማመዛዘን ምርመራችንን እንቀጥላለን።



በሰዋስው ሥርዓት ያለውን የዓረፍተ ነገሩን አቀማመጥ የተመለከትን እንደሆነ «በመጀመሪያው» ተብሎ ከወንጌላዊው የተጻፈ ነገር «ነበረ» ለሚል የግሥ አንቀጽ አጎላማሽ ወይም ተውሳከ ግሥ ሆኖ በማያጠራጥር ጠባይዓዊ አግባብ መነገሩን እናውቃለን። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው የሚል እንዲህ ሆኖ በተነገረበት በዚህ ጊዜ፥ የትኛውን አቋም ይዞ እንደተነገረ ተለይቶ እንዲታወቅ ተገቢና አስፈላጊ ነው።

1፥ የጊዜን አቋም ይዞ /የጊዜ ተውሣከ ግሥ በመሆን/ ጊዜን፤ ዘመንን በማሳየት ወይም ጊዜን ዘመንን እያመለከተ መነገሩ ነውን?

2፥ ሁናቴን /ኋኝነትን/ ወይም ውጥነትን «መወጠንን» እያሳየ የሚያስገነዝበንን ይዞታ እያመለከተ መነገሩ ነውን?

3፥ ህልዎትን «መኖርን» ወይም ኑባሬን ሲያይ ወይም የህልዎትን ኑባሬን አቋም ይዞ የተነገረ ነውን?

በመሠረቱ «በመጀመሪያ» ተብሎ ሲነገር፤ የቃሉ አገባብ ምንም እንኳ በአጐላማሽነት ለግሡ አንቀጽ ተውሣከ ሆኖ መቅረቡ ቢታወቅም ቅሉ፤ በሰዋስው ሥርዓት በእነዚህ ሦስት መንገዶች የሚያሻማ ይዞታ እንዳለው መቼውንም ግልጽ ነው።

ስለዚህ የተገኘው ንባብ ምንን ሊያስገነዝብ እንደተጻፈ አስተውሎ በመመልከት በመጀመሪያው የተባለበትን የአቀራረብ ይዞታን መዝኖ በየትኛው ረድፋዊ የነገር አቅጣጫ ውሎ እንደሚገኝ፤ በጥንቃቄ መርምሮ መፍረድ ቅድሚያ ያለው ተግባር ሆኖ ይገኛል።

ለዚህ ሁሉ ቀና ተመርሆውን ይዘን በመከታተል ቃል ከመቼ ጀምር ይኖር ነበረ? ለሚል ጥያቄ መልስ ያስገኝለታል፤ ወደተባለው «በመጀመሪያው» ሲል ዮሐንስ ወዳቀረበው ተውሣከ ግሥ እንመለስና የትኛውን የዘይቤ ፍቺ እንደሚያንጸባርቅልን በመጓጓት እንጠባበቅ፤

## 1፥ ጊዜን ይሆን?

እንዲህም ከሆነ እላይ በተጠቀሱት ልዩ ልዩ ዘይቤያውያን መንግዶች መሠረት በመጀመሪያው ተብሎ የተነገረው ተውሣከ ግሥ የትኛውን ጊዜ ያመለክት ይሆን? ወይም ራሱ በየትኛው የዘመን ዕርከን የሚገኝ የመጀመሪያነት ይሆን? እንዲሁም ደግሞ መጀመሪያ በመጀመሪያ ተብለው ከተጻፉት ከየትኛው መጀመሪያ... ጋር ይጎዳኝና ይዛመድ ይሆን ብለን ጥያቄያችንን እንቀጥላለን።

### ሀ/ የመጀመሪያ ቀን።

አዎን፥ ቃል ነበረ የተባለበት በመጀመሪያ ምናልባት «ብርሃን ይሁን» ተብሎ ዕለት የተጀመረበት ጊዜን ያመለክት ይሆን? አይመስልም። እንዲያውም አይደለም። ዘፍጥ. 1፥3፤5።

ይሁን ተብሎ የተፈጠረው ብርሃን ከመገኘቱ በፊት ቃል አስቀድሞ የነበረ በመሆኑ፣ እንዲያውም በዚሁ ቃል «ይሁን» ተብሎ ብርሃን እንዲፈጠር መደረጉና ካለመኖር ወደመኖር ተፈጥሮ መምጣቱ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾአልና፣ ቃል የኖረበት መጀመሪያ በዚሁ ብርሃን ይሁን ተብሎ ብርሃን በተፈጠረበት በአንድ ዕለታዊ የጊዜ እርከን /የቀን መጀመሪያ/ እንዳልሆነ በግልጽ ሊታይ ተችሎአል። 2ቆሮ. 4፥6።

ስለዚህ /ብርሃን ይሁን/ ሲል እግዚአብሔር በቃሉ ተናግሮ፣ ብርሃንን እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደመኖር/ ያመጣበት አድራጊና ፈጣሪ ቃሉ ብርሃን ከተፈጠረበት ቀን፥ ከቀን መጀመሪያ ወይም ከመጀመሪያው ቀን በፊት ኖሮአል።

ብርሃን ከተፈጠረበት ከቀን መጀመሪያ ዕለት በፊት ወይም ከዚያ አስቀድሞ የኖረም ከሆነ፣ በዚሁ በተባለው የጊዜ ዕርከን የማይወሰን ሆኖ መገኘቱ፣ ብሩህ በሆነ ገለጻ ታውቆአል።

ይህም ጥያቄ በዚህ ከተዘጋ፣ «በመጀመሪያ» ቃል ነበረ ሲባል ጊዜው መቼ ሊሆን ነው? ወደሚል ጥያቄያችን እንደገና እንመለሳለን።

## ለ/ በመጀመሪያ ሰማይና ምድር ተፈጠሩ።

እስቲ ምናልባት በዚሁ ወደላይ ፈቀቅ ብለን «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ተብሎ በኦሪት ዘፍጥረት መጀመሪያ ምዕራፍ ተጽፎ ወደሚገኝ የጊዜ ዕርከን ላይ ሻገር ብለን እንመርምር።

በኦሪት ዘፍጥረት ላይ «በመጀመሪያ» ተብሎ የተነገረው ነገር፥ ወንጌላዊ ዮሐንስ «በመጀመሪያ» ሲል ከጻፈው ጋር በተውጣጠ ግሥንት አቋሙ ተመኩሳይ /ተመሳሳይ/ ሆኖ መቅረቡ ይታመናል። ይህም በመጀመሪያ የሚል ይሁን እንጂ፣ ወንጌላዊው በመጀመሪያ ቃል ነበረ ብሎ ተናግሮአል። ታዲያ በምሥጢርም በኦሪት ዘፍጥረት «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ተብሎ ከተጻፈው ጋር ተመኩሳይ ወይም ተመሳሳይ እንደሆነ አስቦ መናገሩ ይሆን? የለም! አይደለም።

ወንጌላዊው ዮሐንስ ይህን በሚያስጽፈው በእግዚአብሔር መንፈስ ተቃኝቶ እንጂ፣ ሥጋዊና ውድቅ በሆነ ሰብአዊ አእምሮ እየተመራ የጻፈው አልነበረምና፣ እንደዚህ ያለው ዘረክራካነት በእርሱ ጽሑፍ ሊታይ አይችልም። አልተቻለምም። ነገር ግን በእርሱ አድሮ የተናገረበት የርትዕ መንፈስ ቀጥ አድርጎ ከትልሙ እንዳይወጣ ጠብቆ ሲመራውና ሲያጽፈው መገኘቱን እናያለን። 1ቆሮ 2፥12፥14።

ይኸውም፦ «ቃል በመጀመሪያ ነበረ» ብቻ በማለት ነገሩን ወዝፎ አልተወዉም። እልፍ ብሎ በማቃናት ሁሉ በእርሱ /በቃል/ ሆነ ያለ እርሱ ግን ከሆነው ሁሉ ምንም የሆነ የለም ብሎ መናገሩ የሚታወስ ነው። ቍ. 3።



እንደዚህ በማለቱ ሰማይና ምድርን የሚያህሉ ግዙፋን ፍጡራን ይቅሩ በመጀመሪያ በነበረው ቃል ማንኛውም ሁሉ እንደሆነ ያለ እርሱ የሆነው ሁሉ ምንም የሆነ ነገር እንደሌለ፣ ለባዊ አእምሮ አለኝ ለሚል ሰው በማነህ ማነህ እንዳይደናቀፍ ጥርት አድርጎ በማስረዳት ቀናውን ትምህርት ሲያስጨብጠው እናገኘዋለን።

አዎን፣ መቼም «ምንም ወይም ምንት» የምትባል ነገር እንኳ ከኢምንትነት ወደምንትነት፥ ካለመታየት ወደመታየት ልትበቃ የቻለችው በዚሁ በልዑል እግዚአብሔር ቃል ከሆነ ዘንድ፥ በሰማይና በምድር በመጀመሪያው በነበረ ቃል የተፈጠሩ መሆኑን፥ ገለጻው ያለማወላወል ያጠቃልላልና ነው።

ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመሪያው ቃል ነበረ ማለቱና ከዚሁም በማያያዝ «ሁሉ በእርሱ /በቃል/ ሆነ ከሆነውም አንዳች እንኳን ያለ እርሱ /ያለ ቃል/ አልሆነም።» ማለቱን አንብቦ ወይም ሰምቶ ሲያበቃ፣ በመጀመሪያ የተፈጠሩ ሰማይና ምድር በእርሱ በቃል ከመፈጠር ያመለጡና እውጭ የቀሩ የሚመስለው ይኖር ይሆን?

«በመጀመሪያው በነበረ ቃል ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ /ያለ ቃል/ አልሆነም።» ብሎ ዮሐንስ በተናገረ ጊዜ ምን ሊል አስቦ ነው? ምንስ ማለቱ ነው? ብሎ መጠየቅ መቼም ለመጽሐፍ መርማሪ አስፈላጊው ነው።

ባጭሩ ዮሐንስ ከኢምንትነት ወደምንትነት ካለመኖር ወደመኖር ካለመሆን ወደመሆን ካለመታየት ወደመታየት የመጣ፥ ማናቸውም ዘመደ ፍጥረት ሁሉ፣ በመጀመሪያው በነበረ ቃል ከኢምንትነት ወደምንትነት ካለመኖር ወደመኖር ካለመሆን ወደመሆን ካለመታየት ወደመታየት ካለመገኘት ወደተፈጥሮ አቋም እንደመጣ እያስገነዘበ መናገሩ መሆኑን፥ በደኅና አእምሮ ለሚኖር ሰው ቀጥታ ይገባዋል። ዕብ. 11፥3። ክህ. 9፥6።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን የሚቀበል ፍትሕንና ርትዕን በማስተዋል የሚከተል ሰው የማናቸውም ፍጥረታት ውጥን፥ ወይም መጀመሪያ የሆኑትን ሰማይንና ምድርን ከዘመደ ፍጥረት ሁሉ ነጥሎ ለብቻቸው ይመለከታቸዋል ተብሎ አይታሰብም፣ ይኸውም በአንጻሩ ወንጌላዊው ጥርት አድርጎ ባቀረበው የኃይለ ምሥጢር ማስረጃ መሠረት በመጀመሪያው በነበረ ቃል ሁሉ በእርሱ በሆነ ጊዜ፣ ሰማይና ምድርም በዚሁ ጥንታዊ የተፈጥሮ ክዋኔ ተጠቃልለው መገኘታቸውን ሕሊናን በሚያነጻ አኳኋን ለመረዳት እንደሚያስችል ይገነዘባልና ነው።

እነሆም አሁን ሁሉ በእርሱ በሆነና ያለ እርሱ ግን አንዳች ነገር ስንኳ ሊሆን በማይችል በመጀመሪያው በነበረ ቃል ሰማይና ምድር ከእነዚህ ጋር ተጠቃለው እንዲያውም ፍጥረታት ሁሉ ለማናቸውም ሠርዌ ፍጥረታት የመጀመሪያ /አንጋፋ/ ሆነው መፈጠራቸው ታወቀ።

ታዲያ ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ ሁሉ በእርሱ /በቃል/ ሆነ ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፤ ብሎ የተናገረው፥ «እግዚአብሔር ብርሃን

ይሁን» ካለበት ጊዜ ጀምሮ ሌሎችን የስድስት ቀን ፍጥረታት በቃሉ የፈጠረ ሲሆን፣ ሰማይንና ምድርን ውኃንና ጥልቅን ጨለማን ግን በአርምሞ «በዝምታ» ያለ ቃል ስለፈጠረ ቃል በሰማይና ምድር አፈጣጠር ቦታ የለውም ሲሉ፣ በተነሡት ወገኖች ሕሊናዊ መስሚያ ላይ፥ እንዲህ አድርጎ ድምፀ ነጐድጓዱን ሲያስተጋባባቸው ምን ይሉ ይሆን?

ከላይ እንደተገለጸ ወንጌላዊ ዮሐንስ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ» ሲል ከተናገረው ጋር አከታትሎ በማያያዝ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ብሎ የገለጸው በመጀመሪያ የተፈጠሩትን ሰማይንና ምድርን ያጠቃልላል። ብለን ስንናገር ርትዕ በተሞላ በተመርሆ ልቡናዊ የተነደፈውን ሥርዓተ ኀሠሣ /ምርምር/ ተከትለን መሆኑን እስከዚህ ባለው ገልጸናል።

ይህ በዚህ እንዳለ በደረቅ ንባብ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸ ስለዚህ ነገር የሚያብራራ የኅብረተ ቃላት ማስረጃ ስላለ፣ የማናቸውም ልብ ይነጻ ዘንድ እንደሚከተለው አቅርበናል።

እነሆም ዳዊት በመዝሙሩ «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ ሠራዊታቸውም በአፉ እስትንፋስ» ብሎአል። መዝ. 32፥33፣6። ደግሞ «ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው እርሱ ተናግሮአልና ሆኑ፣ እርሱ አዘዘ ጸኑም» ይላል። መዝ. 32፥33 8፣9።

ጴጥሮስ «ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድርም በእግዚአብሔር ቃል በውኃ እንደጸኑ ተናግሮአል።» 2ጴጥ. 3፥5። ሐዋርያው ጳውሎስ «ዓለማትን በእርሱ በልጁ በፈጠረበት... ብሎአል። ዳግም ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን ብሎአል።» ዕብ. 1፥2። ም. 11፥3።

ስለዚህ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ሲፈጥር በመጀሪያው በነበረ ቃሉ የፈጠረ መሆኑን በግልጽ አስታውቆአል። ቈላስ. 1፥15፣17።

እነሆም በዚህ ሁሉ ማስረጃ ሰማይና ምድር በመጀመሪያው በነበረ ቃል እንደተፈጠሩ መረጋገጡን አይተናል። ይህን ካየን የሰማይና የምድር መፈጠር የእግዚአብሔር የሥራ መጀመሪያ በሆነበት ጊዜ፣ እነዚህ የተጠሩት ሰማይና ምድር ያለ እርሱ ምንም በማይሆን፣ የሆነው ሁሉ በእርሱ በሚሆን በመጀመሪያው ቃል ከኢምንት ወደምንት ካለመኖር ወደመኖር የመጡ ሆነው ተገኝተዋልና ካለመኖር ወደመኖር ያመጣቸው በመጀመሪያው የነበረ ቃል ከዚያ በፊትም ህልው ሆኖ መኖሩን በሚያስገነዝብ አሳብ ላይ እናተኵራለን።



# ምዕራፍ ፲፰

## ቃል ከሁሉ በፊት ነበረ።

አሁን ወንጌላዊው «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ የሆነ የለም» ብሎ ከጻፈውና፤ በኦሪት ዘፍጥረት «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ተብሎ ከተጻፈው ላይ ሳንወጣ ከእነዚህ ተጨምቀው የተገኙና የምናጠናቅቃቸው ፍሬ ነገሮች እንዳሉ ይሰማናል።

ስለዚህ በተወሱት አሳቦች ላይ አእምሮአችንን አቅንተን በሐተታ መልክ ብንነጋገርበት መልካም ይመስለናል። መቼም እየተከታተልነው በመጣን ሐተታ በመጀመሪያው የነበረ ቃል ሰማይንና ምድርን እንደፈጠረ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመስክሮ ተረጋግጦአል፣ የዚህ ሁኔታ መረጋገጥ ግን ራሱ ምን ማለት ነው? ውጤቱስ ምንድን ነው? ብለን በርትዕ መንፈስ እንድናስብና እንድንመረምር ወደምንገደድበት ደረጃ ላይ ሲያደርሰን እናያለን።

አዎን! የሁኔታው መረጋገጥ ሲባል ምን ማለት ነው? ከሚል ጥያቄ ለሚገኝ መልስ አስቀድሞ የሚያዘው ጭብጥ የሰማይና የምድር መፈጠር የእግዚአበሔር የሥራ መጀመሪያ በሆነበት ጊዜ፤ እነዚህ የተፈጠሩት ሰማይና ምድር ሁሉ በእርሱ በሚሆን ያለ እርሱ ግን ምንም ነገር በማይሆን በመጀመሪያው ቃል፥ ከኢምንት ወደምንት፤ ካለመኖር ወደመኖር፤ የመጡ ሆነው መገኘታቸው ነው።

ይህን ጭብጥ ከያዝን፣ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣቸው በመጀመሪያ የነበረ ቃል ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት አስቀድሞ ህልው ሆኖ እንደኖረ የማያወላውል ማስረጃ በመሆን በርትዕ መንፈስ ሊታየን መቻሉ ነው።

አዎን! ሰማይና ምድር በመጀመሪያው በነበረ ቃል እንደተፈጠሩ ሲታወቅ ወዲሁም ደግሞ ሰማይና ምድር ለፍጥረታት መጀመሪያ ሆነው በመጀመሪያው በነበረ ቃል ሲፈጠሩ የመገኘታቸው ሁናቴ ሲገለጽ ምንን ያሳያል? በመጀመሪያው የነበረና ሰማይና ምድር የተፈጠሩበት የእግዚአብሔር ቃል ሰማይና ምድር ከመፍጠሩ አስቀድሞ ህልው ሆኖ የነበረ ለመሆኑ ማስረጃነቱ እሙንና ግልጽ አይደለምን?

እነሆም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ከሚል ጥቅስ ላይ የተነገረው «በመጀመሪያ» የሚል የተውጣጠ ግሡ ኃይለ ቃል እንደዚህ ያለውን ማስረጃ ሁሉ አበረከተ።

እንዲህም ሆኖ ገለጻው በጥራት ከታየ፣ በክፍለ ትምህርቱ ተመርምረውና ተጨምቀው ከተገኙ ዋና ዋና ተጨባጭ አሳቦች የሚከተሉትን ተመልክተን ብናልፍ እየቀደመ ግልጽ ይሆንልናል።

1ኛ፥ ሰማይና ምድር ሲፈጠሩ ቃል አልነበረም ለማለት የማይገባና የማይቻል መሆኑ ነው። አዎን ሰማይና ምድር ሲፈጠሩ ቃል አልነበረም እንዳይባል፣ በመጀመሪያ የተፈጠሩ ሰማይና ምድር በእርሱ ይኸውም በመጀመሪያው በነበረ ቃል የተፈጠሩ ለመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተ ቃላት ተገልጠ ተረጋግጦአልና ነው። መዝ. 32/33፥6። 8፤9። 2ጴጥ. 3፥5። ዕብ. 11፥3።

2ኛ፥ በመጀመሪያው ቃል ነበረ ተብሎ የተነገረ በመጀመሪያ ሰማይና ምድር ሲፈጠሩ ቃል በውጥንት ወይም በአኳኋንነት ረገድ የመጀመሪያ ፍጥረት ስለሆነ ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ ተገኝቶአል። ምክንያቱም ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር የሥራው መጀመሪያ «ለፈጠረው ሌላ ፍጥረት ሁሉ አንጋፋ» ሆነው ስለተፈጠሩ በውጥንት ረገድ የመጀመሪያውን ድርሻ ወይም የመፈጠር ፈለግ የተወጥኖን ቅድሚያ እነርሱ ሰማይና ምድር ይዘውት ለመገኘታቸው ቅዱሳት መጻሕፍት «ብሉይና ሐዲስ» በኅብረት መስክረዋልና ነው። መዝ. 19፥1፤3።

3ኛ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የመፈጠር ተወጥኖ ወይም ምሥረታ የሰማይና የምድር መጀመሪያ ድርሻ ሆኖ ከተገኘ፣ እንግዲያ ለተወጥኖ ተወጥኖ አለበትን? በእውነቱ የለበትምና፣ ሰማይና ምድር በመፈጠር ረገድ የተወጠኑ ጊዜ፣ የመፈጠር ተወጥኖን የሚያሟሽላቸው አንድም ፍጡር ግቡር ሳይኖር፣ የመፈጠር ቀዳሚነት ለእነርሱ ረግቶላቸዋል። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረትና በተመርሆ ልቡናዊም ፍትሕ ለቅን ሕሊና ተገልጾ የሚታይ ነው። ዳዊትም «አንተ አቅደምከ ሣርርታ ለምድር ወግብረ እደዊከ እማንቱ ሰማያት አንተ በመጀመሪያ ምድርን መሠረትህ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው» ማለቱ ይታወሳል። መዝ. 101/102/፥25፤27። ዕብ. 1፥10።

4ኛ፥ ቃል በአኳኋንነት ረገድ «በኑባሬ ቅመም» ከሰማይና ምድር ጋር የተፈጠረ ነው ሊባል እንደማይቻል ግልጽ ሆኖአል። ምክንያቱም ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ሲፈጠር፣ የገዛ ራሱም ፈጣሪ ሆኖ ራሱን ከፍጥረቱ ሳያቀላቅል በቀዋሚነት ከፍጥረቱ ሁሉ በፊት አስቀድሞ መኖሩ፥ ተብራርቶ ታውቆአልና ነው። እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በፊት ነው፣ የሚለውንም ደኅና አድርጎ ማየት ነው። ቈላ. 1፥16፤17።

5ኛ፥ የእግዚአብሔር ቃል በመጀመሪያው የነበረና ከፍጥረትም ሁሉ በፊት የነበረ ሆኖ ግን፥ ልዩ ፍጡር ነው እንዳይባል ደግሞ፣ ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ «የሥራው መጀመሪያ» ወይም ውጥን ሆነው መፈጠራቸው ስለተረጋገጠ ከእነርሱ በፊት ህልው ሆኖ የነበረ ቃል ፍጡር ወይም ግቡር ውጥን ተኳኝ «የቅመም አባሪ» ከመሆን፣ ንጹሕና ነፃ ልዩ መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውሱን በሆነ ገደብ ተመስክሮ አክትሞአል። ዘፍጥ. 1፥1።



6ኛ፥ ቃል ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት ቢኖርም፣ የተፈጠረ ሆኖ፥ ወይም ተፈጥሮ ነው የኖረ እንዳይባልም በመጀመሪያው ቃል ነበረ ተባለ እንጂ ተፈጠረ የሚል አብነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል እንደማይገኝ ታውቆአል። ዮሐ. 1፥1። 1ዮሐ. 1፥2።

7ኛ፥ ሰማይና ምድር በተፈጠሩ ጊዜ የእግዚአብሔር የፍጥረቱ መጀመሪያ ሆነው እንደተፈጠሩ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተረጋግጦ ስለተገለጸ፣ ይኸው እግዚአብሔር ሥራውን የጀመረበት ጊዜንና ድርጊትን ወስኖ ያሳያልና፣ ከተጠቀሱት ፍጥረታት በፊት ምንም ነገር ስላልተፈጠረ ወንጌላዊው ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ብሎ የጠቀሰው በመጀመሪያ፣ ቃልን ከጊዜያት በአንዱ ጊዜ ነበረ ለማለት አስቦ እንደተናገረ፣ ጨርሶ አያመለክትም። ከታሰበበትስ ከዚሁ በጣም የራቀ ሌላ ገለጻ እንዳለው ነው የሚያሳይ።

8ኛ፥ ይህ በኦሪት ዘፍጥረት በመጀመሪያ የተነገረው አጕላማሽ በዮሐንስ ወንጌል በመጀመሪያ ቃል ነበረ ተብሎ የተነገረውን መጀመሪያነት በጊዜ እርከን ለመወሰንና፣ እሥሩ ውስጥ አውሎ ለማቀፍ ያልቻለ ሲሆን፣ በሌላ ወገን ደግሞ ሰማይና ምድር ለእግዚአብሔር የመጀመሪያ ሥራ መሆናቸውን በማረጋገጥ ሲወስን ይገኛል።

9ኛ፥ በውሳኔው ትይዩ ወይም አንጻር ሰማይና ምድር ከተፈጠሩበት ጊዜ በፊት ሌላ የተፈጠረና ፍጡር ግቡር ኳኝ ውጥን የሚባል ምንም ነገር አለመኖሩ ተረጋግጦ ስለተገኘ፣ በዚሁ ማከተሚያ መወሰኑ ነው።

ከዚህ በላይ በዝርዝር በተገለጹት ፍሬ ሐሳቦች ዘንድ፥ የሚከተሉትን ሦስት ማስረጃዎች ከነማብራሪያዎቻቸው በማቅረብ ሐተታውን እንቀጥላለን።

1፥ «በመጀመሪያ፥ በመጀመሪያው» ተብለው በኦሪትና በወንጌል በተነገሩ ተውሣከተ ግሦች መካከል ስላለው ግንኙነትና ልዩነት።

2፥ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ በመጀመሪያ ተብሎ የተነገረው ተውሣከ ግሥ በአንቀጽ አጕላማሽነቱ ያበረከተው ሙያዊ ድርሻ።

3፥ ፈጠረ እንዲሁም «ነበረ» በሚሉ ግሦች መካከል ስለሚያንጸባርቀው ወሳኝ ዘይቤያዊ ፍቺና ትርጕም።

እንግዲህ እዚህ በተጠቀሱት ዝርዝር ነገሮች ያለው ሐተታ በቅን ሕሊና ሆነን ዓይነ ልቡናችንን አንቅተን እንከታተላለን።

# ምዕራፍ ፲፱

## በመጀመሪያና በመጀመሪያው ተብለው በኦሪት ዘፍጥረትና በዮሐንስ ወንጌል በተነገሩት ሁለት ተውሣከ ግሦች መካከል ስላለው ግንኙነትና ልዩነት።

እንደምሰሶዎች አድርገን ስንነጋገርባቸው በቆየን ወንጌላዊው የቃል ህልው ሆኖ መኖሩን ለመግለጽ የአንቀጽ አጐላማሽ አድርጎ በመጀመሪያው ሲል ባቀረበው ተውሣከ ግሥና በኦሪት ዘፍጥረት ሰማይና ምድር የተፈጠሩበትን ጊዜ ወስኖ በአጐላማሽነት ለማስገንዘብ መጀመሪያና በመጀመሪያው ተብለው በተነገሩ ተውሣከ ግሥ መካከል ያለውን ግንኙነትና ልዩነት እንደሚከተለው እያነጻጸርን እናያለን።

ሀ/ ዮሐንስ በመጀመሪያው ብሎ ስለሚናገረውና በኦሪት ዘፍጥረትም በመጀመሪያ ስለተባለው ግንኙነትና ተመሳሳይነት የተውሣከ ግሥን አቋም በመያዝና በቃላት አቀማመጥ በሚሆን ተመኩሳይነት «ሞክሽነት» በመታየታቸው ብቻ መሆኑን ገልጸን እናቆማለን እንገታለን።

ለ/ በኦሪት ዘፍጥረት በመጀመሪያ ተብሎ የተጻፈውን፣ ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመሪያው ብሎ ከጻፈው ያለውን ልዩነት በሚከተለው ይታያል።

1፥ በኦሪት ዘፍጥረት የተነገረው የሰማይና የምድር መፈጠርን የሚገልጽ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር የሥራ መጀመሪያ መሆኑን ወስኖ ሲያሳይ ተነግሮአል።

2፥ በመጀመሪያው ቃል ነበረ ተብሎ በዮሐንስ የተነገረው መጀመሪያ የሚል ቃል ግን፣ እግዚአብሔርን ሰማይና ምድር የሥራው መጀመሪያ እንደነበሩ በማሳየት፥ ካስገነዘበበት ከጊዜ እርከን ወዲያ የሚያሳይ ሆኖአል።

3፥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ከሚል ዐረፍተ ነገር የተነገረ በመጀመሪያ አንድ ድርጊታዊ የሥራ ውጥን የተፈጸመበትን የጊዜ እርከን ወስኖ አሳይቶአል።

4፥ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ሲል ዮሐንስ የጻፈው በመጀመሪያው ግን የቃል ህሉናን እንጂ፣ ድርጊታዊ «የሥራ» ውጥን የተፈጸመበትን የጊዜ እርከን ወስኖ አላሳየም።

እንግዲህ በኦሪት የተነገረው በመጀመሪያ በወንጌል የተነገረው በመጀመሪያ የተለያየ አቋምና ደረጃ፥ አልተጎዳኙም። የጊዜ እርከን እንዳሳዩ፣ ከላይ



በተገለጸው ሚዛናዊ አኳኋን፥ በሚገባ ግልጽ ሆኖ ታውቆ ተጠንቶቀ። አጐላማሽ ሆነው ለቆሙላቸው የግሥ አንቀጾችም አቋማቸውን አቀላቅሉ ከሚያሳይ ተምሳሌታዊ ቁርበተ ነክ አነጋገር ስሜት፥ ተጠብቀው በየዘይቤያቸው ምሥጢራዊ መልስ ተገኝተው እንዲነገሩ አስችለዋቸዋል።

እንኪያስ ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ብሎ ሲያቀርብ በመጀመሪያ ማለቱ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ በመጀሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ተብሎ ከተነገረው በመጀመሪያ ከሚል ቃል ሊያዛምድና ሊያመሳስል ከጅሎ እንዳልተነገገ ወይም እንዳላሰበ ተመዛዝና ጥርት ብሎ ይታያልና የልቡናዊን ተመርሆ ልጓም እንዳንለቅ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው።

# ምዕራፍ ፭

## በኦሪት ዘፍጥረት ያለው «በመጀመሪያ» ተብሎ የተነገረው ተውሳከ ግሥ በአጐላማሽነቱ ያበረከተው ሙያዊ ድርሻ።

ስለ ቃላት የሙያ ችሎታ ከተናገርን ዘንድ ለምሳሌ ተውሣከ ግሥ የግሥ አንቀጽን ሊያጐምስ ስለአንቀጹ በሚቆምለት ጊዜ፣ የግሥ አንቀጹ የያዘውን ፍሬ ነገርና ኃይለ ቃል የሚያቀርበውን የተለያየ መተርጐማዊ ኀሳብ እየመጠነ በሚያሳይበት ጊዜ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚሠራው የቁም ነገር ሙያውን ያስገምታል።

ይህንንም ለማረጋገጥ በኦሪት ዘፍጥረት በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ተብሎ ከተጻፈው ዓረፍተ ነገር በተለይ «በመጀመሪያ» የሚለውን ብቻ ብንወስድና በሥርዓተ ኀሠሣም መሠረት ቁጥራቱን ፈትተን ብንተነትነው፥ አቅርቦልን አበርክቶልን ከሚገኝ አስፈላጊ ትምህርት ጋር የአቋሙን ትርጐምና ዘይቤ በምሥጢራዊ መልኩና በግዕዝ ጠባዩ ሲገልጽልን እናገኛለን።

1ኛ፥ በመጀመሪያ ሲባል፣ «ፈጠረ» ለሚል የግሥ አንቀጽ አጐላማሽ ተውሣከ ግሥ ሆኖ በሰዋስው ትንተና ደረጃ ቀርቦአል።

2ኛ፥ በመጀመሪያ ሲባል፣ ፈጠረ ለሚል የግሥ አንቀጽ አጐላማሽ በመሆኑ ሰማይና ምድር የተፈጠሩበትን የጊዜ እርከን ወስኖ አሳይቶአል።

3ኛ፥ በመጀመሪያ ሲባል፣ ሰማይና ምድር መጀመሪያ ሆነው መፈጠራቸውን አረጋግጦ አንቀጹን ሲያጐላምስ ታይቶአል።

4ኛ፥ «በመጀመሪያ» ሲባል፡- ሰማይና ምድር በመጀመሪያ በመፈጠራቸው ከእነርሱ በኋላ ለተፈጠሩት ፍጡራን መጀመሪያ አንጋፋ «ለሥራው ጅምር ወይም ውጥን» መሆናቸውን ወስኖ ለማሳየት አስችሎአል።

5ኛ፥ «በመጀመሪያ» ሲባል እግዚብሔር ፍጥረትን መፍጠር የጀመረ ወይም የወጠነ ሰማይንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ መሆኑን ወስኖ አሳይቶአል።

6ኛ፥ «በመጀመሪያ» ሲባል ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ሥራው ወይም የሥራው መጀመሪያ እንደሆኑ በማያሻማ ገለጻ ወስኖ አስገንዝቦአል።



7ኛ፥ «በመጀመሪያ» ሲባል፡- ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው አስቀድሞ የተፈጠረ ፍጡር፥ የተሠራ ሥራ፥ የተወጠነ ውጥን፥ ወይም ጅምር ነገር እንዳልነበረ በማያወላውል ገለጻ ወስኖ በማሳየት ለግሥ አንቀጹ አጐላማሽ በሆነበት አቋሙ ከተራ ወይም ድንበር ሆኖ መቆሙን አስገንዝቦአል።

እነሆም በኦሪት ዘፍጥ. 1፥1 ላይ በተነገረ ዓረፍተ ነገር በመጀመሪያ በሚል ተውሣከ ግሥ ዓረፍተ ነገር ፈጠረ ተብሎ ለተነገረ የግሥ አንቀጹ አጐላማሽ ለመሆን በቆመበት አገባብ እላይ በዝርዝር በተገለጹት ኃይለ ቃላት አንጻባርቆ ጠባይዓዊ ግብሩን እንዲያሳይ አስችሎታል። ይኸውም በሚከተሉት ጥያቄዎች ትምህርቱ ይብራራል።

በዚህ ዐረፍተ ነገር እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ብቻ ተብሎ ቢጻፍና በመጀመሪያ የሚል አጐላማሽ ቃል ከዚህ ጋር ባይነገር ወይም ባይጻፍ ኖሮ፣ እንዴት ይሆን ነበር? በውኑ «ፈጠረ» ተብሎ የተነገረ የግሥ አንቀጽ ብቻውን ሰማይና ምድር ከፍጡራን ሁሉ ቀዳማውያን «ግንባር ቀደም» ወይም አንጋፋና የመጀመሪያው ውጥን ሆነው እንደተፈጠሩ ለማሳየት ያበቃ ነበርን? ወይስ እግዚአብሔር መፍጠር የጀመረ የሥራው ውጥን የሆኑትን ሰማይንና ምድርን እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ «ካለመኖር ወደመኖር» በማምጣቱ በመፍጠሩ መሆኑን ለማሳወቅ ባስቻለ ነበርን? ለዚሁም ጥያቄ መልስ በእውነቱ አያስችልም ነበር የሚል ነው።

መቼም ፈጠረ በሚል በግሥ አንቀጽ ላይ በመጀመሪያ የሚል አጐላማሽ ሳይታከልበት ቢነገር ኖሮ ልዑል እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን መፍጠሩን ብቻ ለማስገንዘብ ያስችል እንደነበረ፣ የተገለጸ ነገር ነው። ነገር ግን «ፈጠረ» የሚል የግሥ አንቀጽ በመጀመሪያ ተብሎ የተነገረ ተውሣከ ግሥን ሳይጨምር ብቻውን እንደሆነ እላይ በዝርዝር እንደተገለጸው በጊዜ እርከን ሲፈጸም የታየውን ድርጊት ሁሉ እንዲሁ በጐልህ ተንትኖ ለማስገንዘብ ጊዜውንም ወስኖ ለማሳየት ብቁዕ ሆኖ ባልተገኘም ነበር።

ይህ ብቻ አይደለም፡- «በመጀመሪያ» ተብሎ የተነገረው አጐላማሽ «ተውሣከ ግሥ» ፈጠረ በሚል በግሥ አንቀጽ ላይ ሳይታከል «ሳይጨመር» ቀርቶ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ብቻ ተብሎ ቢነገርና ቢጻፍ ኖሮ፣ ሰማይና ምድር የፍጥረት ወይም የሥራው መጀመሪያ እንደሆኑ፣ እግዚአብሔርም ሰማይንና ምድርን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ሌላን ፍጡር እንዳልፈጠረ፣ የጊዜን ዳርቻና ድካ በማድረግ ወስኖ ማረጋገጡ በእውነት ግልጽ ሆኖ ባልታየና ፈጽሞም ባልታወቀም ነበር።

ምንጊዜም ምስጋና የሚገባው ልዑል እግዚአብሔር ግን የገዛ ራሱንና ግብሩን ለባውያን አድርጎ ለፈጠራቸው ለሰው ልጆች ሲገልጽ፣ የሃይማኖታቸው መሠረት ይሆን ዘንድ ከእስትንፋሱ ባስጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ አንዲት ቃል እንዳትጐድልና፣ ለደካሞች መሰናከል እንዳትሆን፣ በሰፊው ቸርነቱ

ይጠነቀቃልና፣ ከዚሁ ጥቅሳችንም «በመጀመሪያ» የምትል ቃል ወድቃ እንድትቀር አላደረገም። ሉቃ. 16፥17። 2ጴጥ. 1፥20፤21።

መቼም ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር ፍጥረቱ «የሥራው መጀመሪያ» መሆናቸው፣ ይልቁንም ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው አስቀድሞ ምንም ዓይነት ሌላ ፍጡር እንዳልተፈጠረ፣ ወይም እግዚአብሔር የመጀመሪያ ፍጥረቱ ከሆኑት ከሰማይና ከምድር በፊት ምንም ነገር እንዳልፈጠረ የማያሳስት የጊዜና የድርጊት የድንበር መለያ አድርጎ በማረጋገጥ መወሰኑን እናያለን።፡

ይህም በመጀመሪያ የሚል ተውሣከ ግሥ «ፈጠረ» ለሚል የግሥ አንቀጽ አጐላማሽ ሆኖ የጊዜና የድርጊት የድንበር መለያ ሆኖ በመወሰን እንዲነገርና፥ ተጽፎ እንዲገኝ ማድረጉ ነው። ከዚህም ጋር ሰማይና ምድር በመጀመሪያ በመፈጠራቸው፥ ከእነርሱ በኋላ ለተፈጠሩት ፍጡራን መጀመሪያ አንጋፋ የሥራ ውጥን መሆናቸውን ወስኖ ባሳየበት አንጻር፥ «ትይዩ» ይህ በመጀመሪያ የሚል ቃል ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው አስቀድሞ የተወሰነ ውጥን ነገር፥ የተፈጠረና ፍጡር ግቡር እንዳልነበረ ወስኖ መግለጹ መቼውንም የሚሠወር አይደለም። ዕብ. 11፥3።

ዳግም ይህ «በመጀመሪያ» ተብሎ የተነገረና «ፈጠረ» የሚል የግሥ አንቀጽ አጐላማሽ «ተውሣከ ግሥ» የሆነ ቃል የድርጊቱ «የሥራ ውጥን» አፈጻጸምን በሚያስገነዝብ ሁኔታ፥ ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር የሥራው «የፍጥረቱ» መጀመሪያ መሆናቸውንና የጊዜውን ዕርከን በሚያስረዳ ሁኔታም እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን መፍጠር የጀመረበትን ጊዜ ወስኖ በአዎንታ አስገንዝቦአል።

እንደማስገንዘቡም ሁሉ፥ በአዎንታው ትይዩ «አንጻር» በተመጣጣኝነት ደረጃ ቆሞ በሥዋሬ የሚገኝ የአሉታ ኃይለ ቃል እንደመኖሩ ሁሉ፥ ሰማይና ምድር በእግዚአብሔር ከመፈጠራቸው አስቀድሞ፥ አንዳች ፍጡር ነገር እንዳልነበረና፣ እግዚአብሔርም ሰማይንና ምድርን ከፈጠረበት ጊዜ በፊት ምንም ፍጡር የሚሆን ነገር እንዳልፈጠረ፥ እንዳልሠራ ወስኖ ማስታወቁን በአንጻር አወራረድን ሥርዓት የጠነቀቀ መርማሪ ሁሉ የሚደርስበት ነው።



## ምዕራፍ ፲፩

# የአንጻር አወራረድ ሥርዓት ዘይቤ።

ለምሳሌ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገልጸው በሰው ልጆች ታሪክ በመጀመሪያ ወንድሙን የገደለ ማነው? ተብሎ ሲጠየቅ፣ «በመጀመሪያ ወንድሙን አቤልን የገደለ ቃየል ነው» የሚል እርግጠኛ መልስ ይቀርባል። ይህ በአዎንታ የተነገረ ሲሆን፣ በአዎንታው ትይዩ ተመጣጥኖ በሚገኝ የአሉታ ኃይለ ቃል ወንድሙን በመግደል የመጀመሪያ ሰው ሆኖ ከተገኘው ከቃየል በፊት ማንም ወንድሙን የገደለ ሰው እንዳልነበረ ይረጋገጣል። ቧአንጻር አወራረድ ሥርዓት ይህ ዓይነቱ ነው።

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ሲባልም፣ እግዚአብሔር ሰማይና ምድር ከመፍጠሩ በፊት ምንም ነገር ያልፈጠረ መሆኑ በዚህ ለመረዳት ይቻላል።

ስለዚህ በመጀመሪያው የነበረና ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ቃል በመጀመሪያ ከተፈጠሩት ሰማይና ምድር አስቀድሞ ህልው ሆኖ እንደነበረ በማያጠራጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ መታወቁን ይገነዘቧል። ወዲያውም ደግሞ አእምሮን በማምጠቅ የእግዚአብሔርን ቃል የመጀመሪያ ፍጥረት ከሆኑት ከሰማይና ምድር አስቀድሞ ህልው ሆኖ ከመኖሩም በላይ፥ በመጀመሪያ ከተፈጠሩት ሰማይና ምድር በፊት የተፈጠረ ምንም ነገር ስላልነበረ፣ የእግዚአብሔር ቃልም ያልተፈጠረ ሆኖ በመጀመሪያው እንደነበረ ይረዷል። ቈላስ. 1፥16። መዝ. 118/119/89።

እንግዲህ ያልተፈጠረ ፍጡር ባልነበረ ጊዜም ቃል ያልተፈጠረ ሆኖ ከዘላለም በእግዚአብሔራዊ ህልውና ሲኖር ኖሮአል። ዮሐ. 1፥11። ም. 7፥29።

# ምዕራፍ ፳፪

## ፈጠረና ነበረ ስለተባሉት ቃላት ዘይቤያዊ ፍቺ፥ የፈጠረና የነበረ ዘይቤያዊ ፍቺ።

ስለተውሳከ ግሦች የተነገረው በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ወንጌላዊውና በኦሪት ዘፍጥረት በተነገሩ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ላይ ሁለቱ በመጀመሪያውና በመጀመሪያ ተብለው የተነገሩ ተውሳከ ግሦች ሊያጐላምሱአቸው የቆሙላቸው ሁለት የግሥ አንቀጾች እንዳሉአቸው አስቀድመን ተመልክተናል።

ይሁን እንጂ እስካሁን ስለ አንቀጾች አቋም ስለፍቻቸው ውሳኔ አልተናገርንም። ተውሳከ ግሦች «በመጀመሪያና በመጀመሪያው» ተብለው ከኦሪት ዘፍጥረትና ከወንጌላዊው ሲነገሩ ስለ ትምህርተ መለኮት ያበረከቱት ተግባራዊ ሙያቸውን ተመልክተናል።

አሁን ደግሞ ሁለቱ ካጐላመሱአቸው ከግሥ አንቀጾች የሚገኘውን ትምህርታዊ ገለጻን እንመለከታለን። ሊያጐላምሱአቸው ከቆሙላቸው የግሥ አንቀጾች ውጭ ዝንፍ ብለው እስከማይገኙ ድረስ፥ በአጃቢነት አቅዋም የቀረቡ «በመጀመሪያና በመጀመሪያው» የተባሉ ተውሳከ ግሦች ስለ ትምህርተ መለኮት ገለጻ ይህን ያህል ቁም ነገር ካበረከቱ፣ የዋንኞቹ አንቀጾች ትክክለኛ ትርጓሜና ዘይቤያዊ ፍች በእውነተኛ መልክ ተብራርቶ ሲገለጽና ሲታወቅ የትምህርተ መለኮት ገለጻ የቱን ያህል ደምቆ ያንጸባርቅ!

ስለዚህ የግሥ አንቀጾች ዘይቤያዊ ፍች በእውነተኛ መልኩ ወይም አቋሙ ተብራርቶ እንዲታወቅ አስፈላጊ በመሆኑ፣ «ፈጠረና ነበረ» ወደሚሉ የግሥ አንቀጾች ማተኩር ይኖርብናል።

የእነዚህ የተጠቀሱት የግሥ አንቀጾች ያላቸው ዘይቤያዊ ፍችና ጠባይ በእውነተኛ መልኩና አቋሙ ሲገለጽ፣ ቀጥሎ ባለው አቀራረብ እንመለከታለን።

1ኛ፥ «ፈጠረ» የሚል የግሥ አንቀጽ ዘይቤያዊ ፍች ካለመኖር ወደመኖር አመጣ ማለት ነው ወይም አደረገ ሠራ ተብሎም ይተረጐማል።

በግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ዘፍጥ. 1፥1። የተነገረውን ስንመለከት «በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ» ተብሎ እንደተገለጸ እናገኛለን። ይኸውም «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ተብሎ በአማርኛ ተተርጕሞአል።

«ገብረ» የሚል ግሥ አደረገ ሠራ ማለትን ከማንጸባረቁም በላይ ፈጠረ ማለትንም አስገንዝቦአል። በመሠረቱም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና



ምድርን ካለመኖር ወደመኖር ያመጣበትን፣ የፈጠረበትን፥ ያደረገበትን፥ ወይም የሠራበትን ድርጊት ውጥንትን፥ ተከውኖን «ኋኝነትን» ግብርን ጊዜን ማሳየቱ ው።

2ኛ፥ «ነበረ» የሚል የግሥ አንቀጽ ዘይቤያዊ ፍችና ጠባዩ «ኖረ፥ ነበረ» ወይም እንደኖረ ነበረ ማለት ሆኖ ይገኛል። ዘይቤያዊ ፍቹ እንዲህ እንደመሆኑ፣ የተፈጥሮን የተገብሮን የመሄድን የመምጣትን አቋም ከሚመለከት ነገር ሁሉ ፈጽሞ የራቀና የተለየ ነው።

ወደ መሠረተ ዓላማችን ተመልሰን በመጀመሪያው ቃል ነበረ ተብሎ ተነገረውን ስንመለከት ቃል ከተገብሮ ከተፈጥሮ «ከመፈጠር» ካለመኖር ወደመኖር ከመምጣት፥ ወይም ከተከውኖና ከተወጥኖ ከጊዜያት ዕርከኖች «ከጊዜ እዋዴያት» ወይም ከዐውደ ዘመናት ሁሉ ወዲያ፥ ኖረ። ወይም «እንደኖረ ነበረ» የማለት ዘይቤያዊ ፍች ብቻ፥ ይታይበታል። ኢሳ. 40፥8። ም. 45፥21፣23። ኢሳ. 55፥11።

ስለ ሁለቱም የግሥ አንቀጾችና ስለ ዘይቤያዊ ፍቻቸው ልዩነት አየን። የጠባያቸውን ልዩነት ደግሞ እንመለከታለን።

እነሆም «ፈጠረ» የሚል የግሥ አንቀጽ ጠባዩ የገቢር እንደመሆኑ፥ በቀላሉ አንድ ነገር እግብር ላይ፥ ወይም እሥራ ላይ መዋሉን፥ የሚገልጽ ነው። በዓይነትም ተሻጋሪ በመሆን፥ የአንቀጹ ባለቤት አንድን ነገር ማድረጉን ወይም መሥራቱን ይገልጻል።

ለምሳሌ፣ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» በሚባልበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር አንድን ነገር ማድረጉን ወይም መፈጸሙን አሳይቶአል። ይኸውም እግዚአብሔር በመጀመሪያ ያደረገው ነገር ሰማይንና ምድርን መፍጠሩ እንደሆነ ማወቅ አያዳግትም።

«ነበረ» የሚል የግሥ አንቀጽ ግን፣ የመኖር ጠባይን ብቻ ነው የሚገልጽ፣ በዓይነትም የማይሻገር እንደመሆኑ መጠን፥ የመኖርን ወይም የሕይወትን አቋም ማንጸባረቅ በቀር፣ የመደረግን ሆነ የኋኝነትን አቋም፥ ወይም ጊዜያዊ ተከውኖን ያሳይም። ድርጊት ከሚባል ሁሉ ፈጽሞ ነጻ ነው።

በመጀመሪያው ቃል ነበረ በሚባልበት ጊዜም፥ ቃል ኖረ ወይም እንደኖረ ነበረ፣ በማለት፥ መኖርን ከማሳየት በቀር፥ ምንም ዓይነት የመደረግ ድርጊትን ወይም፥ ኋኝነትን የሚገልጽ ትርጓሜ አይገኝበትም።

በሁለቱም ስፍራዎች «ጥቅሶች» ውስጥ ከሚገኙ ዐረፍተ ነገሮች፣ የግሥ አንቀጾች፥ እንደዚህ ሆነው ዘይቤያዊ አቋማቸውን የሚገልጹበት ፍችና ጠባይ ያላቸው እንደመሆኑ መጠን፥ «በመጀመሪያ በመጀመሪያው» ተብለው ሲነገሩ፥ በአፍአዊ ወዘናቸው ተመሳሳይነትና ተመኩሳይነት ያላቸው፥ ተውሳከ ግሶችም የሚያጐላምሱአቸው የግሥ አንቀጾች መስለው፥ የያዙትን ፍሬ ነገርና ኃይለ ቃል በመከተል ማጠናከር እያጐሉ መገኘት የግድ ሆኖባቸዋል።

መቼም ቢሆን ተውሳከ ግሦች ሊያጐላምሱአቸው ከቆሙላቸው ከግሥ አንቀጾች ዝንፍ ብለው እንደማይወጡ በሥርዐተ ሰዋስው የታወቀ ነው።

እንዲህም በመሆኑ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» በተባለ ጊዜ «ፈጠረ» ለሚል ግሥ አጐላማሽ በመሆን የቆመ በመጀመሪያ ተብሎ የተነገረ ተውሳከ ግሥ የድርጊት፥ የተወጥኖን የጊዜን አቋም ወስኖ ማሳየቱ የሚታወስ ነው። «በመጀመሪያው ቃል ነበረ» ተብሎ የተነገረ ግን፥ «ነበረ» ለሚል የግሥ አንቀጽ አጐላማሽ ሆኖ የቆመለት በመጀመሪያ የሚል ተውሳከ ግሥ የቃል ህሉናን መኖርን ወይም ሕይወትን ባጭሩም ሥርዓተ ኑባሬን አንጸባርቆ ከመግለጽ በቀር፥ ድርጊታዊ ሥራን፥ ውጥን የተፈጸመበትን ወይም የተከናወነበትን ሁናቴ ሆነ የጊዜ ዕርከን ወስኖ አላሳየም።

እንግዲያውስ በመጀመሪያው በነበረ ቃል ሰማይና ምድር በመጀመሪያ «የፍጥረት መጀመሪያ» ሆነው የተፈጠሩ ሲሆኑ፣ ቃልን ግን በመጀመሪያው እንደነበረ እንጂ፣ እንደተፈጠረ አላሳየም።

ታዲያ መጀመሪያ መባሉ ምንን ሲያሳይ ይሆን? ከኋኝነትና ከውጥነት ከጊዜም ከዘመንም ውጭ ከተገኘ፣ የቃል ሀልዎትን ኑባሬን ወይም የሀልዎትን፣ ኑባሬን ወይም የሀልዎትን አቋም ይዞ መነገሩ አይደለምን?

አሁን ይህን ቃል ከመፈጠር ንጹሕ ሆኖ ካየነው በኋላ፣ ወንጌላዊው በመጀመሪያው ሲል የተናገረው ምንን እያመለከተ ነው? ብለን እንጠይቃለን? በእውነቱም እዚህ ላይ ቃል «በመጀመሪያው ነበረ ሲል» በመጀመሪያ ማለቱ ሀልዎትን ዘላለማዊነትን እንደሆነ እንረዳለን።

እነሆም በቃሉ ጻድቅና የታመነ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በቅዱስ መንፈሱ ሲያጽፍ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ አሰኝቶ አስጻፈ እንጂ፣ ሰማይና ምድር ነበሩ አሰኝቶ አላስጻፈም።

በአንጻሩም በመጀመሪያው ቃል ነበረ አሰኝቶ አስጻፈ እንጂ፣ በመጀመሪያ ቃል ተፈጠረ አሰኝቶ አላስጻፈም። በዚህም መጠበቂያ ፍጡራን የሆኑ ሰማይና ምድር በዘለዓለማዊ ህልውና የኖሩ ሳይሆኑ፣ በእግዚአብሔር ቃል ለልዩ ልዩ ፍጥረታት መጀመሪያ ወይም ውጥን ሆነው ካለመታየት ወደመታየት መፈጠራቸውን መሠራታቸውን በሚገባ ገልጾአል። ዕብ. 11፥3።

የሁሉ ፈጣሪ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ፥ ካለመታየት ወደመታየት በመጀመሪያ ካመጣቸው ከፈጠራቸው ከሠራቸው ፍጡራን ጋር፥ የማይዛመድ የማይመሳሰል ሆኖ፣ ጊዜ በማይወስነው ዘለዓለማዊ ህልውና ህልው ሆኖ መኖሩን ለይቶ አስታውቆአል።

ፈጣሪንና ፍጡርን የሚያገናኝ ነገር ቢኖር፣ ፈጣሪ ለራሱ ፈቃድ ሲል ፍጥረትን መፍጠሩ ነው። ፍጡርም ለፈጣሪው ጉዳይ ሊውል የመፈጠሩ ምክንያት ነው እንጂ፣ በባሕርይ የሚያገናኛቸው ነገር የለም አልተገኘም። መዝ. 134/135/፥6። ከጊዜ ውጭ መሆኑን አየን።



<u>ወንጌላዊ ዮሐንስ «ቃል ነበረ» ሲል፣ «ነበረ»። ለሚል የግሥ አንቀጽ አጐላማሽ አድርጎ ያቀረበው «መጀመሪያው» የሚል አነጋገር «ቃል» ዓይነተኛና ቀዋሚ ፍች ወይም ዘይቤ ምን ይሆን?</u>

«በመጀመሪያ» ሲል ዮሐንስ ያቀረበው ቃል ዓይነተኛና ቀዋሚ ፍች ወይም ዘይቤው ምን ተብሎ እንደሚተረጐም እንረዳ ዘንድ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ኅብረተ ቃላት መንሥኤ በማድረግ፣ በጥንቃቄ ስንመረምር እንደነበርን የሚዘነጋ አይደለም። ከዚሁ ጥናት ያገኘነውን ውጤት መለስ ብለን በማጠቃለል ብንመለከት መልካም ይመስለናል።

እነሆም ዮሐንስ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ሲል ለቃል ህሉና አጐላማሽ አድርጎ ወዳቀረበው «በመጀመሪያ» ኑ ወዳለው ደግመን በመመልከት በዚህ መዘርዝር እናጣራ።

1ኛ፥ ቃል፣ ዘመናት የማይወስኑት ጊዜያት የማይለኩት ከዘመንና ከጊዜ ነፃ ሆኖ መገኘቱን ተመልክተናል።

2ኛ፥ ቃል ከድርጊታዊ ቁጥር ወይም አኀዝ የማይዛመድ ፈጽሞ ባዕድና ውጫዊ እንደሆነ ተመልክተነዋል።

3ኛ፥ ቃል፥ ተወጥኖ ወይም መወጠን ከሚባል ሁኔታ ንጹሕና አፍአዊ ሆኖ መገኘቱን አስተውለናል።

4ኛ፥ ቃል ከድርጊታዊ ተከውኖ ወይም ከኋኝነት ነጻና ፍጹም መሆኑን ተገንዝበናል።

5ኛ፥ ማንኛቸውም ነገር ለቃል ህሉና ምክንያት እንዳልሆነ የአንድ ሁናቴን መነሻ የሚያሳይ ነገር ሆኖ እንዳልቆመ ተረድተናል።

ባጭሩ ዮሐንስ «በመጀመሪያ» ሲል እዚህ ክፍል ያቀረበው አነጋገር ከላይ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንድም የሚተረጐመው ወይም የሚተረጐምበት ሁኔታ እንደሌለ ተገንዝበናል።

ከእንዚህም መነሻዎች ሁሉ ተዘምዶ የሌለው ንጹሕና ነጻ አፍአዊና ውጫዊ ሆኖ አግኝተነዋል፣ የዚህ ዮሐንስ «በመጀመሪያ» ብሎ ያቀረበልን እውነተኛና ቀዋሚ ፍች ምን ይሆን? ብለን እንደገና ብንጠይቅ፣ ጨርሶ ሕሊናን በሚያነጻ አኳኋን የሚያረካ መልስ ለማግኘት እንበቃለን።

# ምዕራፍ ፳፫

## ዘመናት የማይወስኑት መጀመሪያ «ዘለዓለማዊነት»።

በመሠረቱ ፍጥረታት ከእርሱ ለእርሱ የተፈጠሩት ሆነው የተገኙበት ቃል የኖረበት መጀመሪያ፥ ምን ዓይነት መጀመሪያ ይሆን? ብለን ብንጠይቅ፣ የፍችውን እውነት ለማግኘት እንበቃ ይሆናልና፣ እስቲ እንሞክር፡-

ቃል ከፍጥረት ሁሉ በፊት የፍጥረት ሁሉ ወጣኒና ፈጣሪ ሆኖ እንደነበረ አይተናል። እንግዲያውስ ቃል የኖረበት መጀመሪያ መቼም መች፥ ጊዜና ዘመናት የማይወስኑት ዘለዓለማዊነት፣ የዘላለም ቅድምና ነው።

ይህም ይታወቅ ዘንድ ራሱ እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ «አነ ቀዳማዊ አነ ደኃራዊ፥» እኔ መጀመሪያ ነኝ እኔ መጨረሻ ነኝ ወይም እኔ የፊተኛ ነኝ፣ እኔም የኋለኛ ነኝ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም። እያለ ተናግሮአል። ኢሳ. 44፥6። ም. 48፥12፣13።

ልዑል እግዚአብሔር «መጀመሪያ ነኝ» ብሎ ሲናገር እላይ፣ በዘፍጥረት 1፥1 ከዘረዘርናቸው መነሻነት ካላቸው ነገሮች ሁሉ የራሱን መጀመሪያነት ሲያመሳስል አይደለም።

እግዚአብሔር እኔ መጀመሪያ ነኝ ማለቱ «ዘለዓለማዊ ነኝ» ማለቱ መሆኑን መግለጹ አይደለምን? ዕንባ. 1፥12።

አዎን፥ ለእግዚአብሔር ህላዌ አኗኗር መቼም መች ቢሆን፣ በጊዜና በዘመናት የሚወስነው መጀመሪያነት እንደሌለ፣ የታወቀ ነው። «አንተሰ አንተ ክመ» አንተ ግን ያው አንተ ነህ መዝ. 101/102/፥27።

ይህን ካየን እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ በተናገረው አነጋገር ልክ፥ ሥግው ቃል ራሱ፥ ለባሪያው ለዮሐንስ በራዕዩ ተገልጾ «አነ ውእቱ አልፋ ያሜጋ አነ ቀዳማዊ ወአነ ደኃራዊ ርእስ ወማኅለቅት» አልፋ ያሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ብሎ ሲነግረው እናገኛለን። ራዕ. 22፥13። ም. 8 እነሆም እግዚአብሔር እኔ መጀመሪያ ወይም ፊተኛ ነኝ ብሎ፥ በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ በተናገረው ሥግው ቃልም፣ እኔ መጀመሪያ ነኝ ፊተኛ ነኝ ሲል ለባሪያው ለዮሐንስ በተናገረው መካከልም ምንም ልዩነት እንደሌለ ተገልጾ እናያለን፣ 1ዮሐ. 1፥1።

ስለዚህ ዮሐንስ በወንጌሉ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ሲል ቃልን ዘመንና ጊዜ ሳይወስነው በቅድምና በዘለዓለማዊነት ነበረ ማለቱ መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ ተገልጾ ተብራርቶ ታወቀ ተጠንቀቀ። «ስለዚህ በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ማለትን



«ቃል በዘላለማዊነት ነበረ» ብለን እምነታችንን እያረጋገጥን፣ የቃለ እግዚአብሔር ዘላለማዊነትን ለሚክዱ እንመሰክራለን። 1ዮሐ. 1፥1። ም. 5፥20፣21። እርሱ ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፣ ሮሜ 9፥5። «አሜን።»

# ም ዕ ራ ፍ ፳፬

## ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።

አሁን ወንጌላዊው ዮሐንስ ወደሚያቀርበው፣ ሁለተኛ ትምህርታዊ ገለጻ እንመጣለን። እንደሚታወቀው ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተጻፈ የታመነ ነው። 2ጢሞ. 3፥14-17። በእግዚአብሔር መንፈስ መጻፉ የሚታመንበት መጽሐፍ ቅዱስ፡- ወልድ «ቃል» በሚሰኝበት ምሥጢራዊ ገለጻ መሠረት ዘለዓለማዊ ኑባሬውና ህልውናው እንዴት እንደሆነ? ደግሞ ከምን? በማን ዘንድ እንዳለ፣ እንደነበረ፣ እንደምን ባለው መለኮታዊ መገናዘብ ይኖር «ይገኝ» ይሆን? የሚያሰኙ የአንክሮ የተዘክሮ ጥያቄዎችን በልባችን ውስጥ ፈጥሮ ሲያበቃ፣ ዋና መልሱ ወደሚገኝበት አቅጣጫ፥ አመሥጥሮ ሲጠቁመን እናያለን።

ወንጌላዊው «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» በሚል ገለጻ ብቻ ትምህርቱን ሳይዘጋ፣ በዚያው ላይ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበረ ሲገልጽ እናገኛለን።

በዚህም ጊዜ ዮሐንስ «በመጀመሪያ የነበረው ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ማለቱ ምን አሳብ ቢኖረው ነው? ብለን ከጠየቅን፣ ወንጌላዊው በመጀመሪያ ቃል ነበረ ካለ በኋላ፣ እንደገና «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ ማስረዳት አስፈላጊው መኖሩን እንዳወቀ፣ ሳንገነዘብለት አንቀርም።

በመጀመሪያ የነበረ ቃል የት ዘንድ ነበረ? በማለትና ቃል ከተባለና በህላዌውም ቃል ከሆነ ዘንድ፥ በማን ዘንድ ነበረ? ብለን ከዚያው በሚገኝ ተመርሆ መጠየቅና መረዳት ተገቢያችን እንደነበረ እናስተውላለንና ነው።

በመጀመሪያ የነበረ ቃል የት ዘንድና በማን ዘንድ ነበረ? ስለዚህ፥ ወንጌላዊው በመጀመሪያ የነበረው ቃል በእግዚአብሔር ለሚለው ሐተታዊ ጥያቄ ሲመልስ፣ በመጀመሪያ የነበረው ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ብሎ በማረጋገጥ ለማስታወቅ፥ በሚመራው መንፈስ ቅዱስ መገደዱን እንመለከታለን።

በዚህ አረጋጋጭ ማስታወቂያ ዘይቤያዊው ተመርሆው የቀሰቀሳቸው ጥያቄዎች ሁሉ፥ ብቁዕ መልስ በመስጠት እንዲረኩ ማድረጉን እናያለን። ይኸውም፡-

1፥ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ሲባል ዘለዓለማዊ ሆኖ ይኖር የነበረው ቃል ዘለዓለማዊ ሆኖ ይኖር በነበረ እግዚአብሔር ዘንድ መኖሩን ማሳወቁ ነው።



2፥ሀ. «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ሲል፣ በመጀመሪያው የነበረው ቃል ስሙም ቃል ነውና፣ ቃልም ከሆነ ዘንድ፣ ብቻውን አይኖርምና፣ ቃል ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ በህልውና መኖሩን ማሳወቁ ነው።

ለ. አሁንም «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» የሚል ገለጻው በአንጻር አወራረድ እግዚአብሔር ያለ ቃል ያልኖረ ነውና፣ በዘለዓለማዊነት ይኖር የነበረ እግዚአብሔር በዚህ በመጀመሪያ በዘለዓለማዊነት በነበረ ቃል በህልውና ሲኖር መኖሩን የሚያሳውቅ አብነት ያለው በመሆኑ ይህንኑ ገልጾበታል።

3፥ በመጀመሪያ «በዘለዓለም» የነበረው ቃል ዘለዓለማዊ በሚሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ሲል፣ በዚህ በለባዊነት በቃልነት «በነባቢነት»፥ በእስትንፋስነት ህልውና ከተገለጸው ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር፥ በሌላ ዘንድ አለመኖሩን እንደዚሁም ደግሞ በዘለዓለምነት የኖረ ሌላ ባዕድ አምላክ ያልኖረ መሆኑን አስገንዝቦበታል።

4፥ በመጀመሪያ የነበረ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ሲል፣ ከዘለዓለም በቅድምና ይኖር የነበረ ቃል፥ ከዘለዓለም በቅድምና በነበረ እግዚአብሔር ዘንድ ኖርአል። ኢሳ. 43፥10-13። ይህም እግዚአብሔር የኖረበት ዘመንና ጊዜ ሊወሰንና ሊቈጠር እንደማይቻል ሁሉ፥ ቃልና እስትንፋሱም በእግዚአብሔር ዘንድ በህልውና ሲኖሩ፣ እንዲሁ በዘለዓለማዊ ቅድምና ይኖራሉ እንጂ፣ በዘመን የማይወሰኑ መሆኑን አስታውቆበታል።

ባጭሩ ይህ በለባዊነቱ በቃልነቱ በእስትንፋሱ የተገለጸ አንዱ ልዩና ቅዱስ እግዚአብሔራዊ ህላዌ፥ ያልኖረበት ዘመን አለመኖሩን፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ በሚል ገለጻ አሳውቆበታል።

ትምህርቱን ለመተንተን ያህል፥ የሚቀጥለውን ምሳሌ ወስደን ብንጠቀም መልካም ነው። ቃል ከልብ የሚወጣ የአሳብ መልክ ነው። ከልብ ሳይታሰብ የሚገኝ ቃል የለም። ቃል ከአሳብ የህልውና አንድነት ሳይኖረው እንደምን ሊነገር ይችላል?

ስለዚህ ጌታ በወንጌል «እምተረፈ ልብ ይነብብ አፍ፤ ከልብ ሙላት አፍ ይናገራል» ሲል፣ ቃል ከልብ የሚመነጭ መሆኑን ገልጾአል። ማቴ. 12፥35።

ሳይታሰብ የሚነገር ቃል የለም። ቃል ከአሳብ አንድነት ካልኖረው፣ እንደምን ሊነገር ይችላል? በመካከላቸው ምንም የሚለይ ነገር ሳይኖር፣ ከልብ ሙላት ቃል ሆኖ ይነገራል።

የልባችን አሳብ ከውስጥ ወደውጭ ሲገለጽ ቃል ሆኖ የሚያሳውቀው የሚገልጠው እርሱ ነው። ይኸውም ከውጭ የመጣ ሳይሆን፣ በልብና በሕይወት የማይቋረጥ ዘለዓለማዊ አንድነት ያለው ነው።

ይህም ሲባል የቋንቋን ቃል ማለት አይደለም። የቋንቋ ቃል ከባሕርያዊ ቃል ሚገለጽ ነው። አገላለጹም በአንድ ቅርንጫፍ ይኸውም በአንደበት ወይም በልሳን መነገር ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ ውስጣዊ ቃል በቋንቋ ብቻ ሳይሆን፣ በሰውነት አኳኋንም ሚሠራውን ሥራ ቀርፆ ለመግለጽ የሚያስችል አቅዋም አለው። ይህም በአማርኛ በትግርኛ ቋንቋዎች ተገልጾ ይታያል።

ይኸውም ከተባሉት ቋንቋዎች ውስጣዊ ቃል በአንደበት ወይም በልሳን ብቻ ሚገለጽ ሳይሆን፣ በሰብአዊ አካል ብልቶችም የሰውነትን ሥራና ሁኔታ ሲሠራና ሲገልጥ እንደሚገኝ ይገልጻል ለማለት ነው።

ይኸውም በአማርኛ «አለ» በትግርኛ «በለ» የሚሉ አነጋገሮችን እንውሰድ። የእነዚህን ቃላት ፍቺና መሠረት ምን እንደሆነ ለመረዳት እንጠይቅ። የውስጥ ቃል ሥራን ወይም ንግግርን ነው የሚገልጹ። አለ ወይም በለ ማለት አንድ ለባዊና ነባቢ ሕያው የሆነ ባለቤት በለባዊነቱና በሕያውነቱ እንደተናገረ ወይም ቃሉን ከራሱ እንዳወጣ ነው የሚገለጽ። ይህም በልሳን «በአንደበት» ሲነገር የታወቀ ነው።

በተባሉት ቋንቋዎች ማለት በአማርኛና በትግርኛ ግን ውስጣዊ ቃል ቋንቋን በሚያሰማ በአንደበት ወይም በልሳን ብቻ ሳይሆን በአካል ብልቶች ጭምር ቃሉ እንደሚወጣ ወይም እንደሚነገር ያሳያል።

ቂጭ አለ ልምጥ አለ

ብድግ አለ ለሽ አለ

ቀና አለ እጥፍጥፍ አለ

ቆም አለ ቂጣ አለ ወዘተ...

እነሆም «አለ» የሚል ግሥ የሰውነትን ንግግር ሲገልጽ በዚህ ይታያል። አካል ብልቶች እየተገለጹ አንዳንዱን ሥራ ሲሠራና ሁናቴውንም ሲያስፈጽም አይተናል።

እያንዳንዱን ሥራም ሲሠራ ከአሳብ የተያያዘ ውስጣዊ ቃል በአካል ብልቶች በኩል አኳኋኑን ሲያንጸባርቁ ሲያጐላው እግብር ላይ ማዋሉ አስገንዝቦአል።

ማስገንዘቢያ፡-

በዚህም ምሳሌ መናገሬ ቃል ሲባል የልብ አሳብ የፈቃድ ሕሊና ሆኖ ከውስጥ ከልብ ህልውና የሚኖር መሆኑን ከቋንቋ ቃል ለመለየት አስቤ ነው።

የውስጣዊ ቃል ህሉና እንዲህ ከሆነ፣ ከልብ ተለይቶ የሚታይና የሚሠራ የሚፈጠር ይሆናል ወይ?

በፍጡራን ነፍሳዊ ልቡናና በቃል መካከል ያለውን አንድነት በምንም የማይለይ ሲሆን፣ በእግዚአብሔር ልቡናና በቃሉ በሕይወቱ ያለውን የህልውና አንድነት



ማነው የሚለየው? አርዮሳውያን «ልንለየው የምንችል እኛ ነን» ብለው ተነሥተዋል፣ እንዲህ ያለውን አሳባቸውን እንዲተውና በሕይወት እንዲኖሩ አስቀድመው ቢያስቡበትም መልካም ነበር።

ይህም ተናጋሪ ከሚናገረው ወይም ከሚናገርበት «ባለቤት» ንግግር ተለይቶ በተናጋሪነት ብቻ አይቆምም። ንግግርም ከሚናገርበት ተናጋሪ ተለይቶ ብቻውን አይቆምም። ተናጋሪው በጠባይዑ የተተከለ ሆኖ ከሚገኝበት ቃል ጋር፥ ንግግርም «ቃልም» ከሚናገርበት ተናጋሪ ጋር መኖር ወይም መገኘት ይኖርበታል። አይለይምም ይህን መረዳት የሚያስቸግረን አይሆንም። መዝ. 37/38/፥69። ይህ አባባል በእሙንነቱ ተፈትኖ በተመርሆ ልቡና ሊቃውንት የጸደቀ ነው።

እነሆም ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር የመናገሪያ ቃሉ ሆኖ መገለጹን በመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው ተገልጾልን እናገኛለን። ራእይ 19፥13፣ 14። ኢሳ. 55፥11።

እንግዲህ ይህን ካየን በኋላ፣ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር እንዴት ኖረ? ብለን ብንጠይቅ ጠቃሚ ስለሆነ፣ ለዚሁ የሚቀርበውን የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ እንደሚከተለው እንመልከት።

1፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር፣ የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ ኖረ። መቸም አንባቢ ቃል ብቻውን የማይኖር መሆኑን በመጀመሪያው የነበረው ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ መኖሩን ያስተውላል። ዮሐ. 1-18።

2፥ ቃል ዘመንና ቦታ ለማይወስኑት እግዚአብሔር ቃሉ ሆኖ ኖረ።

3፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር፣ ለማይታይ እግዚአብሔር የማይታይ ምሳሌ ሆኖ ኖረ። ቈላስ. 1፥15-16።

4፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር የእግዚአብሔርን ልብንና ሕይወትን በህልውና ተገናዝቦ በቃልነቱም አቋም ኖረ። ዮሐ. 1፥3፣4። አሞጽ 4፥13። መዝ. 32/33/፣6፣11።

5፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር ችሎታ ቃል ወይም የኃይለ ቃልነቱ ሆኖ ኖረ። ዕብ. 1፥3። ም. 4፥12፣13።

እነሆም ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖር እንዴት ኖረ? በሚል መጠይቅ ደጋግመን ብንጠይቅ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ልቡናዊ ተመርሆ መሠረት ይህንና የመሳሰለውን ልብን የሚያረካ መልስ እናገኛለን።

ይህም የእግዚአብሔር ቃል ከፍጡርነት ወይም ከመፈጠር ነጻ ሁኖ በዘለዓለማዊ ህልውናና በህሉና በእግዚአብሔር መኖሩን የሚያስገነዝብ ነው።

# ምዕራፍ ፳፩

## ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። «እንደምን ነበረ? የት ዘንድ ነበረ?»

አሁን ወንጌላዊው ዮሐንስ ወዳቀረበው ወደዚሁ ትምህርታዊ ገለጻ እንመጣለን።

«ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ዮሐ. 1፥1፣2።

### ቃለ እግዚአብሔር እንደምን ባለ ኑባሬ አለ?

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው አእምሮ ከፍ ወዳለው አምላካዊ ምሥጢር መጥቶ እንዲያይ ሰውን ለሰው ቋንቋ በሚገባ ገለጻ አዘወትሮ ይጋብዘዋል።

እነሆም፦ «ቃል በእግዚአብሔር ህልው ነው» ብሎ፥ ቃል ያለበትን የኑባሬና የህልውና ምጥቀት የትና እንዴት እንደሆነ፣ እያነጻጸርን እንድናስብበት በፍቅር የተሰጡንን ከፍተኞች ምሳሌዎችን ያሳየናል።

ርግጥ ነው ነቢያት የእግዚአብሔርን ክብር እጅግ አስገራሚና አስፈሪ በሆነ ግርማ በራእይ አይተውታል።

ለምሳሌ፦ ነቢዩ ኢሳይያስ «እግዚአብሔር በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፥ የልብሱንም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት አየሁ» ብሎአል። ኢሳ. 6፥1።

ነቢዩ ዳንኤልም፥ «በዘመናት የሸመገለም «ብሉየ መዋዕል» ተቀምጦ ልብሱ እንደበረዶ ነጭ የራሱም ጠጕር እንደ ጥሩ ጥጥ ነበረ። ዙፋኑም እንደ እሳት ነበልባል ነበረ፣ መንኰራኵሮቹም የሚነድ እሳት ነበሩ የእሳት ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር» ብሎአል። ዳን. 7፥9፣10።

እነሆም በዚሁ ታላቅና አስፈሪ ግርማ የልዑል እግዚአብሔር ክብር በተገለጸላቸው ጊዜ፣ ባለራእዮች ነቢያት እጅግ አድርገው ፈሩ። ተንቀጠቀጡ። አዎን፥ የማይወሰነው እግዚአብሔር ምንም እንኳ በራእይ ሁናቴ ተወስኖ ቢገለጽላቸው፣ በጣም ጥቂት የሆኑ ባለ ራእዮች ከመፍራት ከመንቀጥቀጥ አልዳኑም።

ነገር ግን በራእይ ሳይሆን፣ ለሰው ሁሉ አእምሮ ሊገባ በሚችል ግልጽ በሆነ ትርኢታዊ ትምህርት፥ መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ነው» ብሎ ይገልጽልናል።



መጽሐፍ ቅዱስ «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ ሲናገር፣ የእግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ኑባሬነት እንዴት ያለ ህልውናዊ አኗኗር እንደሆነ፣ መጥቀን በንቃት እንድናይ ይጋብዘናል።

«ቃልን በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ነው» ይለዋል እንጂ፣ ረጅምና ከፍ ያለ የሰንፔር ድንጋይ የሚመስል፥ እንደእሳት ነበልባል የሚንቀለቀል ዙፋን ነው» አላለውም። «ቃልን በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ይለዋል እንጂ፣ መቅደሱን የሚሞላ እንደበረዶ የነጻ ልብስና የልብሱ ዘርፍ ነው አላለውም። እይ ተመልከት፦ ቃል ያለበት ህልውና የቱን ያህል ምጡቅ መሆኑን ያሳያል? ተመልከት፦ ቃል እንደ እግዚአብሔር ልብስ ወይም እንደ ረጅም ነበልባላዊ ዙፋን አልተመሰለም። ቃል የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ፥ እግዚአብሔርን እንደሚገልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ተናገረለት።

ነገር ግን እነዚህ ሁሉ በባሕርይ ወይም በጠባይዕ ረገድ ከሰው ሰውነት ጋር፥ ምንም ተዘምዶ የላቸውም። ሰውነት ሌላ ነው። ከልብስና ከወንበር ባዕድና ውጫዊ ነው። በኑባሬ ረገድም ልብስ ወንበርም ከሰው ሰውነት ሌላ ባዕዳንና ውጫውያን ነገሮች ናቸው። የህልውና ትርጉም መገናዘብን ወይም መዋሐድን ሊያሳዩ አይችሉም። በቅኔ መልክ የእግዚአብሔርን ግርማ ገልጸው ያሳዩ ዘንድ ለሰው የተሰጡ የፍቅር ምሳሌዎችና ራእዮች ናቸው።

ስለ ቃል ኑባሬ ግን፣ በደኅና አእምሮ አለን፥ እስካልን ድረስ፣ እንደዚህ አድርገን ልናስብ አንችልም። ቃል ከሰው የሚገኝ፥ ከሰው የሚወጣ፥ በሰው ነፍስ አቋም ደግሞ ከልብ ፈቃድና ከሕይወት ተገናዝቦ በህልውና የሚኖር ነው። ስለዚህ ቃል የሚኖርበት ህልውና ባሕርያዊ ውስጣዊ ነዋሪ ሲሆን፣ ልብስ ወይም ወንበር ከሰው ገላ፥ ሌላ፥ ወይም ከሰውነት ውጭ የሆኑ፣ ሰው ጥሪት ወይም ንብረት አድርጎ የሚጠቀምባቸው ነገሮች ናቸው። ባዕዳንና አፍአውያን መሆናቸውም የተረጋገጠ ነው።

ይህን ማስረጃ ከተመለከትን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ክብርና ግርማ ከሚገልጹት የሰፊሮስ ምስያ ካለው፥ ታላቅ ረጅምና ነበልባላዊ ዙፋን እንዲሁም መቅደሱን ከሚሞላ የልብሱ ዘርፍ፥ እንደ በረዶም ነጭ ከሚሆን እግዚአብሔር ከተጐናፀፈው ልብስ ይልቅ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ የሚኖረውን የእግዚአብሔርን ቃል ያለበት ባሕርያዊ የአንድነት አቋም እንዴት ያለ እንደሆነ ያሳይ የለምን?

አንባቢ ሆይ! «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፣ እምን ላይ እንዳለ ነው የሚያመለክተው? ቃል የሚኖር እምን ላይ እንደሆነ ታስባለህ?

በረጅሙ ዙፋን ላይ በነበልባላዊ የሰፊሮስ ምስያ ዙፋን ላይ ተቀምጦ በሚገኝ መቅደሱን ሞልቶት በሚገኝ፥ እንደበረዶ ነጭ በሆነ ልብስና የልብስ ዘርፍ በተጐናፀፈ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ዘንድ፣ ቃል ህልው ሆኖ

አለ። ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ኢሳ. 6፥10። ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ማለት ይኸው ነው የትርጓሜ ዐቅሙ። ዮሐ. 2፥14።

አዎን፥ የእግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔር ህልውና ሆኖ ከዘላለም መገኘትን፥ ኪሩባዊ ረጅምና ታላቅ የግርማ ዙፋንና መቅደሱን የሚሞላ፥ የብርሃን መጐናፀፊያ ሊደርሱበት ይችላሉን? ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ያለበትን ኑባሬ እስቲ ፈልግ፦

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ ሲናገር እስመ እም ኀቤሁ አነ እኔ ከእርሱ ዘንድ ነኝና ብሎአል። ኑባሬውን «ያለበትን» አኗኗር የት፥ እንዴት እንደሆነ ተመልክተሃልን? ዮሐ. 7፥29።

ቃል በመጀመሪያው ነበረ። በመጀመሪያው የሚለው በዘለዓለማዊነት ነበረ ለሚለው ምሥጢር፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ ነበረ። የሚለው ጉልህ አድርጎ ይገልጸዋል። ቃል በዘለዓለምነት ነበረ ሲል፣ በዘለዓለምነትም ቢሆን፣ ከእግዚአብሔር ልዩ ሆኖ ነበረ አይለውም እኮ ታስተውላለህን?

ወንጌላዊ ዮሐንስ፦ «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» በማለት ጠለቅ ብሎ በመግለጽ፥ የቃልነቱን አቋምና ማንነት ያመለከተናል። ይህም ምሳሌያዊ ገለጻ ያመጣበትን ምሥጢር፥ በጥንቃቄ ብንመለከት፣ ቃል እንደማናቸውም ቁሳቁስ ዕቃ ሆኖ የሚገኝ አለመሆኑን ነው። ዮሐ.1፥1። በባዕድ ነገር የሚመሰል አይደለም።



# ምዕራፍ ፳፮

## ከምንጭ በሚፈልቅ ምንጭ መካከል የባሕርይ ልዩነት የለም።

አስቀድመን ወደ ሰው መንፈሳዊ ሕይወትና ኑሮ በምናተኵርበት ጊዜ፣ ቃል አለ ከተባለ ዘንድ፥ ለቃል ምንጭ የሚሆን ልብ ወይም ልቡና ከዚያ አብሮ አለ። ሕይወትም ከቃልና ከልብ ተገናዝቦ አንድ ላይ ይገኛል።

ስለዚህ፦ «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ሲባል፣ ቃል ከእግዚአብሔርነቱ ልቡናና ሕይወት ዘንድ በህልውና አለ ማለት ነው። ዮሐ.1፥18። ያለ ሕይወትም በልብና ቡቃል ህልውና እንደሚገኝ ለባዊ የሆነ ሁሉ የሚያውቀው ነው።

ቃል ከልብ የሚወጣ የልብ አሳብ «ሕሊና» መልክ ነው። ከልብ ሳይታሰብ የሚነገር ቃል የለም። ታስቦ በሕሊና ደረጃ በአእምሮ ውስጥ ሆኖ፥ ሲወጣ ሲወርድ እየኖረ፣ በአፍ ሳይነገር ወደውጭ ሳይገለጽ የሚገኝበት ጊዜም አለ። ይሁንና ከልብ ሳይታሰብ የሚነገር ቃል የለም። ቃል ከአሳብ የህልውና አንድነት «መገናዘብ» ሳይኖረው እንደምን ሊነገር ይችላል?

ስለዚህ ጌታችን በወንጌል «እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን። ሲያጠቃልልም እስመ እምተረፈ ልብ ይነብብ አፍ። ትርጓሜውም ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፣ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃል። አፍ የሚናገረው ከልብ ምላት የተረፈውን ነው» በማለት አስረድቶአል። ማቴ. 12፥34፤37።

ስለዚህ፥ «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ሲባል፣ ቃል ከእግዚአብሔርነቱ ልቡናና ሕይወት ዘንድ፥ ቃል በህልውና አለ ማለት ነው። ዮሐ. 1፥18። ያለ ሕይወት የልብና የቃልህ ህልውና እንደማይገኝ፣ ለባዊ የሆነ ሁሉ የሚያውቀው ነው።

ቃል ከልብ የሚወጣ የልብ አሳብ «ሕሊና» መልክ ነው። ከልብ ሳይታሰብ የሚነገር ቃል የለም። ታስቦ በህሊና ደረጃ በአእምሮ ውስጥ ሆኖ፣ ሲወጣ ሲወርድ እየኖረ፣ በአፍ ሳይነገር ወደውጭ ሳይገለጽ የሚገኝበት ጊዜም አለ። ይሁንና ከልብ ሳይታሰብ የሚነገር ቃል የለም። ቃል ከአሳብ የህልውና አንድነት «መገናዘብ» ሳይኖረው እንደምን ሊነገር ይችላል?

ስለዚህ ጌታችን በወንጌሉ እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን፥ ሲያጠቃልልም «እስመ እምተረፈ ልብ ይነብብ አፍ። ትርጓሜውም ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፣ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃል። አፍ የሚናገረው ከልብ ምላት የተረፈውን ነው።» በማለት አስረድቶአል። ማቴ. 12፥34-37።

ስለዚህ፥ ከሰው የሚነገር ሁሉ ከልብ የሚኖርና የሚመነጭ ቃል መሆኑን ገልጾአል። በቃልና በልብ መካከል የሚለይ ምንም ነገር ሳይኖር፣ ከልብ ምላት ቃል ሆኖ ይነገራል። የአብና የወልድ አንድነትም እንደዚሁ ነው። 1ዮሐ. 2፥22-24። የአብና የወልድን መለኮታዊ አንድነት በጣም የሚያስረዳ ይህ ነው።

ቃል በልብ ህልው ሆኖ ሲኖር፣ ልገለጽ ባለ ጊዜ፣ የልብን አሳብ ከውስጥ ወደ ውጭ ይገልጻል። ወይም ገቢሩን የልብን ያደርሳል ማለት ነው። የእግዚአብሔር የመፍጠር ሆነ የማዳን ሁናቴ ሁሉ በዚሁ ረገድ ተከናውኖአል። ዘፍጥ. 1፥3፤27። ቈላስ. 1፥16። ዮሐ. 3፥16፤18።

ወንጌላዊው ይህን ሲያብራራ «እግዚአብሔርን ከቶ ያየው የለም። ነገር ግን በእቅፉ የሚኖር አንድያ ልጁ ተረከው» ይላል። ዮሐ. 1፥18። ዕብ. 1፥13።

ስለዚህ ደኅና አእምሮ ያለው ሰው «ቃልን ከልብ ለይቶ ልብንም ያለ ሕይወት አይቶ አንዱ ያለ አንዱ ሕያው ሆኖ ይኖራል» ብሎ ሊያስብ እንደማይችል ሲታወቅ፣ ቀዳማዊ ዘለዓለማዊ የሚሆን ቃለ እግዚአብሔርን ወልድን ህልው ሆኖ ከሚኖርበት ከአብ መለኮታዊ አንድነት ለይቶ፥ ለብቻው ሊያየው አይቻለውምና በአርዮሳዊ ስሕተት አይደናቀፍም።

## የልብና የቃል አንድነት በተግባር

ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው እንደመሆኑ መጠን፥ በቃልነት ስያሜውና በህልውናው፥ ከልብ ጋር ያለው የአንድነት ባሕርያዊ ተዘምዶ እንዴት እንደሆነ አየን።

ከእግዚአብሔር ልባዊ ፈቃድ ጋር ያለውን ተዘምዶ ጠለቅ ብለን ብንመለከት ይበልጥ እንረዳለን።

በመሠረቱ ፈቃድ ሲባል፣ የመፈለግ የመሻት የመውደድ ትርጉም ያለበት ምሥጢራዊ የዕውቀት የምክር፥ ምክርን የመለየት የምርጫ ነገር የሚያጠቃልል የልቡና ጠባይዕ ነው።

እነሆም እግዚአብሔር በፈቃዱ በሰማይና በምድር በባሕር በጥልቆች ያለውን ሁሉ እንዳደረገ እንደፈጠረ እናገኛለን።

«ኵሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር በሰማይኒ ወበምድርኒ በባሕርኒ ወበኵሉ ቀላያት። እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች አደረገ» ሲል ዳዊት ይናገራል። መዝ. 134/135/፥5፣ 6። ም. 113/114፥11።

በዮሐንስ ራእይም ሰማያውያን ኃይላት በእግዚአብሔር ፊት ወድቀው እየሰገዱ የሚከተለውን ተናግረዋል።

«ጌታችን አምላካችን ሆይ፣ አንተ ሁሉን ፈጥረሃል፣ ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና፣ ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል።» ራእ. 4፥10፤11።



እነሆም እግዚአብሔር ካልፈቀደ የሆነም የሚሆንም ነገር ፈጽሞ የለም። የፈቀደው ብቻ ሆኖአል። ተፈጥሮአል። ስለፈቃዱም ሁሉ ሆኖአል ተፈጥሮአልም።

መጽሐፍ ቅዱስ በሚገልጸው መሠረት «እግዚአብሔር ፈቀደ። ቀጥሎም አደረገ፣ ወይም ፈጠረ»፣ ተብሎ በተነገረበት ትይዩ፥ የልብ አሳብ ከቃል ባለው ባሕርያዊ የህልውና አንድነት መገለጽ ተነጻጽሮ ይታየናል።

እንደአቀራረቡም እግዚአብሔር ፈቀደ ሲባል፣ ሰማይና ምድር ባሕርና ጥልቆች የሚኖሩባቸውና ድርጊቶቻቸው ሁሉ ከመፈጠራቸውና ካለመኖር ወደመኖር ከመምጣታቸው ከመገኘታቸውም በፊት፥ ልዑል እግዚአብሔር ከመለኮታዊ ባሕርዩ ውጭ ማንም አማካሪና ረዳት ሳይኖረው፣ ከማንም ባልተበደረው በራሱ አምላካዊ ዕውቀትና ማስተዋል፥ ዘለዓለማዊ በሚሆን ምክሩና ጥበቡ ካለመኖር ወደመኖር ተፈጥረው እንዲመጡና እንዲገኙ ቅዱስ ፈቃዱ ሆነ ማለት ነው። ኢሳ.40፥12-14።

ይህ ቅዱስ ፈቃድ እግብር ይውል ዘንድ ደግሞ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ በቃልነቱ የልብን አሳብ የፈቃድን አቋም የሚገልጽ የእግዚአብሔር ቃል ሰማይና ምድር ባሕርና ጥልቆች ያሉዋቸውም ሁሉ፥ ከመታየታቸው በህሉና ከመገለጻቸው በፊት፥ ተፈቅደው ተወድደው፥ተፈልገው የተመደቡበትን ለባዊ ቅርፀ ኀሳብ፥ ካለመታየት ወደመታየት ካለመኖር ወደመኖር በማምጣት እግብር ላይ አዋለ። ገች ብለው እንዲገኙ አደረገ፣ ኃይላቸውም በእስትንፋሱ አጸና። ዕብ. 1፥1-3። መዝ. 32፥6።

«እግዚአብሔር በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች የፈቀደውን ሁሉ አደረገ» ተብሎ ለተነገረው ትርጉሙ ይህ መሆኑን ልንረዳ እንችላለን።

መቸም ቢሆን «በዘላለማዊ ቅድምናው ህልው «ነዋሪ» ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ካልሆነ በቀር፥ ከሆነው ነገር ሁሉ አንዳች ስንኳ አልሆነም» በሚል ገለጻ የተነገረውን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እዚሁ ላይ እናስታውሳለን። ዮሐ. 1፤1-3።

በመጀመሪያ መጨረሻውን ከጥንት ያልተደረገውን እናገራለሁ፣ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ፣ ተናግሬአለሁ እፈጽምምአለሁ። አስቤአለሁ አደርገውማለሁ። ኢሳ. 46፥10፤11።

ይህንን እያስታወስን እስከኖርን ድረስ፣ በእግዚአብሔር የልብ ፈቃድና በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ በሚኖር ቃል ያለውን ተዛማጅ አንድነት እንዴት እንደሆነ መረዳቱ ግልጽ ሆኖ እየታየን ይሄዳል።

ይኸውም፦ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ከእግዚአብሔር ቃል ተለይቶ ያለ እግዚአብሔር ቃል በአንዳች ድርጊት ላይ ገቢርን ሲፈጽም እንዳልተገኘ በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ ሆኖ መመስከሩ ነው። ሁሉ በእርሱ «በቃል» ሆነ። ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም ዮሐ. 1፥3። ዕብ. 11፥3።

የእግዚአብሔር ቃልም በእግዚአብሔር ህልው ሆኖ እንደመኖሩ፥ በህልውና ከሚኖርበት ከእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ያልተገኘውን አንዳች ነገር ስንኳ ቢሆን፣ በመፍጠር ሆነ በማድረግ እግብር ላይም በማዋል ያልተገኘና የማይገኝ መሆኑ ነው።

የእግዚአብሔር ፈቃድ በቃሉ፣ ቃሉም በውስጣዊ ህልውናቸው ሲታይም በህልውና ተገናዝበው የሚኖሩ ስለሆኑ ቃሉ ገንዘቡ ነው እንጂ ከውጭ የተዋሰው አይደለም።

ጌታችን በወንጌል እንዲህ ይላል፦

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም። ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድም ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋል።» ዮሐ. 5፥19።

«አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል። ዮሐ. 5፥19፣20። «እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና፣ አብ ብቻዬን አይተወኝም» ም. 8፥29። ምሳ. 8፥30።

«አብ በእኔ እንደሆነ፣ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ» ዮሐ. 10፥38።

«እኔ የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አልናገረውም፣ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፣ ባይሆንም እንኳ ስለራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ።» ም. 14፥10፣11። «አብ የሚፈቅደውን ብቻ ወልድ ይፈቅዳል።» ም. 6፥38፤40።

ስለዚህ አብ የፈቀደውን ያሳየውን ወልድ የሚሠራ በሥራ ላይ የሚያውል አሳልፎም አትርፎም የማይሠራ እንደመሆኑ ሁሉ፥ አብም የሚፈቅደውን ከወልድ የሠወረውና ያላሳየው የለም።

ከዚህ የተነሣ ቃለ አብ ወልድ «ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው» አለ። በሌላ ክፍልም «ለእኔ ያለኝ ሁሉ ያንተ ነው ያንተውም ለእኔ ነው» ሲል አንድያ ልጅ ለአባቱ ባለው ክብር መጠን የሚሆን ክብር ያለው ልጅ እንጂ፣ ፍጡር ሊናገርበት በማይችል ቋንቋ ተናገረ።

እንዲሁም ደግሞ እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ አለ። ዮሐ. 17፥4።

ቃል ሆኖ በእግዚአብሔር ህልውና መኖሩን ሲገልጽ ያለበትን ኑባሬ ከየትኛው አምላካዊ አቋም ላይ እንደሆነ አየን። ባየነው ደግሞ በዚሁ አኳኋን በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጾ በእግዚአብሔራዊ ባሕርይ ህልው የሆነውን ወልድን ነው። አርዮሳውያን ከዚህ መለኮታዊ ኑባሬው አውጥተው ፍጡር ሊያደርጉት ነው የሚፈልጉ።



ቃል እግዚአብሔር ነበረ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ካለ በኋላ፣ ምንም ጊዜ ወይም ቦታ ሳይሰጥና ሳያመነታ ከዚያው በማያያዝ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ብሎ ተናገረ ጻፈ። አዎን እውነቱን ነው። ለምን ያመንታ! በዚሁ መካከል ምን ሊያስብና ምን ሊል ኖሮአል!

ዘለዓለማዊ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ፥ ህልው ሆኖ ከኖረ፣ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ብሎ በልብ ሙላት የማይናገርበትና የማይጽፍበት ምንም ምክንያት የለም፦

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መሆኑን የሚያውቅ ሰው ሁሉ፥ ይህ መንፈስ ቅዱስ ምስክሩና ሐዋርያው ለሆነ ዮሐንስ ይህን በትምህርተ መለኮት ምርምር ጥራቱና እውነቱ የወጣለትና በመሠረትነቱ የጸና ዕውቀት እንደገለጸለት ተረድቶ ያምንበታል እንጂ፣ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ሲል ዮሐንስ የሰየመው ስያሜ፥ እንደሆነ አያስብም።

ከጥንት ጀምራ ሐዋርያዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» የሚለውን ትምህርት አምናበት ያለ ስሕተት ጠብቃ ይዛው በተገኘች በመጽሐፍ ቅዱስ ይህ፥ እንደሆነ ይገኛል።

«ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፦ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።» ዮሐ. 1፥1።

## «ቃል እግዚአብሔር ነበረ»

በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ጊዜና ስፍራ ቃል መጀመሪያ እንደነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበረ፣ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚባል ተገልጾ መነገሩን እናውቃለን። ራእይ 19፥13።

በዚህ ጊዜ፦ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ።» ተብሎአል። ይሁን እንጂ፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ይበል እንጂ፣ ቃል አብ ነበረ፣ ቃል መንፈስ ቅዱስ ነበረ አለማለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው ጠንቅቆ ያውቃል ያሳውቃልም።

ወንጌላዊው፦ ቃል እግዚአብሔር ነበረ ነው ያለ፣ ወንጌላዊው «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ሲል ምን ዓይነት ትምህርታዊ ምሥጢር ሊሰጠን ፈልጎ ይሆን?

ከዚህ አስቀድመን ስንከታተለው በነበረው ጥናት ከመጽሐፍ ቅዱስ በተነገረው፦ ስለ እግዚአብሔር ቃል ማንነት በተለያየ ገለጻ ተመልክተናል።

ለማስታወስ ያህል፦

1፥ እግዚአብሔር በቃሉ ተናግሮ ዓለማትን ስለመፍጠሩ-

2፥ በመጀመሪያው ቃል ህልው ሆኖ ስለመኖሩ፡-
3፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ስለመኖሩ፡-
4፥ ስሙ የእግዚአብሔር ቃል ስለመባሉ፡-

በዚህም ሁሉ በባሕርየ መለኮት ህልውና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ እየተገናዘበና በተከሥቶ ህልውና ረገድም ከአብ ዘንድ፥ በቃልነት አቋሙ እየተገለጸ እያንጸባረቀም መታወቁን አይተናል። «እነሆም አሁን ወንጌላዊው «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ አለ»።

## እነሆም አሁን ወንጌላዊው «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ አለ»።

ቃል «ወልድ» በዚህ ሁሉ የምልዐተ መለኮት ኑባሬ፥ ፍጹም ምሉዕ ሆኖ ተገኝቶአል፣ በእውነቱ «ቃል እግዚአብሔር ነው።» እንደምናየውም ከምልዐተ መለኮት ኑባሬ የሚጐድለውም የሚጐድልበትም አንዳች ነገር ፈጽሞ የለም።

ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ብሎ ሊናገር የበቃው ያለ ምክንያት እንዳልነበረ፣ ከዚሁም ለመረዳት ይቻላል። ይኸውም የቃልን «የወልድን» ማንነት በመንፈስ ቅዱስ ገለጻ ከመሠረቱ ጠልቆ ሲመለከተው፣ ፍጥረትን ሁሉ ኋኝ ለማድረግና ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ለመፍጠር ለማጋጠምና በለብዎ በህልዎ የማይወሰን በጠቅላላ በምልዐተ መለኮት ኑባሬ ፍጹምና ልዩ ምሉዕ መገኘቱን አይቶ፥ ከመረዳቱ የተነሣ ነው። ዮሐ. 1፥1፣3።

እነሆም፥ ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚመሰክር ወንጌላዊ፥ ሁሉን የሚችል ሁሉን የሚይዝ ምንም ነገር ለማድረግ የማይሳነው በህልዎም በለብዎም «በመኖርና በዕውቀት» ምሉዕ በኩለሄ በጠቅላላ ፍጹም እንደሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከተረዳ ዘንድ፥ ቃል እግዚአብሔር ነበረ ብሎ በማረጋገጥ የማይናገርበት ምንም ምክንያት እንደሌለ እንደማይኖርም ታይቶታል። 1ዮሐ. 5፥21፣22። በዚሁ በቃል ማለት በእግዚአብሔር ቃል ካለመኖር ወደመኖር ተፈጥሮ ተሠርቶ ተከውኖ የመጣ ፍጥረት ሁሉ ግን፣ ማናቸውም ይሁን፥ የሆነ ቢሆን ከምልዐተ መለኮት ኑባሬ፥ አንድም ድርሻ የለውም። ሊኖረው አይችልም። ከአንድ ቦታ ሲፈልስ፣ በሌላ ቦታ ይገኛል። ይህም ግልጽ ነው። በምልዐተ መለኮት የህልውና ኑባሬ መካከልና፣ በፍጡራን የተፈጥሮ ጠባይዕ መካከል ያለው ልዩነት ፈጽሞ የተራራቀና ከዚህ እስከዚህ ነው፣ ብሎ ርቀቱን ለማሰብም የሚሞከር አይደለም።

እንደምናውቀውም ሁሉ፥ ፍጥረት ሲባል፣ በህልዎና በለብዎ በመኖር «በዕውቀት» ምሉዕ በኩለሄ «በሁሉ ዘንድ ምሉዕ» ሆኖ አይገኝም፣ ፍጥረት እንደመሆኑ በመጠን ተወስኖ የተፈጠረ ነውና፣ እንደዚሁም ፍጥረት ሲባል፣ ሁሉን ለመፍጠርና ማናቸውንም ነገር ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ በኋኝነት ለማዋል ለማስገኘት፥ የሚያበቃ ኃይልና ክሂል በተፈጥሮ ጠባይዑ የለውም።

እርግጥ ነው፥ ፍጥረት ሲባል በእርዝማኔና በእጥረት፥ በስፋትና በጥበት፥ በርቀትና በግዘፍ መካከል እርስ በርሱ የሚበላለጥ ሆኖ ተፈጥሮአል። ይሁን



እንጂ፣ በህልዎና በዕውቀት በሰማየ ሰማያትና በምድር፥ በባሕርና በጥልቆች በየኃዋኀዉ ሁሉ በምልዐት ይኖራል። ማናቸውንም ነገር ካለመኖር ወደመኖር ፈጥሮ ያመጣል የሚባል አንድም ፍጡር አይገኝም።

ስለዚህ፥ በአእምሮ ግዕዛን የተፈጠረ ሆኖ፥ አእምሮው ያልተዛባ ጤነኛ ፍጡር፥ ከምልዐተ መለኮት ኑባሬ ተካፋይነት አለኝ፣ የሚል እንዳልተገኘ እናውቃለን። ተገኘ የሚባል ቢኖር፣ እውነተኛ አምላክ የሚያሰኘን መሠረታዊ ሕገ ባሕርይ ማለት የምልዐተ መለኮትን ኑባሬ ምን እንደሆነ ሳይረዳ፣ በከንቱ ምኞትና በመንጠራራት ብቻ ተነሥቶ፥ አምላክ የሚሆን መስሎት «አምላክ ነኝ» ብሎ ያወራ ዲያብሎስ ብቻ ነው። ኢሳ. 14፥12፣15። ሕዝ. 28፥14፣17። በእርሱ መንገድ የተጓዙ ሠራዊቶቹም እንዳሉ እናውቃለን። ይህም የእእምሮ ዕብደትና ውድቀት ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው።

መቼም እውነተኛው አምላክ፥ ከመጀመሪያው ከዘለዓለም ኢፍጡር ሆኖ በሕያው ባሕርይ ህሉና ነዋሪ፥ ደግሞ «ውስተ ኵሉ በሐውርት መለኮቱ «መለኮቱ በሁሉ ዘንድ በምልዐት ያለ» ሆኖ መገኘት እንዲሁም ሁሉን ለመፍጠር የባሕርይ ክሂልና፣ የባሕርይ ኃይል፥ የባሕርይ ፈቃድና የባሕርይ ጥበብ፥ የባሕርይ ፍቅርና የባሕርይ ቅድስና፥ ሁሉን የመቻልና ሁሉን የመያዝ፥ ሁሉን የመደገፍ ሥልጣን ከባሕርዩ ያለው ነው። በዚህ ሁሉ የባሕርይ ባለ ጸግነት ያለው መሆን አለበት። ከዚሁ ውጭ የሆነና እላይ ከተባለው አንዳች የሌለው ግን፥ ያው የተፈጥሮ መደቡ የለየለት ፍጡር ግቡር ነው። እንደዚህ ሆኖ ተወስኖ ተመጥኖ የተፈጠረ ሆኖ ሳለ «አምላክ ነኝ» ብሎ ቢያወራ፥ ውሸትን ከራሱ ከገንዘቡ ያወጣል። ዮሐ. 8፥42። መዝ. 95/96/፥5፣10። ሁሉን እሠራለሁ ብሎ ቢያወራም ሠርቶ ማሳየት አይቻለውም።

እነሆም መጽሐፍ ቅዱስ ፍጡር ከፈጣሪ የሚለይበትን የምልዐተ መለኮት ኑባሬንና፥ የፍጡራን አቋምን ወስኖ በማሳየቱ አስገንዝቦናል። ማናቸውም ፍጥረት ሁሉ በእርሱ ወደ ሆነና ሁሉን በራሱ ወዳስገኘ፣ ወደ እግዚአብሔር ቃል ብናተኵር፣ ከፍጥረት ውጭ ከዘለዓለማዊ ቅድምና በልዩ የባሕርየ መለኮት ኑባሬ፥ ፍጹም ምሉዕ እንደሆነ ተረጋግጦልን እናገኛለን። ዕብ. 1፥1፣3። ኤፌ. 1፥22። ቈላስ.2፥9። ኤፌ. 4፥5፣10። የባሕርይ አምላክ መለኮታዊ ግብርና የፍጡራን ጠባይዐዊ ግብር ከምንለይባቸው ነገሮች አንዱ የዚህ ሚዛን ነው።

ፍጡራን ከዚህ ባየነው በመፍጠር ሥራ ብቻም ሳይሆን፣ በማዳን ሥራም ቢሆን ችግር አለባቸው።

ለምሳሌ፡-

እግዚአብሔር በባሕርዩ የተኬንዖ የፍቅር ራስን የመለገሥ የጸጋና የርኅራኄ፥ መለኮታዊ ችሎትና ባለጸግነት በምልዓትና በፍጹምነት ከባሕርዩ ሲኖረው፣ ፍጡራን ግን ከዚህ አልፈው ምንስ ቀናነት ቢኖራቸው፣ ይህን የመቻል ዐቅም የላቸውም። ህሉናቸው ሆነ አእምሮአቸው በምልዐት እንዲገኙ አይፈቅድላቸውምም።

ከአንድ ቦታ ሲለቁ በሄዱበት ቦታ ብቻ ይገኛሉ። ፈቃዳቸውም በፈጣሪ ፈቃድ ብቻ የታሠረ ነው። በሁሉም ዘንድ ባለመገኘታቸው፣ ሁሉን ሊረዱ እንኳ አይችሉም። ፍጡር፥ ፍጡር ግቡር ነውና። አርዮሳውያን የእግዚአብሔር ቃል ወልድን እንደነዚህ ሊያደርጉት ይፈልጋሉን?

## ሁሉ በእርሱ ሆነ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በዘለዓለማዊ ህልውና በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረና እርሱ ራሱ እግዚአብሔር የነበረ ቃል በባሕርይ ህልውና ያለውን መለኮታዊ ከሂልና ሥልጣን እንዴት እንደሆነ በሚከተለው ይገልጽልናል። ሁሉ በእርሱ ሆነ። ዮሐ. 1፥3።

አዎን፦ የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ሰማይና ምድር ባሕርና ጥልቆች ያሉባቸውም የሚታይና የማይታይ በጠቅላላው በሰው አእምሮ ዘንድ «አለ» ተብሎ የሚታሰብና ሰውም ያላወቀው ያልደረሰበት ፍጥረት ቢኖር፣ ሁሉ በእርሱ «በቃል» ሆኖአል። ተፈጥሮአልም። ዮሐ. 1፥10። ሮሜ 11፥36። 1ቆሮ. 8፥5። ዕብ. 1፥2 ም.2-10። ም. 11፥3። መዝ. 32/33/፥6፥9። ዘፍጥ. 1፥3። ቈላስ. 1፥15-17።

እነሆም በቃል ፍጥረት ሁሉ ኋኝነት ማግኘቱን፥ እምኀበ አልቦ ኀበቦ «ካለመኖር ወደመኖር» ተፈጥሮ እንደመጣ፣ በጠቅላላው ማናቸውም ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ለመጋጠም እንደበቃ በመጽሐፍ ቅዱስ ኀብረተ ቃላት ተገልጾ እናያለን።

ማናቸውም ተፈጠረ የተባለ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ሊፈጠር፥ ሊሆን መብቃቱ፥ በቃልም ፍጥረት የተባለ ሁሉ ኋኝ ሆኖና ተጋጥሞ መገኘቱ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጕልቶና በርቶ ከተገለጠልን ዘንድ፣ ዓይነ ሕሊናችንን ከዚያው ሳንነቅል፣ ወደውስጡ ብናተኵር፣ ለዚሁ ለተገለጠልን ትርኢት ዓይነተኛ ምንጩ የሚሆን የትምህርተ መለኮት አብነት ሲፈልቅ ልናይ እንችላለን።

## ምልዐትና ፍጹምነት የአንዱ እግዚአብሔር ባሕርይ ብቻ ነው።

የትምህርቱ አብነቱም ሁሉን ለማስገኘት ፍጥረትን ካለመኖር ወደመኖር ለማምጣት የቻለ ፈጣሪ ህላዌ፥ መጀመሪያውኑ ከባሕርዩ ምን ሆኖ መገኘት ቢኖርበት ነው? በባሕርዩስ ምን ሊኖረው? ይጠበቅ ነበር? እያሰኘ፣ ሲፈልቅ የሚታይ መጠይቅ ነው። አዎን ያ፦ ሁሉን ካለመኖር ወደመኖር ለማምጣትና ለማስገኘት ፈጥሮም ለማስተዳደር የቻለ ፈጣሪ ህላዌ፥ ከዘለዓለማዊ ቅድምና የነበረው ልዩ ባሕርያዊ ኑባሬ እንዴት ያለ እንደነበረ ወደመረዳት መርቶ የሚያደርስ ይህ መጠይቅ ነው።

በመሠረቱ ሁሉን ለመፍጠርና ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ለማስገኘት መቻል፥ ለሚከተሉት ቀጥሎ ባሉት ኑባሬዎች ባለቤት ሆኖ መገኘት ነው።



ከዘለዓለማዊ ቅድምና ቅዱስና አፍቃሪ ሆኖ፥ ሁሉን የመቻልና ሁሉን የመያዝ ሥልጣን የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ፥ ምንም ነገር ለማድረግ የማይሳነው ሆኖ፣ ከባሕርዩ መገኘት ነው። ቅዱስና አፍቃሪ እንደሆነ ሁሉን የመቻልና ሁሉን የመያዝ ሥልጣን የባሕርይ ገንዘቡና ምንም ነገር ለማድረግ የማይሳነው ሆኖ፥ በባሕርዩ ከመገኘቱም ጋር፥ ከዘለዓለማዊ ቅድምና ከ-እስከ ሳይባል፣ ምሉዕ በኵለሄ በመሆን፥ በሰማይና በሰማያተ ሰማያት፥ በምድርና በባሕር ምንም ሽፋንና የሚጋርድ ነገር በሌላቸው በጥልቆችና በፍጡራን አእምሮ በማይገመት በኃዋኀው ሁሉ፥ በህልዎ በለብዎ «በመኖር በዕውቀት» ምሉዕ ፍጹም ሆኖ ሳይወሰኑ መገኘት ነው። ዮናስ 1፥9፣ 10። ኢዮብ 22፥12፤ 14። ም. 37፥18፤23። ነህ. 9፥5፣6። መዝ. 88/89/፥6፤ 12። ም. 88/89/፥1፥2። ም. 92/93/፥1፣2። 103/19፤22። ም. 103/104/፥1፤32። መዝ. 101/102/፥25፤27። 38/39/፥5-12። ም. 148. 1፥13። ኤር 23፥23። 2-4። ኤፌ. 4፥5፣6፡ ራእይ 4፥8፤11።

እንግዲህ፥ ሁሉን በቃሉ የፈጠረ እግዚአብሔር በዚሁ ሁሉ፥ ልዩ ፍጹም ምሉዕ ሆኖ ተገኝቶአል። በዚህ ሁኔታ መገኘቱ የባሕርየ መለኮቱ አቋም እንደሆነ ተገልጾአል።

የእግዚአብሔር ቃል ወልድም በዚህ በተነገረው ሁሉ በአባቱ ክብር መጠን ልዩ ፍጹም ምሉዕ ሆኖ በባሕርየ መለኮት ኑባሬ መገኘቱን መጽሐፍ ቅዱስ መስክሮለታል። ዕብ. 2፥12። ኤፌ. 4፥6፤ 10። መዝ. 118/119፥89። ም. 32/33፥6፤9።

የእግዚአብሔር መንፈስም በዚሁ በአብና በቃል መለኮዊ ሁኔታ ፍጹም ምሉዕ ሆኖ ተገኝቶአል። መዝ. 138/139/፥7፦12።

በመጀመሪያው «በዘለዓለም» በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ የነበረ፣ ራሱም እግዚአብሔር የነበረ ቃል ምንም ነገር ለማድረግ የማይሳነው በቅድስና በፍቅር ሁሉን መቻልና ሁሉን መያዝ፥ ሁሉን በሥልጣኑ መደገፍ የባሕርዩ ባይሆን ኖሮ፥ ሁሉን ኋኝ ለማድረግ ካለመኖር ወደመኖር ፈጥሮ ለማምጣት የማይቻለው በሆነ ነበር። ፍጡራን በዚህ ኑባሬ ለመገኘት አይበቁምና፣ እንደዚሁም በሰማይና በሰማየ ሰማያት በምድርና በባሕር በጥልቆችና በኃዋኀው ሁሉ፥ በህልዎ በለብዎ በመኖርና በዕውቀት «ሳይወሰን ምሉዕ በኵለሄ» በምልዐት ህልው ሆኖ ባይገኝ ኖሮ፥ ሁሉን ኋኝ ለማድረግ፥ ካለመኖር ወደመኖር ፈጥሮ አምጥቶ ሁሉን ለመያዝና ለመግዛት፥ በሥልጣኑ ለመደገፍ ባልተቻለውም ነበር። ዕብ. 2፥10፣12። በሁሉም ምሉዕና ፍጹም ሆኖ መጀመሪያ በዘለዓለምነት መገኘት አስፈላጊ ነውና።

ወልድ ቃል በዚህ ሁሉ ምሉዕ ፍጹም ሆኖ በባሕርየ መለኮት ኑባሬ በመገኘቱ ግን፣ ሁሉ በራሱ «ኋኝ ለማድረግ» ቻለ። «ሁሉ በእርሱ ሆነ» ከሚል የፈለቀው የትምህርተ መለኮት ዋና አብነትም ያብራራው ቃል «ወልድ» ሁሉን የመያዝ፥

በሁሉም ዘንድ ፍጹም ምሉዕ ሆኖ በልዩ የባሕርየ መለኮት ኑባሬ በአባቱ መጠንና በባሕርዩ ህልውና አንድነት እንደኖረ፣ ግልጽ ሆኖና ታውቆ መገኘቱ ነው።

## «ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም»።

ወንጌላዊው «ሁሉ በእርሱ ሆነ» ብሎ የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በዘለዓለማዊነት ከእግዚአብሔር ዘንድ በነበረውና፣ ራሱ እግዚአብሔር በሆነው ቃል እንደተፈጠረ መገለጹን፥ ከዚህ በላይ በተብራራው ተመልክተናል።

ወንጌላዊው ከዚህ አከታትሎ «ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» እያለ በጣም ግሩም የሆነውን ምሥጢራዊ ገለጻ ሲያቀርብልን እናያለን።

«እነሆም ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ከሚል ዓረፍተ ነገር ፈንጥቆና አንጸባርቆ የሚታየው የልቡናዊ ተመርሆ አባባል ጥንቁቅ በሆነ አእምሮ አተኩረው ሲመለከቱት፣ ልዩ ልዩ ቀዋሚ ጭብጥ የያዙትን ትምህርቶች ለማግኘት ይቻልበታል።

1ኛ፥ ብሂል «ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ሲባል ከወደ እግዚአብሔር ያለውን አደራረግ እያመለከተ እግዚአብሔር ያለ እርሱ «ያለ ቃሉ» ምንት ወይም አንዳች ነገር ስንኳ ያልሠራና ያልፈጠረ መሆኑን ግልጽ አድርጎ ያስገነዝባል።

እግዚአብሔር ያለ እርሱ «ያለ ቃል» አንዳች ወይም ምንት የሆነችዋን ነገር ስንኳ የማይሠራና የማይፈጥር መሆኑን ጉላ አድርጎ የሚያሳውቅ ኃይለ ቃል አይደለምን? ጉላ አድርጎ ማሳወቅ ብቻ አይደለም። ድንጋጌውንም ጭምር ያስገነዝባል። እነሆም «ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ከሚል አምላካዊ ጥቅስ የሚፈነጥቅ ዘይቤ፥ እግዚአብሔር ያለ እርሱ አንዳች ስንኳ የማይሠራና የማይፈጥር መሆኑንም ጭምር ወስኖ በግልጽ የሚያሳውቅ ሆኖ ተገኝቶአል።

አብ እንዲሆንና እንዲፈጠር የፈቀደውንና የፈጠረውን ሁሉ፥ ያለ ቃሉ ላለመፍጠሩ ወሳኝ ሆኖ የሚያሳውቅ ኃይለ ቃል ነው ሲባልም፣ አብ ብቻውን ሆኖ ያለ ቃሉ አንዳች ነገር ፈጥሮአል ሊባል እንዳይቻል፣ ወይም እስከማይቻል ድረስ፣ ወስኖ አግዶ በማስታወቁ እንደሆነ፣ ሊረዱት የሚቻል ነው።

ይህም ከሆነ፥ ልዑል እግዚአብሔር ያለ ቃሉ ምንት ወይም አንዳች ነገር የማይሠራና የማይፈጥር ለምን ይሆን? ብለን የምንጠይቅ ብንሆን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ በተነገረው መሠረት መልሱ እንደሚከተለው ተብራርቶ እናገኛለን።

ሀ/ መጀመሪያ ነገር:- የእግዚአብሔር ህልውና በባሕርያዊ አቋም በልብና በቃል በሕይወት ጸንቶ ይኖራልና ነው።

ለ/ እግዚአብሔር ያለ ቃሉ አንዳች ስንኳ የማይሠራና የማይፈጥር መሆኑ በዘለዓለማዊ ህልውና ከእርሱ ዘንድ ህልው ሆኖ ከሚገኝ ቃሉ ተለይቶ የማይኖር በመሆኑ ነው። ዮሐ. 1፥18። ም. 7-29። ም. 14፥11። አዎን ዘለዓለማዊ ከሚሆን ቃሉ ተለይቶ እስከሚለተገኘና እስከሚኖረ ድረስ፣ አብ ያለ ቃሉ ምንት ወይም አንዳች ነገር አይሠራም አይፈጥርም።

ሐ/ እግዚአብሔር አብ ለመፍጠር ሆነ ለመጠበቅ ወይም ለማዳንም ያለ ቃሉ «ወልድ» ራሱን የማይገልጽ በመሆኑና ይኸውም አቋም መለኮታዊ ሕገ ባሕርይ ስለሆነበት ነው። ዮሐ. 1፥18። ማቴ. 11፥29። ቈላስ. 1፥19። ዮሐ. 6፥46።

መ/ አድራጊ በሆነ ከባሕርይ ቃል ካልሆነ በቀር፥ ማንኛውንም ነገር ስለማያደርግ ነው። ዕብ. 4፥12።

ከዚህ አስቀድመን አብ ያልፈቀደውን ወልድ አንዳች እንደማያደርግ የተገለጸውን ትምህርት አይተናል። በዚህ ደግሞ አብ ያለ ቃሉ አንዳች አለማድረጉን አይተናልና አንጻጽረን ማገናዘብ ነው።

## 2ኛ፥ ብሂል «ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም»

«ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ሲባል፣ ይኸው ሐረጋዊ አባባል፥ የፍጥረት ሁኔታ ምን ዓይነት አቅዋም ይዞ እንደሚገኝ እያመለከተ አስገኚውንም ያሳየናል፣

ይኸውም:- በእግዚአብሔር ዘንድ በዘለዓለማዊ ህልውና የነበረና ሁሉን የፈጠረ ቃል በእርሱ ለተፈጠረው ሁሉ፥ አስገኚው እርሱ መሆኑን ከመግለጹም በላይ፣ ያለ እርሱ ግን ምንም ይሁን ምንት፥ ወይም አንዳች ነገር ያልተገኘ መሆኑን ያስረዳል።

ይህም እርግጥ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተ ቃላት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ወይደልዎ ለዘእምኔሁ ኵሉ ወዘበእዴሁ ኵሉ። ከእርሱ የተነሣ ሁሉ የሆነ ሁሉም በእርሱ የሆነ» ሲል ለፍጥረት ሁሉ አስገኚው እርሱ መሆኑን አስረድቶአል። ዕብ. 2፥10። ልዑል እግዚአብሔር ለፍጥረቱ መነሻና አድራጊ በሆነለት ፍጥረትን በአስገኘ ቃል በኩል ካልሆነ በቀር፥ በሌላ በኩል ወይም በማናቸውም ረገድ ሊገኝ ሊመጣ እንደማይችል የሚያረጋግጥ ገለጻ ነው።

እንግዲህ ወልድ ፍጥረታትን ያመጣና ያስገኘ ከሆነ፣ ፍጥረታትን መፍጠር ለብቻው ጠቅልሎ አብን ወይም መንፈስ ቅዱስን ፍጥረታትን ከመፍጠር ውጭ አግልሎ እንደማያስቀራቸው የሚመስለው ይኖር ይሆናል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የምናገኘው ኵሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ፥ እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ባለው ሁሉ የፈቀደውን በመንፈሱ የሠመረበትን አስገኝ በሆነ ቃሉ አድርጎአል። በመንፈሱም አጽንቶአል። መዝ. 113/114/፥11። ም. 32/33/፥6። የእግዚአብሔር ህልውና በልብና በቃል ይታወቃልና።

ወልድ በአካል ተለይቶ በባሕርየ መለኮት ህልውና ግን፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አንድ መሆኑን ከሚገለጽባቸው የትምህርተ መለኮት መግለጫዎች አንዱ ይኸው ነው። ዮሐ. 15፥19፤20። ም. 9፥33። አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ግብር፥ አንድ ኃይል፥ የምንለውም ከዚሁ የተነሣ ነው። ሁሉ ከእርሱ፥ ሁሉ በእርሱ ከእርሱ ሁሉ ለእርሱ ነው። ሮሜ 11፥36። ኤፌ. 2፥18። ሮሜ 11፥36።

## የዚህ ክፍል አጠቃላይ ሐተታ «ያለ እርሱ አንዳች ስንኳ አልሆነም»

ወልድ በእግዚአብሔር ህላዌ ያለውን ሥልጣንና ችሎታ እንዴት እንደሆነ፣ ይህ፥ ያለ እርሱ አንዳች ስንኳ አልሆነም የሚል ገለጻ ያጐላዋል። ዮሐ. 1፥3።

በሥሉስ ቅዱስ ባሕርያዊ ህላዌ ጓኝ እንዲሆን የተፈቀደ ፍጥረት ሁሉ ያለ እርሱ «ያለ ቃል» አንዳች ስንኳ አልሆነም።

ታዲያ እንደዚህ ባለው የባሕርየ መለኮት ሥራ የዚህ አድራጊ ፈጣሪ የሆነ፥ ሥልጣንና ኃይል የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አባቱ ለፈጠረው ሁሉና ለሚፈጥረውና ሊፈጥረውም ለፈቀደው ሁሉ፥ እግብር ላይ በማዋል ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ እንዲገኝ የሚያደርግና የሚመግብ ዘለዓለማዊ የአብ ቃል፥ እንዴት ቢሆን እንደምንስ ቢደረግ፣ ፍጡር ሊሆን ይችላል? እንደምንስ ቢታሰብ፥ ፍጡር ለማድረግ ይሞከራል። ዕብ. 11፥3።

ደኅና አድርገን የተመለከትን እንደሆነ፣ አብ ሁሉን እንደፈጠረ፣ ወልድም ሁሉን እንደፈጠረ፣ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን እንደፈጠረ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። መዝ. 32/33/፥6። ኢዮብ 26፥13። ም. 33፤41።

ይሁን እንጂ በእርሱ «በቃል» ካልሆነ በቀር አንዳች ስንኳ አልሆነም» እያለ፣ መጽሐፍ ቅዱስ መናገሩ፥ አብም ሆነ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ «በቃል» ካልሆነ በቀር፥ አንዳች ስንኳ እንዳልፈጠሩ የሚያሳይ አይደለምን?

ይህስ ሁኔታ በሥሉስ ቅዱስ ባሕርያዊ ህላዌ ያለው የወልድ «የቃል» አኗኗር እንዴት እንደሆነ ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ አይደለምን? ሮሜ 11፥36።

መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜን ዘመንን ሳይጠቅስ፣ አልፋ ዖሜጋ ቀዳማዊ ደኅራዊ የሆነውን ዘለዓለማዊ ወልድን ቀዳማዊ ከሆነው አብ ያለ የነበረ የሚኖር መሆኑን እየገለጸ ያስረዳል። ራእይ 22፥14። ም. 1፥8፡ ዕብ. 13፥8። ኢሳ. 43፥10። ም. 44፥6። ሐዋ. 10፥30።

አርዮሳውያን «አንድ ልጅ ነበረው በአባቱ እቅፍ ያለ» የሚሉ ጥቅሶችን እንኳ ተመልክተው «አለ ነበረ» የሚል የግሥ አንቀጽም «ተፈጠረ» ከሚል የግሥ አንቀጽ ምን ያህል የተራራቀ ልዩነት እንዳለ ቢገነዘቡ፥ ምንኛ መልካም በሆነላቸው ነበር? አዎን አብንና ወልድን ከደው የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ከመሆን ሊድኑ በቻሉና «በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት» ከተባሉት



ጋር አንድ ሆነው እርሱ የሰጠውን የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች በሆኑ ነበር፣ 1ዮሐ. 2፥22፤25። 2ዮሐ. 9።

በዚህ ሁሉ ፍጥረትን የማስገኘትና የመፍጠር የማድረግ ችሎታ ሥልጣንም መብት ያለው በእርሱ ካልሆነ በቀር አብና መንፈስ ቅዱስ እንዳልፈጠሩ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጥለት እግዚአብሔር ቃል ወልድን፥ «ፍጡር» ነው የሚሉ ቢኖሩ፣ ምን ማለታቸው እንደሆነና ወዴት መውሰዳቸው እንደሆነ፣ ጠንቀቅ ብለው ቢያስቡበትና፣ ልባቸውን ወደ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ተመርሆ ቀና አድርገው እንዲመለሱ ልናሳስባቸው እንወዳለን።

እስቲ አብ ያለ እርሱ «በቃሉ ካልሆነ በቀር» አንዳች ነገር ስንኳ እንዳልፈጠረ፣ ዳሩ ግን «ሆነ፣ ተደረገ፣» የተባለ ሁሉ፥ በቃል እንደሆነ እንደተደረገ፣ ወይም እንደተፈጠረ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ቁልጭ ብሎ እየታየ፣ ቃልን «ፍጡር ነው» ሲሉ አብን ምን ማድረጋቸው ነው? ወይስ ሁሉን የፈጠረና ያስገኘ ቃልን «ፍጡር ነው» ካሉ በኋላ፣ ቃሉን ፍጡር እያሉ አብን በፍጡር ድጋፍ ፍጥረትን ፈጠረ ሊሉ ነው?

ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ከመቀበል ውጭ፥ ወልድን እንስድባለን ብለው በተነሡበት እንቅስቃሴያቸው፥ ከዚህ የተመርሆ ልቡናዊ ውጥረት ውስጥ የሚገቡ እነርሱ ራሳቸው ናቸው።

ሁሉን የሚችል የሚሳነው ነገር የሌለ አንዳች ነገር የማይጐድለው ብለን የምናምነውንና የምናመልከውን እግዚአብሔርን አንዳችን ነገር እንዳልፈጠረ፣ ቢፈጥርም ከፍጡር ድጋፍ አግኝቶ እንደፈጠረ ማሰባቸው አይደለምን?

3ኛ፥ ብሂል፡- «ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ዮሐ. 1፥3። «ከሆነውም ሁሉ አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፣ ምን ማለት ነው? አብ ያለ እርሱ አንዳች ስንኳ አልፈጠረም ማለት መሆኑ ግልጽ አይደለምን? እንግዲያውስ አብ ያለ እርሱ «ያለ ቃል» ምንትን ካልፈጠረ፣ ሁሉ በእርሱ የሆነበትን ቃልን ፈጠረ ለማለት እንዴት ይቻላል?

1፥ አብ ብቻውን ሆኖ ያለ ቃሉ አንዳችን ነገር ፈጠረ ሊባል እንዳይቻል፣ ወይም እስከማይቻል ድረስ፣ ያለ እርሱ አንዳች ስንኳ አልሆነም። «አልተፈጠረም» የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ወስናና አግዶ ይዞታል።

2፥ አብ ምንት የሆነችውን ነገር እንኳ የፈጠረ በቃል እንጂ፣ ያለ ቃል አይደለም። ያለ ቃል ምንትን አልፈጠረም። እንግዲያውስ በቃል በኩል ካልሆነ ምንትን ያልፈጠረ እግዚአብሔር ቃልን አልፈጠረም። አዎን ያለ ቃል ምንትን ሳይፈጥር፣ ቃልን ይፈጥራልን? የዚህም ዋና ፍሬ ነገር እግዚአብሔር በቃል ካልሆነ በቀር፥ አንዳችን ወይም ምንትን ነገር ስንኳ እንዳልፈጠረ፣ በግልጽ መነገሩ ነው። እንዲህ ሆኖ ተገልጾ

ሳለ፣ ቃል እንደምን ተፈጠረ ሊባል ይቻላል? መቼም ያለ እርሱ አንዳች ነገር ስንኳ ሊሆን፣ የማይቻል ነውና፣ ቃል ከአብ ጋር ሆኖ የገዛ ራሱን ፈጥሮአል ሊባል ነው? ወይስ ምናልባት ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊት ቃል የገዛ ራሱን ፈጠረ ሊባል ነው? ይታሰብበት።

አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ የማይፈጠር ሆኖ ሳለ፣ የገዛ ራሱ ህልው ከመሆኑ በፊት፥ ራሱን ፈጠረ ለማለት ያስችላልን? እነዚህን ጥያቄዎች ለሰው ማቅረባችን፥ ሰው አመዛዛኝና ሕሊና አለው እንላለንና፣ ሰው ሊሆን ባለው ነገር ይመረምራል ይፈትናል ብለን ነው።

አዎን፥ ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስን ገለጻ ትቶ፥ በራሱ ፍላጎት የገዛ አእምሮውን እየገፋ ወደ ውጥረትና ወደ ጭንቀት ሊያስገባ አይፈቅድም ብለን በማመን ነው።

እነሆም መጽሐፍ ቅዱስ «ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም» ከማለቱ በፊት፥ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ በመጀመሪያ «በዘለዓለማዊ ቅድምና» ህልው ሆኖ ይኖር እንደነበረ ገልጾአልና፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ የነበረ ቃል ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊትም ተፈጥሮአል። የሚያሰኝ ነገር እንዳልነበረበት፥ ታውቆ ያደረ ነገር ነበረ። ዮሐ. 1፥1።

## የ3ኛ ብሂል ተጨማሪ መግለጫ።

ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም ዮሐ. 1፥3። እዚህ ላይ እንደተገለጸ፣ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ የነበረ ቃል፥ ሁሉ በእርሱ ሆነበት ያለ እርሱ ግን አንዳች ነገር ስንኳ አልሆነም።

ሁሉ በቃል መሆኑ፥ ያለ እርሱ ግን አንዳች ነገር ያልሆነ መሆኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ካስገነዘበ፣ ያለ ቃል አንዳች ነገር ያለመሆኑ ደግሞ፥ እግዚአብሔር ያለ ቃሉ ወይም ከቃሉ ተለይቶ፥ አንዳች ነገር አለማድረጉንና አለመፍጠሩን አረጋግጦ የሚያስረዳ ጭብጥ ነው። «ሆኖአል»።

ከቃሉ ተለይቶ ወይም በቃሉ በኩል ሳይሆን፣ አንዳች ነገር አለማድረጉንና ምንም አለመፍጠሩን ደግሞ፥ ቃሉን ያልፈጠረ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ዘይቤ ነው። ይኸውም ጉልህ ሆኖ እንዲታወቅ ያደረገው ገለጻ፥ ያለ ቃሉ አንዳች ነገር ስንኳ፣ ያላደረገና ያልፈጠረ መሆኑ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከዘለዓለም በእርሱ ዘንድ ህልው ሆኖ በነበረ ቃል፥ ሁሉን ሲፈጥር፥ ያለ ቃሉ ይኸውም በቃሉ ካልሆነ በቀር፥ አንዳችን አልፈጠረም አለ እንጂ፣ ቃልን እስካልፈጠረ ድረስ ቃልን ፈጠረ አላለም። ወይም በቃል ሁሉን እስካልፈጠረ ድረስ፥ ቃልን ፈጠረ አላለም። መጽሐፍ ቅዱስ ካላለም፣ ያልተባለውን ጨምሮ መናገር ሌላ አቅጣጫ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ከተባለው ጨምሮ ወይም አጉድሎ መናገር በምን አቋም ላይ መገኘት



እንደሆነ የታወቀ አይደለምን? ምሳ. 30፥6። ራእይ 22፥18፣19። ዮሐ. 8፥44።

እንግዲህ እግዚአብሔር በቃሉ ካልሆነ በቀር፥ አንዳች ስንኳ ካልፈጠረ፣ ቃልን እንዴት ፈጠረ። ሊባል ይገባል? በእርሱ ህልው ሆኖ በሚኖር በቃሉ ካልሆነ በቀር፥ ምንም ሥራ አልሠራም፣ ምንም ፍጥረት አልፈጠረምና ነው። ምንም ወይም አንዳች የሚለውም ሌላውን ፍጥረት ሲያመለክት የተነገረ ነው እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ሲያመለክት አይደለም። ምንም ወይም አንዳች የተባለው ፍጥረትም እንኳ ቢሆን፣ በቃል በኩል ካልሆነ አልተፈጠረም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ «በቃል» ሁሉ ሆነ ተገኘም፣ ያለ እርሱ «ያለ ቃል» ግን፣ አንዳች ወይም ምንት ስንኳ አልሆነም። አልተገኘምም ብሎአልና ነው። ይኸውም ቃል የተፈጠረ ወይም ፍጡር ነው ተብሎ በምኞት እንኳ እንዳይታሰብ የኃይለ ቃሉ ጭብጥ እንደዘጋው ይታያል።

በቃል ካልሆነ በቀር፥ ኋኝ ሆኖ የተገኘና የተፈጠረ ምንም ነገር የለም። ዘለዓለማዊ በሆነ ሀልዎ በልቡናው በቃሉ በሕይወቱ ህልውና፥ ሕያው ሆኖ ከሚኖር እግዚአብሔር በቀር፥ በእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን፣ እንዲያው ተፈጥሮ ተሠርቶ ተደራጊ ሆኖ የተገኘ፥ ምንም ወይም ምንት የሚባል ነገር ፈጽሞ አልነበረም።

«ህልዎና ኋኝነት» ግሣውያን ስሞች የሚታየውን ዘይቤያዊ አቀማመጥ ሊመለከት የሚሻ ቢኖር፣

ሀ/ «በህልዎ» ሲባል በመጀመሪያው የነበረ ቃሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው እንደሆነ ኖሮአል።

ለ/ «በኋኝነት» ሲባል ግን፥ ፍጥረት ሁሉ በአስፈላጊ ጊዜ፣ በቃል የተከወነ የተፈጠረ የተሠራ የተደረገ ሆኖ ለመገኘት በቅቶአል። እንዲሁም በመሆኑ በህልዎ በመጀመሪያ «በዘለዓለምነት» ከእግዚአብሔር ዘንድ ቃል ህልው ሆኖ ኖሮአል። በቃል ከተሠራ ከተደረገ ከተፈጠረ ከተከወነ አስቀድሞ ግን፣ የተሠራ የተፈጠረ የተደረገ የተከወነ ምንም ወይም ምንት የለም። ባጭሩ መፈጠር ወይም ኋኝነት መደረግ ወይም መሠራት የለም አልነበረም ማለት ነው። በእርሱ በኩል ካልሆነ አንዳች ስንኳ አልሆነም ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ አረጋግጦ ተናግሮ የለምን?

ሁሉ በእርሱ በቃል ሆነ ተፈጠረ እንጂ፣ ከሆነውም ሁሉ በቃል ካልሆነ በቀር፥ እንዳልተፈጠረና፥ ካለመኖር ወደመኖር ሊመጣ እንዳልበቃ ሁሉ፥ ቃል ወልድም የአብ ቃል ሆኖ፥ ከዘለዓለም በህልዎ መኖሩን የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ሆኖ ጊዜና ዘመን ሊለየው በማያስችል ህልውናዊ አቋም በተዋሕዶተ መለኮት መገለጹን፥ መጽሐፍ ቅዱስ እያስረዳ ሳለ፣ ያልተፈጠረውን የእግዚአብሔር ቃልን እግዚአብሔር ፈጠረው ማለት መቼም ከግፈኞች የሚሠነዘር የዱብ ዕዳ ነው። ዮሐ. 1፥3። ቈላስ. 1፥15። ዕብ. 1፥3። ዮሐ. 12፥44።

መጽሐፍ ቅዱስ ወልድን የእግዚአብሔርን ቃል የእግዚአብሔር ጥበብ የባሕርዩ ነጸብራቅ በሚል ገለጻ ማስታወቁ፥ ሰው የራሱን ቃል የራሱን ጥበብ ከሰብአዊነቱ ከሁለንተናው አብሮ ቃል ሆኖ እንዲያገኘው ታውቆ ያደረና ቃሌን ጥበቤን ፈጥሬ ያመጣሁት ነኝ ብሎ ሊያምን ስለማይችል፤ ወልድም የአብ ቃል የአብ ጥበብ ተብሎ ሲነገርለት፤ የዘለዓለማዊ ሕያው እግዚአብሔር ህልውናም ያለ ቃልና፤ ያለ ጥበብ ስለማይገኝ፤ ቃሉንና ጥበቡን ሊፈጥር አለመቻሉን እንዲረዳበት የተሰጠው መግለጫ ነው።

እንዲሁም ወልድን የክብሩ ነጸብራቅ በሚል አቀራረብ መገለጹ፥ ሰው በመብራትና በነጸብራቁ ያለውን ባሕርያዊ አንድነት ያውቃልና፤ ወልድም ከአብ ያለው አንድነት መከፈል መለየት የማይታይበት ባሕርያዊ መሆኑን ለመገንዘብ ያስችለዋል ተብሎ ነው።

ሰው በሚያውቀው ቋንቋና በሚያስተውለው ዕውቀት ሥውር የሆነ አምላክ ራሱን እንደዚህ አድርጎ ሊገልጽ በመፍቀዱ ምስጋና እያቀረብን ልናመልከው ሲገባን፤ ከሰዎች መካከል፥ «ኢፍጡር የሆነ ቃሉን» በፍጡር አመድ ሊለውሱት መጣጣራቸው፤ እጅግ አድርጎ የሚያሳዝን ነው።

አጠቃላይ።

ሀ/ ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም።

ለ/ ወልድም ሊገለጽለት ከሚፈቅድ በቀር ማንም አብን የሚያውቅ የለም ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ገልጦ ያስረዳል። ማቴ. 11፥27።

ሁሉ በወልድ ሆነ እንጂ፤ ያለወልድ ግን አንዳች አልሆነም ሲል፥ ያለወልድ ምንም አልተፈጠረም ወደተከውናም አንዳች ነገር ቢሆን እንኳ አልመጣም ማለቱ መሆኑን አስገንዝቦአል።

ደግሞ ወልድ ሊገለጽለት ከሚፈቅድ በቀር ማንም አብን የሚያውቅ የለም ሲል፤ ለማንም ቢሆን አብን ለማወቅ ወልድ ካልፈቀደና ካልገለጸለት በምንም አኳኋን ሊያውቅ አይቻለውም። ማለቱ መሆኑን ያስረዳል።

እንግዲህ እንደመጽሐፍ ቅዱስ አባባል፥ በመፍጠር ረገድ ያለ ቃል ምንም ነገር ሊሆንና ሊፈጠር አልተቻለም። በማወቅ የማይቻለው ሆኖአል። ይህም በመገለጽና በመፍቀድ ለእግዚአብሔራዊ መገለጽና መታወቅ ቁልፉ መሆኑን ነው የሚያሳይ።

እንግዲህ እንደመጽሐፍ ቅዱስ አባባል፥ በመፍጠር ረገድ ያለ ቃል ምንም ነገር ሊሆንና ሊፈጠር አልተቻለም። በማወቅ ረገድም ወልድ ካልገለጸለትና ሊገለጽለትም ካልፈቀደ፤ ማንም አብን ሆነ ወልድን ለማወቅ የማይቻለው ሆኖአል። ይህም በመገለጽና በመፍቀድ ለእግዚአብሔራዊ መገለጽና መታወቅ ቁልፉ መሆኑን ነው የሚያሳይ።



ወልድ ቁልፉ ነው ሲባልም፤ በመፍጠር ረገድ ሁሉ በእርሱ መሆኑንና ያለ እርሱ ግን፥ አንዳች ስንኳ ሊሆን አለመቻሉን፤ በማወቅ ረገድም፥ ወልድ ካልገለጸለትና ሊገለጽለትም ካልፈቀደ በቀር፥ ከፍጡራን ወገን ማንም አብን ሆነ ወልድን ሊያውቅ አለመቻሉን፤ መጽሐፍ ቅዱስ ባስገነዘበው መሠረት ነው። ማቴ. 11፥26፤27።

ኃይለ ቃሉን የተመለከትን እንደሆነ፤ እግዚአብሔር ዓለማትን ለመፍጠር ቢፈቅድም እንኳ፤ ያለ ቃሉ ወይም በቃሉ በኩል ካልሆነ በቀር፥ ምንም «አንዳች» ስንኳ፤ አለመፍጠሩን ነው። ደግሞ አብ ራሱን ሊገልጽ ቢፈቅድም በወልድ በኩል ነውና፤ ወልድ ካልገለጸለትና ሊገለጽለትም ካልፈቀደ በቀር፥ ከፍጡራን ማንም አብን ሆነ ወልድን ሊያውቅ የማይቻለው መሆኑን ነው። ሉቃ. 10፥22።

በአንድ አምላክነት በአንድ ፈቃድ ለሚኖር ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይሁን አሜን።

እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር ያለ ቃል ምንም እስከማይፈጥር ድረስ አብ ራሱን ሊገልጽም ያለወልድ ወልድም ካልፈቀደና ካልገለጸ በቀር ማንም አብን ሊያውቅ የማይችል እስኪሆን ድረስ በመለኮታዊ ፈቃድና አንድነት ያለው የወልድ ሥልጣን እስከዚህ መሆኑ ታይቶአል። ዮሐ. 14፥6። ዮሐ. 4፥12።

ታዲያ እንደዚህ ባለ የባሕርየ መለኮት ሥራ፥ ይህን ያህል አድራጊ፥ ፈጣሪ የሆነ ሲፈቅድና ሲገለጽ ብቻ አብም በእርሱ ሊገለጽ ፈቃዱ የሆነ፥ አባቱንና ራሱን የመግለጽ ሥልጣንና ክሂል ያለው ወልድ፥ ፍጡር ሊሆን ይችላልን? እባካችሁን እናንተ አርዮሳውያን በቅንነት አስቡ?

## ሁሉን መቻል የአንዱ የእግዚአብሔር ጠባይዓዊ ግብር ብቻ ነው።

በዚህ ላይ ያለው ጥያቄ አርዮሳውያን «ፍጡር ሁሉን ይችላል» ሲሉ፤ ፍጡር ሁሉን ለማድረግ ሆነ ሁሉን ለመቻል ብቁ ይሆን ዘንድ፦ ሊመስላቸው የቻለ እንዴትና እንደምን ሆነው ቢያስቡና ቢሳሳቱ ነው? የሚል ነው።

በዚሁ ክፍል ወደምንናገርበት ፍሬ ነገር ከመግባታችን በፊት፥ መንገዱ ይነጻልን ዘንድ፤ «ሁሉ» ስለሚል ቃል ዋናውን ትርጉም ለመረዳት እንሞክር። በእውነትም «ሁሉ» ሲባል፤ ምን ትርጉም ይዞ ይነገራል? አዎን በተለይ በዚህ በምንናገርበት ክፍል «ሁሉ» ተብሎ ሲነገር የምናየው፤ ጠቅላላ ፍጥረትንና በጠቅላላ የፍጡራን የኋኝነታቸውን ድርጊት እያመለከተ እንደሚነገር ነው። መዝ. 103/104/፥24። ም. 144/145/፥9፤10።

ይህን ካየን ዘንድ፥ በእግዚአብሔርና በተነጻጻሪው «ሁሉ» በተባለው ፍጥረት መካከል ያለው ልዩነት እንደሚከተለው ተገልጾ እናያለን።

ሀ/ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ነው፤ ሕያውና ኢፍጡር ነው። ጠቢብና ከሀሊ «ቻይ» ነው። ኃያልና ምሉዕ በኩለሄ «በሁሉ የሞላ» ነው። መላኪ «ገዥ» ነው።

ለ/ «ሁሉ» ተብሎ የሚጠራ ደግሞ ፍጥረት በበኩሉ፥ የተፈጠረና የተሠራ፥ የተደረገ፥ የሆነና ካለመኖር ወደመኖር በፈጣሪው ፈቃድና ሥምረት በተፈለገ ጊዜ ተፈጥሮ፥ ተሠርቶ፥ ተከውና የመጣ፤ ደግሞ በፈጣሪው ምግብና «አስተዳደር» የሚኖር ነው።

እንግዲህ «ሁሉ» የተባለው ፍጥረት እንደመሆኑ መጠን፥ ዘለዓለማዊና ሕያው ከሚሆን ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሥምረት የተነሣ፤ በተወሰነ ጊዜ፤ በተፈለገበት ቅፅበት ተፈጥሮ፥ ካለመኖር ወደመኖር የመጣ ሆኖ ሲገኝ፤ በምንም በማናቸውም፥ ከእግዚአብሔር ባሕርይ ሊመስልና ሊመሳሰል አይችልምና፤ የፍጡርነት፥ የኋኝነት አቋሙን ብቻ ይዞ ይጸናል።

እንደዚሁም በመሆኑ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለው የባሕርይ ልዩነት ፈጽሞ የተራራቀ ነው። መዝ. 101/102/፥22-27።

ጠበብ ባለ አቀራረብ ብንመለከት እንኳ፤ በአጠቃላይ «ሁሉ» ተብሎ በሚነገረው በፍጥረት መካከልና፤ ከዘለዓለም ሕያው ሆኖ በሚኖር እግዚአብሔር መካከል፥ በእግዚአብሔርነቱ በፈለገው ጊዜ በፈጠረው ፍጡር መካከል ወዳለው ርቀትና ጊዜ፤ አተኩረን ብንመለከት፤ ዘመኑ ምን ያህል እንደሆነ መቀና ለመናገር ለሰው ይሳናል። በዚህም ሁኔታ ያለውን ልዩነት በሰው አእምሮ ሊመጠን የማይቃጣ፤ እንዲያውም የማይታሰብ ነው። እግዚአብሔር ያለጊዜ የሚኖር ሲሆን፥ ፍጡር ግን በተወሰነ ጊዜ የተፈጠረ ነው። ባጭሩ ፈጣሪ መጋቢ ሲሆን፤ ፍጡር ግን ተመጋቢ፥ ነው። ፈጣሪ ሰጭ ሲሆን፤ ፍጡር ግን ተሰጭ ነው። ፈጣሪ ወሳኝ ሲሆን፤ ፍጥረት ሁሉ ደግሞ ተወሳኝ ነው። 1ቆር. 4፥7።

ይህም ብቻ ሳይሆን፤ ፈጣሪ ሠሪ በሆነ በእግዚአብሔር መካከልና የተፈጠረ የተሠራ ሆኖ በሚገኝ «ሁሉ» በፍጡር መካከል ያለው ልዩነት የትና የት እንደሚራራቅ ለባዊ ነባቢ የሆነ ሰው ሁሉ ይረዳዋል። ሮሜ 1፥19-22።

ይህን መሠረት ሳንለቅ፤ ሁሉ የሚለውን ቃል እንደያዝን፤ ሁሉን የሚችል፥ ሁሉን የያዘ፥ ሁሉን የሚመግብና የሚጠብቅ እግዚአብሔር ሲባል የልቡናውና የቃሉ የእስትንፋሱ «የሕይወቱ» ባሕርያዊነት ሲገለጽበት ልናይ እንችላለን።

አዎን፦ የእግዚአብሔር ርቀትና ስፍሐት፥ «ቻይነት» ምሉዕነትና ሥልጣን ግርማና ጽንዕ የዘለዓለማዊ የሕያው ባሕርየ መለኮት ጠባዩ መሆኑ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የተመሰከረ ነው። ሮሜ 1፥21። ዮሐ. 17፥24፤25። 1ጢሞ. 6፥16። ራእይ 10፥11።

የዚህ ባሕርይ ባለቤት ወይም በዚሁ ባሕርይ ያለና የሚኖር እንደመሆኑ፥ የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ በወሰነበት ጊዜ፤ ፍጥረትን ሁሉ «ለማን? በማን?» ፈጥሮ ሁሉን የሚችል ሁሉን የሚይዝ ሁሉን የሚገዛ፤ ሁሉን የሚመግብና ሁሉን



የሚጠብቅ እንደተሰኘበት፤ መጽሐፍ ቅዱስ ገልጾ ያብራራው መሆኑ የታወቀ አይደለምን? ቈላስ. 1፥16።

አዎን፤ እግዚአብሔር ሁሉን መቻሉ፥ ሁሉን መፍጠሩ፥ ሁሉን መያዙ፥ ሁሉን መመገቡና መጠበቁ፥ በማን፤ ለማን ነበረ? ቢባል፤ ያለ እርሱ አንዳች ነገር ስንኳ በማይሆን ነገር ግን ሁሉ በእርሱ በሆነበት በቃሉ ለቃሉ «በእግዚአብሔር ቃል» ለመሆኑ ከዚህ ቀጥለው የተጻፉ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያረጋግጣሉ።

«ሁሉ ለእርሱ ሆነ፤ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነምና» ዮሐ. 1፥3። በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ፤ ኃይላቸውም በአፉ እስትንፋስ ነው።» መዝ. 32/33/፥6። «ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ» ዕብ. 1፥2፡ «ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። እርሱም ከሁሉ በፊት ነው።» ቈላስ. 1፥16።

«ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናውቃለን» ዕብ. 11፤3።

እነሆም በምልዐትና በርቀት፥ በገናንነትና በፍጹምነት በእዘዝና በሥልጣን ሕያውና የባሕርይ አምላክ ሆኖ፥ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር እግዚአብሔር ሁሉን የሚችልና የቻለ ሁሉን የፈጠረና የያዘ፤ ሁሉን የመገበና የጠበቀ በቃሉና በቃሉ ከሀሊነት ነው።

ምክንያቱም ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ሁሉ እንዲሆን እንዲፈጠር ለማድረግ የቻለው በቃሉ ከሀሊነት ሲሆን፤ ያለቃሉ ማለት በቃሉ በኩል ሳይሆን፤ አንዳች ስንኳ አላደረገምና ነው። እነሆም ያለቃሉ ቻለ፤ ሁሉን ፈጠረ፤ ሁሉን ያዘ ሊባል እንዳይቻል፤ ወዲያና ወዲህ ለማጠማዘዝ በማያስችል የጭብጥ ገለጻ ታጥሮ ተገድቦ በመገኘቱ ይታወቃል። የጭብጥ ገለጻውም «ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ ያለ እርሱ ግን አንዳች እንኳ አልሆነም» የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ጉልቶ በርቶ የተጻፈ ቃል ነው። ዮሐ. 1፥3።

ይህ ኃይለ ቃል ቀጥሎ ያሉት መሠረተ ኀሳቦችን ወስኖ ያስረዳል።

1ኛ፥ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ካልሆነ በቀር፥ አንድ ስንኳ እንዳልፈጠረ እንዳላደረገ፤ ግልጽና ጉልህ ሆኖ መታየቱ ነው።

2ኛ፥ ሁሉን መቻል ሁሉን መፍጠር፥ ሁሉን መያዝ ባጭሩ የሚሳነው ነገር የሌለ ሆኖ መገለጽና መታወቅ፥ ያለ እርሱ አንዳች ስንኳ ሊሆን ባልተቃጣበት በቃሉ ተችሎና ተፈጥሮ ኋኝ ሆኖና ተደግፎ መገኘቱ ነው። ዕብ. 1፥2።

ስለዚህ ሁሉን የቻለ ሁሉን የፈጠረ ሁሉን የያዘ የሚሳነው ነገር የሌለ ተብሎ የተነገረለት አንዱ እግዚአብሔር በአድራጊ ቃሉና በመንፈሱ «በሕይወቱ» እንደሆነ ተረጋግጦ ታወቀ። መዝ. 32/22/፥5-9።

እንግዲህ እዚህ ላይ እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉን የፈጠረና፤ በቃሉ በኩል ካልሆነ ግን አንዳች ስንኳ ያልፈጠረ ሊፈጠርም ያልቃጣ ሆኖ ሳለ፤ ይህን ሁሉን

በእርሱ ሲፈጥር፥ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ ሊፈጥር ያልቃጣበት ቃሉን፥ ፍጡር ለማድረግ «ፍጡር ነው» የሚሉ ወገኖች፥ ሁሉን ከሚችል ሁሉን ከፈጠረ ሁሉን ከያዘ እግዚአብሔራዊነቱና ባሕርያዊ ህልውናው ሊገነጥሉት የሚከጅሉ መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ነው።

ሆነ የተባለ ነገር ሁሉ፥ በእርሱ ሆኖአል፤ ያለ እርሱ «ያለቃሉ» ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም። በሚለው ውስጥ ወሳኝ ኃይለ ቃል፥ እንዳለ አተኩረው ሊመለከቱ ይገባቸው ነበር። አብ ሁሉን የሚችል ሁሉን የሚፈጥር ሁሉን የሚይዝ ሆኖ የተገለጸው በእርሱ በኩል ካልሆነ በቀር፥ አንዳች ስንኳ እንዲሆን ለማድረግ ወይም ለመፍጠር ባልቃጣበት ዘለዓለማዊ ቃሉ፥ ሁሉን ስለቻለና ስለፈጠረ፤ ስለያዘና ስለገዛ፤ ስለመገበና ስለጠበቀ፤ አይደለምን? እንዲህስ መሆኑ፥ ቃል በአንድ በእግዚአብሔራዊ ህልውና ስላለው አንድነት አይደለምን?

ቃል እግዚአብሔር በመለኮታዊ የባሕርይ ህልውና አንድ ስለመሆኑ፤ በእርሱ ሁሉ እንደሆነ፤ ሁሉ እንደተቻለ፤ ሁሉ በእርሱ እንደተፈጠረና እንደተጠበቀ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው ማስረጃ በቂ ነው። ከፍጡራን ወገን ግን፥ ሁሉን የሚችል፥ ሁሉን የሚፈጥር፤ ሁሉን የሚይዝ ለመሆን የሚቻለው አለን? ሁሉን ለመቻል፥ ሁሉን ለመፍጠርና የሚሳነው ነገር የሌለ ለመሆን፤ ሁሉን ለመመገብ ለመጠበቅ ብቃት ያገኘ ተብሎ፥ የሚታሰብ ፍጡር ይኖራልን?

ፍጡራንን ለማምለክ ፈልገው የእግዚአብሔር የመለኮታዊውን ክብርንና የባሕርያዊ የግብር ስምን፥ መናኛ ነገር ይመስል፥ ከአንድ እግዚአብሔር ተወስዶ ከአምላካዊ ባሕርይ ውጭና ባዕድ ለሆነ ፍጡር ሲሰጥ መኖሩ፤ በአሕዛብ ዘንድ የተለመደ ነው።

መቼም ፍጡራንን አማልክት አድርገው ለማምለክ የሚወዱ ፍጡራን ከእግዚአብሔር ባሕርይ በቀር፥ ለማንም የማይቻለውን ሁሉን ቻይነት፥ ሁሉን መፍጠር፥ ሁሉን መያዝ ወደ ፍጥረት እጅ ለማግባት ይጥራሉ። ነገር ግን ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ይህ መለኮታዊ ባሕርይን የሚጠይቅ ሁናቴ ነው እኮ!

እነሆም ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡-

«ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ፤ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፤ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።» ነገር ግን ይህ ዕውቀት በሁሉ ዘንድ አይገኝም አንዳንዶች ጣዖታትን እንደለመዱ ናቸው። 1ቆሮ. 8፥6።

አዎን ልማድ ክፉ ነው። በፍጡራን ጣዖት ማምለክ የለመዱ ጣፋጩን የባሕርይ አምላክን አምልኮት በለመዱት በፍጡር እሬት በርዘው የጣዖታት ምሬትን መጠጣት ይወዳሉና፤ አያስደንቀንም።

«ሁሉን መቻል ሁሉን ማድረግ፥ ሁሉን መፍጠርና፥ ሁሉን መያዝ፤ የአንዱ የእግዚአብሔር የባሕርይ ግብር ብቻ ስለሆነ፤ ፍጡር የሚባል ነገር በተጨማሪነት የማይካፈልበት የአብና የልጁ የመንፈሱ የግል የባሕርዩ ገንዘብ መሆኑን ሐዋርያት



ጳውሎስና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እያስታወቁ ያስጠነቅቃሉ። ፍጡራንን ተስፋ ማድረግና ጣዖታትን ማምለክ የለመዱ ክፍሎች፥ ፍጡራን ግቡራን የሆኑ ሁሉ፥ ሁሉን ለማድረግ ሁሉን ለመያዝ ሁሉን በሥልጣናቸው ለመቈጣጠር የሚችሉ ይመስላቸዋል። ሁልጊዜም እምነታቸውንና ተስፋቸውን በእነዚህ ፍጡራን ላይ ያደርጋሉ። እነርሱንም ያመልካሉ።

ሥሉስ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው። አምልኮትም ክብርም ስግደትም ለእርሱ ብቻ ነው። ሁሉን የሚችል ሁሉን የሚይዝ እርሱ ብቻ ነው።

ከዚህ የመለኮታዊ ህልውና አንድነት ታስሮበት ከሚገኝ ግብረ ባሕርይ፥ ሁሉን መቻልና ሁሉን መያዝ ሁሉን መፍጠርና ሁሉን ማድረግ ለአብ ብቻ ሰጥቶ፥ ወልድን በስተውጭ ለማድረግ የሚቻል አይደለም። እንዳይቻል የሚያደርገውም ሁሉ በእርሱ ሆኖአል። ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም። በሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ተጠብቆአልና ነው።

አሁንም ደግሞ የመለኮታዊ ህልውና አንድነት ታስሮበት የሚገኝ ግብረ ባሕርይ፥ ይኸውም ሁሉን መቻልና ሁሉን መያዝ፥ ሁሉን መፍጠርና ሁሉን ማድረግ ለወልድ ብቻ ሰጥቶ፥ አብን በስተውጭ ለማድረግ የማይቻል ሆኖ ይገኛል። እንዳይቻል የሚያደርገውም ራሱ ወልድ በወንጌል በተናገረው ነገር ተገልጾ ተብራርቶአል። ይኸው ራሱን ከእግዚአብሔር አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቴ ነው በማለቱ ለተቃወሙት አይሁድ የመለሰላቸው ቀጥሎ ያለው ቃል ነው።

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ፤ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም። ያ የሚያደርገውን ሁሉ፥ ወልድ ያደርጋልና።» ዮሐ. 5፥18።

«በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ፤ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ። ባይሆንስ ስለራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ።» ዮሐ. 14፥11።

እነሆም፡- እዚህ ላይ ወልድ ቃለ እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ከአብ ተነጥሎ ምንም ሊሠራ ሊያደርግ እንደማይችልና፤ አብ የሚሠራውንና የሚያደርገውን ግን ራሱ እንደሚያደርገው ሲሆን፤ ሁሉን መቻል ሁሉን መፍጠር ሁሉን መሥራት ሁሉን ማድረግና ሁሉን መያዝ የአብና የልጁ የባሕርይ ግብርም፥የአብና ወልድ የባሕርይ ህልውናን ገልጾ የሚያስገነዝብ ነው። አብና ወልድም ያለ መንፈስ ቅዱስ አልፈጠሩም እነሆም ኢዮብ 33፥4። ም. 26፥13። መዝ. 32/33/፥6።

ይህም በአብና በልጅ መካከል አንዱ ፍጡር፥ ሁለተኛው ፈጣሪ፥ ወይም አንዱ ሁሉን ሲፈጥር፤ ሁለተኛው ሆነ ሦስተኛው የማይፈጥር አድርጎ በማሰብ ውጥረት ውስጥ ገብቶ ከመጨነቅ የሚያዋጣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብ የተገለጸ ቀና ትምህርት ነው።

ፍጡራን የሆኑ የእግዚአብሔር መላእክትም «የእግዚአብሔር ልጆች» ተብለዋል። ኢዮብ 1፥8፡ ም. 2፥1። ም. 38፥7።

ፍጡራን የሆኑ የሰው ልጆች «የእግዚአብሔር ልጆች» ተብለዋል። መዝ. 31/82/፥6። ሮሜ 8፥14፤15። ገላ. 4፥5፤6።

ይሁን እንጂ የተጠቀሱትን ጥቅሶች በልቡናዊ ተመርሆ የሚመለከት ሰው ምን ዓይነት ትርጉም ይሰጣቸዋል? በውኑ እነዚህ «ልጆች» ተብለው የተጠሩና እዚህ ላይ የተጠቀሱት ፍጡራን የእግዚአብሔር ልጆች ሆኑ ተብሎ ሲነገርላቸው፤ በጥንት ጀምሮ አልተፈጠሩም፤ አልተሠሩም፤ አልተደረጉም፤ ካለመኖር ወደመኖር በእግዚአብሔር ቃል ተፈጥረው አልመጡም ማለት ነውን?

እንደዚህ ይሆናል ብሎ የሚያስብ መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበና ለባዊ ነባቢ ነኝ የሚል ሰው ይኖር ይሆን? እርግጥ ነው፤ ፍጡራን በእግዚአብሔር ጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል። ታዲያ የእግዚአብሔርን ልጅነት በጸጋ ያገኙት እንጂ፤ በጸጋ ያገኙት ልጅነት /ልደት/ ከጥንት ከመጀመሪያ የተፈጠሩበትን የተፈጥሮ ባሕርያቸውን ደልዞና የመፈጠራቸውን ታሪክ ፍቆ እንዳልተፈጠሩ እንዳልተሠሩ፥ ካለመኖር ወደመኖር በእግዚአብሔር ቃል እንዳልመጡ ሊያደርጋቸው እኮ አይችልም። ይህም እርግጠኛ ነገር ነው።

ስለዚህ እንደዚህ ያለው ፍጡራን በጸጋ ያገኙት የእግዚአብሔር ልጅነት፤ ወልድ ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር ካለው ዘለዓለማዊና ባሕርያዊ ልደት ጋር ሊመሳሰል፤ ሊመጣጠን ሊተካከል የማይችል ነውና፤ ይህ ግንዛቤ የአርዮሳውያንን ዓላማ አክሽፎታል። አዎን በአርዮሳውያን ዘንድ በባሕርዩ መፈጠር የሚባል ነገር የማይኖርበትን ወልድ ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደበትን ዘለዓለማዊንና ባሕርያዊን ልደት ለማኪያኪያስና ለማቃለል ፍጡራንስ የእግዚአብሔር ልጆች ይባሉ የለም ወይ? በሚል ምጸታዊ ፈሊጥ ወልድን ለመስደብ ታስቦ ነው። አዎን በአርዮሳውያን አስተሳሰብ እንደዚህ ያለው ምጸታዊ ትችት ሲፈለሰፍ፤ መነገሩ ለዚሁ መሆኑ ግልጽ ነው።

በአባቱ ህልውና ህልው ሆኖ የሚኖረውን የእግዚአብሔርን የባሕርይ ልጅ ዘለዓለማዊ ከሚሆን፤ ከባሕርየ ልደቱ ጽንዕ ስቦ አውርዶ ከፍጡራን ጐን ለመደርደር የታቀደ ደባ መሆኑ የታወቀ አይደለምን? አርዮሳውያን ከጭንቅላታቸው ውስጥ የወልደ እግዚአብሔርን ባሕርየ ልደት ለመውጋት በፍጡራን የጸጋ ልደት መጠጋት ትልቅ የሽፍጥ ዘዴ ነው ብለው አስበዋል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የተጠጉበትን የሸመቁበትን ሽፍጥ የሚያቀልጥ ጽኑና ቀዋሚ ትምህርትን አስቀድሞ አዘጋጅቶላቸው መኖሩን ፈጽመው ዘንግተዋል።

## የወልድ ባሕርየ ልደት በመጽሐፍ ቅዱስ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ያየን እንደሆን የወልድ ባሕርየ ልደት ራሱ ወልደ እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም ተገልጾ፥ ተሰውሮ የነበረውን



የሰማይን ምሥጢር በወንጌሉ በገለጸልን በሐዲስ ኪዳን ዘመን ቀርቶ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንኳ፤ ጭራሹን ሥዉር አልነበረም። ተገልጾ ከተነገረ ቈይቶአል። እርሱንም እንደሚከተለው ለማየት ይቻላል።

ለመረዳት ይቻል ዘንድ በብሉይ ኪዳን በመጽሐፈ ምሳሌ ወይም በመጽሐፈ ተግሣጽ ላይ ም. 30፥2-4። ባለው ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ባጎር በተባለ ጠቢብ ሰው በኩል ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናግሮ ነበር።

## «ስሙ ማነው? የልጁስ ስም ማነው?»

ባጎር ወደ ሰማይ ያረገ የወረደስ ማነው? የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማነው?... ስሙ ማነው? የልጁስ ስም ማነው? አለ።

እነሆም በዚሁ በተነገረው ቃል ላይ፥ ጸጥ ብለን ብንመለከት፤ የፈለግነውን ትምህርት ልናገኝ እንችላለን። ባጎር በዚሁ ገለጻ ከተናገራቸው ቃላት መካከል «ልጅ» የሚለውን ቃል ጠቅሶ የልጁስ ስም ማነው? ብሎአል።

ባጎር «ልጅ» የሚለውን ስም ጠቅሶ የእግዚአብሔር ልጅ ስም መጠራቱ ወይም ሲጠራ መገኘቱ፥ ዋና የነገሩ ማዕከል ሆኖ ሲታይ... ዳሩ ግን ደግሞ በዚሁ ጐን ስሙ ማነው? ብሎ ጠይቆ ከማለፍ በቀር፥ አባት መጠሪያ የአባትን ስያሜ ሳያነሣ የጥቅሱን ዓረፍተ ነገር ማቆሙን እናያለን።

እንግዲህ ባጎር /አጉር/ ልጅ የሚለውን ስም ብቻ ጠርቶ አባት የሚለውን ስም አለማንሣቱ ስለምን ይሆን? ወይስ ምን ማለቱ ነው? ብለን እንድንጠይቅ የአቀራረቡ ሁናቴ ያስገድደናል።

አዎን፥ ባጎር የልጁ ስም ማነው? ብሎ የልጅን ስም ሲጠቅስ ስሙ ማነው? በማለት ብቻ አባት የሚለውን ስም ሳያነሣ ሲቀር የሚያጠያይቅ ነገር እንደጣለብን፤ ግልጽ ነው።

የትምህርተ መለኮት አብነቱ ይኸው ነውና፤ መጠይቃዊ ኀሠሣው አስፈላጊ ነው። ጠቢቡ ባጎር «ልጅ» ብሎ የልጅን ስም ከጠራሁ፤ ጠያቂዎች ከዚያው በሚገኝ ተመርሆ «አባት» የሚልን ስም ያገኙታል። ይኸውም ልጅ የሚል ስም ያለ አባት /አባትን ሳያስከትል/ ብቻውን አይገኝምና ነው። ብሎ እንዳሰበ ነው የሚያሳይ። በእውነቱም ባጎር ልጅ የሚል ስም ጠርቶ ከተናገረ፤ ልጅ ከሚል ስም ጋር አባት የሚል ስም ከዚያው እንዳለ ማወቅና መረዳት አይሳናቸውም፤ ያለ ችግር ያውቁታል ብሎ በጠያቂዎቹ አመዛዛኝ የአእምሮ ኃይል አሳቡን የጣለ ሆኖ ነው የሚታየው።

ባጎር እንዲህም ቢል እውነቱን ነው፤ ከማለት የሚያሸሽ ምክንያት የለም። «ልጅ» የሚል ስም ከተገለጸ «አባት» የሚል ስም ከዚያው ጐን እንደሚገኝ፤ «አባት» የሚል ስም ከተነገረም «ልጅ» የሚል ስም ከዚያው እንደሚያንጸባርቅ

በመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተ ቃላት ጕልቶ የታየ ነውና። ይህም ይታወቅ ዘንድ በዚሁ በባኅር ገለጻ ትይዩ ዮሐንስ በራእዩ ቀጥሎ ያለውን መሰል ቃል ጽፎልን ይገኛል።

እነሆም በዚሁ በዮሐንስ ራእይ በተገለጸው ሁለት ስሞች ተጫፍረው መጻፋቸውን ሲታይ፣ አባት የሚል ስም በአባትነቱ ተጠቅሶ ሲጻፍ ልጅ የሚል ስም ግን ልጅ በሚል ተነግሮ አልተጻፈም። ይሁን እንጂ «ስሙና የአባቱ ስም» ሲባል ስሙ ተብሎ ተጠቁሞአል። ራእይ 14፥1። ይኸውም ስሙ ተብሎ የተጠቆመው ልጁ ለመሆን አያጠራጥርም። አባቱ ተብሎ የተጠራው ስም ያሳውቀዋልና ነው። እነሆም በዚሁ ጥቅስ ስሙና የአባቱ ስም ተብለው ከተጫፈሩት ስሞች መካከል፥ በተለይ ስሙ የሚለው ቃል የሚጠቁመው ማንን እንደሆን አልታወቀምና ልጁን የሚያንጸባርቅ አይደለም፣ ስለ ልጅ አልተነገረም ሊባል አይቻልም። እንዲህ እንደማይባል መጽሐፍ ቅዱስን በተመርሆ ልቡናዊ አሠሣ የሚያጠና የመጽሐፍ ቅዱስን ሰው ያውቀዋልና ነው።

አባት ከተባለ ልጅ እንዳለው ይታወቃል፣ ልጅ ከታወቀም አባት እንዳለው ይታወቃል። ይህም ዕውቀት የስም ዕውቀት ብቻ ሳይሆን ህሉናንም ጭምር የሚያስገነዝብ ነው፣ የዚህንም እርግጥ ይታወቅ ዘንድ አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አባትህ ወዴት ነው? ብለው በጠየቁት ጊዜ፣ ጌታችን መልሶ፣ እኔንም አታውቁም፣ አባቴንም አታውቁም እኔንስ ብታውቁኝ ኖሮ፥ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር ብሎ የመለሰላቸውን አረጋጋጭ መልስ ልናይ እንችላለን። ይህ እውነት ነው። አይሁድ ልጁን ልጅ ብለው ቢያውቁ ኖሮ፥ አባቱን ማወቅ ባልተሳናቸውም ነበርና ነው፣ እርሱን ማወቅ አባቱን ማወቅ መሆኑን መረዳት ያቃታቸው፣ በእምቢታቸው ልባቸውን ስላጨለሙት ብቻ ነው። ዮሐ. 8፥9።

ታዲያ... አርዮሳውያን ወልድን አውቀው አብን ለማወቅ እንዲበቁ ስንመኝላቸው ወልድን አናውቅም በማለት፥ ልባቸውን በእልህ እንዳያጨልሙት አሁን ጊዜ ሳለ፣ እናሳስባቸዋለን። ወልድ ያልተፈጠረ የአብ ልጅ ነው፣ ፍጡራን ግን ከተፈጠሩ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅነት ያገኙት በጸጋ ነው። ፍጡራን መጀመሪያ ተፈጥረው ሲያበቁ፣ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑበትና የተባሉበት የጸጋ ልጅነት፥ ወልድ በባሕርየ ልደቱ የተወለደበትን ልደት ስቦ የባሕርይ ልጅ የሆነ ወልድን ፍጡር ልጅ ሊያደርገው አይችልም የወልድ ልደት የባሕርይ ስለሆነ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም ነውና። ሚክያ. 5፥2። 1ዮሐ. 1፥1።

## የእግዚአብሔር ልጅ የወልድ አባት ዘለዓለማዊ ነው።

የዚሁ ልጅ አባት እግዚአብሔር አብ ከመቼ ዘመን ጀምሮ ኖረ? የልጅ አባት የሆነውስ መቼ ነው? ብለን እንጠይቅ።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው እግዚአብሔር አብ መጀመሪያ ነው መጨረሻም ነው። ባጭሩ ዘለዓለማዊ ነው። «ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አነ ቀዳማዊ ወአነ ደኅራዊ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ።» እግዚአብሔር ይላል



እኔ መጀመሪያ ነኝ፣ እኔ መጨረሻ ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም ኢሳ.43፥10-13። ም. 44፥6።

እነሆም እዚህ ላይ እንደተገለጸው መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ የገዛ ራሱ መጀመሪያና መጨረሻ የሆነ እግዚአብሔር አብ፣ በዘለዓለማዊነት ሕያው እንደሆነ ብቻ የሚታወቅ ነው። 1ዮሐ. 2፥13። የገዛ ራሱ ለዘለዓለሙ ሕያው ነኝ እንዳለ ሁሉ፣ የዘመንና የጊዜ ቍጥር አይነገርለትም። እንዲሁ በዘለዓለም ሕያውነቱ ብቻ እግዚአብሔር አብ እንደሆነና እንደተባለ ይኖራል። ኢሳ. 40፥28። መዝ. 89/90/፥2። ዘዳግ. 32፥40።

እንዲሁ እንደመሆኑ ደግሞ የሚወደው የአንድያ ልጁ አባት እንደሆነ ኖሮአል፣ ይኖራልም። በልጅ በኩል ያለው ነገር እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ወልድም እንደ አባቱ ዘለዓለማዊ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ወልድን «መጀመሪያም ነው፣ መጨረሻም ነው፣ «አነ ውእቱ አልፋ ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ራእይ 22፥13። ም. 18።

እነሆም ያለ፣ የነበረ የገዛ ራሱ መጀመሪያና መጨረሻ የሆነ ወልድ በዘለዓለማዊነቱ ሕያው ሆኖ እንደሚኖር ብቻ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ ታውቆአል። 1ዮሐ. 1፥1። ሚክ. 5፥2። ሮሜ 9፥5። ይኸውም የሚያሳየው ወልድ ለአብ እንዳለው መጠን፥ ዘለዓለማዊነት እንጂ፣ ጊዜና ዘመን የማይቈጠርለት ዘለዓለማዊ አምላክና ዘለዓለማዊ ልጅ በመሆን ጕልቶ መታወቁ ነው። ዮሐ.17፥1-2፤5። ዮሐ. 5፥20። ሮሜ 9፥5። ነቢዩ ሚክያስ «አወጣጡ ከጥንት ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ ብሎ» የተናገረለትን እዚህ ላይ ያስታውሷል። ሚክ. 5፥2።

የዘለዓለም እንደመሆኑ መጠን ያለ ልጅ አብ ወይም አባት ተብሎ እንደማይጠራ ደግሞ ልንገነዘብ ይገባል። ዮሐ. 8፥19። ም. 14፥9-13።

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ማስረጃ ቅደም ተከተል የሌለበት የአብና የወልድ ዘለዓለማዊ አንድነት ካየን ዘንድ፣ ዮሐ. 10፥30። አብ፥ አብ የተባለ እንዴት ነው? ወልድስ ወልድ የተባለ እንዴት ነው።

በዘለዓለማዊነት የኖረ እግዚአብሔር አብ እንዴት አብ ተባለ? ብለን በተመርሆ ልቡና ብንጠይቅ፣ በዘለዓለማዊነት የኖረ እግዚአብሔር አብ አብ መባሉ ልጅ ሳይኖረው አብ ተባለን? የሚል መጠይቃዊ... መልስ ቀርቦልን እናገኛለን።

ይህም በዘለዓለማዊነት የኖረ እግዚአብሔር አብ አብ ተብሎ ያለ ልጅ እንዳልተጠራ እናስተውላለን። እንደዚሁም ሁሉ በዘለዓለማዊነት የኖረ ወልድ ልጅ ሲባል ልጅ ተብሎ ያለ አባት እንዳልተጠራ ማስተዋል በሚቻለን መጠን የምናስተውለው ነው። 1ዮሐ. 2፥23።

ስለዚህ ነው ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር አብ የሚወደው አንድ ዘለዓለማዊ ልጅ ነበረው የምንለው ማር. 12፥6።

ስለዚህ ነው ማንም ከቶ የማያየውን አባቱን የሚተርክ አንድ ልጅ በአባቱ እቅፍ አለ የምንለው።

ይህም እርግጥ ከሆነ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ በማያስተባብሉት ጥሬ ንባብ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ፡- የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው በሚል ዓረፍተ ነገር የሚገኙ በዘርፍ አያያዥ የተያያዙ የሙያ ስሞችም፣ ከዚሁ መሠረት እንደማይወጡ መረዳት ያሻል።

እነሆም «የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው» በሚል ዓረፍተ ነገር የሚገኙትን ስሞች ፍጥረት የሚል ስምን «በኵር» በሚል ትርጉም ለመለወጥ በኵር የሚል ስምንም ፍጥረት በሚል ስያሜ ለውጦ ለመተርጐም ፈጽሞ የማይቻል ነው።

የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው የሚለውን ንባብ እንዲያው በመሰለኝ ተነሥቶ «በኵር ፍጥረት ነው» ብሎ መተርጐም፡- ያ የበሬ ቀንድ ነው ተብሎ የተነገረውን ቀንዱ በሬ ነው ብሎ በችኮላ እንደመንከስ ይሆናል እንጂ በሰዋስው ደንበኛ አዋጅ ፈጽሞ የሚያስኬድ መንገድ የለበትም።

በሰዋስው ደንበኛ አዋጅ እንደዚሁ ካሉ የቃላት አቀማመጥ የተገኘውን እጐት ከሚገኘው የስም ፍች ተለውጦ ያለ ስሙ ስም፥ ያለ ግብሩ ግብር ሲወርስ የሚታይበት ቦታ የለም። አርዮሳውያንም ቢሆኑ እንደዚህ ካለ የቃላት አቀማመጥ ይዞታና ሙያ ውስጥ የሚገኙ ስሞች የሚለወጡበት ሕጋዊ የሰዋስው ማስረጃ ሊያቀርቡ አይችሉም። ካቀረቡም ልናይላቸው ዝግጅዎች ነን። ሄዶ ሄዶም ጉዳዩ እስከዚህ ከደረሰ፣ ታዲያ በቈላስ. 1፥15፣16። በምትገኘው «የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው» ተብላ በተነገረችው ጥቅስ ብቻ ነው ወይ? በኵር በፍጥረት የሚለወጥላቸው? አትለወጥላቸውምና አርዮሳውያን በውል ያስቡበት።

## የሚያፈቅረው አንድ ልጅ ነበረው።

«የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው» እዚህ ጥቅስ ላይ ባለው ኃይለ ቃል፥ ቆም ብሎ ይመለከት ዘንድ፡- የቃላቱንም ይዞታ እንደምን እንዳሉ በጽሞና ይመረምራቸው ዘንድ አድርገን ለተመልካች አንባቢ አቅርበንለታል። ይህን ብሎ የተናገረው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ በመጽሐፍ ያሰፈረው ግን ወንጌላዊው ማርቆስ ነው።

«ወቦቱ አሐዱ ወልድ ዘያፈቅሮ «የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው» ማር. 12፥6።

ሀ/ «አንድያ ልጅ»

ለ/ «የሚወደው»

ሐ/ «ነበረው»

ወንጌላዊው ማርቆስ ስለ ወልድ ሲናገር፣ ሦስት መሠረታውያን መግለጫዎችን ለእግዚአብሔር ልጅ ያቀርብለታል።



1ኛ፥ አንድ የሚል ቅጽል ነው። አንድ ልጅ ይላል አዎን የእግዚአብሔር ልጅ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ብቻውን አንድያ ልጅ ነው። ይህም እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና ተብሎ የተነገረለት፤ እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጅ እርሱ ተረከው ተብሎ በቅዱሳት መጽሐፍት የተመሰከረለት ነው። ዮሐ. 3፥16። ም.1፥14፤18። ቀጥሎ ያሉትንም ተመሳሳዮችን ጥቅሶች ተመልከት። ዮሐ. 3፥18።

አንባቢም «አንድያ ልጅ በተባለ ጊዜ፣ ለልጁም ምን ዓይነት ባሕርያዊ መሠረት እንዳለው ሳይገነዘብ አልቀረም። በጣም ርቆ ሳይሄድ ይህ አንድያ ልጅ በአባቱ ክብር መጠን የሚሆን ክብር እንዳለው፣ እንደዚሁም ማንም ሊያየው የማይችለውን እግዚአብሔርን በአባቱ እቅፍ ያለ አንድያ ልጅ ብቻ የተረከው ወይም የገለጸው መሆኑን፣ በማስተዋል ሳይረዳ እንደማይቀር እናስባለን።

ስለዚህ አንባቢው እንደዚህ ያለው በክብር አባቱን የሚተካከል፥ በአባቱ እቅፍ ሆኖ ማንም ሊያየው የማይችልን አባቱን የሚገልጽ መሆኑን እያየ፣ «ፍጡር ነው» ብሎ ያስባል ብለን አንገምትም።

አዎን፥ መላእክትም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል። ወልድ በኵረ አኃው በተሰኘበት መንገድም፣ ምእመናን የሰው ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች ተሰኝተዋል። ኢዮብ 2፥11። ሮሜ 8፥30።

ይሁን እንጂ፥ ወልድ ለአባቱ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጅ በተባለበት ዘለዓለማዊ ልደቱ አንድ ልጅ እርሱ ብቻ ነው።

2ኛ፥ «የሚወደው» የሚል ቅጽል ነው።

አዎን፡- አብ ልጅን ይወዳል። መጀመሪያ ነገር፥ አንድያ ልጅ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የክብሩ መንጸባረቅ፥ የአካሉም ምሳሌ ነውና ዕብ. 1፥2፣3። ዮሐ. 3፥35፤36። ም. 5፥20። ማቴ. 3፥17። ማር. 1፥11። ሉቃ. 3፥22። ዮሐ. 17፥5፤26።

እነሆም እነዚህን ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን የተመለከተ አንባቢ፥ አብ ልጁን የሚወድበት ፍቅር፥ በባሕርይ ህልውና ልዩ ፍቅር እንደሆነ፣ ለአንድያ ልጅ ብቻ ተቀዳሚና ተከታይ ለሌለው ልጅ ብቻ ለሆነ፥ ያለው ፍቅር መሆኑን ይገነዘባል።

ወንጌላዊው ማርቆስ «የሚወደው አንድያ ልጅ ነበረው» ሲል ከብዙ ልጆች መካከል የተወደደ ልጅ አላለውም። ለአንዱ እግዚአብሔር ያለው አንዱ ሆኖ የሚወደው ይኸው አንዱ ልጁን መሆኑን ነው የገለጸ።

3ኛ፥ «ነበረው» የሚል ግሣዊ አንቀጽ ነው።

የዚሁ «ነበረው» ተብሎ ለተነገረው የግሥ አንቀጽ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ወንጌላዊው ማርቆስ ለእርሱም «ለእግዚአብሔር» «አንድ የሚወደው ልጅ

ነበረው» ሲል ይናገራል። ለእግዚአብሔር የነበረው ምን ነበር? ተብሎ ቢጠየቅ፣ አንድ የሚወደው ልጅ ነበረው ሲል ወንጌላዊው ማርቆስ ይመልሳል።

እነሆም ለእግዚአብሔር የነበረው ልጅ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የማይባል፣ ከዘለዓለም ያለና የነበረ ልጅ መሆኑን ማርቆስ ይገልጻል።

አንባቢም ከዚህ ቀደም ወንጌላዊው ዮሐንስ ሲናገር፣ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ማለቱን ይኸውም ቃል በእግዚአብሔር ህልውና ሆኖ መኖሩን እንጂ የተፈጠረ ነው አለማለቱን ያስታውሳል። ዮሐ. 1፥1-3።

ወንጌላዊ ማርቆስ፥ ቃልን ወልድ በሚል ስሙ ሲገልጸው፣ ለእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነበረው በማለት፥ ከመፈጠር ለይቶ እንዳሳወቀው እናገኛለን።

ስለዚህ፥ ለእግዚአብሔር የሚወደው አንድያ ልጅ ነበረው የሚል ገለጻ ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ካለው ጋር ተጎዳኝቶ ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በአንዱ እግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ መኖሩን አብራርቶ ያስረዳል።

እነሆም ዮሐንስ ቃል ቢለው፣ ማርቆስ ወልድ ቢለው፣ ሁለቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ህልው ሆኖ መኖሩን ብቻ ገልጸዋልና ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት ተቀብለን የወልድን ዘለዓለማዊ ህልውናን ከሚክዱና ፍጡር እያሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ከሚባዝኑት አርዮሳውያን የምንሸሽ ስለዚህ ነው።

## የአብና የወልድ ባሕርያዊ መተዋወቅ።

አሁንም ጌታዬን ወልደ እግዚአብሔርን በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ለባሕርይ አምላክነቱ በመመስከር አከብረዋለሁ።

ይኸውም፡- ስለወልድ ህላዌ መለኮት፥ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስም ስላለው ስለ ህልውና መገናዘብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጹትንና መሠረታዊ ኃይለ ቃል ያለባቸውን ትምህርቶች ባጭሩ በማቅረብ ነው። እርግጥ ነው፡- የተባሉትን መሠረታውያን ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልፍሎ በማውጣት እያንደንዳቸውን በተለያዩ አርእስቶች ቢተነትኑአቸው፥ በየራሳቸው ልዩ ልዩ የትምህርተ መለኮት ማብራሪያ መጻሕፍት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። በመሠረቱ እነዚህን አብነቶች በተለያዩ አርእስት አስፍቶ አምልቶ ለመጻፍ የሚቻልበት ጊዜ ይኖራል፡-

እስከዚያ ግን፥ የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በህላዌ መለኮቱ ስላለው የባሕርይ አንድነትና፥ በአምላካዊ ህልውናም ስላለው መገናዘብ የሚገለጹ መሠረታዊ ኃይለ ቃል ያለባቸውን ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይዞታቸው ምን ያህል የበለጸገ መሆኑን፥ ለትምህርተ መለኮት ሰው ይታየው ዘንድ ብቻ፥ በማጠጋጋትና አጠር አጠር ባለ ገለጻ በዚሁ ክፍለ ትምህርት ለማቅረብ አሰብሁ፡-



ይህን ከገለጽሁ ዘንድ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በራሱ ትርጓሜ የገዛ ራሱን እንዲተረጒም፣ የገዛ ቃላቱን ከቃላቱ ጋር እያነጻጸርሁ በማመልከት፥ በተመርሆ ልቡናዊ እያመዛዘነ ፍትሕን ለሚሰጥ አንባቢ፥ ገለጻዬን ቀጥሎ ባለው ሁናቴ ማቅረቤ ነው። የክፍለ ትምህርቱ መሠረታዊ ቃልም የሚከተለው ይሆናል፡-

«ወልድን ማን እንደሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም። አብንም ማን እንደሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያውቅ የለም» ሉቃ. 10፥22።

ይህን ከዚህ በላይ የተነገረውን ጥቅስ በየጥቂቱ እያመጣጠን በመከፋፈል ጠንቀቅ ብለን ብናጠና፣ የትምህርተ መለኮትን ገለጻ በሚያንቃቃ አኳኋን ለመረዳት ያስችለናል።

ስለዚህ ጥቅሱ በሦስት ረድፍ መድበን፥ በጥያቄ በሐተታ እንመረምረዋለን።

1፥ «ወልድን ማን እንደሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም» በሚለው ላይ፡-

2፥ «አብንም ማን እንደሆነ ከወልድ በቀር የሚያውቅ የለም» በሚለው ላይ፡-

3፥ «ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር፥ ማንም አብን የሚያውቅ የለም» በሚለው ላይ ነው።

እንግዲህ እነዚህን ነው በሦስት ክፍለን አርእስት የምንላቸው፡-

ነገር ግን፡- «ወልድን ማን እንደሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም» በሚለው ትምህርት ላይ ስለሚገኘው አሳብ ምን ገለጻ እንዳለ እንመለከታለን። ከዚሁም በከፊል የሚያውቅ የለም በሚለው ሐረግ ላይ አስቀድመን ብናተኩር መልካም ነው።

አዎን «የሚያውቅ የለም» ተብሎ የተነገረውን ማንን ሲያመለክት ነው? ይህን አጣርቶ ማብራራት ያስፈልጋል።

መቼም «የሚያውቅ የለም» ተብሎ የተነገረው፥ ከአንዲት ህላዌ መለኮት ውጭ ለሆኑት ለተሠሩት ለፍጡራን ወገን የተነገረ መሆኑን ሩቅ ሳንሄድ፣ ለመረዳት እንችላለን «የሚያውቅ የለም» ተብሎ ሲነገር፣ ለፍጥረት ወገን ብቻ እንደሚያሰማ ግልጽ ነውና።

አንዳንድ ሰዎች ግን፣ በዚሁ ጥቅስ የአብና የወልድ መተዋወቅ ሲገለጽ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስም ስላልተጠቀሰ፣ «ማንም አያውቅም» ተብሎ የተነገረው፥ መንፈስ ቅዱስንም እንደሚመለከት አድርገው አስበዋል። ይህ አስተሳሰባቸው ግን፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አሳብ ውጭና የመጽሐፍ ቅዱስን ጠቅላላ እውነት ካለመረዳት የተነሣ የሚወረዛ ስሕተት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ራሱ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ፣ በግልጽ ተመስክሮአል። የሐዋ. 5፥3፤4። 1ቆሮ. 12፥7፤11። የሐዋ. 13፥2፤4። አዎን፥ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የእግዚአብሔር መንፈስ

ስለሆነ፣ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እንደሚያውቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ታውቆና ተገልጾ ያደረ አይደለምን?

መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር፥ ሁሉን ይመረምራልና በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር፥ ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር፥ ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር፥ ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም። የሚለውን ደኅና አድርጎ ማስተዋል ነው። 1ቆሮ. 2፥10፤12።

እነሆም በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር፥ ለእግዚአብሔር ያለው ማንም አያውቅም ተብሎ ተጽፎአልና፣ በዚህ ጊዜ ወልድ ያውቃል ተብሎ አልተጠቀሰምና፣ እንግዲያውስ ወልድም አብን አያውቅም ሊባል ነዋ? የለም፣ አይደለም። ቅን ሰው ሆኖ እንዲህ ብሎ የሚያስብ ያለ አይመስልም። እንደዚሁም ሁሉ ወልድን የሚያውቅ የለም ተብሎ የተነገረው ከባሕርይ መለኮት ውጭ ለሆነው ለማናቸውም ፍጡር ሁሉ እንጂ፣ ለመንፈስ ቅዱስ እንዳልሆነ ጠንቅቆ ያውቃል።

አዎን፥ መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ ህልው እንደመሆኑ፣ የተዋሕዶተ መለኮት ባሕርያዊ ዕውቀት ገንዘቡ ነውና፣ ለእግዚአብሔር ያለውን ጠልቆ ያውቃልና ወልድን የሚያውቅ የለም። ተብሎ ከተነገረላቸው ከማናቸውም ፍጥረታት የሚዳበል አይደለም።

ወልድ ማን እንደሆነ የሚያውቅ የለም የሚባልና መባልም የሚገባው፥ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ህልውና ውጭ ለሆነ ፍጡር ግቡር ለሆነ ፍጥረት ብቻ ነው።

አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስም በሚተዋወቁበት ዕውቀት መካከል ቦታ አግኝቶ ለመግባት ፍጡር፥ ግቡር ለሆነ የተፈጥሮ የተገብሮ ባሕርዩ የማይፈቅድለት ለመሆኑ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ነውና፡-

ስለዚህ ወልድ ማን እንደሆነ የሚያውቅ የለም ተብሎ ሲነገርለት የሚያሰማው፥ ፍጡር ግቡር ለሆነ ለማናቸውም ፍጥረት እንደሆነ፣ በጥብቅ መረዳት ያሻል።

መንፈስ ቅዱስ ግን በእግዚአብሔር ህልውና ተገናዝቦ የሚኖር የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፣ ወልድን ያውቀዋል ስለሚያውቀውም ይመሰክርለታል፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ ራሱ ጌታችን በወንጌል እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱ ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል ብሎአል። ዮሐ. 15፥26። የሐዋ. 5፥32። ስለዚህ «መንፈስ ቅዱስ በባሕርይ ህልውና ወልድን የሚገናዘበው ስለሆነ፣ ያውቀዋል» ብሎ መጽሐፍ ቅዱስን የሚቀበል ሰው ያለ መጠራጠር ያምናል።

እንግዲህ ስለመንፈስ ቅዱስ አቋም ይህን ካየን፣ በዚህ በተጠቀሰው ክፍል ሲነገር የምንሰማው፡- ስለአብና ስለ ወልድ መተዋወቅ ብቻ በመሆኑ፥ መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ ስላለው መተዋወቅ በሰፊው የምናብራራበት አንድ ርእስ



ነገር ከፍተን እስክንገልጸው ድረስ፣ በዚሁ በያዝነው የጥቅሳችን ርእስ፥ የሁለቱን የአብና የወልድ መተዋወቅ እንዴት እንደሆነ፣ አስቀድመን በዝርዝር ለመረዳት ብንሞክር መልካም ነው። ይህም ጠባብና ቀጭን ለሆነ ለሰው አእምሮ የተመጣጠነ የአጠናን ዘዴና ፈሊጥ ነው።

አሁን ወልድን ማን እንደሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም በሚል ዐረፍተ ነገር ላይ በተለይም ለዐረፍተ ነገሩ ባለቤት የሆነ የሚያውቅ የለም የተባለው የተነገረው ከአብና ከወልድ ህልውና ውጭ ስለሚገኙ ፍጡራን እንደሆነ፣ መረዳት አያዳግተንም።

አዎን፥ በእውነቱ ከፍጡራን ወገን ራሱ ወልድ ሳይገለጽለት «ወልድን ዐውቃለሁ» የሚል ይኖር ይሆን? ዮሐ. 7፥28።

ለምሳሌ ከድሮ ጠቢባን አንድ ባጎር የሚባል ጠቢብ የተናገረውን ከብሉይ ኪዳን አቅርበን እንመልከት።

ይህ ሰው፥ ወደ ሰማይ ያረገ የወረደስ ማነው? የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማነው? የልጁስ ስም ማነው? ይህን ታውቅ እንደሆነ ብሎ ጠይቆአል። ምሳሌ. 30፥2፤4።

እነሆም ጠቢቡ ባጎር ማንም ሰው ይህን ከላይ የተነገረውን ያውቅ እንደሆነ፣ ዐውቃለሁ ብሎ እንዲገለጽለት መጠየቁ ነበር። ዳሩ ግን ይህን የሚያውቅና ዐውቃለሁ የሚል ሰው ስላልተገኘ ጥያቄው ከዚያው እንዳለ መልስም አንክሮም ሆኖ ቀርቷል።

ይህም ማለት የሰማይ መላእክትም የአዳም ልጆችም በዚሁ ጥያቄ ቢጠይቁ «ቢጠየቁ» መልሱ እንዲሁ አንክሮ ብቻ እንደሆነባቸው ይኖራል ማለት ነው። ኤፌ. 31፥9፤10።

እንግዲህ ባጎር የልጁ ስም ማነው? ሲል፣ ወልድን ጠርቶ ማንነቱን ግን ለማወቅ እንዳልቻለ ሁሉ፥ ለባዊ ፍጥረት ወልድ የሚልን ስም ሊያውቅ ይችላል፣ በዚሁ የተመርሆ ኅሠሣም ለልጅ አባት እንዳለው ሊያውቅ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ወልድ ማን እንደሆነ፣ ማናቸውም ፍጡር ሊያውቀው አይችልም።

ሌላው ይቆየንና ወልድ በአባቱ ዘንድ ባለው የዕበየ መለኮቱን፥ የግርማ መለኮቱን የጽንዐ መለኮቱን አቋም በየጥቂቱ እያመጣጠን በማቅረብ በፍጡራን ሊገመገም ይቻል ወይስ አይቻል እንደሆነ፣ ሁኔታውን እያመዛዘን በማየት እንሞክር።

እስቲ ከመጽሐፍ ቅዱስ መንሥኤ እያመጣን ከጥሬ ንባቡ ባልተራራቀ የአቀራረብ ገለጻ ወደማመዛዘኑ እንግባ፡-

## ወልድ በአባቱ ዘንድ ያለው መለኮታዊ ዕበይና «ታላቅነት» ግርማ፥ ጽንዕ እንዴት ነው?

1ኛ፥ «ወልድ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። እያለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ቈላስ. 1፥15። እንግዲህ እግዚአብሔር የማይታይ ሲባል

የማይታየው ለማን ነው? ቢሉ፡- ፍጡራን ለሆኑ ለማናቸውም ነው» ከማለት በቀር ሌላ መልስ አለ ይሆን? 1ጢሞ. 6፥16። እንኪያስ ወልድ ለማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ስለሆነ፣ በሥጋ ከመገለጹ በፊት፥ ለማናቸውም ፍጡር አይታይምና፣ ማናቸውም ፍጡር አላየውምና፣ ማናቸውም ፍጡር ስላላየው፣ ወልድንም ማን እንደሆነ አያውቀውም። ዘዳግ.4፥12፣15። ቈላስ. 1፥15፣16።

2ኛ፥ ወልድ ለማይለወጥ እግዚአብሔር ምሳሌው ነው። እነሆም ምሳሌው የሆነ ወልድም የማይለወጥ ነው። ሚልክ. 3፥6። ዕብ. 1፥3፣11፣12። ያዕ. 1፥17። መዝ. 101/102/፥25-27። ዕብ. 13፥8።

ይኸውና ጌታ ሆይ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ። ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ። ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፣ እንደ መጐናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ተብሎ ለተነገረለት እግዚአብሔር በዕበየ መለኮቱ የማይለወጥ መሰሉ ለሆነ ወልድ ተነግሮለት ይገኛል። ዕብ. 1፥11።

ታዲያ እንደልብስ የሚያረጀው እንደ መጐናጸፊያም የሚጠቀለለው ሲለውጠው የሚለወጥ የሚለዋወጥ የሚጠፋ ፍጥረት ነው። አንተ ግን ያው አንተ ነህ የሚሰኘውን የማይለወጠውን ወልድን ማን እንደሆነ ሊያውቀው ይችላልን? የሆነ ቢሆን ማንም ፈጽሞ ሊያውቀው ሊጠነቅቀው አይችልም። ዕብ. 13፥8። ያዕ. 1፥17።

3ኛ፥ ወልድ ማንም በማይቀርበው ብርሃን ለሚኖር እግዚአብሔር ብርሃኑ ነው። ኢሳ. 61፥ ሉቃ. 1፥78፤79። ስለዚህ ማንም በማይቀርበው ብርሃን ለሚኖር እግዚአብሔር ምሳሌ የሆነውን ወልድ ፍጡራን ወገኖች እንኳን ሊያውቁት ሊደርሱበትም አይችሉም። ዮሐ. 12፥45፣46። 1ጢሞ. 6፥16። ሕዝ. 1፥26።

4ኛ፥ ለዚሁ ማንም ለማይቀርበው ማንም ቢሆን ሊቀርበው ለማይቻለው የመለኮታዊ ብርሃን ህሉና «አኗኗር» ወልድ ነጸብራቁ «ፀዳሉ» ነውና ማናቸውም ፍጡር አፍጦ ሊያየው መርምሮ ሊያውቀው አይችልም። ዕብ. 1፥3።

5ኛ፥ የጌታን ልብ ማንም አያውቀውም ተብሎ የእግዚአብሔር ልብ ማናቸውም ፍጥረት ሊያውቀው እንደማይችል በቅዱስ መጽሐፍ ተነግሮአል። ሮሜ 1፥34።

እነሆም ወልድ በእግዚአብሔር ልብ ሕሊናው «የልቡ አሳብ» የተጠነቀቀ ሆኖአል። ታዲያ ይህን ዐውቃለሁ እጠነቀቃለሁ የሚል ፍጡር ይኖር ይሆን? እንደማይኖር እናውቃለን። እንግዲህ ያው ይህን ያላወቀ ፍጡር



ወልድን አላወቀምና ማንም ቢሆን ወልድን ማን እንደሆነ ሊያውቅ አይችልም። 1ቆሮ. 2፥16። ም. 1፥25። ቈላስ. 2፥2፤3።

6ኛ፥ ሁሉን ለሚችል አምላክ ሁሉን በመፍጠር ሥልጣኑ ቃል እየተደገፈ የሚይዝ ወልድ ምሳሌው ነውና፣ ውሱን ሰው ወይም ውሱን የሆነ ፍጥረት ሁሉን በመቻል የማይወሰነውን ወልድን በተወሰነ ሥጋ እስካልተገለጸ ድረስ፣ ማን እንደሆነ ሊያውቀው አይችልም። 1ቆሮ. 8፥6። ዕብ.1፥3።

7ኛ፥ ዓለም በወልድ ተፈጥሮአል፤ በእርሱም ሆነ ዓለም ግን ወልድን አላወቀውም። ዮሐ. 1፥10።

እነሆም ይህ ከዚህ በላይ የቀረበው ማስረጃ ፍጥረት ወልድን ሊያውቅ ያልቻለበትን ምክንያት የሚዘረዝር ሲሆን፣ ወልድ በሥጋ ከመገለጹ በፊት የነበረበትን አኗኗር የሚያሳይ ነው።

በዚህ ደግሞ ፍጥረት የዕውቀት መሥፈሪያ ሊኖረው አይችልምና ባለማወቁም የሚያስደንቅ ነገር የለበትም።

## አብ ግን ወልድን ያውቀዋል።

1፥ አብ በወልድ፥ ወልድም በአብ ህልዋን ናቸውና፣ በዚህ በህልውና መለኮት ጽንዕ ይዞታ አብ ወልድን ያውቀዋል። ዮሐ. 14፥10፤11። ም. 17፥21፤22።

2፥ ወልድ የማይታይ መሰሉ «ምሳሌው» ወይም ለማይታይ ባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ የሚገልጸው ነውና፣ አብ ወልድን ያውቀዋል። ዮሐ. 10፥15።

3፥ አብ የማይጠፋ የማይለወጥ ባሕርይ አለው። ለዚሁ ለማይጠፋና ለማይለወጥ ባሕርዩ ወልድ የማይጠፋና የማይለወጥ ምሳሌው ስለሆነ አብ የማይጠፋና የማይለወጥ ምሳሌው የሆነውን ወልድን ምንም ቢሆን የማይጠፋና የማይለወጥ መሆኑን ያውቀዋል። ዕብ. 1፥3።

4፥ አብ ማንም በማይቀርበው ብርሃን ይኖራል። ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ለሚኖር አብ ወልድ ምሳሌው ነውና፣ ብርሃን የሆነው አብ ምሳሌው የሆነውን ብርሃን ወልድን ያውቀዋል። ኢሳ. 60፥1-3። ቍ. 19፣20። ዮሐ. 12፥46። ም. 1፥9። ሉቃ. 1፥78። ራእይ 21፥23።

5፥ ወልድ የአብ የአካሉ ምሳሌ ነው። ዕብ. 1፥3። ወልድ የአካሉ ምሳሌ ስለሆነ፣ አብ በአካል የሚመስለውንና የሚተካከለውን ወልድን ያውቀዋል። ዮሐ. 10፥30። ቈላስ. 1፥15።

6፥ አብ ለማይታዩት የማይታይ ነው። ቈላስ. 1፥15። እነሆም ለማይታዩት የማይታይ እግዚአብሔር የማይታይ ምሳሌው የሆነውን ወልድን ያውቀዋል። ዘኍል. 12፥8። ዮሐ. 5፥37። ም. 6፥46።

7፥ ወልድ ማንም ሊቀርበው ለማይችል ብርሃን ነጸብራቁ ነው። ዕብ. 1፥3። እነሆም ማንም ሊቀርበው ለማይችል አብ ወልድ ነጸብራቁ ሆኖአልና። ከሌላ ሳይሆን ከገዛ ራሱ ባሕርይ የሚፈልቀውን ነጸብራቅ ወልድን አብ ያውቀዋል። 1ጢሞ. 6፥16።

8፥ ወልድ ማንም ለማያውቀው ለእግዚአብሔር ልብ ቃሉ ነው። አብ ወልድን ቃሉ ሆኖ ከዘለዓለም መኖሩን ያውቀዋልና በዚህ ልቡናው ወይም ዕውቀቱ አብ በእርሱ ዘንድ ህልው ሆኖ የሚኖር ቃሉን ወልድን ያውቀዋል። ሮሜ 11፥34። ኢሳ. 14፥24። ም. 55፥11። ዮሐ. 7፥29።

9፥ አብ የሕይወት ምንጭ ነው፣ ወልድም ከሕይወት ምንጭ የሚፈልቅ የሕይወት ምንጭ እንደሆነ አብ ወልድን ያውቀዋል።

10፥ እግዚአብሔር ባለጠጋ ነው። የሚሳነው ነገር የለም። ሁሉን ቻይ ነው፤ ሁሉ በእርሱ በሚሆን፤ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ ሊሆን በማይችል ባለጠጋና የሚሳነው የሌለው ወልድ ምሳሌው ነውና፣ ለአብ ያለው ሁሉ ለወልድ ገንዘቡ በሆነበት ይዞታ፥ ወልድን ያውቀዋል። ሮሜ 10፥12። ም. 11፥33። 1ዜና መዋ. 29፥12። ዮሐ. 1፥3። 2ቆሮ. 8፥9። ዮሐ. 16፥15።

11፥ እግዚአብሔር የሚያቃጥል እሳት ነው፤ ወልድም ለዚሁ ለሚያቃጥል እሳት ምሳሌ ነውና፣ አብ እንደ ራሱ የሆነውን ወልድን ያውቀዋል። ዘዳግ. 4፥24። ዕብ. 12፥29። 2ተሰሎ. 1፥6፤7።

12፥ ወልድ በእግዚአብሔር መልክ የሚኖር ነው። በዚህ መለኮታዊ መልክ የሚኖረው ወልድ ከአባቱ አንድነት ያለው ነውና አብ ያውቀዋል። ፊልጵ. 2፥6። ዮሐ. 10፥30።

13፥ መንፈስ ቅዱስም የአብና የወልድ መንፈስ ስለሆነ ከአብም ስለሚወጣ፣ ከወልድም የሚነሣ ገንዘቡ ስለሆነ፣ ወልድን ያውቀዋል። ይመሰክርለታልም። ማቴ. 10፥20። ዮሐ. 15፥ 26። ም. 16፥13፡ በጠቅላላው አብ ወልድን በሁሉም ረገድ ያውቀዋል። ይኸውም በባሕርይ በስም፥ በእኩልነት በአካል በግብር በመለኮታዊ ህልውና፥ በተከሥቶ ህልውና ፈጽሞ ያውቀዋል።

## አብን ማን እንደሆነ ከወልድ በቀር የሚያውቅ የለም።

ወልድ አብን ሲያውቅ ፍጡራን ግን አብን ለማወቅ ስላለመቻላቸው፣ ቀጥሎ ባለው በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ማስረጃ እንመለከታለን።

ፍጡራን አብን ሊያውቁ ከማይችሉበት ሁኔታ አንዱ፡-

1ኛ፥ ፍጡራን ከአብ ያልፈለቁ ሆነው የመገኘታቸው ሁኔታ ነው። እንዲያውም ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ወደሚኖር አብ፥ ሊቀርቡ አይችሉም። እነሆም ፍጡራን ስንኳን ከእርሱ ሊፈልቁ ማንም ሊቀርበው በማይችል



ብርሃን ወደሚኖረው አብ ሊቀርቡ አልቻሉምና፣ አብን ሊያውቁ አይችሉም። 1ጢሞ. 6፥16።

ወልድ ግን አብን ያውቀዋል። ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ «ዘውእቱ ፀዳለ ስብሐቲሁ፦ ማለት እርሱ የክብሩ መንጸባረቅ ነው» እንዳለው ሁሉ እርሱ ወልድ የክብሩ መንጸባረቅ ስለሆነ አብን ያውቀዋል። ዕብ. 1፥3።

ሐዋርያው «እርሱ የክብሩ መንጸባረቅ» ሲለው፣ ወልድን ግን እንደሆነ ገልጾታል። ወልድ የዚያ ሊቀርበው ይችል ዘንድ ማንም የማይቃጣበት አብ፥ የዚያ የማይሞትና ጨለማ የሌለበት፤ አብ፥ ለዚያ ከፍጥረት ልዩ ባሕርይ ለሆነና ብርሃን ለሆነ አብ ነጸብራቁ፥ ለዚያ ለጽድቅ ፀሐይ ለአብ ፀዳሉ፥ ወይም ጨረሩ እንደሆነ ነው ያስገነዘበለት። 1ጢሞ. 6፥16። 1ዮሐ. 1፥7። ራእይ 21፥23። ሚልክ. 4፥2። ያዕ. 1፥16፤17።

ሐዋርያው እንዲህ ባለው ኃይለ ቃል ተናግሮ በሚያመለክተን ምሥጢራዊ ትርኢት ምንን ሊያስረዳን ፈልጎ ይሆን? ብለን እንጠይቃለን።

አዎን፥ ሁላችን እንደምናውቀው የፀሐይ ቢሆን የማናቸውም መብራት ፀዳል «ጮራው» ወይም ነጸብራቁ ካለበት ከግዕዘ ጠባይዑ ህሉና፥ ይኸውም ማለት ከፀሐዩ ሆነ ከመብራቱ ዘንድ፥ ወደ ውጭ ወደ አካባቢው የሚፈልቅና ብርሃኑን የሚያስተጋባ ነው እንጂ፣ በመቀራረብ እንደሚጐራበት ወይም በማጣበቂያ እንደሚጣበቅ ባዕድ ነገር መስሎ፥ ከፀሐዩ ሆነ ከመብራቱ የሚገናኝ አይደለም።

አዎን፥ ሁላችን እንደምናውቀው የፀሐይ ቢሆን የማናቸውም መብራት ፀዳል /ጮራው/ ወይም ነጸብራቁ ካለበት ከግዕዘ ጠባይዑ ህሉና ይኸውም ማለት ከፀሐዩ ሆነ ከመብራቱ ዘንድ ወደ ውጭ በመቀራረብ እንደሚጐራበት፥ ወይም በማጣበቂያ እንደሚጣበቅ ባዕድ ነገር መስሎ ከፀሐዩ ሆነ ከመብራቱ የሚገናኝ አይደለም።

ይህም እውነትና እርግጥ በመሆኑ ከፀሐዩ ባሕርያዊ ህልውና ወይም ከመብራቱ ግዕዘ ጠባይዕ በአንድነት እየኖረ፣ ወደ ውጭ ወይም ወደ አካባቢው ሁሉ የሚፈልቅና የሚያንጸባርቅ፥ ድምቀቱንም የሚያስተጋባ ከመሆኑም በላይ፥ «ጮራ ከፀሐይ ሲወጣ» ነጸብራቅ ከመብራቱ ሲያስተጋባ፣ በባሕርይ ህልውናና ህልው ሆኖ ሳይለወጥ መገኘቱን የባሕርይ ሕግ እንደሆነ እናውቃለን።

እርግጥ ነው፥ አንዳንድ ጊዜ ሁለት ስሞች በዘርፍ ተያይዘው ሲነገሩ የምናይ መሆኑ ዕውቅ ነው።

ለምሳሌ፡-የሰው ልብስ ተብሎ የሚነገረውን ፍሬ ነገር ብንወስድ፣ ልብሱን የለበሰው ማን ነው? ቢባል፣ ልብሱን የለበሰው ሰው ሲሆን፣ ልብሱ ደግሞ በሰው የተለበሰ ሆኖ እናገኛለን። እነዚህ ሁለት ቃላት አፍአዊ አቋም ሲታይ ሰው ያው ሰው ነው፤ ልብስም ያው ልብስ ነው።

በነጸብራቅና በመብራት መካከል ወይም በፀዳሉና «በጮራው» በፀሐዩ መካከል ግን እንዲህ አይደለም። ይኸውም የባሕርይ አንድነት ወይም ግዕዘ ጠባይዕ እንጂ፣

በሁለቱ መካከል ባዕድነትና ልዩ የተውሶ የተለብሶ ሁናቴ አይገኝም። ከባዕድነት «ቡዓዴ» ሆነ ከተለጣፊነት «ከተላጽቆ» ፈጽሞ የራቀ ነው።

ሐዋርያው በዚህ ምሥጢራዊ ምሳሌ ወልድን ለዚያ ለማይሞትና ጨለማ ለሌለበት ማንም ለማያየውና ሊቀርበው ለማይቻል «ሊሉየ ባሕርይ»፥ ከፍጥረት ልዩና የተለየ ባሕርይ፥ ከፍጡራን ልዩ ለሆነ ለብርሃን አብ ነጸብራቅ፥ ወይም ለዚያ ለጽድቅ ፀሐይ ለአብ ፀዳሉ «ጮራው» መሆኑን ይገልጸዋል። ዮሐ. 8፥9። ዕብ. 1፥3።

እንባቢ ሆይ፥ ሐዋርያው ምን ማለቱ መሆኑን ቀና በሆነ በተመርሆ ልቡናዊ የተመለከትህ እንደሆነ፤ የወልድ መገኛ ከሌላ ባዕድ ነገር ሳይሆን፤ ለዚያ ማንም ለማያውቀውና ለማይቀርበው፥ ጨለማ ለሌለበትና ለማይሞት ለአንዱ ልዩና ሕያው ባሕርይ ለሆነ ለብርሃን አብ፥ የማይለይ ነጸብራቁ ሆኖ ነው።

ለዚያ ለአርያማዊው የጽድቅ ፀሐይ ለሆነ ለአብ በዘለዓለማዊ ህልውና እውነተኛ ጮራው «ጨረሩ» ነው በማለት ሐዋርያው የሚያቀርበው ገለጻ ለማስተዋል የሚቻልና አስቸጋሪ ያልሆነ ገለጻ ነው።

ነጸብራቅ ከፀሐይ ወይም ከብርሃኑ ፈልቆ ፀሐዩን ሆነ ብርሃኑን ወደ ውጭ እንደሚገልጽ ሁሉ፥ ወልድም ባሕርያዊ መገለጫው ወይም ምሳሌው ሆኖ አብን ያውቀዋልና ይገልጸዋል።

ሐዋርያው ስለ ወልድ ነጸብራቅነት ሲናገር ወልድ ከባሕርየ መለኮት ውጭ ተገኝቶ፥ ለአብ እንዳንጸባረቀለት አይልም። ወልድን የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ ነው ብቻ ይለዋል። ስለዚህ መሠረትም አብ ወልድን ያውቀዋል።

ለፍጡራን ወልድ ካልገለጸላቸው በቀር ወልድን ለማወቅ ስላለመቻላቸውና፦ የአብና የወልድ መተዋወቅ የባሕርይ መተዋወቅ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያቀርበው ስለ «ታላቅነት» መለኮታዊ ትምህርት እዚህ ላይ በመጠኑ ላብራራ እወዳለሁ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም መልኩንም አላያችሁም ብሎ እንደተናገረው ሁሉ፥ በእውነቱ ፍጡራን አብን ሊያውቁት አልቻሉም። ዮሐ. 5፥37።

ወልድ ግን አብን ያውቀዋል። ምክንያቱም ወልድ የገዛ ራሱ የአብ ቃል ስለሆነ፤ የገዛ ራሱም «ከአብ ወጣሁ» እያለ ለአብ ቃልነቱን ስለገለጸ፤ ቃል ሆኖ የተገኘበትንና የወጣበትን አብን ያውቀዋል። ዮሐ. 1፥1። ም. 8፥42።

የቃል ከአብ ዘንድ መገኘትና መውጣት እንደምንድን ነው? የቃል ከአብ ዘንድ መገኘትና ከአብ ዘንድ መውጣት፥ ቃል በልብ ህልው ሆኖ ሲገኝና በነቢብም «በመነገርም» ሲወጣ እንደሚታወቅ ዓይነት አድርገው የሚገነዘቡት ሁናቴ ነው። ኢሳ. 14፥24-27። በዚሁ ትምህርት ልብ ተብሎ ሲነገር፤ አንዳንድ ሰዎች ዛሬ በቀዶ ጥገና ስለሚለዋወጠው ስለ ሥጋ ልብ የሚነገር ይመስላቸው ይሆናል።



የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረተ ኀሳብ ያየን እንደሆነ ግን፤ ልብ ልቡና ሲባል፤ በግዘፍ ስላለው ስለ ሥጋ ልብ ሳይሆን፤ በዐውደ ዕውቀት ስላለ ስለ ለበዎና አሳብ የሚነገረውን ነው የሚያስገነዝበን። አዎን መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ልብ ወይም ልቡና እንደሚለው እናገኛለን። 1ሳሙ. 1ሳሙ. 7። ኤር. 17፥10። አሞጽ 4፥13። ማር. 7፥6። ምሳሌ. 4፥23። መዝ. 50/51/፥ 10፤17። የሐዋ. 13፥22። ቃልም ከዚያ ዘንድ አለ። ኢሳ. 45፥23። ም. 55፥8፤11።

ቃልን ከቀዋሚ ባሕርይ በስተውጭ አግኝቶ አንሥቶ ወይም ቀጥቅጦ እንደሚሠሩበት እንደ መዶሻ ወይም እንደ መጥረቢያ ያለ ነገር አይደለም። ፈጽሞም አይመሳሰልም።

ማንም ቢሆን ለባዊ ነባቢ ነኝ የሚል ሰው ከእርሱ ዘንድ ነኝ፤ ደግሞ ከአብ ዘንድ ወጣሁ እያለ የገዛ ራሱን የሚገልጽን ቃል፥ እንደዚህ አድርጎ ከባሕርየ መለኮት ውጭ በተፈጠሩት መሣሪያዎች አምሳል፤ ቢመስለው፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ፊት ለፊት ይጋጫል። ዮሐ. 7፥29። ም. 8፥42። ም. 16፥28። ም. 17፥8።

ሐዋርያትም ወልድን ከሌላ ሳይሆን፤ ከአብ ዘንድ ወጣ ብለው እንዳመኑበት፤ በእነዚህ ጥቅሶች ተገልጾ እናገኛለን። ዮሐ. 16፥30። ም. 17፥8። በነቢያት በሐዋርያት መሠረት የታነፀች ቤተ ክርስቲያንም ቃል እግዚአብሔር ወልድን፥ በአብ ዘንድ ህልው እንደሆነና ከአብ እንደወጣ ታምናለች። ኤፌ. 20፥22።

የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረተ ኀሳብ ያየን እንደሆነ ግን፤ ልብ ልቡና ሲባል፤ በግዘፍ ስላለው ስለ ሥጋ ልብ ሳይሆን፤ በዐውደ ዕውቀት ስላለ ስለ ለበዎና አሳብ የሚነገረውን ነው የሚያስገነዝበን። አዎን መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ልብ ወይም ልቡና እንደሚለው እናገኛለን። 1ሳሙ. 7። ኤር. 17፥10። አሞጽ. 4፥13፡1 ማር. 7፥6። ምሳሌ. 4፡23። መዝ. 50/51/፥10፤17። የሐዋ. 13፥22። ቃልም ከዚያ ዘንድ አለ። ኢሳ. 45፥23። ም. 55፥8፤11።

እኛም ትክክለኛ በሚሆን በተመርሆ ልቡናን፤ አሳብ ወደ ውጭ የሚያስተጋባ ወይም የሚገልጽ ነው ማለታችን እንግዳን ነገር አፍልቀን መናገራችን አይደለም። ይህ ሁኔታ ምንጊዜም በሰው ሕይወት የሚታወቅና በመጽሐፍ ቅዱስም ገልጾ ያስገነዘበው ነው። ኢሳ. 14፥24። ም. 46፥10። ም. 55፥18። ዘፍጥ. 1፥3። መዝ. 32/33፥6፤9-11።

ከሰው ልብ አሳብ ይፈልቃል። ይህ አሳብ «ሕሊና» ከውስጥ ወደ ውጭ ሲገለጽ ቃል ሆኖ ይወጣል። ወይም ይነገራል።

ሰው ሁሉም እንደሚያውቀው ቃል ከውጭ የመጣ ለልብ እንግዳ የሆነ ነገር ሳይሆን፤ በልብ ህልው ሆኖ የኖረና የልብ አሳብ እሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ የሚገለጽና የሚገልጽ ቃል ነው። አሞጽ. 4፥13።

ምናልባትም ቃል ስንል በዓለማችን ውስጥ በልሳን በአንደበት ስለሚናገሩበት ስለ ቋንቋዊ ቃል ብቻ የሚያስቡ ሰዎች ይኖራሉ።

እኛ ግን ልንገልጸው የምናስበው ስለ ልሳን ወይም ስለ ቋንቋ ቃል አይደለም። እርሱማ ከሰውስ ተነግሮ ቋንቋን በማያውቅ ሰው ረገድ ሳይሰማ ይቀር ይለምን? ቃል እያልን የምንናገረው ስለ እርሱ ብቻ አይደለም።

ለምሳሌ፡- ብዙ ጊዜ በልብህ አስበህ በልሳንህ ወይም በአፍህ ሳትገልጸው ማለት ሳትናገረው ነገር ግን እውስጥህ በአእምሮህ ዐውቀኸው ለጊዜው ያስቀረኸው ወይም ያቆየኸው አሳብ እንዳለህ ወይም እንደነበረህ አታስታውስም ወይ? አዎን ታስታውሳለህ። ብለን እናምናለን፣ ታዲያ ይህን አሳብ ምን ትለዋለህ?

ልብ ስንልም በቀዶ ጥገና ዘዴ የሚለዋወጥ የሥጋ ልብን እያሰብን ሳይሆን፣ ስለ ዕውቀታዊ ልቡና እያሰብን መናገራችንን፥ ለባዊ ሰው ያውቅልናል።

እንግዲህ «እኔ ከእርሱ ነኝና ዐውቀዋለሁ» የሚለው ቃል ከእርሱ የሆነበትን አብን ያውቀዋል የባሕርይ መተዋወቅ ይኸው ነው። ዮሐ. 7፥29።

## አብን ማን እንደሆነ ከወልድ በቀር የሚያውቅ የለም።

ወልድ አብን ሲያውቅ፣ ፍጡራን ግን አብን ለማወቅ ስላለመቻላቸው ቀጥሎ ባለው በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ማስረጃ እንመለከታለን።

ፍጡራን አብን ሊያውቁ ከማይችሉበት ሁኔታ አንዱ፥ ፍጡራን ከአብ ያልፈለቁ ሁነው የመገኘታቸው ሁኔታ ነው። እንዲያውም ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ወደሚኖር አብ ሊቀርቡ አይችሉም። እነሆም ስንኳን ከእርሱ ሊፈልቁ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ወደሚኖር አብ ሊቀርቡ አልቻሉምና፣ አብን ሊያውቁ አይችሉም። 1ጢሞ. 6፥16።

ወልድ ግን አብን ያውቀዋል። ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ «ዘውእቱ ፀዳለ ስብሐቲሁ፡- ማለት እርሱ የክብሩ መንጸባረቅ ነው» እንዳለው ሁሉ እርሱ ወልድ የክብሩ መንጸባረቅ ስለሆነ አብን ያውቀዋል። ዕብ. 1፥3።

ሐዋርያው «እርሱ የክብሩ መንጸባረቅ» ሲለው ወልድን ማን እንደሆነ ገልጾታል። ወልድ የዚያ ሊቀርበው ይችል ዘንድ ማንም የማይቃጣበት አብ፥ የዚያ የማይሞትና ጨለማ የሌለበት፣ ከፍጥረት ልዩ ባሕርይ የሆነ ብርሃን አብ ነጸብራቅ፤ የዚያ የጽድቅ ፀሐይ የአብ ፀዳል ወይም ጨረር እንደሆነ ነው ያስገነዘበለት። 1ጢሞ. 6፥16። ዮሐ. 1፥7። ራእይ 21፥23። ሚልክ. 4፥2። ያዕ. 1፥16፤17።

ሐዋርያው እንዲህ ባለው ኃይለ ቃል ተናግሮ በሚያመለክተን ምሥጢራዊ ትርኢት፥ ምንን ሊያስረዳን ፈልጎ ይሆን? ብለን እንጠይቃለን፡- አዎን፥ ሁላችን እንደምናውቀው የፀሐይ ቢሆን የማናቸውም መብራት ፀዳል «ጮራው» ወይም ነጸብራቁ ካለበት ከግዕዘ ጠባይው ህሉና ይኸውም ማለት ከፀሐዩ ሆነ ከመብራቱ ዘንድ፥ ወደ ውጭ ወደ አካባቢው የሚፈልቅና ብርሃኑን የሚያስተጋባ ነው እንጂ፣ በመቀራረብ እንደሚጐራበት ወይም በማጣበቂያ እንደሚጣበቅ ባዕድ ነገር መስሎ፥ ከፀሐዩ ሆነ ከመብራቱ የሚገናኝ አይደለም።



ይህም እውነትና እርግጥ በመሆኑ፥ ከፀሐዩ ባሕርያዊ ህልውና ወይም ከመብራቱ ግዕዘ ጠባይዕ በአንድነት እየኖረ፣ ወደ ውጭ ወይም ወደ አካባቢው ሁሉ የሚፈልቅና የሚያንጸባርቅ፥ ድምቀቱንም የሚያስተጋባ ከመሆኑም በላይ ጮራ ከፀሐይ ሲወጣ ነጸብራቅም ከመብራቱ ሲያስተጋባ በባሕርይ ህልውና ህልው ሆኖ ሳይለወጥ መገኘቱን የባሕርይ ሕግ እንደሆነ እናውቃለን።

እርግጥ ነው፥ አንዳንድ ጊዜ ሁለት ስሞች በዘርፍ ተያይዘው ሲነገሩ የምናይ መሆኑ ዕውቅ ነው።

ለምሳሌ፡- «የሰው ልብስ» ተብሎ የሚነገረውን ፍሬ ነገር ብንወስድ ልብሱን የለበሰው ማን ነው? ቢባል፣ ልብሱን የለበሰው ሰው ሲሆን፣ ልብሱ ደግሞ በሰው የተለበሰ ሆኖ እናገኛለን። እነዚህም ሁለት ቃላት አፍአዊ እንጂ ውስጣዊ የባሕርይ ግንኙነት የላቸውም። ዘወትር እንደምናውቀው ሰው ያው ሰው ነው። ልብስም ያው ልብስ ነው።

በነጸብራቅና በመብራት መካከል ደግሞ በፀዳሉና «በጮራው» በፀሐዩ መካከል ግን እንዲህ አይደለም። ይኸውም የባሕርይ አንድነት ወይም ግዕዘ ጠባይዕ እንጂ፣ በሁለቱ መካከል ባዕድነትና ልዩ የተውሶ የተለብሶ ሁናቴ አይገኝም። ከባዕድነት «ቡዓዴ» ሆነ ከተለጣፊነት «ከተላጽቆ» ፈጽሞ የራቀ ነው።

ሐዋርያው በዚሁ ምሥጢራዊ ምሳሌ ወልድን የዚያ የማይሞትና ጨለማ የሌለበት ማንም ለማያየውና ሊቀርበው ለማይቃጣ ሊሉየ ባሕርይ ከፍጡራን ልዩ ለሆነ ብርሃን አብ፥ ነጸብራቁ፥ ወይም ለዚያ ለጽድቅ ፀሐይ ለአብ ፀዳሉ «ጮራው» መሆኑን ይገልጸዋል። ዮሐ. 1፥8፤9። ዕብ. 1፥3።

አንባቢ ሆይ፥ ሐዋርያው ምን ማለቱ መሆኑን ቀና በሆነ በተመርሆ ልቡናዊ የተመለከትህ እንደሆነ የወልድ መገኛ ከሌላ የተገኘ ባዕድ ነገር ሳይሆን ወልድ ራሱ ለዚያ ማንም ለማያውቀውና ለማይቀርበው ጨለማ ለሌለበትና ለማይሞት ለአንዱ ልዩና ሕያው ባሕርይ ለሆነ ለብርሃን አብ፥ የማይለይ ነጸብራቁ ነው።

ለዚያ አርያማዊው የጽድቅ ፀሐይ ለሆነ ለአብ በዘለዓለማዊ ህልውና እውነተኛ ጮራው «ጨረሩ» ነው በማለት ሐዋርያው የሚያቀርበው ገለጻ ለማስተዋል የሚቻልና አስቸጋሪ ያልሆነ ገለጻ ነው።

ነጸብራቅ ከፀሐይ ወይም ከብርሃኑ ፈልቆ ፀሐዩን ሆነ ብርሃኑን ወደ ውጭ እንደሚገልጽ ሁሉ፥ ወልድም ባሕርያዊ መግለጫው ወይም ምሳሌው ሆኖ አብን ያውቀዋል ይገልጸዋልም።

ሐዋርያው ስለ ወልድ ነጸብራቅነት ሲናገር ወልድ ከባሕርየ መለኮት ውጭ ተገኝቶ ለአብ እንዳንጸባረቀለት አይልም። ወልድን የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ ነው ብቻ ይለዋል።

ፍጡራን አብን ሊያውቁ የማይችሉበት ሌላ ምክንያት ደግሞ፥ ከእርሱ ማለት ከባሕርዩ ያለመሆናቸው ነው።

«ከፍጡራን ወገን አብን ማን እንደሆነ የሚያውቀው የለም» ሲባልና ወልድ ግን አብን ስለሚያውቅበት ባሕርያዊ ይዞታ ከዚህ አስቀድመን እንደተመለከትነው ከመጽሐፍ ቅዱስ በተገኙ ማስረጃዎች የተብራሩ መግለጫዎችን አግኝተናል።

አሁንም የትምህርተ መለኮትን መሠረታዊ ይዞታ በምናስተውልበት ረገድ ከቅዱሳት መጻሕፍት በሚገኙ መመሪያዎች ጥናታችንን እንቀጥላለን።

ይኸውና ፍጡራን በየራሳቸው ከዘመናት በአንድ ዘመን፥ ከጊዜያትም በአንድ ጊዜ ካለመኖር ወደ መኖር ሲመጡ፣ በቃሉ ተፈጥረው እንጂ፣ ከራሱ ከባሕርያዊ ህልውናው ተገኝተው አይደለም። ከጊዜያት በአንድ ጊዜ ከዘመናት በአንድ ዘመን ሲመጡም፣ ኋኝ ሆነው ካለመኖር ወደመኖር ካለመታየት ወደመታየት ተፈጥረው ተሠርተው የመጡ ወይም የተገኙ ናቸው።

ስለዚህ ከእርሱነቱ ሳይፈጠሩ የመጡ አይደሉምና፣ ዘለዓለማዊ አብን ሊያውቁት አይችሉም።

ለ/ ወልድ ግን አብን ያውቀዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «እኔ ከእርሱ ዘንድ ነኝና፣ ዐውቀዋለሁ» ብሎ ከነምክንያቱ ገልጾአል ዮሐ. 7፥29።

ከነምክንያቱ ሲባል፡- «እኔ ከእርሱ ዘንድ ነኝና ማለቱ ነው የሚል የዐረፍተ ነገር ሐረግና» ዐውቀዋለው ላለው ምክንያታዊ ማስረጃ እንደሆነ ዕውቅ አይደለምን?

እኔ የምገኘው ከእርሱ ዘንድ ስለሆነ፣ «ከእርሱ ከባሕርዩ ነኝ» ከማለት በቀር፥ ሌላ ብሂል እንደሌለበት ግልጽ ነው። ከእርሱ ዘንድ ከባሕርዩ ነኝ እንጂ፣ ከሌላ አልተገኘሁም» ማለት ነው።

ይህም አባባል እንደፍጡራን ካለመኖር ወደመኖር ተፈጥሮ እንዳልመጣ የማያጠራጥር ማስረጃ ሲሆን፣ ከእርሱ ከአብ ዘንድ ሆኖ የመገኘቱ አቋም፥ መለኮታዊ የባሕርይ ህልውናን የሚያስገነዝብ ገለጻ ነው።

አዎን፥ ሌሎች ተፈጥረው ነው። እርሱ ግን ከአብ በባሕርይ ህልውና ተገኝቶ ነው። ይህም ከፍጡራንና ከእርሱ መካከል ያለውን የተራራቀ ልዩነት ያስገነዝባል። ዳግመኛም ወልድ ተብሎ ለተጠራበት ለተረከቦ ስሙም መሠረታዊ መግለጫ ነው።

ስለዚህ በዚሁ ገለጻ የባሕርይ ህልውና አንድነት እንጂ፣ ወልድ ከዚህ ውጭ የሆነ ሌላ መነሻ እንደሌለበት አስረድቶአል።

በሌላ ገለጻ «ከእርሱ ዘንድ ነኝና ዐውቀዋለሁ» ሲል አብ በሚያውቀኝ ዕውቀት አብን ዐውቀዋለሁ በማለት የህልውናን መተዋወቅ አስገንዝቦአል። አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን ዐውቀዋለሁ። ዮሐ. 10፥14፣15።



በሌላ ስፍራም «እኔና አብ አንድ ነን» በማለት ተናግሮ እንደነበረ ይታወሳል። ዮሐ. 10፥30።

«እኔና አብ አንድ ነን» ማለቱም የአካላት የጋርዮሽ አንድነትን ማስረዳቱ ነበረ። በዚሁ ጥቅስ ከእርሱ ዘንድ ነኝና ብሎአል እንጂ፣ ከእርሱ ጋር ነኝ አላለም። አስተውል።

ይኸውም ዐውቀዋለሁ ሲል ለተናገረበት ምሥጢር ዕውቀቱ መገኛው አብ ከመሆኑ የተነሣ እንደሆነ፣ ለይቶ ለማሳወቅና ለመግለጽ መፈለጉን የሚያሳይ ነው። በዚሁ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ከአብ ጋር ነኝ ብሎ አለመናገሩም፣ ይህን ከሌላ ቦታ ገልጾታልና፣ ወልድ ከአብ ጋር ያለው አንድነት በአካል የጋርዮሽ አንድነት ብቻ ሳይሆን፣ ወልድ ዋዌ «አጫፋሪ» በማይታይበት በአብ ዘንድም፥ ህልው ሆኖ፥ ከአብ ባሕርይ ባለመለየት መገኘቱን ብሩህ አድርጎ ለማስገንዘብ ነው።

መቼም ከአብ ዘንድ መገኘት አብን ለማወቅ እንዴት መሠረት ይሆናል? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። ጥያቄው ደገኛ /መልካም/ ጥያቄ ነው።

ለዚሁ የሚሰጠው መልስ እኔ ከእርሱ ዘንድ ነኝና ዐውቀዋለሁ ብሎ የተናገረው ጌታ ራሱ ነው። እንመርምር ካልን ደግሞ ወልድ ከእርሱ ይኸው ማለት ከአብ መገኘት የራሱን ባሕርይ ማወቅ ስለሆነ፣ እንዲያውም ከዚህ የሚበልጥ ለማወቅ የሚቀርበው ምንም ነገር እስከማይኖር ድረስ ወሰኖ የሚያሳይ ዕውቀት ሆኖ ይገኛል።

ፍጡራን አብን ከማወቅ የሚወስኑአቸው መሠረታውያን ግዴታዎችና ወልድ ግን አብን ከማወቅ የማይገታባቸውን ባሕርያውያን ግን ይዞታዎች ያሉ በመሆኑ ነው።

እነዚህ ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚገኙባቸው ክፍሎች በዝርዝር አቅርበን በኀሠሣ ተመርሆ ልቡናዊ ብናብራራቸው የትምህርተ መለኮትን መሠረታዊ ይዘት ያሳዩናል።

ፍጡራን አብን ከማወቅ የሚያግዱዋቸው ግዴታዎችና ወልድ ግን አብን ከማወቅ የማይወሰንባቸው፣ ባሕርያውን ግን በዝርዝር እነሆ፡-

1ኛ፥ ፍጡራን በቃሉ የተፈጠሩና የተሠሩ ሥራው እንጂ፣ ከባሕርዩ የተገኙ ቃሉ አይደሉም። ወልድ ግን የአብ ቃሉ ነው። መዝ. 32/33/፥6። ዮሐ. 1፥1።

2ኛ፥ ፍጡራን በተወሰነ ጊዜና ዘመን ካለመኖር ወደመኖር ኋኝ ሆነው የመጡና የተፈጠሩ ናቸው። ወልድ ግን ከእርሱ ከራሱ ከአብ በዘለዓለም ህልው ሆኖ የኖረ ነው። ዕብ. 11፥3። ዮሐ.1፥1።

3ኛ፥ ፍጡራን ማንም ሊቀርበው ወደማይችል ወደ አብ ሊደርሱ አይችሉም። ወልድ ግን የአብ የክብሩ መንጸባረቅ ነው። 1ጢሞ. 6፣16። ዕብ. 1፥1-3።

4ኛ፡ እንዲሁም እኔና አብ አንድ ነን ባለው መሠረት በአካል ተተካክሎ በባሕርይ ህልውና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በህልውና ስለሚኖር ነው። ዮሐ. 10፥30። ዕብ. 1፥3።

## ፍጡራን አብን አያውቁትም።

ከዚህ በላይ ፍጡራን አብን የማያውቁባቸው መሠረታውያን ግዴታዎች እንዳሉና፦ ወልድ ግን አብን የሚያውቅበት ቀዋሚ ዕውቀት የባሕርዩ ስለመሆኑ እየተነጋገርንበት መጥተናል።

በመሠረቱም፦ ፍጡራን አብን ለማወቅ የማወቅ ብቃት ከማያገኙባቸው ነገሮች አንዱ፤ ቀጥሎ ያለውን እንመለከታለን።

ይኸውም ፍጡራን በቃሉና በመንፈሱ ከእግዚአብሔራዊ ህላዌው በስተውጭ ተፈጠሩ እንጂ፤ ከባሕርዩ አልመጡም አልተወለዱም። መዝ. 32/33/፥6-9። ኢዮብ 26፥13። ም. 33፥4። ዮሐ. 15፥26።

ስለዚህ ፍጡራን፤ አብን ማን እንደሆነ ማወቅ ይሳናቸዋል። ኢዮብ 36፥26። ወልድ ግን ያውቀዋል ምክንያቱም አባቱ ነውና፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ፦ አይሁድ ጌታ ኢየሱስን «አባትህ ወዴት ነው?» ብለው በጠየቁት ጊዜ፤ የመለሰላቸውን መልስ በጥንቃቄ ብንመለከት እንረዳዋለን።

እንዲሁም ደግሞ፦ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው። አላወቃችሁትም። እኔ ግን ዐውቀዋለሁ ብሎአል። ዮሐ. 8፥55።

እዚህ ላይ ልብ ብለን ብናስተውል፦ እናንተ አምላካችን ነው የምትሉት የማታውቁት፤ እኔ ግን አባቴ መሆኑን አውቃለሁ። ማለቱን ልንገነዘብ አይገባንምን?

በዚሁ አንጻር ወይም ትይዩ ደግሞ፦ ወልድ አብን ማወቁ፤ የሚያስደንቅ አይደለም። ምክንያቱም በህልውና ህልው ሆኖ የሚኖርበት፤ ከእርሱ ዘንድ የወጣበትና የተገኘበት ባሕርዩ ከወዴት እንደሆነ ስለሚያውቅ ነውና፤ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለዚህ ሲናገር፤ «ከወዴት እንደመጣሁ ወዴት እንደምሄድ ዐውቃለሁና» ብሎ በመናገሩ ገልጾታል። ዮሐ. 8፥14። ዳግም እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና ብሎአል። ዮሐ. 8፥42። ም. 16፥27፤28።

እንግዲህ ከወዴት እንደመጣ የባሕርዩን ምንጭ የሚያውቅ ወልድ፦ ፍጥረት በማያውቀው አኳኋን ተወልዶ በወልድነቱ «በልጅነቱ» አባቱ አብ መባሉን የገለጸ ወልድ ዘለዓለማዊ መለኮታዊ የሆነውን አብን በዚሁ ሁሉ ያውቀዋል። ባጭሩ ልጅ ያለው አባት እንዳለው፤ የታመነ ነውና፤ ቅደም ተከተል በሌለበት በዘለዓለማዊ ቅድምና በመወለድ አባቱን የገለጸ ወልድ አከሉ መሰሉ የሆነውን አብን ያውቀዋል። የባሕርይ ዕውቀት ይሏል ይኸው ነው። ምሳሌ 34፥4። መዝ. 2፥7። ዕብ. 1፥3።



በማየት ይዞታ ፍጡራን አብን ለማየት ስላለመቻላቸው።

ማንም ሊያየው ወደማይችል ወደ አብ፤ ፍጡራን ስላለመድረሳቸው መሆኑን ከዚህ አስቀድመን ሳንነጋገርበት አልቀረንም።

በዚህ ጊዜ አብን ስለማወቅ ሁኔታ በሚመለከት ነጥብ፥ በወልድና በፍጡራን መካከል ያለውን ልዩነት እያነጻጸርን በምናስተያይበት ጊዜ፤ ፍጡራን አብን ሊያዩት ስላለመቻላቸው፤ ይልቁንም ወደዚሁ ማየት እንኳ ሊደርሱ ስላለመቻላቸው አቅርበን ብንነጋገርበት በይበልጥ እንደሚብራራልን የሚታመን ነው።

አዎን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ፍጡራን አብን ሊያዩ እንዳልቻሉና፤ እንደማይችሉ፤ ማየታቸው ይቅርና ማንም ሊያየው ወደማይችል አብ ከቶ ሊደርሱ እንደማይቻላቸው ተነግሮና ተገልጾ ይገኛል። ዮሐ. 1፥18። 1ጢሞ. 6፥15፤16።

እንግዲህ ፍጡራን አብን ያውቁታል? ወይስ ሊያውቁት አይችሉም? በሚል ጥያቄ ላይ ስንመረምር ፍጡራን አብን ሊያዩት ያልቻሉበት ምክንያት አለመቻላቸውን፥ ስናይ፤ ምን እንላለን? መልስ ሆኖ የሚቀርብን መጀመሪያ ነገር ፍጡራን መቼ አዩትና ነው? ማየታቸው ይቅርና እንዲያውም ወደ እርሱ መቼ ይቀርቡና ነው? የሚል ይሆናል።

አዎን፥ ለማወቅ አስቀድሞ ማየት፥ ለማየት ደግሞ አስቀድሞ ወደ እርሱ መጠጋት መቅረብ፤ ከሆነም አይቀር ከዚያው መገኘት፥ በቅድሚያ አስፈላጊ አልነበረምን?

ስለዚህ ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገልጽ፦ «አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእርሱ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር እርሱ አብን አይቶአል።» ብሎ እንደተናገረ ይታወሳል። ዮሐ. 6፤46።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብን ለማየት አስቀድሞ መሆን ያለበትን ነገር ሆኖ መገኘት እንደሚገባ ገልጾአል። ይህም መጀመሪያ ነገር ከእርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ መገኘት ነው። ከእርሱ ከእግዚአብሔር የሆነ እርሱ አብን አይቶአል።

ከእርሱ ከእግዚአብሔር ካልሆነ ግን ማንም ይሁን ማን አብን አላየም። ዮሐ. 6፥4፤6።

ስለዚህ ማንም ይሁን ማን ከእርሱ ዘንድ ካልሆነ፤ አብን ለማየት እንደማይቻለው ይህ ኢየሱስ የተናገረው ቃል በቁርጥ ወስኖ ያሳየናል።

እንግዲህ ከእርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ የተባለው ማነው? ከልጁና ከቅዱስ መንፈሱ በቀር፥ ማን ሊሆን? መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ዘንድ በህልውና የሚኖሩና ከእርሱ ዘንድ የሚሆኑ ቃሉና፥ መንፈሱ እንደሆኑ ይገልጽልናል። እነሆም እግዚአብሔርን ሊያዩ የሚችሉ ቃሉና መንፈሱ ብቻ እንደሆኑ ግልጽ አይደለምን? መዝ. 32/33/፥6።

ደግሞ ከእርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያልሆኑስ እነማን ናቸው? ብለን እንጠይቃለን? በውኑ ከእርሱ ከእግዚአብሔርነቱ ህላዌና ባሕርይ ያልሆኑ ከፍጡራን ወዲያ ሌላ ይኖራልን? በእርግጥ ያለ ጥርጥር ከእርሱ ከእግዚአብሔርነቱ ህላዌና ባሕርይ ያልተገኙ ፍጡራን ብቻ መሆናቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ተመርሆ እናውቃለን። ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም። ዮሐ. 1፥3።

ይህም ከሆነ፥ ፍጡራን አብን ለማየት ያልቻሉበት ምክንያት ግልጽ ሆኖ እየታየን ይመጣል።

1፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ «ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር ማንም አብን ያየ የለም» እንዳለው ሁሉ፦ ፍጡራን አብን ለማየት አለመቻላቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ስላልሆኑ ነው። መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም። በአባቱ እቅፍ ያለ፥ አንድ ልጅ እርሱ ተረከው። ዮሐ. 1፥18። ም. 6፥4፤6።

2፥ እንዲያውም ሐዋርያው ጳውሎስ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል። አንድ ሰው ስንኳ አላየውም እንዳለው ሁሉ ፍጡራን ሊቀርቡትና ሊያዩት ስለማይችሉ ነው። 1ጢሞ. 6፥16።

እዚህ ላይ አብን ያየ ማንም የለም ሲል ማንን እያመለከተ የተናገረው ነው? ብለን እንጠይቃለን። «አብን ያየ ማንም የለም» ሲል ከፍጡራን ወዲያ፣ ማን ይሆናል? ያው አብን የማያዩ የተፈጠሩ ፍጡራን ናቸው። ዘጸአ. 33/20፤23።

ሐዋርያው ጳውሎስ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል። አንድ ስንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም። ብሎአል። ወልድ ግን የዚሁ ብርሃን ነጸብራቅ ነው። ዕብ. 1፥3።

**አሁን ደግሞ «ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር፥ አብን የሚያውቅ የለም ብሎ» ጌታችን በተናገረው ላይ፥ ምርመራና ጥናት እናደርጋለን። ወልድ ሊገልጥለት ካልፈቀደ በቀር፥ ማንም አብን የሚያውቅ የለም።**

በመጽሐፍ ቅዱስ በአብና በወልድ መተዋወቅ ስላለው የተዋሕዶተ መለኮት ቀዋሚነት ከዚህ በላይ በወሰድነው ትምህርት ተመለከትን።

እነሆም በዚሁ ገለጻ ለማንም ቢሆን ወልድ ሊገልጽለት ካልፈቀደና ካልገለጸለት በቀር፥ አብንና ወልድን ለማወቅ እንደማይቻል፣ ግልጽ ሆኖ ተነግሮ እናገኛለን። የአብን ሆነ የወልድን ማንነት ለማወቅ የሚቻለው፥ ወልድ ሲፈቅድና ሲገልጽ ብቻ ነው።

ይኸውም፥ ፍጡር የሆነ ሁሉ አብንና ወልድን እንዲያውቅ፥ የሚገልጽና ሊገለጽለትም የሚፈቅድ ወልድ ስለሆነ፣ ከእርሱ ዘንድ ካልተሰጠና ካልተገኘ በቀር፥ ይህ እውቀት በምንም በማናቸውም ሊገኝ የማይቻል መሆኑን፥ ለይቶ ያስገነዘበናልና ነው።



በዚህም ጊዜ ከፍጡራን ወገን ለሆነ ሁሉ፥ አብንና ወልድን እንዲያውቅ ወልድ ሊገልጽለት ባይፈቅድስ እንዴት ይሆናል? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። መልሱ ግን ሩቅ አይደለም፤ ወልድ አብን ማን እንደሆነ ያውቅ ዘንድ ለማንም ሊገለጽ ባይፈቅድና ባይገልጽለት፤ ማንም ማን ይሁን ሳያውቅ ይቀራል እንጂ፣ ማንም በገዛ ራሱ ተነሥቶ አብንና ወልድን ሊያውቅ አይችልም።

ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ሊገልጽለት ከሚፈቅድ በቀር፥ አብን ሆነ ወልድን የሚያውቅ የለም ብሎ የተናገረው ኃይለ ቃል ጽኑዕና እሙን እንደሆነ ይቆማል። ምክንያቱም ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንጂ፣ ቃሉ አያልፍምና ነው። ማቴ. 24፥35። ዮሐ. 8፥14።

አሁንም በዚሁ ገለጻ ላይ፥ ሌላ ጥያቄ ይኖራል። ይኸውም ከፍጡራን ወገን አብንና ወልድን እንዲያውቅ፣ ወልድ ሊገልጽለት ባይፈቅድና ባይገልጽለት፥ አብና መንፈስ ቅዱስ አይገለጹለትምን? የሚል ነው።

መልሱ አዎን፥ አብንና ወልድን እንዲያውቅ ወልድ ሊገልጽለት ባይፈቅድና ባይገለጽለት፥ አብና መንፈስ ቅዱስ አይገለጹለትም። ምክንያቱም አብን ሆነ ራሱን «ወልድን» ለፍጡራን የሚገልጽና የሚፈቅድ ወልድ ሆኖአልና ነው።

ይህንንም ስንል ከመጽሐፍ ቅዱስ በተገኘው ማስረጃ እንጂ፣ ከኅሳባችን አንቅተን አይደለም። ኢሳ. 48፥16።

1ኛ፥ እነሆም አብ ወልድ ሊገልጽለት ለፈቀደው እንዲገልጽ ፈቃዱ ለመሆኑ፥ ራሱም አብ በወልድ እንዲገለጽ እንጂ፣ በሌላ በኩል እንዲገለጽ ፈቃዱ ላለመሆኑ፥ አክብሮ መስክሮ እንዳስታወቀለት እናገኛለን። ዮሐ. 8፥54። ሉቃ. 9፥49። ዮሐ. 12፥28።

ጌታችን በወንጌል ስለዚህ ሁናቴ በተናገረበት ርእስ፥ አዎን አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና፣ ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል ብሎ ተናግሮአል። ማቴ. 11፥26። ዮሐ. 17፥10።

2ኛ፥ መንፈስ ቅዱስም ወልድን ያከብረዋል። ስለዚህ ወልድ ሊገልጽለት ለፈቀደው ከወልድ ወስዶ ይገልጽለታል እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ያልወሰደውን ከገዛ ራሱ ለማንም አይገልጽለትም ሊገልጽለትም አይፈቅድም። የሐዋ. 2፥33። ዮሐ. 14፥26። ም. 15፥26። ዮሐ. 5፥32።

የእውነት መንፈስ ከገዛ ራሱ አይናገርምና፣ የሚመጣውንም ይነግራችኋል እርሱ ያከብረኛል። ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና፣ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው። ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ። ዮሐ. 16፥13፤15። ኤፌ. 1፥13።

ስለዚህ ወልድ ሊገልጽለት ለፈቀደው፥ መንፈስ ቅዱስ ሊገልጽለት ይፈቅዳል እንጂ፣ ወልድ ሊገልጽለት ላልፈቀደ፥ መንፈስ ቅዱስ ሊገልጽለት አይፈቅድም። ዮሐ. 15፥26። የሐዋ. 1፥4። 5፤8። 1ቆሮ. 12፥3። ገላ. 3፥5።

እንግዲህ እላይ እንዳየነው አብ ራሱን በወልድ እንዲገልጽ፣ ወልድም አብን ሆነ ወልድነቱን ሊገልጥለት ለፈቀደ እንዲገልጽ፣ አብ ፈቅዶአል። መንፈስ ቅዱስም ወልድ ሊገልጥለት ለፈቀደ እንዲገልጽ ፈቃዱ ሆኖአል። 1ቆሮ. 12፥3-11።

ወልድም ለማንም ቢሆን አብንና ራሴን እንዲያውቅ የምገልጽና የምፈቅድ እኔ ከሆንሁ፣ ለመግለጽ ባልፈቅድስ ምን አለብኝ? ብሎ በእርሱነቱ «በወልድ» በኩል እንዲገለጽ ፈቃዱ የሆነውን አብን የሚጨቁን ሳይሆን፣ አብ በልጁ ሊገለጽ በፈቀደበት ጊዜ ሁሉ፥ ወልድ ለመግለጽ ይፈቅዳል።

ራሱ ወልድ እኔ ዘወትር ደስ የሚያሰኘውን አደርጋለሁና አብ ከእኔ አይለይም። የላከኝን ፈቃድ እንጂ፣ ፈቃዴን አልሻምና፣ ሲል እያረጋገጠ ከአብ ፈቃድ የተለየ ሌላ ፈቃድ እንደሌለው ገልጾ የለምን? ዮሐ. 5፥20። ም. 6፥38።

እነሆም አብ በወልድ እንዲገለጽና ወልድም ሊገለጽለት ለፈቀደው እንዲገልጽ ፈቃዱ ሲሆን፣ ወልድም አብ በፈቀደው ፈቃድ መሠረት አብንና ራሱን ከመግለጽ በቀር፥ ሌላ ፈቃድ የሌለው መሆኑን፥ ኃይለ ቃሉ ግልጽ አድርጎ ያብራራል። መንፈስ ቅዱስም አብ በወልድ እንዲገለጽ የፈቀደው ፈቃድና ወልድም ለፈቀደለት እንዲገለጽ የሚፈቅደውን ፈቃድ አክብሮ ፈቅዶአል። እነሆም በዚህ የሦስቱ ፈቃድ አንድ እንደሆነ ይታያል።

እንግዲህ ይህ ዞሮ ዞሮ የተዋሕዶተ መለኮት አንዲት ፍጽምት ፈቃድ ብቻ ሆና መገኘትዋን ተጨባጭ አድርጎ የሚያስገነዝብ ነው። ሮሜ 11፥36። ኤፌ. 2፥18። 1ቆሮ. 12፥4፤8።

በዚህም የሥሉስ ቅዱስ እግዚአብሔራዊት ፈቃድ እንደ መሆንዋን በአንዲት የእግዚአብሔር ህልውናም ሦስት ፈቃድ የሚባል ነገር የሌለና፣ የማይኖር መሆኑን ለማየት ይቻላል። 2ቆሮ. 1፥20-22። ኤፌ. 2፥18። 2ቆሮ. 13፥14።

1፥ ከዚህ ጋር ወልድ ራሱን አብን ለሚፈቅደው የሚገልጽ መሆኑ፥ ከጊዜ በአንዱ ጊዜ የመጣለት ሳይሆን፣ የመለኮት ህልውና ዘለዓለማዊ ባሕርያዊ ግብር ነው።

2፥ አብም በወልድ እንዲገለጽ መሆኑና መፍቀዱ፥ ከጊዜያት በአንዱ ጊዜ የመጣለት ሳይሆን፣ የመለኮት ህልውና ዘለዓለማዊና ባሕርያዊ ግብር ነው። ማቴ. 11፥26።

3፥ መንፈስ ቅዱስም፥ በወልድ እንዲገለጽ በመፍቀድና የሚገለጽ መሆኑ፥ ወልድም አብንና ራሱን ያውቅ ዘንድ ለፈቀደለት እንዲገለጽ ፈቃዱ መሆኑና፣ ከወልድም ወስዶ መግለጹ፥ የመለኮት ህልውና ዘለዓለማዊ ባሕርያዊ ግብር እንደሆነ እናገኛለን። ዮሐ. 16፥6፣7። ሮሜ 11፥36።



# ምዕራፍ ፳፰

## ዋ ሕ ድ ወ በ ኩ ር

አርዮሳውያን ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጾ በተመርሆ ልቡናዊ ተገናዝቦ የተገኘውን፣ ይህን ሁሉ ማስረጃ እያዩ፥ እርሱን ወደ ጐን አግልለው በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ሁሉ በእርሱ ሆነ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አይሆንም።» ተብሎ የተነገረለትን ቃል ከራሳቸው በፈጠሩት ዘለፋ ፍጡር ነው ሊሉት ይፈልጋሉ።

ይህም አባባላቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቈላስይስ ሰዎች ከጻፈው ከምዕራፍ አንድ ቍጥር አሥራ አምስትና አሥራ ስድስት ላይ ባለው ጥቅስ እንደተደገፈ አድርገው ያስባሉ። ከቶውንም ይህ ጥቅስ ለአስተሳሰባቸው ታላቅ ምሽግ እንደሆነ ይገምታሉ። ይህ አስተሳሰባቸው ግን ጨርሶ ስሕተት ነው።

መቼም ከዚህ አስቀድመን ከተመለከትናቸው ክፍሎች «ቃል እግዚአብሔር ነበረ» ተብሎ ከተነገረለት በቀር፥ ዓለማት የተፈጠሩበት ሌላ ፍጡር ቃል ይኖራል ብለን አይደለም። ዳሩ ግን ሐዋርያው ጳውሎስ ለእነርሱ ሌላ ትምህርት እንደሰጣቸው አድርገው የሚያስመስሉትን ማስመሰል እስቲ በበጎ ፈቃድ እንይላቸው እንመልከትላቸው ብለን ነው።

አሁን እንግዲህ፡- አርዮሳውያን ወደ መሸጉበት ወደ ጥቅሱ ምሽግ እንግባና እግዚአብሔር ቃል ወልድን ፍጡር ወይም ፍጥረት ይለው እንደሆነ ሙሉ ቃሉን በጥሬ ንባብ እንዳለ አቅርበን እንመልከት።

«ዘውእቱ አምሳሊሁ ለእግዚአብሔር ዘኢያስተርኢ። በኵሩ ዘላዕለ ኵሉ ተግባሩ እስመ ቦቱ ፈጠረ ኵሎ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ፡- እመኒ መናብርት ወእመኒ አጋዕዝት ወእመኒ መኳንንት ወእመኒ ቀደምት ኵሉ ቦቱ ኮነ ወኵሉ በእንቲአሁ ተፈጥረ።»

እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት፥ ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና፣ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። ቈላስ. 1፥15፤16።

እነሆም፡- ይህን በጥሬ ንባብ የቀረበውን ሙሉ የጥቅሱን ቃል አተኵረን በማየት ላይ ነን። ከላይ ከታች ከቀኝ ከግራ፣ ደኅና አድርገን መመልከት ይገባናልና ነው።

ታዲያ፡- በዚሁ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ፍጥረት ወይም ፍጡር ነው የሚል ገለጻ አለወይ? በእውነቱ የምናየውን ብንናገር፣

የእግዚአብሔር ቃል ወልድን «የፍጥረት ሁሉ በኵር» ሲለው ብቻ እናገኛለን እንጂ፤ «ፍጥረት ወይም ፍጡር ነው» ሲለው አናገኝም።

አንባቢ ሆይ፥ ይቅርታ አድርግልኝና እባክህን ልጠይቅህ፡- በውኑ በዚሁ ጥቅስ በኵርን ፍጥረት ወይም ፍጡር ሲለው አይተሃልን? አይተህ እንደሆነ ተናገር። ካየህ ለምን ብለህ ትደብቀዋለህ? ተናገር፡- እግዚአብሔር እንደሆነ ከፍጥረት አይደገፍ እርሱ የእውነት አምላክ ነው።

እነሆም መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተጻፈ የሚረጋገጠው በዚህና በመሳሰሉ ሁሉ ከእውነት ፈቀቅ አለማለቱን በማስተማመኑ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በእግዚአብሔር እውነትና ጽድቅ የተመሠረተ የባሕርየ መለኮቱ ግብር «መገለጽ» እንደመሆኑ፥ የሰው ልጆች ሁሉ ቃሉ ወደተገለጸበት እግዚአብሔራዊ ፈቃድ እንዲመጡና እንዲቀርቡ ይስባቸዋል እንጂ፤ እርሱ ራሱ በልጓም ተሸብቦ ወደ ወሰዱት ቦታ እንደሚነዳ ፈረስ አይደለምና፤ ሰዎች ወደ ፈለጉት ወደ ራሳቸው ፍላጎት እንውሰድህ ቢሉት አይወሰድላቸውም። እስቲ በሚከተሉት አርእስት እንመርምረው፡-

1፥ ምናልባት በሰዋስው ደንብ ይኖር ይሆን?

«የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው» ተብሎ በሚነገር የዓረፍተ ነገር ሐረግ፥ በኵር ተብሎ የተነገረው ስም ፍጥረት ተብሎ በመለወጥ የሚተረጐምበት ፈሊጥ በሰዋስው ደንብ ይኖር ይሆን?

በመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው፡- «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ... የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው» የሚል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸበት ጥሬ ንባብ፤ ቃሉ እንዲሁ ሆኖ ከተገኘ «የፍጥረት በኵር» በሚባልበት ጊዜ በኵርን ፍጥረት፤ ወይም ፍጥረትን በኵር ነው የሚያሰኝ የሰዋስው ደንብ የለም። በጥሬ ንባቡ «ፍጥረት በኵር ነው ወይም በኵር ፍጥረት ነው» ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብ ቢገኝ ኖሮ ግን፤ በኵር ተለውጦ ፍጥረት፤ ወይም ፍጥረት ተለውጦ በኵር እንደሚሆን ለማሳየት ባስቻለ ነበር።

ይህ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብ ተጽፎ መገኘት ነበረበት። በጥሬ ንባቡ መጽሐፍ ቅዱስ ካልገለጸው ግን፤ ሰዋስዋዊ ደንብ ሕገ ባሕርዩን ለቅቆ ቃላቶቹን ከአቀማመጣቸው፤ ሊያወጣቸውና ሊለውጣቸው አይቻለውም። አሁን ከዚህ ሳንርቅ ቀጥሎ ባለው ሰዋስዋዊ መመሪያ እንነጋገራለን። ስለምን ቢሉ፤ አንዳንድ ቃላት በአገባብ ከመያዛቸው የተነሣ አንዱ ቃል እጐኑ ካለው ቃል በመለዋወጥ የራሱን ይዞታ ጥሎ፥ የሌላውን እጐኑ ያለውን ቃል ፍች የሚቀበል የሚወስድ የሚመስላቸው ሰዎች ተገኝተዋልና፤ ነገሩን በትክክል አይተው ልባቸው እንዲነጻላቸው ስለፈለግን ነው።

እንግዲህ ለማንኛውም የቃላቶቹን ልዩነት ደኅና አድርገው በመመርመር እንዲመለከቱአቸው፤ በትምህርተ ሰዋስው በየአቋማቸው እንዴት እንደሚጠበቁ ለማሳየት የሚቀጥሉት ምሳሌዎችን ለማስረጃ አቅርበናል።



እርግጥ ነው፡- በዘርፍ ሙያ ረገድ ስም ከሌላው ስም ጋር በዘርፍ አያያዥ አማካይነት ይቀናጃል። ቅጽልም በቅጽልነት ወይም በቅጽል አስተኔ ሙያ ከስም ጋር ተያይዞ ይገኛል። ይሁን እንጂ፤ በዚህ የሙያ ይዞታ ማናቸውም ስም ለገዛ ራሱ የተሰየመበትን የራሱን ዘይቤ የሚያንጸባርቅበትን የመጠሪያን ስያሜ ትቶ ወይም ለቅቆ፥ ከአጠገቡ በሚገኝ ስም ሊለወጥና ያለ ስሙ ነሥቶ «ወስዶ» ሊሰየም አይችልም።

ለምሳሌ፡-

ሀ/ «ይህ የቶማስ አህያ ነው»

ለ/ «ያ የበሬ ቀንድ ነው» የሚል ዓረፍተ ነገርን እንውሰድና እንነጋገርበት።

ሀ/ እነሆም በአንደኛው ዓረፍተ ነገር፡- «ይህ የቶማስ አህያ ነው» ተብሎ የተነገረውን ወስደን በምንተነትንበት ጊዜ አህያው ቶማስ ነው የማለትን ፍች አንሰጠውም። ገንዘብ ወይም ንብረት መሆኑን ያሳያል እንጂ፤ አህያው ተለውጦ ቶማስ እንደሆነ አያሳይምና ነው። እንደዚህ አድርጎ በማለዋወጥ መናገርም ፈጽሞ ስሜት የሌለው ነው።

ለ/ በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር «ያ የበሬ ቀንድ «የሚለውን አነጋገር» በሬ ቀንድ ነው ወይም ቀንዱ በሬ ነው» የሚል ዓረፍተ ነገር ቀንድ በሬ ነው ለማለት እንደማያስችል እናውቃለንና ነው።

«ያ የበሬ ቀንድ ነው» ተብሎ በተነገረው ዓረፍተ ነገር የሚገኙ ስሞች የሙያ አቀማመጣቸው በዘርፍ አያያዥ አቀናጅነት የተያያዙ መሆናቸው እርግጥ ነው። ይሁን እንጂ ስሞቹን አንዱ ለሌላው ተለዋጭ በሚያደርግበት አቋም ያልተመሠረቱ መሆናቸውን ደግሞ እናውቃለንና ያ የበሬ ቀንድ ነው። ወይም በሬው ቀንድ ነው እንደማያሰኝ ፈጽመን እንረዳለን።

2፥ «እባብ ያየ በልጥ በረየ»

የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ... የፍጥረት ሁሉ በኵር ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብ እንደዚሁ ቅልብጭ ብሎ የሚታየውን፤ በሰዋስው ደንብም የቃላቶቹን አቀማመጥ በሚገባ ጠብቆ የሚገኘውን የዓረፍተ ነገር አሰካክ፥ አርዮሳውያን ለዋውጠው ለመናገር የሚፈልጉት፥ ስለምን ይሆን? ብለን እንጠይቃለን።

ምናልባት ፍጥረት የሚል ስም በኵር ከሚል ስም ጋር፥ አብሮ አንድ ላይ ተጽፎና ተቀራርቦ ስላዩና በኵርን «ፍጥረት» ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረለት መስሎአቸው ይሆን?

አንዳንድ ጊዜ እንደሚታይ ቅዱሳት መጻሕፍትን በትምህርተ መለኮት ኀሠሣ ወይም በልቡናዊ ተመርሆ መንገድ፥ እንደ ሥርዓቱ ያልተከታተሉ ወገኖች፥ ይህን በመሰለ የገበሬ አስደንግጥ ንባብ፥ የሚሰናከሉ መሆናቸው የታወቀ ነውና፤ ከዚህ የተነሣ ይመስላል «እባብ ያየ በልጥ በረየ»።

ይሁን እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ምስክርነት፡- በመሆን እንጂ፣ «በይመስላል» እንደማይተረጐም እናውቃለን።

እነሆም፡- «የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው» የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ንባብ በራሱ አቋም ግልጽ ሆኖ የተጻፈና የቃላቱ አቀማመጥም በማያደናግር አቋም ጸንተው የሚታዩ ስለሆነ፣ የሚያስደንግጥ ጠባይ አይገኝበትም። አቀማመጡም በጉት የቅኔ መንገድ የተመሠረተ አይደለም። «ፍጥረት» የሚል ቀዋሚ ስያሜ ቀርቶበት «ፍጥረት» ተብሎ ተለውጦ፥ መሰየም አለበት የሚል የአርዮሳውያን አባባል፥ ሌላ ምሥጢር ኖሮት ሳይሆን፣ ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ትወቀጥ እንደሚባለው ሁሉ ሆኖ እናገኘዋለን።

ይህም በኵር የሚል ስም፥ ፍጥረት ከሚል ስም ጐን አብሮ ከተገኘ፥ ዘንድ ፍጥረት መባል አለበት ሲሉ፥ አርዮሳውያን ያስቸኳይ አዋጅ እንዳወጁበት ነው የሚያሳይ።

አሁን በኵር ማለት ምን ማለት ስለመሆኑ እንነጋገርበታለን። በመጽሐፍ ቅዱስ አብነት «በኵር» የሚል ቃል የሚያሳየው ስለመፈጠር ሳይሆን፣ በልደት ላይ የተመሠረተና የማያሻማ ትርጉምን ይዞ ነው።

ይኸውም፡- በመጽሐፍ ቅዱስ «በኵር» የሚል ቃል በማናቸውም የልደት ዓይነት፡- ይኸውም በባሕርይ ልደት ሆነ በግብር ልደት ሲነገር፣ የልደትን መሠረት ይዞ እንጂ፣ መፈጠርን ወይም ተፈጥሮን በሚመለከት ሁናቴ የተነገረበት ቦታ አይገኝም።

1፥ የባሕርይ መወለድ ከአንድ ወላዲ «ወላጅ» ምንጭ መፍለቅ፥ ወይም መውጣት ነው። ይኸውም በመፈጠር በመሠራት ወይም በመደረግ መምጣት ማለት አይደለም። መፈጠር ግን ተፈጥሮ ተሠርቶ ተበጅቶ መገኘት ነው። ከአንድ ወላዲ ወይም ወላጅ ፈልቆ ወይም መንጭቶ መገኘት አይደለም። የግብር ልደት ሲባል ደግሞ፥ የባሕርይ የመፈጠር ትርጉም ሳይኖርበት፥ እንዲሁ የሚሰጥ ልጅነት ነው። በእነዚህ በተጠቀሱ አቋሞች ላይ ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ መረዳት፥ ስለ ብኵርና ለሚወሰደው ትምህርት በጣም ጠቃሚ ነው።

ለምሳሌ፡-

1ኛ፥ አዳም ሁለት መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፣ ልጁንም በምሳሌው እንደመልኩ ወለደ፣ ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን። ዘፍጥ. 5፥3። እነሆም በአዳም ምሳሌና በመልኩ የተወለደ ሴት፥ ለአዳም የባሕርይ ልጅ ነው። ይህ የባሕርይ ልደትን ያመለክታል።

2ኛ፥ «አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ተባለ» ሉቃ. 3፥38። ነገር ግን አዳም የእግዚአብሔር ልጅ የተባለበት በመፈጠሩ እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ባሕርይ ፈልቆ መንጭቶ ስለተገኘ አይደለም። ይህ የአዳም ልጅነት የግብር ልጅነት ነው። ዘፍጥ. 1፥26-28። ም. 2፥7። ይህ ደግሞ የግብር ልደትን ያስገነዝባል።



እነሆም የቃላቱን ልዩነትና አቀማመጥ ከመሠረቱ አጠናቅቆ መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ይህም እርግጥ ከሆነ፣ የበኵር መሠረትና መዋቅር የተነገረባቸውን አቋሞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅሰን እናቀርባለን።

ሀ/ በኵር ሲባል ቀዳማዊ ወይም መጀመሪያ ሆኖ፥ በልደትና መገኘት እንደሆነ እናያለን።

ለ/ በኵር ሲባል ቀዳማዊ ወይም መጀመሪያ ሆኖ ተወልዶ ለሌሎች የልደት ተከታታዮች አበጋዝ ወይም አለቃ መሆን ነው።

ይኸውም፡- በቅድሚያ በመገኘቱ ወደ ወላጅ «የአባቱ አከል መሰልነት» የሚመለከት ይዞታ ነው። ዘፀአ. 13፥3። ሉቃ. 2፥23፤24። ይዞታውም የወላጅ መሰል ሆኖ መቆሙን የሚያስገነዝብ ነው። እንደዚሁም ቀዳሚ ሆኖ በመወለድ በመገኘቱ ቀጥለው ለሚወለዱት ወንድሞቹ መነሻ በመሆን የእነርሱ በህሉና መገኘትና ለማስከተል አስችሎአልና፣ አበጋዛቸው አለቃቸው ለመሆን ያበቃዋል።

እነሆም በኵር በሚል ቃል ውስጥ፥ ሁለት አሳቦች እንዳሉ እናያለን።

ሀ/ ቀዳማዊ ሆኖ ከወላጁ በመውጣት ስላለው ይዞታና፡-

ለ/ ቀዳማዊ ሆኖ በልደት ከመገኘቱ የተነሣ ለሌሎች አበጋዝ ወይም አለቃ መሆንን ስለሚያስችለው ይዞታ ነው።

እነዚህን ለይቶ ለመረዳት ቀጥሎ ያለውን መረጃ መከታተል ያስፈልጋል።

1፥ ቀዳማዊ ሆኖ መወለድ የሚለወጥ አይደለም። የቀዳማዊነቱም ታሪክ አይሻርም፣ ቀዳማዊ ሆኖ መወለዱ የተፈጸመ ታሪክ አለውና፣ የተወለደ ሰው ከወላጁ አንድ ጊዜ፣ ተወልዶአልና፣ ቀዳማዊ ሆኖ እንዳልተወለደ ሊቈጠር፥ ሊደረግ የሚያበቃ ምክንያት የለምና ነው።

2፥ ቀዳማዊ ሆኖ ከወላጁ ተወልዶ ሳለ፣ ለሌሎች ወንድሞች አበጋዝ ወይም አለቃ የመሆን ብኵርና ግን፣ ቀዳማዊ ሆኖ ለተወለደ ለበኵር ጸንቶለት ሊኖር፣ የተመደበ ሲሆን፣ በአግባቡ ከሥርዓቱ ውጭ ከተገኘ ግን ብኵርናው ቀዳማዊ ሆኖ ላልተወለደ ለተከታይ ወንድሙም ሊተላለፍለት ይችላል።

ይህን ለመረዳት የኤሳው ብኵርና በሽያጭ ለያቆብ ተላልፎአል። ዘፍጥ. 25፥31-34። ም. 27፤36። ዕብ. 12፥16።

የሮቤል ብኵርናም በነውር ሥራ ለዮሴፍ ሊተላለፍ በቅቶአል። ዘፍጥ. 48፥3፤4። ም. 49፥26።

እነሆም የእነዚህ ሰዎች የኤሳውና የሮቤል ብኵርና ተወሰደባቸው ሲባል፣ ቀዳማዊ ሆነው የተወለዱበት ብኵርናቸው አይደለም። ቀዳማውያን ሆነው

የመወለዳቸውና «በኵር» የመባላቸው ታሪክ፥ እንዳለ እንደተጠበቀ ነው። ነገር ግን ቀዳማውያን ሆነው ከመወለዳቸው የተነሣ የነበራቸው ለሌሎች አበጋዝ ወይም አለቃ የመሆን የበረከት ብኵርና፥ በሠሩት ነውር ምክንያት ተገፈው፥ ቀዳማውያን ሆነው ላልተወለዱት ለያዕቆብና ለዮሴፍ ሊተላለፍ በቅቶአል።

ይኸውም የኤሳው የሮቤል መደበኛ ብኵርና ከእነርሱ ቀጥለው ለተወለዱት ወንድሞቻቸው ተላልፎላቸው፥ ሥልጣናቸው ወይም መብታቸው ተወስዶባቸዋል ማለት ነው።

እንግዲህ የወንድሞች አለቃና አበጋዝ የመሆን መብት ያለበት ብኵርና፣ ግምባር ቀደም በመወለድ ብቻ ሳይሆን፣ ከወላጅ ያለው የመወለድ መሠረት ሳይኖጋ፣ ተከታይ ሆኖ፣ በመወለድም ሊገኝ ይችላል ማለት ነው።

እርሱም የወንድሞች አለቃ ወይም አበጋዝ መባል ሲሆን፣ በያዕቆብና በዮሴፍ እንደታየው፥ የሀብተ በረከት ይዞታ የሹመት መብት ያለበት በኵር መሆኑ ነው። አሁን በአባት በኵል የሚመጣው ብኵርናንና ሁኔታውን አየን።

በእናት በኩል ስለሚወርደው ብኵርና።

በእናት በኩል ይኸውም በሴት ረገድ ስለሚመጣ ብኵርና እንዴት እንደሆነ እንመለከታለን።

በእናት «በሴት» በኩል የሚመጣ ብኵርና በአባት በኩል እንደሚመጣ ብኵርና የተደራረበ ምሥጢር የለውም። ይኸውም በቀዳማዊነት መወለድን ብቻ መሠረት ያደርጋል። ይኸውም «ኵሉ ዘይፈትሕ ማኅፀነ እሙ ቅዱስ ይሰመይ ለእግዚአብሔር የእናቱን ማኅፀን የሚፈታ ወንድ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው» በሚል መነሻ በኵር መባሉ ይገኛል ማለት ነው። ይህ ሂደት በደረጃው የእንስሳትን በኵር የሚያከል ነው።

ይህ ዓይነቱ ብኵርና በእናቱ ረገድ የሚታይ ስለሆነ፣ የእናቱን ማኅፀን የሚፈታ ወንድ ይሁን እንጂ፣ ወንድሞችን ቢያስከትልም ባያስከትልም በኵር መሰኘትን አያስቀርበትም። ዘጸአ. 13፥1፣2።

ለምሳሌ የአንዱ ልጅዋ የሶምሶን እናት የማኑሄ ሚስት፥ አንድ ልጅዋ ሶምሶን «የእናቱን ማኅፀን የሚፈታ ወንድ ልጅ ሁሉ» በተባለው መሠረት በእናቱ ረገድ በኵር ነው። የተቀደሰ ሆኖ ቀርቦአል። በመወለዱ ረገድ ማኅፀንዋን ፈትቶአልና ነው። መሳፍ. 13፥1-25።

ይህ ዓይነቱ ብኵርና ቀዳማይ ሆኖ፥ ከእናት ማኅፀ ን ከመውጣት ጋር የተሣሠረ ነው እንጂ፣ ተከታታይ ወንድሞችን ከማስከተል ወይም ካለማስከተል ጋር የተያያዘ አብነት የለውም። ማቴ. 1፥24። ሉቃ. 2፥7 23፣24።

እነሆም በሰው ልጆች ዘንድ፥ በኵር የባሕርየ ልደት ጠቀስ «በኵር» የሚል ቃል የተመሠረተባቸው አሳቦች ከዚህ በላይ አየን።



በአጠቃላይም፦

1ኛ፥ በቀዳማዊነት በመወለድ የሚገኙና ቀዳማዊነቱም የማይካድና፥ ታሪክ የማይሽረው እንደ ኤሳውና እንደ ሮቤል ያለው ብኵርና።

2ኛ፥ በታሪክ ቀዳማዊ ሆና የመወለድ ይዞታ ሳይኖርበት የልቅናና የአበጋዝነት መብት በውርስ በመጉናጸፍ የተገኘ እንደ ያዕቆብ እንደ ኤሳው ያለ ብኵርና።

3ኛ፥ በእናት ረገድ የሚመጣ የእናት ማኅፀን የሚከፍት ወንድ ልጅ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን ተብሎ በተደነገገው ሕግ መሠረት ወንድሞችን ባያስከትልም፣ ለወንድሞች አለቃ ወይም አበጋዝ የመሆን ሀብተ በረከት ባይኖርበትም በኵር የሚሰኙበት ብኵርና ናቸው። እነዚህ ሁሉ በመሠረቱ በባሕርየ ልደት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

# ምዕራፍ ፳፱

## በብሉይ ኪዳን በባሕርየ ልደት የተመሠረተ ሌላ የብኵርና አቋም ይገኛል።

እነሆም በኦሪት እንደተገለጸው ከእንስሳና ከቡቃያ ከዘርም ቀዳማዊ ሆኖ የሚያፈራና የሚወለድ ሁሉ በኵር ይባል ነበር።

ነጠል ተደርጎ ሲነገርም፦

1፥ ከዘር፥ ከቡቃያ ቀደምትነት ይዞ ወይም በመጀመሪያ የሚያፈራው «ቀዳምያት» ይባል ነበር።

2፥ ከእንስሳ ከሰው ቀዳማዊ ሆኖ የሚወለድ ግን፣ በኵር ወይም በኵራት ይባል እንደነበረ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ክፍሎች እናገኛለን። ይህም ሁኔታ ፍሬ ሆኖ በቅድሚያ መውጣትን፣ «መድረስን» ልጅ ሆኖ በቀዳማዊነት መውጣትን ወይም መወለድን፥ ወይም ሌሎችን ቀድሞ መገኘትን ያስገነዝባል። ፍሬ ከዘሩ ውስጥ አፍርቶ የሚገኝ እንጂ፣ ከውጭ ተሠርቶ የሚመጣ እንዳልሆነ በሚታወቅበት መጠን፥ ፍሬ ቀዳማዊ ሆኖ በማፍራቱ በኵራት ቢሰኝም ተፈጥሮ ተሠርቶ አይደለምና፣ ብኵርናው ከባሕርየ ልደት መመሥረቱ ስለዚህ ነው።

3፥ የግብር ልደት ብኵርና። «እስራኤል የበክር ልጂ ነው»

በመጽሐፍ ቅዱስ ልዑል እግዚአብሔር «እሥራኤል የበኵር ልጄ ነው» ተብሎ ሲናገር ይገኛል። ይህ ዓይነቱ ልደት የባሕርይ ልደት ባይሆንም እንኳ፣ በጸጋ ልደት እሥራኤል የበኵር ልጅ ተብሎ ተጠርቶበታል። ዘፀአ. 4፥22፤ 23።

ይህ እሥራኤል የእግዚአብሔር የበኵር ልጅ የተባለበት ብኵርና ማንን ያስከትላል? ቢሉ፥ አሕዛብ በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ፣ እሥራኤልን በእምነት ተከትለዋል። የእግዚአብሔር ልጅነት አግኝተዋልና፣ አሕዛብ ተከታዮች ወንድሞች መሆናቸውን ያሳያል።

ይህንም፥ ሐዋርያው በደሴተ ፍጥሞ በራእይ ተገልጾለት ጽፎት እናገኛለን። ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ከእያንዳንዱ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎች ከበኵራቱ ቀጥለው ግን ማንም ሊቈጥራቸው የማይችል ከአሕዛብና ከቋንቋዎችም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች እንደ ነበሩና፣ እነርሱም ነጭ ልብስ ለብሰው የዘንባባን ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆመው አየሁ። ብሎአል። ራእ. 7፥3-17።



ይህም እሥራኤል በአብርሃም እምነት ከአሕዛብ አስቀድመው በመግባት በኵራት እንደተባሉ ከአሕዛብ ደግሞ በእነርሱ ፈር ያንኑ አብርሃም ባመነበት እምነት አምነው በሃይማኖት ተከታትለው እንደቀጠሉ ይህ ራዕይ አሳይቶአል። ሮሜ 4፥12-23።

እነሆም የእሥራኤል ብኵርና ማንን ያስከትላል? ለተባለው ጥያቄ አሕዛብን በእምነት የእግዚአብሔር ልጅነት ማግኘታቸውን ተገንዝቦ እሥራኤልን እንደ ተከተሉ አይቶ መረዳት ነው። ኤፌ. 2፥11-22።

ይህ በግብር ልጅነት የተመሠረተ ብኵርና ነው፣ ይሁን እንጂ፣ በዚህም እንኳ ቢሆን ብኵርና በመፈጠር እንዳልተቋቋመ ለማየት ነው የምንችለው። ገላ. 3፥29።

በአጠቃላይ ስንመለከት የሰዎችን ሆነ የእንስሳቱን ባሕርየ ልደትና ባሕርየ ልደት ጠቀስ ብኵርና ስናይ፣ ቀዳማዊ ሆኖ መገኘትን ብቻ ሳይሆን፥ ከእናቱ ከሚወርደው ብኵርና በቀር፥ ተከታዮችን ማስከተልና ግምባር ቀደም ሆኖ፣ መገኘትን ሌሎችን ቀድሞ መገኘትን የያዘ ነው።

በዚሁ ምክንያት ደግሞ «በኵር» ወይም በኵራት ወይም ቀዳምያት የሚል ስያሜ እንደመጣ ልንገነዘብ እንችላለን።

### የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በየትኛው ሁኔታ «በኵር» ተባለ?

ከዚህ በላይ ስለ በኵር የተነገረውን የተመለከተ ሰው የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ከዚህ በላይ ስለ በኵር ከተነገሩት ዝርዝሮችና ሁኔታዎች በየትኛው ሁኔታ «በኵር» እንደተባለ ለመረዳት እንደሚሻ የታወቀ ነው። እውነትም የእግዚአብሔር ቃል ወልድ «በኵር» ሲባል እላይ ከተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎች በየትኛው ነው «በኵር» የተባለ? ብሎ መጠየቅ የተገባ ነው። ይህን ለመረዳት መጀመሪያ ነገር የወልድ ዋሕድ ብሑት «ልደት» ቃለ እግዚአብሔር አቋም መመልከት ያሻል።

እነሆም ወልድ ቃለ እግዚአብሔር ከዘለዓለም ከአብ ባሕርይ በተወለደበት ልደቱ፥ ወልድ ዋሕድ «አንድያ ልጅ» ብሑት ልደት፣ ቀዳሚና ተከታይ የሌለው በልደት ብቻኛ የሆነ አንድያ ልጅ ይሰኛል።

በዚህም ልደቱ በኵር አይሰኝበትም። ምክንያቱም ግልጽ ነው።

1ኛ፥ ከአብ የወጣበት የልደት ፀአት «መውጣት» ዘለዓለማዊ ነውና። መዝ. 109/110/፥3። ሚክ. 5፥2።

2ኛ፥ ከአብ የወጣበት ፀአት «መውጣት» ከጊዜያት በአንዱ ጊዜ የሆነ ሳይሆን፣ ከዘለዓለማዊ ፀአት «አወጣጥ ነጸብራቅ» ነውና፥ ዕብ. 1፥3። ዮሐ. 1፥18።

ማብራሪያ፦ ማለት በዚህ በባሕርይ ልደቱ ወልድ ዋሕድ «ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጅ ብሑተ ልደት በልደት ብቸኛ አንድ ለአባቱ ነውና፤ እንዲህ ያለ በመሆኑ በኵር አይባልበትም። ይኸውም እርሱ ከአባቱ በተወለደበት በባሕርይ ልደት ከአባቱ በባሕርይ የተወለዱ ሌሎች ተከታዮች ወንድሞች የሉትምና። በዚሁ ረገድ ብኵርና የሚያሻው አይደለም።

3ኛ፥ በዚህ በባሕርይ ልደቱ ዋሕድ «አንድያ ልጅ» እንደመሆኑ እንደዚሁም በባሕርይ ህልውና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ተገናዝቦ በአንዲት ተዋሕዶተ መለኮት ይኖራል። እንደዚሁም በዕሪና በአካል አብንና መንፈስ ቅዱስን መስሎና አክሎ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፥ ይተካከላልና። ዮሐ. 10፥30። ዕብ. 1፥3።

ታዲያ ወደዚህ የልዕልና መለኮት ደረጃ የሚደርስ ከየት ይመጣል? ከሌለስ ለአንዲያ ልጁ ተከታይ የሚሆን ከየት ይገኛል?

4ኛ፥ ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተወለዱ ሌሎች ልጆች ስለሌሉ፤ የሚከተሉት የሉምና።

5ኛ፥ የእግዚአብሔር ባሕርይ ያላቸው ሌሎች አልተገኙምና፤ በዚሁ ረገድ ወልድ፥ በባሕርይ ልደቱ ለማን በኵር ይሆናል?

ይሁን እንጂ፤ የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ዋሕድ «ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁ» በሚሰኝበት አቅዋም በዚሁ ገለጻ እንደተነገረ ሆኖ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ የተጠገቀቀ ሆኖአል።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውና ለአባቱ አንድያ ልጅ መሆኑ ከታወቀና ከተጠነቀቀ፤ ታዲያ «በኵር» ተብሎ መጠራቱ በምን መንገድ ነው? ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ወልድ «በኵር» ተብሎ የተነገረለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ነውና።

መጽሐፍ ቅዱስ ወልድ ቃለ እግዚአብሔርን በኵር ከማለቱም በኵር ስለተሰኘበት ሁናቴም ብሩህ አድርጎ ሳይገልጸው አላለፈም። ብቻ እኛ ንቃት በተመላ መንፈስና በቅንነት የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተዋል ዝግጁዎች መሆን ይኖርብናል።

እነሆም «ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ» እንዲሉ፥ ሁኔታውን ከመሠረቱ ብናመጣው ሳንጠቀም አንቀርም።

እነሆም ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከአባቱና ከቅዱስ መንፈሱ ዘንድ በህልውና ተገናዝቦ የኖረ፥ ለአባቱ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጅ እንደመሆኑ፥ ከአባቱና ከቅዱስ መንፈሱ ጋር ምንም ባዕድ ነገር ባልነበረ ጊዜ፤ በዘለዓለማዊነት ሲኖር፤ ዓለማት እንዲፈጠሩ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆነ።



ይህ እግዚአብሔራዊ በጎ ፈቃድም ዓለማት እንዲፈጠሩ ብቻ ሳይሆን፤ ዓለማት እንዲፈጠሩ ምክሩና ጥበቡ፥ ኃይሉ በሚሆን በአንዲያ ልጁ መደብ ወሰነ። ኤፌ. 1፥11።

ይህም ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ በጎ ፈቃድ እንደተወሰነና እንደተመደበ አልቀረም። በጊዜው ጊዜ የአብ ምክሩ፥ ጥበቡ፥ ቃሉ በሚሆን በእግዚአብሔር ቃል ወልድ ዓለማት ተፈጠሩ።

ይኸውና፦ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሁኔታ መሠረት አድርጎ፥ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን «የፍጥረት በኵር» ሲለው እንመለከታለን። ቈላስ. 1፥15፤16።

ይሁን እንጂ ይህ ብኵርና በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች በኵር ይሰኙበት እንደ ነበረ ብኵርና አይደለም። ከመሠረቱ፤ አይመሳሰልም። ትንሽ መመሳሰል የሚታይበት በአልቅናና በአበጋዝነት ብቻ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን በኵር ለመሆን ይበቁበት የነበረ ሁናቴ ከዚህ አስቀድመን እንደገለጽነው ከወላጅ አባታቸው ተወልደው ከዚያው ከወላጅ አባታቸው ለተወለዱት ወንድሞቻቸው አበጋዝ ወይም አለቃ በመሆን ነው።

የወልድ ቃለ እግዚአብሔር «የፍጥረት በኵር» መባል ግን በመሠረቱ ይህን የሚመስል አይደለም።

ሀ/ እርሱ በዘለዓለም ልደት ከአብ ባሕርይ ተወልዶአል።

ለ/ እነርሱ «ፍጥረታት» ግን፤ ከአብ ባሕርይ ያልወጡ ያልተወለዱ ፍጡራን ናቸው።

አንድያ ልጅ «ወልድ» በኵር ሲባል፤ ሰዎች «በኵር» ይባሉበት በነበረ ሁናቴ እንዳልተጠራበት ያሳየናል።

ስለዚህ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን «የፍጥረት በኵር» ሲለው ምን ተገንዝቦ እንደተናገረ እንዲገልጽልንና እንዲያስገነዝበን ሐዋርያው ጳውሎስን ራሱን ብንጠይቀው የተሻለ ይሆናል።

በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የሚናገር ቅዱስ ጳውሎስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን ለምን «የፍጥረት በኵር» እንዳለው በቂ ማስረጃ አቅርቦ እንጂ፤ እንዲያው በደፈናው ተናግሮ እንዳላለፈ በማመን በጉጉት ለመረዳት መሻታችንን ማነቃቃት ይኖርብናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድን «የፍጥረት በኵር» ያለበትን ምክንያት ሲያስረዳ፤ ከዚህ ቀጥለው በሚገኙት በሦስት መሠረታውያን ነጥቦች እንደሆነ አበጥሮ ሲገልጽልን እናገኛለን።

እነዚህ፦

1ኛ፥ ፍጥረታት የተፈጠሩበት በእርሱ «በወልድ» ስለ መሆኑ፦

2ኛ፥ ፍጥረታት ካለመኖር ወደመኖር አቋም ተፈጥረው የመጡበት ምክንያት ለእርሱ «ለወልድ» እንዲሆኑ ተፈልጎ ስለመሆኑ፡-

3ኛ፥ ፍጥረታት በህሉና አቋም ለመገኘታቸው መነሻው ከእርሱ የተነሣ ስለመሆኑ ናቸው።

ሐዋርያው ቃለ እግዚአብሔር ወልድን «የፍጥረት በኵር» ያለበትን በእነዚህ ነጥቦች ሲጠቀም፣ ምክንያትና ማስረጃ ባለው አቀራረብ መሠረታዊ ትምህርቱን ገልጸባቸዋል።

## 1ኛ፥ «ሁሉ በእርሱ ተፈጠረ»

ፍጥረታት በእርሱ «በወልድ» ስለተፈጠሩ ወይም ስለተሠሩ «የፍጥረት በኵር» ነው ለማለቱ ሐዋርያው ጳውሎስ በሚከተለው ገለጻ ሲያስረዳ ይታያል።

ገለጻውም የሚታዩትንና የማይታዩትን ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው የሚል ነው። ቈላስ. 1፥15፣16።

እነሆም ሐዋርያው «የፍጥረት በኵር ነው» ያለበትን ሲያስረዳ፣ ከሚታይ ከማይታይ ጀምሮ የፈጠራቸው ሥርዌ ፍጥረታት ሁሉ፥ በእርሱ ስለተፈጠሩበት፣ መሆኑን ገልጾ የለምን?

አዎን፡-

ሀ/ ፍጥረታት ሁሉ በእርሱ በቃል ስለተፈጠሩ፡-

ለ/ ፍጥረታት ሁሉ ያለ እርሱ ስላልተፈጠሩ፡-

ሐ/ ፍጥረታት በቅደም ተከተል ቢፈጠሩም እንኳን ያለ እርሱ ፈጽመው ስላልተፈጠሩ፥

መ/ ሁሉም ያለምንም አጋዥ በእርሱ ብቻ ስለተፈጠሩ የፍጥረት በኵር ነው።

ታዲያ ይህ ሐዋርያው «የፍጥረት ሁሉ በኵር» ያለበት በቂ ምክንያት አይደለምን? ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ስላወቀ አምኖበት፣ በቂ ማስረጃ አድርጎ አቅርቦታል።

«ሁሉ በእርሱ ተፈጥሮአልና» የሚለውን ሰዋስዋዊ አገባብ ምን ማስረጃ ይዞ እንዳቀረበ አስረጅነቱ ለየትኛው የግሥ አንቀጽ እንደሆን ሊያተኵሩበት ይገባ የለምን?



## 2ኛ፥ «ሁሉ ለእርሱ ተፈጠረ»

ፍጥረታት ካለመኖር ወደ መኖር ደረጃ «አቅዋም» በእርሱ በወልድ የመጡ ሲሆን፣ ካለመኖር ወደመኖር የመጡበትም ምክንያት አለ። ይህ ምክንያት ምን ይሆን? አያሰኝምን የሚያጠያይቅ ነው።

ሐዋርያው የዚህን አጠያያቂ ምክንያት መሠረት ሲገልጽ፣ ወልድን የፍጥረት በኵር ያለበትን ማስረጃ አድርጎ አቅርቦት ይገኛልና፣ ከእርሱ ብንሰማ መልካም ነው። የሐዋርያው ቃል በቀጥታ ከፍጥረታት ሁሉ በፊት በኵር ነው።

«ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ይላል» ቈላስ. 1፥15፣16። በዚሁ ገለጻው ሐዋርያው «ሁሉ በእርሱ ተፈጥሮአል» ከማለቱም በላይ «ሁሉ ለእርሱ ሊሆን ተፈጠረ» ብሎአል። በዚህ ክፍል «ለእርሱ ተፈጠረ» በሚል ሐረግ ላይ እንድናተኵር ያስገነዝበናል። «ለእርሱ ተፈጠረ» ሲባል ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩ ለእርሱ እንዲሆኑ ታስበው ታቅደው መፈጠራቸውን የሚያስገነዝብ ነው። ፍጥረታት የተፈጠሩት በእርሱ «በወልድ» ሲሆን ቀድሞውኑ ለእርሱ እንዲሆኑ ታስቦ ነውና፣ በዚሁ ምክንያት ወልድ «የፍጥረት በኵር ነው።»

«ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ለእርሱም ሆነ» በማለት የፍጥረት መፈጠር ዋና ምክንያት ለእርሱ እንዲሆን ታስቦ ነው ከማለቱ የተለየ ትርጕም አለውን?

እነሆም የፍጥረት መፈጠር ዋናው ምክንያት ለእርሱ እንዲሆኑ ስለነበረ፣ እርሱ የፍጥረት በኵር ሆነ።

ቃሉን በጥሩ ዓይን ካነበብነው ሐዋርያው ወልድን «የፍጥረት በኵር» ላለበት መንሥኤ ማስረጃ አድርጎ ካቀረባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ይህ አንዱ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም ታላቅ ነው።

## 3ኛ፥ ሁሉ ከእርሱ የተነሣ ሆነ።

ፍጥረታት በህሉና «በመኖር» አቋም ለመገኘታቸው መነሻ ከእርሱ የተነሣ ስለመሆኑ ሐዋርያው ይናገራል።

ወልድን የፍጥረት በኵር ካሰኙት ምክንያቶች አንዱ፥ ይህ እዚህ ላይ ርእስ ሆኖ የተጠቀሰው ነው።

ሐዋርያው ፍጥረታት በህሉና «በመኖር» አቋም መገኘታቸው ከእርሱ «ከወልድ» የተነሣ መሆኑን ገልጾ አቅርቦታል።

ይህንም የሰው ልጆች የመዳን ራስ ሆኖ መገኘቱን በገለጸበት በዕብራውያን መልእክቱ ላይ በቀዋሚ ማስረጃነት አቅርቦት እናገኘዋለን። «ወይደልዎ ለዘበእንቲአሁ ኵሉ ወእምኔሁ ኵሉ፡-» ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ሊያመጣ የመዳናቸውን ራስ በሕማማት ይፈጽም ዘንድ ከእርሱ የተነሣ ሁሉ በእርሱ ሊሆን ይገባዋል ይላል። ዕብ. 2፥10።

ፍጥረት በእርሱና ለእርሱ በመፈጠራቸው ምክንያት «ወልድ» «የፍጥረት በኵር» እንደተሰኘ ከተመለከትናቸው ዝርዝሮች ተገንዝበናል። እዚህ ላይም ከእርሱ የተነሣ ሁሉ ሆነ ወይም ተፈጠረ በማለት ሐዋርያው ያቀረበውን እንመለከታለን።

እስቲ፡- አስቀድመን በእርሱ ለእርሱ፥ ከእርሱ የተነሣ በሚሉ በሰዋስው አገባቦች አቀማመጥና ይዘታ ያለውን ልዩነት እናስታውስ።

ይህን በአእምሮአችን እንደያዝን ከላይ በዝርዝር ያየነውን ይኸውም ፍጥረት «በእርሱ ለእርሱ» የመፈጠራቸው ይዘታ ወልድን «የፍጥረት በኵር» ሊያሰኘው እንደበቃ እያሰላሰልን፥ አሁን ደግሞ ፍጥረታት ከእርሱ የተነሣ ተፈጠሩ ሲል ስላቀረበው መግለጫ እንዲብራራልን እንጠይቃለን።

አዎን፥ ፍጥረታት ለእርሱ እንዲሆኑ በመፈጠራቸው መካከልና «ፍጥረታት ከእርሱ የተነሣ ተፈጠሩ» በማለት መካከል ያለው ልዩነት እንደምንድን ነው?

የአገባቦቹን ምሥጢራዊ ምክንያት መሠረት በማድረግ ስንገልጽ፡-

1፥ ፍጥረት ለእርሱ እንዲሆኑ ወይም ለእርሱ እንዲኖሩ ተፈጠሩ ሲባል፣ ለእርሱ ክብርና ምስጋና ሊኖሩ ተፈጠሩ ያሰኛል።

2፥ ፍጥረታት «ከእርሱ የተነሣ ተፈጠሩ» ደግሞ ማለት የእነርሱ ክዋኔ «መሆን» ወይም በህሉና አቋም መገኘት ከእርሱ «ከወልድ» የተነሣ ሆነ ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ የእነርሱ ክዋኔ ወይም መፈጠራቸው መሠረቱ ከእርሱ የተነሣ ነው ማለት ይሆናል። በተነገረው ንዑስ ሐረግ ላይ ብታተኵር እነዚህ ኀሳቦች ሲፈልቁ ታያቸዋለህ።

እንግዲህ ለፍጥረት ህሉና ወይም ለአቋማቸው መነሻ፥ እርሱ «ወልድ» መሆኑ ከታወቀ ዘንድ፥ በመነሻነቱ «የፍጥረት በኵር» ሆነ ማለት ነው።

እነሆም፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ወልድን «የፍጥረት በኵር» ባለ ጊዜ፣ ያቀረባቸው እነዚህ በእርሱ «በወልድ» ፍጥረታት ሁሉ መፈጠራቸውንና፥ ለእርሱ በእርሱ መፈጠራቸውን፥ ከእርሱም የተነሣ በእርሱ መፈጠራቸውን የሚገልጹ መሠረታውያን አብነቶችን ነው።

ሐዋርያው ወልድን በኵር ሊያሰኙ ብቁ እንደሆኑ አምኖባቸው፣ በመሠረታዊ ብቃታቸው ምክንያት ማስረጃ አድርጎ እነዚህን መሠረታውያን አብነቶችን አቅርቦልናል።

እኛም ሐዋርያው ወልድን በኵር ይሰኝባቸዋል ብሎ ባቀረበልን ዘይቤያውያን ማስረጃዎች ብቁዕነት በመመራት፥ የሐዋርያውን ትምህርትና እምነት እንከተላለን።

ይህን በምናይበት ትይዩ ሐዋርያው ጳውሎስ ያቀረባቸው ማስረጃዎች በኵር ሊያሰኙ አይበቁም። ወልድ የፍጥረት በኵር እንዲሰኝ ከፍጥረት ጋር አብሮ



መፈጠር አለበት የሚል የአርዮሳውያን አባባል መሠረታዊ ከሆነ ትምህርት አስተሳሰብ ፈጽሞ የራቀና ውጭ ነው።

ይህም ይታወቅ ዘንድ ከዚህ ቀጥለን የምናቀርበው መሠረተ ኀሳብና አስተሳሰብ መመልከትና አመዛዝኖ መፍረድ ይጠቅማል።

1ኛ፥ በቀላሉ ቢታይ እንኳ «የፍጥረት በኵር» ሲል የተናገረው ሐዋርያ ጳውሎስ ወልድን «የፍጥረት በኵር» ላለበት ምክንያት ከላይ የተገለጹትን ማስረጃዎች አቅርቦአል እንጂ፣ «ፍጥረት ስለሆነ» የፍጥረት በኵር ነው ያላለ መሆኑን ማስተዋል ያሻል። በዚህም ወልድን «የፍጥረት በኵር» ሲል በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ለትምህርቱ አመንጭ ባለቤት ከሆነው ከጳውሎስ ይልቅ፣ አርዮሳውያን ይበልጥ ያውቃሉን? ደግሞስ የጳውሎስን ማስረጃዎችን ለመናቅና ለማቃለል የሚበቁ ሰዎች ናቸውን? የሚል ጥያቄ ይከተላል።

2ኛ፥ ወልድ ከእግዚአብሔር የተወለደበት ዘለዓለማዊ የባሕርይ ልደት እግዚአብሔራዊ ነውና። ተደልዞ ወይም ተፍቆ ተለውጦ ፍጥረት እንዲሆን ለማድረግ የማይቻል መሆኑ ነው። መዝ. 109/110/፥3። ም. 2፥7፡ ዮሐ. 16፥18-30። ዕብ. 1፥3።

እንግዲያው ወልድ ቃለ እግዚአብሔር ፍጥረታትን በራሱ፥ ለራሱ፥ ከራሱ የተነሣ ፈጠረና፣ ፍጥረትን ከፈጠረ ዘንድ የማይለወጠው ባሕርዩን ለውጦ «ፍጥረት ይሁን» ይባላልን? ደግሞስ ይሆናልን? ሚልክ. 3፥6። ዕብ. 1፥10-12። ም. 13፥8።

ለመሆኑ ፍጥረትን በመፍጠር ሥራ ተካካሁ ብሎ፥ የማይለወጠውን ባሕርዩን ፍጥረት እንዲሆን ለማድረግ ለዋጩ ማነው? የገዛ ራሱ ነው? ወይስ ከፍጥረት ወገን? ፍጥረትን ስትፈጥር ከፍጥረት ተካክተሃልና፥ እንግዲህ ፍጥረት መሆን አለብህ ብሎ የሚለውጠው አለን?

እስቲ ይህን በጸጥታ እንዲታሰብበት ለአንባቢ እንተወውና ቀጥሎ ወደሚገኙ ፍሬ ነገሮች እንሻገር።

በዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ባቀረበው ማስረጃ መሠረት፥ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ለፍጥረታት ህሉና «መገኘት» ወይም ለአቋማቸው አድራጊና ሠሪ ምክንያትና መነሻ እርሱ ራሱ መሆኑ ከታወቀ ዘንድ፡- በዚሁ ሁናቴ ደግሞ የፍጥረት በኵር ስለመሰኘቱ ሁኔታ አተኵረን ልናይ ይጋብዘናል።

እነሆም ሐዋርያው ጳውሎስ፡-

ለፍጥረታት አለቃና አበጋዝ መሆንን የሚያስገነዝብ ብኵርና በዚሁ መንገድ ሊኖር እንደሚችል እላይ በተዘረዘሩት ማስረጃዎቹ አስታውቆአል።

ሐዋርያው በዚሁ ብቻ ሳይወሰን አሁንም እላይ በተገለጸው ብኵርናና የብኵርና ይዞታ መሠረት የወልድ ዘለዓለማዊ የባሕርይ ልደቱ እንደተጠበቀ፣ በኵር

የተሰኘባቸውን ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን በዚሁ ጐን እያከታተለ ሲያቀርብልን እናያለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወልድ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን፥ የባሕርይ ልጅነቱ እንደተጠበቀ፣ የእግዚአብሔር ድርጊት «ሥራ» ለሆነ ሁሉ፥ ዓላማ ግንባር ቀደም ሆኖ በመገኘት በኵር የተሰኘባቸውን ተግባሮች እንደሚከተለው ይገልጻል።

እነሆም «በኵሩ ዘላዕለ ኵሉ ተግባሩ» ለተግባሩ ሁሉ በኵር ነው ማለቱን መሠረት አድርጎ በሚከተሉት ተግባሮች ወልድን በኵር ሲለው እናገኛለን።

ይኸውም የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና፣ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ቈላስ. 1፥15፤16።

በዚህ በሐዋርያው ገለጻ ውስጥ፥ ምን መሠረታዊ አሳብና ትምህርት እንዳለበት፣ ወደ ጥቅሱ በማተኰር እንይ። አዎን፥ ፍጥረታት ሲፈጠሩ ቅደም ተከተልና ልዩ ልዩ የዓይነትና የመጠን፥ የክብር ሆነ የአኗኗር፥ የመዓርግ ደረጃ፥ እንዲሁም የሚታይና የማይታይ አቋም ሁናቴም ይኖራቸዋል።

ይህም እርግጥ ነው። ዳሩ ግን በአፈጣጠር ረገድ አንዱ ሌላውን አልፈጠረውም። ድርጊት ወይም ተግባር ለሆነ ሁሉ ምክንያትና መነሻ በሆነው በቃለ እግዚአብሔር ወልድ እያንዳንዱ በነፍስ ወከፍ ተፈጥሮአል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ለዚሁ ሁሉ ፍጥረት አስገኚው ነው። ይህን ፍጥረት ካለመኖር ወደመኖር ያመጣው ዓለመ ዓለማት ነው። ዓለመ ዓለማት እንደመሆኑ መጠን ደግሞ «በኵር» ነው።

ሀ/ የሚታይ ፍጥረት በእርሱ «በወልድ» እንደተፈጠረ ሁሉ፥ የማይታይም በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። ለሚታየው፥ የማይታየው ፍጥረት አልፈጠረውም። ለማይታየውም ፍጥረት፥ የሚታየው ፍጥረት አልፈጠረውም። ዕብ. 11፥3።

ለ/ መናብርት ወይም ዙፋናት በእርሱ «በወልድ» እንደተፈጠሩ፣ አጋዕዝት ወይም ጌትነትም በእርሱ ተፈጥረዋል። መናብርት አጋዕዝትን አልፈጠሩም፣ አጋዕዝትም መናብርትን አልፈጠሩም።

ሐ/ አለቅነት «ሊቃናት» በእርሱ በወልድ እንደተፈጠሩ፣ ሥልጣናትም ኃይላትም በእርሱ ተፈጥረዋል። ሊቃናት ኃይላትን አልፈጠሩም። ኃይላትም ሊቃናትን አልፈጠሩም። ሁሉም በእርሱና ለእርሱ «ለወልድ» ተፈጥረዋል።

በጠቅላላው የተፈጠሩ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በነፍስ ወከፍ እያንዳንዱ በእርሱና በወልድ ለእርሱ ተፈጥረዋል።



ተፈጥሮአቸውም በእርሱ ለእርሱ፥ ከእርሱ የተነሣ ስለሆነ፣ በዘለዓለማዊ ልደት ከአብ ባሕርይ ተወልዶ፥ ከዘለዓለም ይኖር የነበረ እግዚአብሔር ቃል ወልድ አስገኚያቸው ሆነ። በመሠረቱም በኵራት ሆነ።

እነሆም፥ ሐዋርያው ጳውሎስ «በኵረ ፍጥረት፥ የፍጥረት በኵር» ያለበት ምሥጢርና ሁናቴ እላይ እንዳየነው በዝርዝር ማስረጃ አድርጎ ባቀረበው መግለጫ አስታውቆአል።

ከዚህ በላይ ያየነው የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ሥጋን ለብሶ ሰው ሳይሆን፣ ፍጥረታትን ከራሱ ለራሱ፥ ከርሱ የተነሣ ፈጥሮ በማስገኘቱ፥ የፍጥረት በኵር የተሰኘበትን አብነት እንዴት እንደሆነ የተገለጸበትን ክፍል ነው።

እነሆም ከዚህ ቀጥለን ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ለብሶ መሢሕ በሆነበት ተግባር፥ በኵር ተብሎ የተጠራባቸውን ድርጊቶችና ገለጻዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት እንመለከታለን።

እነሆም ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ተገልጾ፥ ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ከታወቀ በኋላ፣ በኵር ተብሎ የተጠራባቸው ድርጊቶች ከብኵርናው ስያሜ ጋር አብረው በግልጽ ተጽፈዋል።

ይህም አብነታዊ ትምህርቱን ብንመለከት መልካም ነው። በዘለዓለምነቱ የሚኖር ልዑል እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት በምክረ ትሥልስቱና በበጎ ፈቃዱ ዓለማትን ለመፍጠር በአንድያ ልጁ «በቃሉ» እንደወሰነና በእርሱ ለእርሱ ከእርሱ የተነሣ ዓለማትን እንደፈጠረ ታውቆአል። ሮሜ 11፥35-38። ኤፌ. 3፥9። ም. 1፥11።

## የድኅረ ትስብእት ብኵርና (ሥጋ ከመልበሱ በኋላ)።

ከዚህ በላይ ያየነው የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ሥጋን ለብሶ ሰው ሳይሆን፣ ፍጥረታትን በራሱ፥ ለራሱ፥ ከራሱ የተነሣ ፈጥሮ በማስገኘቱ የፍጥረት በኵር የተሰኘበትን አብነት እንዴት እንደሆነ የተገለጸበትን ክፍል ነው።

እነሆም ከዚህ ቀጥለን ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ለብሶ መሢሕ የሆነበትን ተግባር በኵር ተብሎ የተጠራባቸውን ድርጊቶችና ገለጻዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት እንመለከታለን።

እነሆም ቃለ እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ተገልጾ ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ከታወቀ በኋላ፣ «በኵር» እየተባለ ሲጠራ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን። በኵር እየተባለ የተጠራባቸው ድርጊቶች ወይም ተግባሮች ከብኵርና ስያሜ ጋር አብረው በግልጽ ተጽፈዋል።

ይህም አብነታዊ ትምህርቱን ከመሠረቱ ብንመለከተው መልካም ነው። በዘለዓለምነቱ የሚኖር ልዑል እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት በምክረ ትሥልስቱና በበጎ ፈቃዱ ዓለማትን ለመፍጠር በአንድያ ልጁ «በቃሉ»

እንደወሰነና በእርሱ ለእርሱ፥ ከእርሱ፥ የተነግ ዓለማትን እንደፈጠረ ታውቆአል። ሮሜ 11፥36፤38። ኤፌ. 3፥9። ም. 1፥11።

እንደዚሁም ሁሉ፥ በኋለኛው ዘመን በኃጢአት የወደቁትን የሰውን ልጆች ለማዳን በምክረ ትሥልስቱና በበጎ ፈቃዱ ወሰነና በዚሁ በአንድያ ልጅ በወልድ፥ የደኅንነት መደላድል የሆኑትን ድርጊቶች ሠራና አቆመ።

እነሆም ከዘለዓለማዊ ልደት ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተወለደው ልጅ ዘመኑ ሲደርስ ከድንግል ማርያም ሥጋን ለብሶ፥ ሰው ሆኖ ተገልጾ፥ ለደኅንነት መሠረት በሆኑት አምላካውያን ድርጊቶች «በኵር» እየተባለ ተጠራ።

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኵር» ተብሎ የተጠራባቸው ድርጊቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ተገልጸዋል።

1ኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ «የሙታን በኵር» ተብሎአል። ራእ. 1፥5።

2ኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ «የትንሣኤ በኵር» ተብሎአል።

3ኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኵረ አኃው» የወንድሞች በኵር ተብሎአል።

4ኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉ የምትሆን «የቤተ ክርስቲያን ራስ» ተብሎአል።

ይኸውና በዘለዓለም ልደት ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተወለደው ወልድ፥ በመሢሕነት አቋም በተገለጸ ጊዜ፤ የቆመባቸውን ግብራት ከላይ በጠቀስናቸው ዝርዝሮች ካየን፤ አሁን እንደምን ባለ አገባብ በኵር እንደተሰኘ መጽሐፍ ቅዱስ በሚሰጠው ገለጻ፤ በዝርዝሮቹ ላይ አጠር አጠር እያደረግን በሐተታ እናብራራለን።

## 1ኛ፥ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የሙታን በኵር ስለመሰኘቱ።

እነሆም የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ የሙታን በኵር ተብሎ ተጽፎለት እናገኛለን። ራዕ. 1፥5። ቆላስ. 1፥18። ይህስ እንዴት ነው? ብለን እንጠይቃለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ «የሙታን በኵር» ያለበትን ምሥጢር መጀመሪያነትን በሚያንጸባርቅ ትርጓሜ ወስደን በአፍአዊ ታሪክ ከተመለከትነው፤ የሐዋርያው አባባል ጨርሶ ሊገባን አይችልም ነበር።

ይኸውም፦ በሰው ልጆች ታሪክ መጀመሪያ የሞተው አቤል የተባለ የአዳም ልጅ መሆኑን እናውቃለንና ነው። ዘፍጥ. 4፥8-10። ታዲያ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሳያውቅ ቀርቶ ነውን? ይልቁንም እርሱ ከልጅነቱ ጀምሮ የኦሪትን ሕግ የተማረ ፈሪሳዊ ምሁር አይደለምን? የሐዋ.22፥3። ፊልጵ. 3፥5።

ከሰው ሁሉ በፊት በመጀመሪያ የሞተው አቤል መሆኑን ጳውሎስ ያጣዋል ብሎ ጳውሎስን የሚተች ሰው ጳውሎስ ማን መሆኑን የማያውቅ ይሆናል። ገላት. 1፥13፤14። ዕብ. 12፥24።



ቅዱስ ጳውሎስ በተገለጸለት መሠረታዊ ትምህርት ከአፍአዊ ታሪክም በላይ፥ ተመሥጥሮ የሚታየውን የወንጌል ጥቅስ መልእክት እንዳለው የታወቀ ነው። ኤፌ. 3፥3፤4። ቈላስ. 2፥2፤3።

እርሱም በእግዚአብሔር ፈቃድና ምክር፥ ዓላማና እቅድ ስለ ሰው ደኅንነት በክርስቶስ የሚከናወን ታላቅ ተግባር ነው። ይኸውና ጳውሎስ አመሥጥሮ የሚያተኵረው ወደዚሁ ነው።

እንዲህም ከሆነ ሐዋርያው ክርስቶስ «የሙታን በኵር» ሲል መጀመሪያነትን ከሚያንጸባርቅ ታሪካዊ ይዞታ ይልቅ፥ ከፍ ያለ ትምህርት ይኖረዋልና የአስተሳሰቡን ገለጻ በናፍቆት ብንከታተል ጠቃሚ ይሆናል።

እንደሚታወቀው ሁሉ ኃጢአት ወደ ዓለም በገባ ጊዜ ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ። የኃጢአት ዋጋ ሞት ነውና። ሮሜ 5፥5-12። ሕዝ. 18፥4። ሮሜ 6፥23።

ይህም በሰው ሁሉ ላይ የመጣው ሞት ሦስት ዓይነት ጠባይ እንዳለው በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾአል።

1፥ ሞተ ነፍስ። ዘፍጥ. 2፥17። ኤፌ. 2፥1። ሮሜ 6፥20፤21።
2፥ ሞተ ሥጋ «የሥጋና የነፍስ መለየት» ዘፍጥ. 3፥19። ሮሜ 5፥14።
3፥ ሞተ ፍዳ «ሞተ ኵነኔ፦» ዕብ. 9፥27። ራእይ 20፥14።

እነሆም፦ በኃጢአት ምክንያት በሰው ላይ በእነዚህ ሦስት ዓይነቶች የተገለጸው ሞት በሰው ሁሉ ላይ ነግሦ ሲኖር ነበር። ሮሜ 5፥12-14።

ዳሩ ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ፤ በባሕርይ ህልውና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አንድ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ በድንግል ማርያም ማኅፀን ሥጋ ሆኖ፥ ተወልዶ፥ ያለ ኃጢአት በዚህም ምድር ኖሮ ሲያበቃ፤ ስለ ሰው ሁሉ በቀራንዮ ተሰቅሎ በሞተ ጊዜ፤ ሞቱ የሰውን ሁሉ ሞት አጠቃለለ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የሰውን ሁሉ ሞት ስላጠቃለለው ስለአንዱ ስለ ክርስቶስ ሞት ሲናገር፦ «አንዱ ስለሁሉ ሞተ፤እንግዲያውስ ሁሉ ሞቱ» ብሎአል። 2ቆሮ. 5፥14።

አንዱ ክርስቶስ ስለ ሁሉ ስለ ሞተ ሁሉ መሞታቸው እንደምንድን ነው? ብለን መጠየቅ ያስፈልጋል።

በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን የቀመሰ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ሁሉ ቢሞት፤ ሁሉ ሞተዋል። ዕብ. 2፥9። ኢሳ. 53፥4-8።

ስለ ሁሉ የሚል የቤዛነት ምሥጢር ያለበት ቃል ሁሉን ወክሎ ወይም ስለ ሁሉ ተተክቶ መሞትን ያስገነዝባል። ወካዮቹም በፊንታቸው ለተተኩላቸው እንዲቆሙላቸው ያገናዝባቸዋል። በእግዚአብሔር ጸጋ ክርስቶስ የሞተው ስለ ሁሉ ነውና፤ አንድም ሳይቀር ሁሉ ሞተዋል። ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ ነውና

የወንጌል ምሥጢር ነው። 2ጢሞ. 1፥9፤10። ሞትና የሞት ባለሥልጣን ዲያብሎም የተሻሩበት በዚሁ አፈጻጸም ነው። ዕብ. 2፥14፤15።

ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ «የሙታን በኵር» ላለበት ማስረጃ በዚሁ ብቻ አይገታውም። ቀጥለን በምናቀርበውም ምክንያቱን ጕላ አድርጎ እያብራራ ያመጣዋል። ይኸውም:-

«በሕይወት ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ፣ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለ ሁሉ ሞተ» ይላል። 2ቆሮ. 5፥15።

«ያሉት ሁሉ ለራሳቸው እንዳይኖሩ፣ ነገር ግን ለሞተላቸውና ለተነሣላቸው እንዲኖሩ እርሱ ስለ ሁሉ ሞተ።» መባሉ እንደምንድን ነው? ብለን እንጠይቃለን።

ማንም ቢሆን ለራሱ የሚኖር ወይም ለራሱ የሚሞት አካቶ እስከማይገኝ ድረስ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ሁሉ ሞቶአልና የሰው ሁሉ ሞት በእርሱ ሞት ተጠቃሏልአል።

ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ አያይዞ የጻፈውን ይመለከቷል። ከእኛ አንድ ስንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፣ ለራሱም የሚሞት የለም። በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን፣ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን። ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና፣ ሕያውም ሆኖአልና። ሮሜ 14፥7-9።

አሁን አንባቢ:- ከሐዋርያው ጳውሎስ በቀረቡ ጥቅሶች በተለይም «ለእርሱ እንዲኖሩ» በሚሉ ሐረግ ላይ ቢያተኵር፣ ከዚህ ከክርስቶስ አምላካዊ አሠራር ምክንያትና ዋና የነገሩ ማዕከል ሆኖ የተገለጸ ነገር የቱ እንደሆነ ያስተውላል።

አዎን፥ ከዚህ አስቀድሞ ፍጥረታት በእርሱ «በወልድ» ሲፈጠሩ ለእርሱ ለወልድ በመፈጠራቸው ወልድ የፍጥረት በኵር እንደተሰኘበት የሚታወስ ነው። ለእርሱ እንዲሆኑ ተፈጥረዋልና።

በዚህ ጐን ደግሞ እርሱ አንዱ ክርስቶስ የሞተው፥ የሞቱት ሁሉ ለእርሱ ለሞተላቸውና ለተነሣላቸው እንዲኖሩ መሆኑን ሐዋርያው መሠረታዊ ምክንያት አድርጎ አቅርቦት ይታያል።

እነሆም ሐዋርያው ክርስቶስን «የሙታን በኵር» ያለበትን ምሥጢርም ለእርሱ እንዲኖሩ በሚል መሠረታዊ ምክንያት እንደገለጸ አተኵረው ሊገነዘቡት የሚገባ ነው።

ፍጥረታት በእርሱ የተፈጠሩበት ዋና ምክንያት፥ ለእርሱ «ለወልድ» እንዲሆኑና እንዲኖሩ መሆኑ:- የፍጥረት በኵር እንዳሰኘው ሁሉ፥ አሁን ስለሁሉ የሞተበት ምክንያትም፣ ሙታንና ሕያዋን የሆኑም፥ የሙታንና የሕያዋን ጌታ ይሆን ዘንድ ለሞተላቸውና ለተነሣላቸው ለእርሱ «ለወልድ» እንዲኖሩ ስለሆነ፣ በዚሁ መሠረታዊ ምክንያት «የሙታን በኵር» ሆነ።

ሐዋርያው እንዲህ አድርጎ ትምህርቱን አመሥጥሮ ይገልጸዋል እንጂ፣ አርዮሳውያን «የሙታን በኵር» ያለውን የሙታን መጀመሪያ ብለው ለአቤል እንደሚሰጡት ያለ አደናጋሪ ትችት አይደለም።



2ኛ፥ ወልድ «ኢየሱስ ክርስቶስ» የትንሣኤ በኵር ስለመባሉ:-

ኢየሱስ ክርስቶስ «የትንሣኤ በኵር» ሲባል፣ እርሱ ስለ ሰው ሁሉ ራሱን አሳልፎ በመስጠት በመስቀል ላይ ተሰቅሎና በመቃብር ተቀብሮ ከሙታን ተለይቶ ከመነሣቱ በፊት ከሞት የተነሡ ሰዎች እንዳልነበሩ ታስቦ የሚነገር አይደለም።

ልዑል እግዚአብሔር በነቢያቱ በኤልያስና በኤልሣዕ ሙታንን አስነሥቶ ነበር። 1ነገሥ. 17፥21-23። 2ነገሥ. 4፥32-37። ም. 13፥20፤21።

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምኵራቡን አለቃ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት አስነሥቶአታል። ሉቃ. 8፥49-56። ማር. 5፥38-34።

ደግሞ በናይን አገር የነበረችውን የአንዲት መበለት ልጅ ከሞት አስነሥቶታል። ሉቃ. 7፥1-16።

እንደዚሁም የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛርን ከመቃብር አስነሥቶታል። ዮሐ. 11፥43፤44።

እነዚህ ሁሉ በቀደምትነት እርሱ ክርስቶስ ከሙታን ከመነሣቱ በፊት ከሞት የተነሡ ነበሩ።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስን «የትንሣኤ በኵር» ሲለው፣ ታሪካዊ ቅድሚያን በሚያንጸባርቅ መንገድ አይደለም።

ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ «የትንሣኤ በኵር» ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲነገር፣ መሠረታዊ ምክንያቱ ምን ይሆን?

ከዚህ ቀደም ብለን እንዳየነው በመጀመሪያው አዳም በሰው ሁሉ ላይ የመጣው ሞት፥ በዓይነቱ ሞተ ነፍስ፥ ሞተ ሥጋ፥ ሞተ ፍዳ፥ «ሞተ ኵነኔ» ተብሎ በሰው ሁሉ ሞት ላይ ነግሦ ሲኖር፣ የሁለተኛው አዳም «የክርስቶስ» ሞት የሰው ሁሉ ሞት ሆኖ በመቈጠሩ ስለተጠቃለለ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሙታን በኵር እንደተባለ ተመልክተናል።

ይህንም በአእምሮአችን ይዘን በዚሁ ጐን የተነገረውን «ክርስቶስ የትንሣኤ በኵር» የተባለበትን መሠረት መረዳት ሩቅ አይሆንብንም።

መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለሚከተሉት ሦስት ተግባሮች መሠረት እንደሆነ ይነግረናል።

1ኛ፥ ስለ ሰዎች ኃጢአት እንደሞተ ለሚያምኑበት ያጸድቃቸው ዘንድ:- ከፍርድ ነፃ ያወጣቸው ዘንድ የማጽደቅ ትንሣኤ እንደሆነ:- ሮሜ 4፥24፤25።

2ኛ፥ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ለሚሳተፉም በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ የሚያስችላቸው የልቡና ትንሣኤ እንደሆነ፤ ሮሜ 6፥9-11። ኤፌ. 2፥1፤6፤7።

3ኛ፥ በጠቅላላው የሞቱትን ሁሉ ሊፈርድላቸውና ሊፈርድባቸው የሚነሣበት የሥጋ ትንሣኤ እንደሆነ ነው። ፊልጵ. 3፥21። ዮሐ. 5፥25-29።

ስለዚህም የአንዱ የክርስቶስ ትንሣኤ ለሰው ልጆች ሁሉ የትንሣኤ መሠረት ነው። ወደፊትም ለመቅደም ወደ ኋላም ፈጽሞ ለመቅረት እስከማያስችል ድረስ፣ ትንሣኤ የተባለውን ሁሉና የሚነሣውን ሁሉ ለራሱ እንዲሆን አድርጎበታልና። በዚሁ ብቁ መሠረታዊ ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ «በኵረ ትንሣኤ» ተሰኝቶበት እናገኛለን። 1ቆሮ. 15፥20-25። ቍጥር. 54፤55።

እነሆም የአንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የሰው ልጆች ሁሉ ሊነሡበት ላላቸው ትንሣኤ ግንባር ቀደም ወይም ፈለግ እንደሆነ ተገልጾ የሚታይበት መንገድ ይኸው ነው። የሐዋ. 17፥30፤31።

የክርስቶስ ትንሣኤ በታሪክ ረገድ ከእርሱ በፊት እንደተነሡ እንደነ አልዓዛር ትንሣኤ ያለ አይደለም።

የክርስቶስ ትንሣኤ ከሥር ከመሠረቱ የአዳም ኃጢአት ካመጣው በሰው ሁሉ ላይ ሰፍኖና ነግሦ ከሠለጠነው ሞት የሚያስነሣና ማንንም ሳያስቀር በማስነሣት ሁሉን ለራሱ እንዲሆን የሚያስገዛበት ትንሣኤ ነው። 1ቆሮ. 5።

ሁሉን በራሱ አስነሥቶ ለገዛ ራሱ እንዲሆን ማስገዛቱ ደግሞ በኵር ሊያሰኘው መቻሉ መሠረታዊና ብቁዕ ምክንያት ነው። 1ቆሮ. 15፥20-23።

## 3ኛ፥ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ «የወንድሞች በኵር» ስለመባሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለብዙ ወንድሞች በኵር» ተብሎ ተነግሮለት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ይገኛል። ጥሬ ቃሉን አይተን ለመረዳት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች ከጻፈው መልእክቱ ውስጥ በምዕራፍ 8፥28-30። ላይ ተገልጾ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔር ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚደረግ እናውቃለን። ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአልና፣ አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፣ የጠራቸውን እነዚህን ደግሞ አከበራቸው ይላል።

ይህስ እንደምንድን ነው? ቢሉ፣ ቃለ ወንጌሉን አምነው በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ ሀብተ ወልድናን ስመ ክርስትናን የተቀዳጁ ክርስቲያኖች ሁሉ እንደሚያውቁት፣ ወልድ ተብሎ ለተቀበሉት ሁሉና በስሙ ለሚያምኑ፣ በወልድነቱ ሥልጣን ሰጣቸው። ቲቶ 3፥4፤4። ዮሐ. 1፥12። በሰጣቸው በልጅነት መብትም እንዳይሰጉ መልኩን እንዲመስሉ አድርጎ፥ ሳያፍርባቸው ወንድሞቼ በማለቱ ቀደሳቸው። የዚህንም እውነት፣ በሚከተሉት ጥቅሶች ተመልከት። ዕብ. 2፥10-12፤17።



በእነዚህ ጥቅሶች እንዳየነው ቤተ ክርስቲያን በቤተ መቅደስ፥ በሙሽራ ስትመሰል ክርስቶስ ደግሞ ራስዋ ሆኖ ተገልጾአል።

በዚሁ ምሥጢር ደግሞ፦ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ አካሉ ሆና እርሱ ደግሞ የእርስዋ የአካሉ ራስ ወይም አለቃ መሆኑ ነው።

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ መሆኑ፣ እንደምንድን ነው? ቢሉ የተዋበችና ቅድስት ያለ ነውር የሆነችና ክብርት አድርጎ ለራሱ እንዲያቀርባት ስለፈለገ በመሆኑ ላይ ተመሥርቶ ይገኛል።

ይኸውም፦ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ በሚከተለው ጥቅስ ጐላ አድርጎ አቅርቦታል። «ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑን እንደወደዳት... በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለእርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። እድፈት የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ» ይላል። ኤፌ. 5፥26፤27።

አንባቢ ሆይ፥ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ በሚለው ላይ ይልቁንም ለራሱ በሚለው ምክንያታዊ ማስረጃ ላይ ዓይነ ልቡናህን ብታሳርፍ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነበትን አገባብ ልታይና ልትረዳ ትችላለህ።

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገላትንና የፈጸመላትን ተግባሮች ሁሉ ምን አስቦ ነው? ተብሎ ቢጠየቅ፥ እርሱ ራስዋ እንዲሆን እርስዋም ደግሞ ለእርሱ አካል እንድትሆን ስለፈለገ መሆኑ አሣሪ ጉዳይ ሆኖ ተገልጾአልና፣ እንኪያስ እርስዋ አካሉ፥ ከሆነች ዘንድ እርሱ ራስዋ ለመሆኑ ብቁ ማስረጃ አልሆነምን? ራእይ 19፥8፤9። መኃ.መኃ.2፥16። መዝ. 44/45/፥9-11።

እነሆም ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ የተባለበትን መሠረታዊ ምክንያት እንዲህ አድርጎ ሐዋርያው ጳውሎስ አቅርቦታልና ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ ሆነ ማለትን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራስ እንዲሆን ዘለዓለማዊነቱን ትቶ ከእርስዋ ጋር ተፈጠረ ብለን አናምንም። እንኳን አባባሉ አስተሳሰቡም ክህደት ነው።

እነሆም ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ወልድ ቃለ እግዚአብሔር፦ የእግዚአብሔር ተግባር ለሆነ ሁሉ ፈጣሪና አዳኝ በመሆን ግንባር ቀደም፥ ፈለግ በመሆን በኵር ተብሎአል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ተግባሮች ሁሉ ለእርሱ እንደሆኑና በእርሱ እንደተንጠለጠሉበት አድርጎ እንዳቀረበው ይታያል። ይኸውም፦ በሥጋ ከመገለጹ በፊትና በሥጋ ተገልጾ መሢሕ ሆኖ በመምጣቱ።

ሀ/ በሥጋ ከመገለጹ አስቀድሞ፦

1፥ ለፍጥረት «መፈጠር በኵር»

በእነዚህ ጥቅሶች እንዳየነው ቤተ ክርስቲያን በቤተ መቅደስ፥ በሙሽራ ስትመሰል ክርስቶስ ደግሞ ራስዋ ሆኖ ተገልጾአል።

በዚሁ ምሥጢር ደግሞ፡- ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ አካሉ ሆና እርሱ ደግሞ የእርስዋ የአካሉ ራስ ወይም አለቃ መሆኑ ነው።

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ መሆኑ፣ እንደምንድን ነው? ቢሉ የተዋበችና ቅድስት ያለ ነውር የሆነችና ክብርት አድርጎ ለራሱ እንዲያቀርባት ስለፈለገ በመሆኑ ላይ ተመሥርቶ ይገኛል።

ይኸውም፡- ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ በሚከተለው ጥቅስ ጉላ አድርጎ አቅርቦታል። «ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑን እንደወደዳት... በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለእርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። እድፈት የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ» ይላል። ኤፌ. 5፥26፤27።

አንባቢ ሆይ፥ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ በሚለው ላይ ይልቁንም ለራሱ በሚለው ምክንያታዊ ማስረጃ ላይ ዓይነ ልቡናህን ብታሳርፍ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነበትን አገባብ ልታይና ልትረዳ ትችላለህ።

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገላትንና የፈጸመላትን ተግባሮች ሁሉ ምን አስቦ ነው? ተብሎ ቢጠየቅ፥ እርሱ ራስዋ እንዲሆን እርስዋም ደግሞ ለእርሱ አካል እንድትሆን ስለፈለገ መሆኑ አሣሪ ጉዳይ ሆኖ ተገልጾአልና፣ እንኪያስ እርስዋ አካሉ፥ ከሆነች ዘንድ እርሱ ራስዋ ለመሆኑ ብቁ ማስረጃ አልሆነምን? ራእይ 19፥8፤9። መኃ.መኃ.2፥16። መዝ. 44/45/፥9-11።

እነሆም ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ የተባለበትን መሠረታዊ ምክንያት እንዲህ አድርጎ ሐዋርያው ጳውሎስ አቅርቦታልና ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ ሆነ ማለትን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራስ እንዲሆን ዘለዓለማዊነቱን ትቶ ከእርስዋ ጋር ተፈጠረ ብለን አናምንም። እንኳን አባባሉ አስተሳሰቡም ክህደት ነው።

እነሆም ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ወልድ ቃለ እግዚአብሔር፡- የእግዚአብሔር ተግባር ለሆነ ሁሉ ፈጣሪና አዳኝ በመሆን ግንባር ቀደም፥ ፈለማ በመሆን በኵር ተብሎአል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ተግባሮች ሁሉ ለእርሱ እንደሆኑና በእርሱ እንደተንጠለጠሉበት አድርጎ እንዳቀረበው ይታያል። ይኸውም፡- በሥጋ ከመገለጹ በፊትና በሥጋ ተገልጾ መሢሕ ሆኖ በመምጣቱ።

ሀ/ በሥጋ ከመገለጹ አስቀድሞ፡-

1፥ ለፍጥረት «መፈጠር በኵር»



ሀ/ ለሚታየውና ለማይታየው ፍጥረት

ለ/ ለመናብርት «ዙፋናት»

ሐ/ ለአጋዕዝት «ጌትነት»

መ/ ለሥልጣናት «ሥልጣናት»

ሠ/ ለኃይላት «ለመላእክት» «አለቅነት ወይም ሥልጣናት»

ለ/ በሥጋ ተገልጾ መሢሕ ከሆነ በኋላ፣

ሀ/ ለሙታን በኵር

ለ/ ለሕያዋን ለሚነሡ በኵር።

ሐ/ ለወንድሞች በኵር።

መ/ ለአካሉ ለቤተ ክርስቲያን ራስ።

በጠቅላላ አብ ፍጻሜ ሁሉ ያድርበት ዘንድ ወዶአል። ቈላስ. 1፥25-20። ለሁሉም መነሻ እርሱ ነው። እርሱ ግን በአብ ህልው ሆኖ በዘለዓለማዊነቱ የኖረ ነው። 1ዮሐ. 1፥1፤2።

አርዮሳውያን ከዚህ በላይ ያሳየነውን ገለጻ ተረድተው ወደላይ ከፍ ብለው ቢመለከቱ ኖሮ፥ «በኵር» በሚለው ራስ ላይ የመለኮታዊ ባሕርይ ጌጥ ሲከልለውና ሲጠብቀው ሊመለከቱ በቻሉ ነበር። ይኸውም «የማይታይ የእግዚአብሔር ምሳሌ» የሚል ኃይለ ቃልና መግለጫ ነው።

## «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ»

ሐዋርያው ጳውሎስ «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ» ሲል ለበኵር መግለጫ ማድረጉ እንደምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ ቀጥሎ ያለውን አሳብ ልናገኝ እንችላለን።

1ኛ፥ ምናልባትም አንዳንዶች ሰዎች «በኵር» የተባለውን ስም ወስደው በመናኛ አፈታት ተርጕመው እንዳይሰናከሉበት ይህን አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ስለተረዳው ነው ልንል እንችላለን።

2ኛ፥ በዚሁ ጥቅስ «በኵር» ብሎ የሚናገርለት ማንን ሲያይ እንደሆነ ሐዋርያው የገዛ ራሱ ጠንቅቆ ያውቀዋልና ነው።

ሐዋርያው በዚሁ ክፍል ውስጥ «በኵር» ብሎ የሚናገርለት ለዚያ ከሁሉ በላይና ለተባረከ ታላቅ አምላክ፥ ዓለሙ ሁሉ በእርሱ ለእርሱ ለተፈጠረ፥ የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ የባሕርዩ ምሳሌ ለሆነ፥ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ለሚመራ፥ ለእግዚአብሔር አንድያ ልጅ እንደሆነ፣ የሚያውቅና

ዐውቆም የሚያምንበት ነው። ሮሜ 9፥5። ቲቶ 2፥13። ዕብ. 1፥2፤3። 1ቆሮ. 2፥8። ቈላስ. 1፥14፤15።

ስለዚህ ሐዋርያው በዚህ ጥቅስ የእግዚአብሔር ቃል ወልድን «በኵር» በሚል ገለጸው ላይ ከአንዳንዶች ወገኖች «በኵር» ተብሎ ለተነገረው ቃል መናኛ አፈታት እንዳይሰጠው በእግዚአብሔር ልጅና እግዚአብሔር በቃሉ በፈጠራቸው ፍጡራን መካከል ያለውን የጠባይዐዊ መደብ ልዩነት ወስኖ በሚገልጽ፦ «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ» በሚል የመጠበቂያ ቅጽል ለበኵር ቀጽሎፈት እናያለን።

ይኸው በኵር ለሚል ስም ገላጭ አድርጎ «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ» ሲል ለበኵር የቀጸለው ቅጽል በኵርን ከፍጡራን፥ እንዲሁም ፍጡራንን ከበኵር አለመቀላቀላቸውን ገልጾ በየጠባይዓዊ አቋማቸው ብቻ ሆነው እንዲታዩ ልይት አድርጎ የሚያሳውቅና የሚያስረዳ ኃይለ ቃል አይደለምን?

አዎን «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ» የሚል ቃል ማንም ቢሆን ሊያየው የማይችልን እግዚአብሔርን፥ አንድያ ልጅ ብቻ ሆኖ ለሚገልጸው ለባሕርይ ልጅ ፍጥረታትን ካለመኖር ወደመኖር ላመጣና ላስገኘ ለበኵሩ ካልሆነ በቀር ማንንም ፍጡር የማያዳብል ለማዳበል የማያስችልና ማንንም ወደዚሁም ማዕረግ ለመድረስ የማያበቃው ቅጽል ነው። 1ጢሞ. 6፥16። ዕብ. 1፥3።

ከዚሁም ጋር ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ «የማይታይ የእግዚአብሔር ምሳሌ» ብሎ ለፍጥረት ቀጽሎለት እንዳልተገኘ አንባቢው መቼውንም ያስተውላል።

እንግዲህ በዚህ ክፍል በኵር የተሰኘው ወልድ መሆኑንንና እርሱም የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ እንደተባለ አይተናል። ታዲያ «በኵር» የተሰኘው ወልድ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ካየን ዘንድ እግዚአብሔርን በምን ይመስለዋል? ብለን እንድንጠይቅ አስፈላጊ አይደለምን?

## አዎን «በኵር የተሰኘው ወልድ እግዚአብሔርን በምን ይመስለዋል»?

አስቀድመን፦ «የእግዚአብሔር ምሳሌ» ሲባል ምን ማለት ነው? ብለን እንጠይቃለን። ጥያቄውም ቀለል ካለው ደረጃ ብንጀምር ክፉ አይደለም። አዎን፥ እግዚአብሔር ምንን ወይም ማንን ይመስላል? ቀይ ነው ወይስ ጥቁር? ረጅም ነው ወይስ አጭር? ቀጭን ነው ወፍራም?

በበኩሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እየኖረ እንዲህ ባለ ሁኔታና መልክ እግዚአብሔርን የሚገምተውና የሚያስበው ሰው ያለ አይመስለኝም። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ህላዌ የተማረ ሰው እርሱ እግዚአብሔር ብቻ የማይሞት፥ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል። አንድ ሰው ስንኳ አላየውም ሊያየውም አይቻለውም። 1ጢሞ. 6፥16።

ዳግም መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም።



ዮሐ. 1፥18። ም. 6፥46።

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው። የሚሰግዱለትም በመንፈስ ብቻ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» ተብሎ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረው ስለ እግዚአብሔር እንደሆነ ያውቃልና ነው። ዮሐ 4፥24።

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚሁ ጥቅስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ የሚል ቃል እንደመሆኑ ሁሉ በሚታይ ቀለምና፥ መጠን፥ በሚዳሰስና በሚለካ፥ ባጭሩም በአምስት ህዋሳት በሚገኝ መታወቂያ የሚታወቅ እንዳልሆነ አስገንዝቦአል። ኢሳ. 44፥12-17። ኤር. 10፥ 2-11።

ይህም ይታወቅ ዘንድ በመጽሐፍ ቅዱስ በማያስተባብሉት ገለጻ ከተነገረው በጥቂቱ ጠቅሰን እንመለከታለን፦

«እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ ይላል ቅዱሱ» ኢሳ. 40፥25። ኢሳይያስ፦ «እግዚአብሔርን በምን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በማን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?

«የተቀረፀውን ምስል ሠራተኛ ሠርቶታል።»

«አቤቱ ከአማልክት እንዳንተ ያለ ማነው?» ዘጸአ. 15፥19።

ሙሴ፦ «እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ። እንዳትረክሱ የተቀረጸውን ምስል እንዳታደርጉ።» ዘዳግ. 4፥15።

ዳዊት፦ «አቤቱ ከአማልክት የሚመስልህ የለም። እንደ ሥራህም ያለ የለም።» መዝ. 85/86፥8።

ጳውሎስ፦ «እግዚአብሔርን በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም።» ይላል። የሐዋ. 17፥29

ሰሎሞን፦ «የእስራኤል አምላክ አቤቱ በላይ በሰማይ በታችም በምድር አንተን የሚመስል አምላክ የለም።» 1ነገሥ. 8፥23።

ስለዚህ የማይታየውን የእግዚአብሔርን መልክ የሚገልጽ ነገር በዓለማችን እንደማይገኝ የታወቀ የተጠነቀቀ ጉዳይ ነው። ሮሜ 1፥21-25።

ወልድ ግን የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ቈላስ. 1፥15። 2ቆሮ. 4፥4።

የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ የሆነበትን ምሳሌ የሚመስል ከፍጥረት ወገን የለም፤ አይገኝምም። ዘኍል. 12፥9።

እርሱ ወልድ ብቻ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑን ሲያረጋግጥ እግዚአብሔር ሌላ ምሳሌ የለኝም አለና፤ ከእርሱ ከወልድ በቀር የሚመስለው የሚተካከለው እንደሌለ ወስኖ በቁርጥ አስታወቀ። ኢሳ. 40፥25፥18። ዕብ.

1፥3። ዮሐ. 18፥30። ስለ ልጁ ልጅ ሆኖ የአካሉም ራዕይ ሆኖ ይመስለዋልና፣ እርሱ ብቻ ሊገልጸው ብቁዕ ስለሆነ ነው። ዕብ. 1፥1-3። «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው ከቶ አንድ ስንኳ የለም፣ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድያ ልጁ እርሱ ተረከው» ዮሐ. 1፥18።

## ወልድ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ስለመባሉ፡-

ወልድ የእግዚአብሔር ምሳሌ የተባለበትን መሠረት ከመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው በሁለት ትርኢታዊ ስልት ብንመለከት ይበልጥ ለማስተዋል እንችላለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

1ኛ፥ በተከሥቶ ህልውና ረገድ ይህም ማለት ባህርይንና የባህርይን ግብር በመግለጽ የሚታይ የመመሳሰል ይዞታ፡-

2ኛ፥ በትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» መመሳሰል በአንድ አይነት አቋም የመታየት ይዞታ ነው።

በእነዚህ በሁለት አርእስቶች ያለውን የመመሳሰል ሁኔታ እንደ ቅደም ተከተሉ እንመለከታለን።

አስቀድመን በአንደኛ ትርኢታዊ አቀራረብ ስላለው ባህርይና የባህርይ ግብርን ስለመግለጽ በተነገረ መመሳሰል፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተመለከተውን እንይ፡-

ሀ/ መጀመሪያ ነገር ልጁ «ወልድ» ልጅ በመሆን፡- እግዚአብሔርን አባቱን ይመስለዋልና ልጅ ሆኖ አባቱን መግለጹ ነው። ምሳሌ 30፥4።

ይህም ንባብ እንዲብራራ ከተፈለገ ግንም ቢሆን እግዚአብሔርን ሊተርከው ወይም ሊገልጸው ቀርቶ፥ ከቶም እግዚአብሔርን ያላየ መሆኑን፥ በአንድ ወገን ማየትና በዚያው ንጽጽር ግን፣ ወልድ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ በመሆን አባቱን አክሎ መስሎ በአንድያ ልጅነቱ የማይታየውን እግዚአብሔርን ተርኮትና ገልጾት መገኘቱን መረዳት ነው። ዮሐ. 1፥18። ም. 6፥46

በዚህም ከእግዚአብሔር ባህርይ ባልተወለዱት ፍጡራን መካከልና በእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ ወይም በአንድያ ልጅ መካከል ያለውን ፈጽሞ የተራራቀ ልዩነት እንዳለ በጉልህ እነጻጽር፡-

ለ/ ወልድ ፍቅር ለሚሆን ለእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ የእግዚአብሔርን ፍቅር በራሱ ገልጾአል። 1ዮሐ. 4፥7። ዮሐ. 15፥13። 1ዮሐ. 3፥16።

ሐ/ ወልድ በባሕርዩ ጻድቅ ለሚሆን ለእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ የእግዚአብሔርን ፍቅር በራሱ ገልጾአል። ኤር. 9፥24። መዝ. 118/119/፥137፣142። ም. 142/143/፥1-2። ዳን. 9፥14። ኤር. 33፥16። ም.23፥5፣6። ሮሜ 3፥21-25። ገላ. 2፥16።



መ/ ወልድ የእግዚአብሔርን ምሳሌ ሆኖ የማይጠፋና ጨለማ የሌለበትን የእግዚአብሔርን ብርሃን በራሱ አብርቶ አሳይቶአል። 1ጢሞ. 6፥16። 1ዮሐ. 1፥7። ሉቃ. 1፥78፣79። ዮሐ. 1-9። ም. 12፥44-46።

ሠ/ ወልድ ሁሉን የፈጠረ የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ፥ ፍጥረታትን እምኀበ አልቦ ኀበቦ «ካለመኖር ወደ መኖር» በማስገኘት የተፈጠሩት ፍጥረታት የአንዱ የእግዚአብሔር ፍጡራን መሆናቸውን ገልጾአል። ዮሐ. 1፥3። ቆር. 8፥6። ዕብ. 1፥1-3። ሮሜ 11፥36።

ረ/ ወልድ የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ፥ የባሕርዩን ክብር አንጸባርቆአል። ዕብ. 1፥3። ሚልክ. 4፥2።

ሰ/ ወልድ ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ በችሎቱ ወይም በከሀሊነቱ ቃል ሁሉን ደግፎ መያዙን ገልጾአል። ዕብ. 13። ዮሐ. 1፥3።

ሸ/ ወልድ የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ፥ በቃልነቱ የእግዚአብሔር ልብንና ሕይወትን ገልጾአል። አሞጽ 4፥13። ሮሜ 11፥34-36።

ባጭሩ ወልድ የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ፥ የማይታይ ግብረ ባሕርዩን ገልጾአል። ይኸውም፡- እግዚአብሔራዊ አፍቃሪነቱን ቸርነቱን፥ ለጋሥነቱን፥ መሐሪነቱን፥ ርኅራኄውን፥ ጠባቂነቱን፥ እውነተኛነቱን፥ ቀጥተኛነቱን፥ ትክክለኛነቱን፥ ፈራጅነቱን ገልጾአል።

አዎን፥ በዚህ ሁሉ አባቱን መስሎ የአባቱን ጠባይና ግብር ገልጾአልና ወልድ «የእግዚአብሔር ምሳሌ» መባሉ በእውን ከሥተት የተመሰከረ ነው። ዮሐ. 5፥30-32።

በአጠቃላይም፡- ወልድ እግዚአብሔር አብን ይመስለው እንደሆን፥ ወይም አይመስለው እንደሆን፣ የገዛ ራስን በቅንነትና በትሕትና መርቶ እርሱን ማየትና አባቱን አይቶ ማስተያየት ነው።

የገዛ ራሱ ወልደ እግዚአብሔር የሰው ልብ እንዲነጻ የሰጠው መመሪያ ይኸው ነው። «እኔን ያየ አብን አየ» ብሎአል። ዮሐ. 14፥9።

ይኸውና አብ በወልድ ወልድም በአብ ባላቸው በባሕርያዊ የህልውና መገናዘብ መሠረት፣ በተከሠተ ህልውና ረገድ ወልድ በአብ እንዳለ ሆኖ፥ የእግዚአብሔር አብ መልክ በወልድ መልክ መታየቱ «መገለጹ» ወልድ የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ፥ አባቱን እንደሚገልጸው በዚሁ ማስተዋል ነው። ዮሐ. 14፥8-11። ም. 5፥37።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ፥ ወልድን ዘውእቱ አርአያሁ ለእግዚአብሔር፥ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ የሚኖር ሲል ይህን ትምህርት ይበልጥ ያጕላዋል። ፊል. 2፥6።

እነሆም ወልድ እዚህ ላይ በተመለከትነው ሁሉ የባሕርይ አባቱን እግዚአብሔርን ሲገልጽ፥ የእግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑን አሳይቶአል። አሁን

ደግሞ፡- በትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት ያለውን መመሳሰል እንመለከታለን፡-

ይህ በዚህ ርእስ የተገለጸው ትምህርት መቼም ለአርዮሳውያን እንደ ማይዋጥላቸው እናውቃለን። ይሁን እንጂ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመሥርቶ የተገለጸው ቀዋሚ ትምህርት ለአንዳንድ ሰዎች አይዋጥላቸውም በማለት ቀዋሚ ትምህርትን ሠርዞ እንደሌለ አድርገው ለማስቀረት ለሚያደርጉት ጥረት እጅን መስጠት ይገባል ብለን አናስብም።

መጀመሪያ ነገር፡- ይህ የአካላት ዕሪና «መተካከል» መመሳሰል በአንዱ እግዚአብሔር በሦስት አካላት አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ጉልህ ሆኖ የተገለጸ የታወቀ ነገር ነው። ማቴ. 28፥19-20። ም. 3፥17። ሉቃ. 3፥21፤22። 2ቆር. 13፥14።

እነሆም አንዱ እግዚአብሔር በሦስት አካላት ይኸውም አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የዕሪና የመተካከል መመሳሰል እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ተገልጾልን እናገኛለን። በዚሁ ትምህርታዊ ገለጻው ወልድ የእግዚአብሔር ምሳሌ የተባለበትን ምሥጢርም በይበልጥ ለመረዳት የሚያበቃ ትምህርት አለበት፡-

ይኸውም፡- ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱትን ዝርዝር ነገሮች በጥንቃቄ ብንመለከታቸው የምንረዳው ነው።

1ኛ፥ እነሆም የማይወሰን አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ 1ነገሥ. 8፥27። በአካላት ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት ወይም መመሳሰል ሲታይ ደግሞ፡-

አብ የማይወሰን ኢዮብ 36፥26።

ወልድ የማይወሰን ኤፌ. 4፥9፤10።

መንፈስ ቅዱስ የማይወሰን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። መዝ. 138፥/139/፥7-9። ዮሐ. 14፥16፤17።

2ኛ፥ ረቂቅና የማይዳሰስ አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፤ ዮሐ. 5፥24። በአካላት ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት «መመሳሰል»። ደግሞ፡-

አብ ረቂቅ የማይዳሰስ። ዮሐ. 4፥23፤24።

ወልድ ሥጋ ከመልበሱ በፊት ረቂቅ የማይዳሰስ። ቈላስ. 1፥16።

መንፈስ ቅዱስም የማይታይ ረቂቅና የማይዳሰስ መንፈስ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። ዮሐ. 3፥5-8።



3ኛ፥ ቀዳማዊ ዘለዓለማዊ አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፤ ኢሳ. 44፥6። መክ. 89/90/ በአካላቱ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት «መመሳሰል» ያየን እንደሆነ ደግሞ ፡-

አብ ቀዳማዊ ዘለዓለማዊ። ኢሳ. 63፥16።

ወልድ ቀዳማዊ ዘለዓለማዊ። ዮሐ. 1፥1፤2።

መንፈስ ቅዱስ ቀዳማዊ ዘለዓለማዊ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። ዕብ. 9፥14።

4ኛ፥ በመሠረቱ የማይለወጥ የማይለዋወጥ አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፡- በአካላቱ ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት «መመሳሰል»፡-

አብ የማይለወጥ የማይለዋወጥ ሚልክ. 3፥6።

ወልድ የማይለወጥ የማይለዋወጥ፤ ዕብ. 13፥8። ም. 1፥10-12።

መንፈስ ቅዱስ የማይለወጥ የማይለዋወጥ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን።

5ኛ፥ በመሠረቱ ፍጹም፥ የባሕርይ ባለጸጋ «ባዕል» አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በአካላት የዕሪና «የመተካከል» አንድነት መመሳሰል ደግሞ፡- አብ የባሕርይ ባለጸጋ «ባዕል»። ሮሜ 11፥33። ወልድ የባሕርይ ባለጸጋ «ባዕል» 2ቆር. 8፥9። መንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ባለጸጋ «ባዕል» እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። 1ቆር. 12፥11-13።

6ኛ፥ በመሠረቱ ሁሉን የሚችል አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፤ ኢዮብ 42፥2። በአካላት ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል አንድነት «መመሳሰል» ደግሞ፡- አብ ሁሉን የሚችል፡- ዘጸአ. 6፥2። ኢዮብ 40፥2። ወልድ ሁሉን የሚችል። ዕብ. 1፥3። መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የሚችል እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን፡- መክ. 138/139/፥7-14።

7ኛ፥ በመሠረቱ ሁሉን የሚያውቅ አንዱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ፡- በአካላት ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል አንድነት» መመሳሰል ደግሞ፡-

አብ ሁሉን የሚያውቅ።

ወልድ ሁሉን የሚያውቅ፡- ዮሐ. 2፥14፤15። ም. 16፥30።

መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የሚያውቅ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። መዝ. 138/139/፥7-12።

8ኛ፥ በመሠረቱ የሁሉ ጌታ አንዱ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ ተገልጾ ሳለ፡- 1ቆር. 12፥6። በአካላቱ ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት መመሳሰል ደግሞ፡-

አብ የሁሉ ጌታ፦

ወልድ የሁሉ ጌታ። የሐዋ. 10፥36።

መንፈስ ቅዱስ የሁሉ ጌታ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን። 1ቆሮ. 12።

9ኛ፥ በመሠረቱ አንዱ እግዚአብሔር ብቻ አንድ አምላክ መሆኑ ታውቆ ሳለ፦ 1ጢሞ. 1፥17፤11። በአካላት ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት «መመሳሰል» ደግሞ፦

አብ አምላክ፦ ገላ. 1፥4። ወልድ አምላክ ሮሜ 9፥5። 1ዮሐ. 5፥20። ይሁዳ 25። 1ዮሐ. 5፥19፤20።

መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጾ እናገኛለን፦ የሐዋ. 5፥4፤9፡ 1ቆሮ. 12፤6፤፥11።

እነሆም እዚህ ላይ ባቀረብነው መዘርዝር እንደተመለከትነው አብ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በትርኢታዊ የዕሪና «መተካከል» አንድነት ያላቸው ፍጹም አንድነት ወይም ተመሳሳይነት በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው መሠረት ተመለከትን።

እነሆም አሁን ሐዋርያው ጳውሎስ ወልድን «የማይታይ እግዚአብሔር ምሳሌ» ያለበትን ምሥጢርና ስንፍፍቀው የነበረን ገለጻ ከመሠረቱ እንደተረዳኝ እስባለሁ።

እነሆም ከዚህ በላይ እንዳየነው፤ «አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ» በዚሁ ትርኢታዊ የዕሪና «የመተካከል» አንድነት ያለውን ፍጹም የሆነ ተመሳሳይነትን አየን፦ እንግዲህ «የእግዚአብሔር ምሳሌ» ነው በሚል መሠረታዊ ቃል ተነሥተን ወልድ አብን እንዴት ይመስለዋል? ብለን ለጠየቅነው ከዚህ በላይ በተገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፤ መልሱን ሳንረዳ አንቀርም። ሐዋርያው ወልድን የእግዚአብሔር ምሳሌ ያለበትን ምሥጢር ማየት አይገደንም። ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ምስጋና ክብር ይሁን አሜን።

## የአርዮሳውያን ስድብ።

አርዮሳውያን የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ከባሕርየ መለኮቱ ውጭ አድርገው ለማሳየት ለማቃለል ያልተጠቀሙበት ስድብና ነቀፋ የለም ይህም። በዕውቀትና ከፍ ባለ መራቀቅ እንጂ በቀላሉ እንደመጣላቸው በመናገር ብቻ ያደረጉት አይደለም።

አርዮሳውያን ቃለ እግዚአብሔር ወልድን በተቻላቸው ኃይል ለማጥቃት አስበውበት ሆነ ብለው አቅደው የተነሡበት መሆኑን ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ቢኖር የሚከተለውን ይመልከት፦



እነሆም፦ «እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን» ብለው በሰየሙት መጽሐፋቸው በገጽ 38 መሥመር 17 ላይ፥ የዚህ ዓለም አምላክ የተባለው ዲያብሎስ ከመፈጠሩ ከብዙ ጊዜ በፊት ወልድ ተፈጠረ። ብለው ጽፈዋል። በሌላ ቦታ ደግሞ «የአጥቢያ ኮከብ የተባለው ዲያብሎስ ነው» ይላሉ።

አንባቢ ሆይ፦ ይህ አነጋገር ከአርዮሳውያን አንደበት ሲወጣ፤ ከዚህ አልፎም አርዮሳውያን በጽሑፍ ጽፈው እየናኙት ስታይ፤ የሚያስደነግጥ ሁኔታ ሳይሰማህ አይቀርም፦

ይኸውም አርዮሳውያን እስከዚህ ድረስ በእግዚአብሔር ቃል ወልድ ላይ፥ የምፀት ስድብ ለመሳደብ የቱን ያህል እንደተነሡበት ትመለከታለህና ነው።

ምናልባትም አርዮሳውያን ይህን አባባላቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ለማስመሰል፦ ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ፦ ከአጥቢያ ኮከብ በፊት ከሆድ ወለድሁህ ተብሎ የተነገረውን ይጠቅሱልህ ይሆናል። መዝ. 109/110/፥4። ይህን ጥቅስ ከተቀበሉት፤ እስቲ በጥቅሱ ውስጥ ያሉትን ቃላት በማተኮር እንያቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው «ከአጥቢያ ኮከብ በፊት ከሆድ ወለድሁህ» ነው። በዚህ ጥቅስ ያሉት ቃላትን በማስተዋል ካየን፦ ወልድን «ከአጥቢያ ኮከብ በፊት ከሆድ ወለድሁህ» ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን እንጂ፤ አርዮሳውያን ከአጥቢያ ኮከብ «ከዲያብሎስ» ከብዙ ጊዜ በፊት ፈጠርሁህ ተብሎአል ወይ? አልተባለም እኮ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ካላለስ አባባላቸው በሐሰት የተመሠረተ መሆኑ ግልጽ አይደለምን?

አሁንም በዚሁ ጥቅስ ከሚገኙት ቃላት «ወለድኩከ እምከርሥ ከሆድ ወለድሁህ» በሚል ኃይለ ቃል ላይ፥ ትኩረት እናደርጋለን።

«ከሆድ ወለድሁህ» የሚል ኃይለ ቃል፥ ከራሱ ከእግዚአብሔርነቱ፤ መውጣቱን ሲያስገነዝብ ከባሕርየ መለኮቱ ውጭ ካለመኖር ወደመኖር ካመጣቸው ከፍጡራን ለይቶ ባሕርያዊ ልደቱን እንዲያስታውቅለት ግልጽ ነው።

ይኸውም ማለት፥ በዚሁ ጥቅስ ከሆድ ወለድሁህ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ሲሆን፤ በጊዜው ከተፈጠረው ከአጥቢያ ኮከብ ለይቶ፥ የባሕርይ ልደቱን አስታውቆለት ይገኛል። ይኸውም ራሱ ወልድ «ከአብ ወጣሁ» ብሎ በተናገረው ተገልጾአል። ዮሐ. 1፥27፤28።

አርዮሳውያን ግን «የአጥቢያ ኮከብ ዲያብሎስ ከመፈጠሩ ከብዙ ጊዜ በፊት ወልድ ተፈጠረ» ሲሉ መጥቀሳቸው የእግዚአብሔር ቃል ወልድን በዘመን ብቻ አበላልጠው፥ በተፈጥሮ ረገድ ግን አጥቢያ ኮከብ ከሚሉት ከዲያብሎስ ጋር የተፈጥሮ ጓደኛ ለማድረግ መጣራቸው ነው። እንዲያውም የእግዚአብሔርን ቦታ ለመቀማት የዲያብሎስን መንገድ ተከትሎ ከእርሱ ጋር አላሴረም እያሉ መሪነትን ለዲያብሎስ ይሰጣሉ። <u>እግዚ. እው. ይሁን</u፤ ገጽ. 38፥20።

በእነርሱ ዘንድ መፈጠርና ከባሕርይ መወለድ ትርጉሙ አንድ ነውና፤ ከዚህ ጋር ወልድን ከሆድ ወለድሁህ ካለው፤ የአጥቢያ ኮከብ የሚሉትን ዲያብሎስን «ወለድሁህ» እንዳለው በማስመሰል ዲያብሎስን ኢፍጡር ለማድረግ የሚሞክሩ ይመስላሉ።

ይሁን እንጂ ሁሉ በእርሱ ሆነ፤ ያለ እርሱ ግን አንዳች ስንኳ አልሆነም። የተባለው የእግዚአብሔር ቃል በእግዚአብሔራዊ በጎ ፈቃድ ካለመኖር ወደመኖር ፈጥሮ ካመጣቸው ፍጡራን ሁሉ ጋር ያመጣውን የአጥቢያ ኮከብ «ዲያብሎስን» ምንም እንኳ ወለድሁህ እንዳለው ለማስመሰል፥ ቢሞክሩ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን «ወለድሁህ» ያለው ቃለ እግዚአብሔር ወልድን እንጂ፤ ዲያብሎስን ወለድሁህ አይለውም።

አርዮሳውያን ወልድን የአጥቢያ ኮከብ ከሚሉት ከዲያብሎሳቸው ከብዙ ጊዜ በፊት ተፈጠረ ብለው የሚናገሩት፡- ወልድን ከዲያብሎስ ጋር ለማቀራረብና ዲያብሎስን ከእግዚአብሔር አብ ሆድ ከተወለደው፤ ከወልድ ጋር ለማጉዳኘትና አስተካክሎ ለማሳየት መሆኑ ግልጽ ነው። ይኸውም ዲያብሎስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ታላቅ የአደራ ሥራና ኃላፊነትም ተሰጥቶት ነበር። ይኸውም በሰው ላይ ገዥነት ነበር ብለው ዲያብሎስን የእግዚአብሔር ልጅና የሰው ገዥነት እንደተሰጠው አድርገው ይናገራሉ። እግዚ. እው ይሁን ገጽ. 49። መሥ. 13። ይሁን እንጂ፤ እግዚአብሔር ቃል ወልድ በዘለዓለምነት ከአብ ዘንድ ህልው ሆኖ መኖሩን፥ ከአጥቢያ ኮከብ ብቻ ሳይሆን፤ የገዛ ራሱ ካለመኖር ወደመኖር ካመጣቸው ከሰማያትና ከሰማየ ሰማያት ከምድርና ከጥልቆች፤ ከሚታዩና ከማይታዩ ፍጥረታት ሁሉ አስቀድሞ በማይወሰን ጊዜና ዘለዓለማዊነት በአብ ዘንድ «ከአብ ሆድ» መወለዱን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። መቼም መጽሐፍ ቅዱስ ፍንጭ አልሰጣቸውም እንጂ፤ አርዮሳውያን ጥረታቸው ዲያብሎስን ልዑል የሆነ መለኮታዊ ስፍራን ለማስያዝ ኖሮአል።

የሕያው እግዚአብሔርን ልጅ ቢያዋርዱና ቢሰድቡ ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ ልቆና፥ መጥቶ መለኮታዊ ስፍራ የሚይዝላቸው መስሎአቸው ይሆን?

ዲያብሎስን ለማወደስና ለማመስገን ብለው የእግዚአብሔርን ልጅ እስከዚህ ድረስ መሳደባቸውና ማዋረዳቸው ለገዛ ራሳቸው ይብላኝላቸው እንጂ፤ ወልድን እንደሆነ ከባሕርይ ልደቱ የሚያፈናቅለው ምንም ነገር አይገኝም። 1ዮሐ. 5፥20፤21።

ከዚህ አስቀድሞ፡- የዲያብሎስ ምኞት ፈጻሚዎች ለሆኑና ከእግዚአብሔር ነን ለሚሉ አይሁድ ኢየሱስ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናግሮአል። ከእግዚአብሔር ብትሆኑ በወደዳችሁኝ ነበር እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና። ዮሐ. 8፥42።

እንደዚሁም፡- እናንተ የአባታችሁን ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ። እውነትም በእርሱ ዘንድ ስለሌለ በእውነት



አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና፤ እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለሆንሁ አታምኑኝም ብሎአል። ዮሐ. 8፥43፤44።

አንባቢ ሆይ፡- እዚህ ላይ ወልድ ራሱ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁ ብሎ የገለጸውንና፤ «ከሆድ ወለድሁህ» የሚለውን በጽሞና ሆነህ ኃይለ ቃሉን ተገንዘብ።

በአንጻሩ ደግሞ፡- አርዮሳውያን የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ለመሳደብ ሲሉ ፍጡር መልአክ ከነበረውና አምላክነትን ተመኝቶ ከወደቀው ዲያብሎስ ጋር፥ በተፈጥሮ ሊያጉዳኙት ማሰባቸውንና እስከዚህ ድረስ ለስድብ መነሣሣታቸውን ተመልከት። ታዲያ እነዚህ የማን ወገኖች እንደሆኑና ለማን እንደሚሠሩ ይታዩ የለምን? ዮሐ. 8፥43፤44።

እኔ መጀመሪያ ወይም ፊተኛ ነኝ ብሎ፥ በነቢዩ በኢሳይያስ አፍ በተናገረውና፤ ሥግው ቃልም እኔ መጀመሪያ ነኝ ፊተኛ ነኝ ሲል ለባሪያው ለዮሐንስ በተናገረው መካከልም ምንም ልዩነት እንደሌለ ተገልጾ እናያለን፤ 1ዮሐ. 1፥1።

ስለዚህ ዮሐንስ በወንጌሉ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ሲል ቃልን ዘመንና ጊዜ ሳይወስነው በቅድምና በዘለዓለማዊነት ነበረ» ማለቱ መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ ተገልጾ ተብራርቶ ታወቀ ተጠንቀቀ። «ስለዚህ በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ማለትን «ቃል በዘላለማዊነት ነበረ» ብለን እምነታችንን እያረጋገጥን፤ የቃለ እግዚአብሔር ዘላለማዊነትን ለሚክዱ እንመሰክራለን። 1ዮሐ. 1፥1። ም. 5፥20፤21። «እርሱ ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ ሮሜ 9፥5። «አሜን።»

## ተፈጸመ።